# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሐገረ ስብከት ውስጥ በሚደረጉ ስብከቶች ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ጥናት


በ

ቤተልሔም ኃይሉ ደስታ



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY



አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲ ፋክልቲ
የኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር
ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ማስተርስ ዲግሪ
ከፊል ማሟያ የቀረበ


ጥር፣ 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሐገረ ስብከት ውስጥ በሚደረጉ ስብከቶች ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ጥናት

በ
ቤተልሔም ኃይሉ ደስታ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲ ፋክልቲ
የኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር
ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ማስተርስ ዲግሪ
ከፊል ማሟያ የቀረበ

ጥር፣ 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሐገረ ስብከት ውስጥ በሚደረጉ ስብከቶች ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ጥናት

በ
ቤተልሔም ኃይሉ ደስታ

አማካሪ
ዮናስ አድማሱ (ዶ/ር)

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲ ፋክልቲ
የኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር
ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ማስተርስ ዲግሪ
ከፊል ማሟያ የቀረበ

ጥር፣ 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

## ምስጋና

ይህ ጥናት ከጅምሩ አንስቶ አሁን የደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ ስህተቶቼን እየነቀሱ በማሳየትና የሚቃኑበትን መንገድ በመጠቆም፣ መጻሕፍቶችን በማዋስ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለመምህሬና ለአማካሪዬ ለዶ/ር ዮናስ አድማሱ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

ለጥናታዊ ፅሁፌ መሰረት የሆኑ መረጃዎች በመስጠት፣ ለቃለ መጠይቅ በመተባበር በትህትና ተቀብለው ላስተናገዱኝ መረጃ አቀባዮቼ በሙሉ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

ከፎክሎር ፅንሰ ሀሳብ ጋር እንድተዋወቅ ብቻም ሳይሆን ሙያውን እንደሙያ እንዳከብረውና እንድወደው ላደረጉኝ መምህሬ ለዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ያለኝን ላቅ ያለ አክብሮት በዚህ አጋጣሚ ልገልፅ እወዳለሁ፡፡

እጅግ በተጣበበ ሁኔታ ላይ ባሉበት ጊዜ እንኳን እኔን ተቀብለው ከማነጋገር፣ መፅሀፍ ከማዋስ ላልቦዘኑት ለመምህሬ አቶ መስፍን መሰለ ስለሰጡልኝ ጊዜና ስላዋሱኝ መፅሀፍ "ሳይሆን" ስላስተማሩኝ ቅንነት ላመሰግናቸውና እግዚአብሔር ይስጥልኝ ልል እወዳለሁ፡፡

በአጠቃላይ ለትምህርቴ በተለይ ደግሞ ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መሳካት እናቴ ወ/ሮ ጥሩወርቅ ደመቀ ካበረከተችው አስተዋፅኦ አንፃር ሲታይ የእኔ ጥረት ኢምንት ነው፡፡ እናት አለሜ እኔን በመሸከም ለማይላጠው ትከሻሽና ለመኖሬ ምክንያት በመሆንሽ አመሰግንሻለሁ፡፡ እንዲሁም ለስኬት እበቃ ዘንድ ከሀሳብ አንስቶ እስከ ማቴሪያል እገዛ ድረስ ድጋፍ ለሆኑኝ ቤተሰቦቼ፤ የውዲያነሽ፣ ህይወት፣ ብርሃኑ፣ ቀለሚ እና አስቴር ሃይሉ እግዚአብሔር በበጎ ያስባችሁ እላለሁ፡፡

ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ በመፃፍና በማረም ብቻም ሳይሆን እንደጓደኛ ከጎኔ በመቆም ጭምር ለረዳችኝ ሰብለ፤ በማንኛውም ረገድ ላልተለዩኝ ጓደኞቼ ህይወት፣ ሜሮንና ትዕግስት እግዚአብሔር ይስጥልኝ እላለሁ፡፡

## አጠቃሎ

ቃላዊ ዝርው ተረኮች ለባህል ባለቤቶቹ (ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን) ያላቸውን ፋይዳ ወይም ተግባር መመርመርና ክዋኔያቸውን የክዋኔ አውድን መቃኘት የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ነው። በዚህ መሠረት የተረኮቹ ክዋኔ፤ የከዋኙና የታዳሚው ማንነትና መስተጋብር፣ የክዋኔ አውድ፣ የአከዋወን ስልት ምን ይመስላል? ተረኮቹ በባህል ባለቤቶቹ ዘንድ ያላቸው ተግባር ምንድነው? እንዲሁም ተለይተው የሚታወቁበት ስያሜና የአመዳደብ ስርዓት አላቸው ወይ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል። በውጤቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በባህል ባለቤቶቹ ዘንድ ተለይተው የሚታወቁበት አንድ ወጥ ስያሜም ሆነ የአመዳደብ ስርዓት እንደሌላቸው ለማሳየት ተሞክሯል። ይሁንና በተረኮቹ ክዋኔ ሂደት ታዳምያንና ከዋኞቹ ከሚፈፅሟቸው ልዩ ልዩ ተግባራትና በውስጠ ታዋቂነት ከሚያንፀባርቁት አመለካከት በመነሳት ተረኮቹን እውነተኛና ፈጠራዊ በሚሉ አበይት ምድቦች ለመክፈል ተሞክሯል።

በጥናቱ ሂደት ተራኪዎች በክዋኔ ላይ ልዩ ልዩ የአከዋወን ስልትን እንደሚከተሉ የታየ ሲሆን፣ ከትረካ መስመር መውጣት /digression/፣ ድግግሞሽ እና ወደረኛ ቅንብር ከስልቶቹ መካከል ተጠቃሽ እንደሆኑ በጥናቱ ተጠቁሟል።

ጥናቱ በስብከት ስርዓት ወቅት የሚከወኑ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ከፎክሎር ተግባራዊ ጥናት /functionalist approaches/ አንፃር ትንታኔ ሰጥቷል። በዚህ መሠረት ተረኮቹ የቤተ ክርስቲያኑን እሴት የማስተማር፣ ምዕመናን ከቤተ ክርስቲያኑ የእሴት ስርዓት አፈንግጠው እንዳይወጡ የመቆጣጠርና የማግታት እንዲሁም ለምዕመናኑ ስነልቡናዊ እፎይታን የመስጠት ፋይዳ እንዳላቸው ለማሳየት ጥረት ተደርጓል። ከነዚህ ተግባራት ጎን ለጎን ዝርው ተረኮቹ ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ቅንብብ ዘልቀው በመውጣት በተራቹ ማህበረሰብ፣ ማህበራዊ ህይወት ዙሪያ የማሄስ ተግባርን እንደሚፈፅሙ ለመጠቆም ተሞክሯል።

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ... iii

አጠቃሎ... iv

ምዕራፍ አንድ ... 1

መግቢያ ... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ... 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ... 2

1.3. የጥናቱ አላማ ... 3

1.4. የጥናቱ ወሰን (scope of the study) ... 3

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ... 4

1.6. ያጋጠሙ ችግሮችና የተሞከሩ መፍትሄዎች ... 4

1.7. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ... 5

1.8. የአጠናን ዘዴ ... 7

ምዕራፍ ሁለት ... 8

የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ክለሳ ድርሳን ... 8

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ... 8

2.2. ክለሳ ድርሳን ... 12

2.2.1. አውዳዊ ጥናት (contextual analysis) ... 12

2.2.2. ተግባራዊ ጥናት (functionalist approaches) ... 14

ምዕራፍ ሦስት ... 17

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረክ ዓይነቶች ... 17

3.1. እውነተኛ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ... 20

3.1.1. ትውስታዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች /reminiscences/ ... 24

3.1.2. ሂሳዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ... 25

3.2. ፈጠራዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ... 26

3.2.1. ተረቶች /folktales/ ... 29

3.2.2. ቀልዶች /jokes/ ... 30

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ክዋኔ /performance/ ... 34

4.1. የመከወኛ አውድ /context/ ... 35

4.2. ከዋኝ /performer/ ........ 41
4.3. ታዳሚ /audience/ ........ 45
4.4. የአከዋወን ዘዴ (ስልት) ........ 53
4.4.1. ከትረካ መስመር መውጣት /digression/ ........ 53
4.4.2. ከፍተኛና ዝቅተኛ የድምጽ መጠንና ፍጥነት ........ 61
4.4.3. ቆምታ /pause/ ........ 62
4.4.4. ድግግሞሽ /repetition/ ........ 64
4.4.5. ወደረኛ ቅንብር /parallelism/ ........ 67
ምዕራፍ አምስት ........ 69
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተግባራትን /functions/ መሠረት ያደረገ ትንታኔ ........ 69
5.1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እሴት የማስተማር ተግባር ........ 70
5.2. የመቆጣጠር እና የመግታት ተግባር ........ 74
5.3. ስነልቡናዊ እፎይታን የማስገኘት/የመስጠት ተግባር ........ 78
5.4. የማህበራዊ እሴቶችን ተገቢነት ወይም ጠቀሜታ ከፍ የማድረግ ተግባር ........ 82
5.5. የማህበራዊ እሴት ተገቢነት ላይ ጥያቄ የማንሳት ተግባር ........ 85
ማጠቃለያ ........ 87
ዋቢ ጽሑፎች ........ 89
አባሪ አንድ
አባሪ ሁለት
አባሪ ሦስት
አባሪ አራት
አባሪ አምስት

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ዘንድ በሚታይ አንድ ፎክሎራዊ ገፅታ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ዋነኛ ትኩረት ላይ መሠረት በማድረግ የጥናቱ ዳራ እንዲሁም ጥናቱን ለመከወን አነሳሽ የሆነው ዋነኛ ምክንያት ይገለፃል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የጥናቱን ወሰን እና ዓላማ አስመልክቶ ቅኝት ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በምዕራፉ የጥናቱ መከወን ሊኖረው የሚችለው ጠቀሜታ የሚጠቆም ሲሆን ጥናታዊ ጽሑፉን በመከወን ሂደት የተከተልኩት የመረጃ አሰባሰብ እና የአጠናን ዘዴም በዝርዝር ይቀርባል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

በኢትዮጵያ ስነቃልን ማጥናት በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ገደማ እንደተጀመረ /ፈቃደ፣ 1996 እ.ኤ.አ/ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በአማተርና በፕሮፌሽናል ባለሙያዎች ስነቃል ሲጠና መቆየቱን ፈቃደ ሲጠቁሙ በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎችና ስነፅሁፍ የትምህርት ክፍል በ1958 ከተቋቋመ በኋላ በስነቃል ዙሪያ ተማሪዎች የዲግሪ ማሟያ ፅሁፎችን ማቅረብ መጀመራቸውን ይገልፃሉ፡፡ በሂደትም በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ቲሲሶች መፃፍ መጀመራቸውን ይጠቁማሉ፡፡

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅራቢ ባለኝ መረጃ መሠረት ባለፉት ጥቂት አስርት አመታት በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ትኩረታቸውን አድርገው የቀረቡ ዲማፆችም ሆኑ ቲሲሶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን የመከወኛ አውዳቸውን ጨምሮ ዋነኛ ትኩረታቸው አድርገው አላጠኑም፡፡

ይሁን እና ሃይማኖት ዓለምን የምናይበትን፣ ከዓለም ጋር ያለንን መስተጋብር የምንወስንበትን አንፃር ይሠጠናል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በአንድ ሰው አመጋገብ፣ አለባበስና በሚመሠርተው ማህበራዊ ህይወትና በጥሬ ሀብት አጠቃቀሙ ላይ በአጠቃላይ የየእለት ህይወቱን በሚመራበትና በሚረዳበት ሁኔታ ላይ የሚያሳድረው የራሱ የሆነ ተፅዕኖ አለው /Bowman፣ 2003፣ 280/፡፡ በየትኛውም የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ በተለይ ደግሞ በፎክሎር ጥናት መስክ የሠውን ልጅ አጠቃላይ ባህርይ ለመረዳት በሚደረግ ጥረት ሃይማኖትን ማጥናት ብቸኛውም ባይባል አንድ አማራጭ ሆኖ ሲታይ ቆይቷል፡፡ ስብከት ሀይማኖታዊ አስተምህሮ ወይም የእሴት ስርዓት ወደ ምዕመን የሚደርስበት አንዱ ድልድይ ነው፡፡

በስብከት ስርዓት ውስጥ ተጠቃለው የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በአንድ በኩል ሃይማኖታዊ አስተምህሮንና የእሴት ስርዓትን ወደ ምዕመኑ የሚያደርሱ ሲሆን በሌላ በኩልም ተረኮቹ የተራቹን ማህበረሠብ /የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ማህበረሠብን/ አመለካከት፣ እምነት፣ ዝንባሌ ወዘተ. የሚያንፀባርቁ ናቸው። እነዚህን ቃላዊ ዝርው ተረኮች በቅርበት ማጥናት ተራቹን ማህበረሠብ ለመረዳት የሚያስችል አንድ መንገድ ሲሆን በዚህ መሠረት ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን የመከወኛ አውዳቸውን ጨምሮ ማጥናትን ዋነኛ ትኩረቱ አድርጓል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በሚከወኑበት ተፈጥሯዊ አውድ ሳደምጥ ብዙ አመታትን አሳልፌያለሁ። ይሁን እና ይህን ጥናት በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ለመስራት በተለይ አነሳሽ የሆነኝን ተረክ የሰማሁት ከአስር አመት በፊት ከአንድ ታዳጊ ህፃን አንደበት ነው። ህፃኑ በአንድ ሰንበት ከወላጅ እናቱ ጋር በቤተ ክርስቲያን በተገኘበት ወቅት ከሀያሉ አንበሳ አንስቶ እስከ ደካማዎቹ እንስሳት ድረስ አንድም ሳይቀሩ በአመፅ ስለተነሱባትና እግዚአብሔር አምላክ ድንጋይ አልብሶ ስለአዳናት ኤሊ ታሪክ ይሰማል[*]። በጊዜው ታዳጊ ህፃኑ እድሜው በሚፈቅድለት መጠን ይህን ታሪክ ተረድቶ አድንቆታል። እኔም በተመሳሳይ ስለፎክሎር ፅንሰ ሀሳብ ምንም አይነት ግንዛቤ ባልነበረኝ በዛ ወቅት ተራ ሰው ሊረዳ በሚችለው ደረጃ የተረኩን ኪናዊ ውበትና ፋይዳ አጣጥሜያለሁ፣ አድንቄያለሁ። በዚህ ተረክ ዓይን ከፋችነት ሌሎች በየአብያተ ክርስቲያን የሚነገሩ መሰል ተረኮችን ለአመታት ትኩረት ሰጥቼ ሳደምጥ ቆይቻለሁ። በጊዜ ብዛት ከፎክሎርና ከስነፅሁፍ ፅንሰ ሀሳብ ጋር ስተዋወቅ ለቃላዊ ዝርው ተረኮች ያለኝ አተያይ እየሰፋና እየተጠናከረ ሄዷል። ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊጠኑ ይገባል የሚል እምነትም አድሮብኛል። በዚህ መሰረት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ቲሲስ ለመስራት ሳቅድ በአብያተ ክርስቲያናቱ የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ማጥናት ተቀዳሚ ምርጫዬ ሊሆን ችሏል።

---

[*] ይህ ተረክ ከመስክ የተሰበሰቡ ተረኮች በቀረቡበት አባሪ ሁለት ውስጥ በተራ ቁጥር ስልሳ ስድስት ስር ቀርቧል። "ገላጭ ተረቶች /explanatory tales/. . . በአንድ ማህበረሰብ የሚታዩትን ተፈጥሯዊ እና ህይወታዊ ክስተቶች እና ሀሳቦች ኬትመጣ /origin/ ለመግለጽ እና ለማብራራት የሚሞክሩ ናቸው" (ፈቃደ፣ 1991፣ 57-58)። ይህም ተረት ከዚህ ጎራ የሚመደብ ሲሆን ከዋኞች ከማህበረሰቡ የፈለቁ ተረኮችን፣ ተረኮቹ ከሚከወኑበት ተፈጥሮአዊ አውድ (ከአብያተ ክርስቲያኗ ወይም ከአጠቃላይ የስብከት ስርዓቱ) ዓላማና መንፈስ /mood/ ጋር በማዛመድ የሚጠቀሙ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

### 1.3. የጥናቱ አላማ

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሚካሄድ የአምልኮ ስርዓት ወቅት የሚታዩ ፎክሎራዊ ባህርያትን በተለይ ደግሞ በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ማጥናት የአማንያኑን አጠቃላይ የህይወት ገፅታ፤ እምነት፣ ፍልስፍናና የእሴት ስርዓት ለመረዳት በሚደረግ ጥረት በግብአትነት የሚያቀብለው አንድ ቁምነገር ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም "ተረኮች ስለ አማልክት፣ ስለ ቅዱሳን፣ ስለነብያት ወዘተ. እየተነገሩ የሚያስተምሩና የሚያዝናኑ፣ ለአድማጩ የሕይወትን ሚስጢራዊነት ገልፀው የሚያሳዩ ናቸው፡፡" (ፈቃደ፣1991፣53)፡፡ ይህ ጥናት በቤተ ክርስቲያኗ በሚደረግ የስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ትኩረቱን በማድረግ የተረኮቹን፡-

- የክዋኔ አውድና የአከዋወን ዘዴን (ስልትን) ማጥናትን
- ተረኮቹ ለተራቹ ማህበረሰብ ያላቸውን ፋይዳ መመርመርን አቢይ አላማው

አድርጓል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ጥናቱ ስብስብ ተረኮችን በአይነት መመደብን በንኡስ አላማነት ይዞ ቀርቧል፡፡ እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስም በጥናቱ፡-

- የተረኮች ከዋኞችና አድማጮች እነማን ናቸው?
- የክዋኔ አውዱ፤ ከጊዜ፣ ከቦታና ከሁኔታ አንፃር ምን መልክ አለው?
- በተረኮቹ ክዋኔ ሂደት የከዋኞችና የታዳምያን መስተጋብር ምን ይመስላል? በመስተጋብሩ ውስጥ የሚታዩ ምግባራትስ የባህል ባለቤቶቹ ለተረኮቻቸው ያላቸውን አመለካከት በምን መልኩ ያንፀባርቃሉ?
- ተራቹ ማህበረሰብ ተረኮቹን ለይቶ የሚያውቅበት ስያሜና ስርዓት አለው ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች ተነስተው መልስ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡

### 1.4. የጥናቱ ወሰን (scope of the study)

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሚካሄድ የአምልኮ ስርዓት ላይ ከመደበኛው ሃይማኖታዊ ስርዓት ጋር ተዛንቀው ሌሎች በርካታ ፎክሎራዊ ባህርያት ሲካሄዱ ይታያሉ፡፡ Danielson (2003) እንደሚሉት አንድ አንድ ሀይማኖታዊ ፎክሎሮች በአምልኮ ስርዓቱ ውስጥ እጅግ የተለመዱ ተግባራት ከመሆናቸው የተነሳ ተግባራቱን እንደ አንድ ፎክሎራዊ ባህርይ ለማሰብ ፈታኝ ይሆናል፡፡ ይሁን እና እንደ Danielson ገለፃ እነዚህ ተግባራት በተለምዷዊው የፎክሎር ዘውግ (genre) ስር ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው(2003፣504)፡፡ ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ስርዓት ወቅት ከሚታዩ በርካታ ፎክሎራዊ ባህርያት መካከል ትኩረቱን በስብከት ስርዓት ወቅት በሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ አድርጓል፡፡ በስብከት ስርዓት ወቅት ከሚነገሩ ተረኮች መካከልም ጥናቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ

በቀጥታ ምዕራፍና አንቀጽ እየተጠቀሰ የሚተረቱትን ተረኮች ወደጎን በማለት (ተረኮቹ የሚጠኑበት የራሳቸው አግባብ እንዳላቸው ሳይዘነጋ) ትኩረቱን ከሰባኪው እና ከምዕመኑ ግለሠባዊና ማህበራዊ ገጠመኝ እየፈለቁ የእሴት ስርዓቱን እና አምልኮአዊ ተግባሩን በሚገልጽባቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ወስኗል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅራቢ ባለኝ መረጃ መሰረት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሚካሄድ የስብከት ስርዓት ላይ የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከሚነገሩበት ተፈጥሯዊ አውድ ላይ ተሰብስበው አልተጠኑም፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ተግባራዊ መሆን፡-

- የባህል ባለቤቶቹን ስነ ልቡናና ለዓለም ያላቸውን አጠቃላይ አተያይ ለማወቅ በሚደረግ ጥረት እንደ አንድ ግብአት ሆኖ ሊያገለግል፣
- በቤተ ክርስቲያኗ በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ተረኮች ተቀርሰው ለትውልድ እንዲተላለፉ ሊያገለግል፣
- በዘርፉ ቀጣይ ጥናት ለሚያደርጉ ባለሙያዎች እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

## 1.6. ያጋጠሙ ችግሮችና የተሞከሩ መፍትሄዎች

ከመረጃ አቀባዮች ጋር መልካም ግንኙነት መመስረት አለመቻል ይህን ጥናት በመከወን ሂደት ያጋጠመኝ ቀዳሚው ችግር ነበር፡፡ በዚህ ጥናት ቁልፍ የመረጃ አቀባይ የሆኑት ሰባክያነ ወንጌል "አፍራሽ ተልዕኮ" ይዘው ሊመጡ የሚችሉ ግለሰቦች ሊኖሩ ይችላሉ ከሚል ስጋት ይገፍው ከተነሳሁት አላማ ጋር በቀላሉ ሊቀበሉኝ አልቻሉም ነበር፡፡ ይሁን እና በቤተ ክርስቲያኑ "ቤተኛ" የሆኑ ምእመናንን፣ ከሰባክያኑ ጋር እንዲያስተዋውቁኝ እገዛ በመጠየቅ ችግሩን በተወሰነ ደረጃ ለመቅረፍ ችያለሁ፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን መረጃ በመሰብሰብ ሂደት በዋናነት መሠናክል የሆነብኝ ጉዳይ አመዛኙ ሰባክያነ ወንጌል የሚያካሂዷቸውን ስብከቶች በመቅረፀ ድምፅ እንዳስቀር ፈቃደኛ አለመሆናቸው ነበር፡፡ ስብከቶቹ አንዴ በመቅረፀ ድምጽ ከተወሰዱ በኋላ ከእኛ እውቅና ውጪ ለገበያ ሊቀርቡ ይችላሉ ከሚል ስጋት እንዲሁም የቤተ እምነቱን ስርዓት ለማጉደፍ በተዛባ መልኩ እንጠቀሳለን (misquote እንደረጋለን) ከሚል ፍራቻ አብዛኛዎቹ ሰባክያነ ወንጌል የሚያካሂዷቸውን ስብከቶች በመቅረፀ ድምፅ እንዳስቀር ለመፍቀድ ተቸግረው ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለይ አንዳንድ አንጋፋ ወይም አበው የቤተ ክርስቲያኗ ሰባክያን በመቅረፀ ድምፅ ስብከቶቻቸውን ማስቀረፅ

ክርስቲያናዊ ትህትናን ማጓደል፣ አንድ ሰባኬ ወንጌል ከአምላክ እንጂ ከሱ የሆነ አንድም ነገር ለምዕመኑ አይሰጥም የሚለውን እምነት በመጣስ ግብዝ መሆን ወይም ውዳሴ ከንቱ ፈላጊነት፣ እንደሆነ በማመናቸው ለጥያቄዬ አወንታዊ ምላሽ አልሰጡኝም፡፡ ይሁን እና ከሰባክያነ ወንጌላውያኑ ጋር በተደጋጋሚ በመገናኘት፣ በመቅረፀ ድምፅ የማስቀራቸው ስብከቶች አንዳቸውም ለጠቀሷቸው አፍራሽ አላማዎች እንደማይውሉ ለማስረዳት ሞክሬያለሁ፡፡ ካሴቶቹ የአብያተ ክርስቲያኑን በጎ ገፅታ ሊያሣዩ የሚችሉ ቅርሶች ሊሆኑ እንደሚችሉም ሰባክያነ ወንጌሉን ለማሳመን ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ከዚህም ባሻገር ስብስቦቹ ተአማኒነት ያላቸው መሆናቸውን ለማሳየት ስብከቶቹን በመቅረፀ ድምጽ መያዜ ወሳኝነት እንደሚኖረው መረጃ አቀባዮቹን በማስረዳት በመጨረሻ የአብዛኞቹን መረጃ አቀባዮች ይሁንታ ለማግኘት ችያለሁ፡፡

## 1.7. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወደ መስክ* ያደረኩት ጉዞ በሶስት ምዕራፎች የተካሄደ ነበር፡፡ የመጀመሪያው የመስክ ቆይታ ከጥር 15 - የካቲት 6፣ 2002 ዓ.ም. ድረስ ለሀያ ሁለት ቀናት የተካሄደ ነው፡፡ በነዚህ ቀናት ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ የሚሆኑትንና ተጠኚ ተረኮችን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚከውኑትን ሰባክያነ ወንጌል* የማፈላለግ የመተዋወቅና ይገቼው የተነሳሁትን አላማ የማስተዋወቅ ስራ አከናውኛለሁ፡፡

ሰባክያነ ወንጌሉን ለማግኘትና ለመተወቅ የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅሜያለሁ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከስነ ፅሁፍና ፎክሎር የትምህርት ክፍል ማንነቴንና ለምን አላማ እንደምንቀሳቀስ የሚገልፅ ደብዳቤ በማፃፍ ወደ ማህበረ ቅዱሳን ሄጃለሁ፡፡ በወቅቱ በልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉ ሰባክያነ ወንጌል ስምሪት ዙሪያ ይሰሩ ከነበሩት ዲያቆን ዳዊት ጋር በመገናኘት ቁጥራቸው ወደ ሃያ የሚጠጋ ሰባክያነ ወንጌልን ስምና አድራሻ /የስልክ/ ለማግኘት ችያለሁ፡፡ ምንም እንኳን ከማህበረ ቅዱሳን ባገኘሁት አድራሻ መሠረት አመዛኙን ሰባክያነ ወንጌል በስልክ ለማግኘት ብችልም ይገቼው የተነሳሁት ዓላማ ላይ ጥርጣሬ ስላደረባቸው የአመዛኙን ሰባክያነ ወንጌል ትብብር ለማግኘት አልቻልኩም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ወደ ልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያናት አዘውትረው የሚሄዱና ሰባክያነ ወንጌሉን በቅርበት የሚያውቁ ለእኔም ቅርበት ያላቸውን ሰዎች በአገናኝነት በመጠቀም ከሰባክያነ ወንጌሉ

* በዚህ ጥናት ዋነኛ መረጃዎቼን፣ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹን የሠበሠብኳቸው በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ስር ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ነው፡፡ በዚህ ጥናት መስክ ስል በዋናነት አብያተ ክርስቲያናቱን የሚመለከት ሲሆን ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የተሰበሰቡበት የአብያተ ክርስቲያናቱ ዝርዝር በአባሪ አምስት ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል፡፡
* ዋነኛ የመረጃ አቀባዮቼ /የሰባክያነ ወንጌል/ ዝርዝር በአባሪ አራት ውስጥ ቀርቧል፡፡

ጋር ለመተዋወቅ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ በዚህ መንገድ ያገኘኋቸው ሰባክያነ ወንጌል ላስተዋወቁን ሰዎች ካላቸው እምነትና አክብሮት እኔንም በተሻለ እምነትና ፈቃደኛነት ተቀብለውኛል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያን የስብከት ስርዓት ላይ በመገኘት፣ ሰባክያነ ወንጌሉ ስብከት ሲያደርጉ በመከታተልና ሰብከው ሲጨርሱ በግንባር ቀርቤ በመተዋወቅ በስልክ ልመሰርተው ከቻልኩት የተሻለ ግንኙነት ለመመስረትና ተጨማሪ የመረጃ አቀባዮችን ለማግኘት ችያለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከላይ በጠቀስኳቸው መንገዶች የተዋወኳቸው ሰባክያነ ወንጌል ሌሎች ሰባክያነ ወንጌልን /ባልደረቦቻቸውን/ እንዲያስተዋውቁኝ በመጠየቅ ተጨማሪ መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት ችያለሁ፡፡

ሁለተኛው የመስክ ቆይታዬ፣ ከየካቲት 8፣ 2002 ዓ.ም. - ግንቦት 16፣ 2002 ዓ.ም. ድረስ ለሶስት ተከታታይ ወራት የዘለቀ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የጥናቱ መሠረት የሆኑ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተሠብስበዋል፡፡ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹን ለመሠብሠብ፣ መረጃ አቀባዮች ለስብከት አገልግሎት በሚገኙባቸው አብያተ ክርስቲያናት፤ በአመሻሽ ጉባኤዎች፣ የቀትር ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊት /በተለይ በዓቢይ ፆም ወቅት/፣ በንግስ ቀናት ታቦት አውደ ምህረት ላይ በሚቆምበት ጊዜ እንዲሁም በሰንበት ቅዳሴ ላይ ተገኝቻለሁ፡፡ በዚህ ወቅት በመስክ በነበረኝ ቆይታ ለዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ ከዋሉ ስልሳ ስድስት ቃላዊ ዝርው ተረኮች መካከል ሃምሳ ዘጠኝ ያህሉን በቀጥታ ከሚከወኑበት ተፈጥሯዊ አውድ በተሳታፊ ተመልካችነት ሰብስቤያለሁ፡፡ እነዚህ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተጠቃለው የሚነገሩባቸውን ሙሉ የስብከት ስርዓቶች ጨምሮ በሃያ ሁለት ያህል የቴፕ ካሴት የተሠበሠቡ ሲሆን በቴፕ ካሴቶቹ /በመቅረፀ ድምፁ/ ለመያዝ ያልተቻሉ መረጃዎች ደግሞ በፅሁፍ ማስታወሻና በፎቶግራፍ እንዲቀሩ ተደርጓል፡፡* ከዚህ ጎን ለጎን በዚህ ወቅት ከመስክ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ለማጠናከር የሚረዳኝን ሀሳብ ለማግኘት ከስምንት ያህል የቤተ ክርስቲያኗ ሙያተኞችና ሰባክያነ ወንጌል ጋር ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ በቃለመጠይቅ ሂደት ወቅትም ሰባት የሚሆኑ ተጨማሪ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ሰብስቤያለሁ፡፡

ሶስተኛው የመስክ ቆይታ ከግንቦት 17-25፣ 2002 ዓ.ም. ገደማ ድረስ የዘለቀ ነው፡፡ በዚህ ወቅት የቤተ ክርስቲያኗ ምዕመናን ቃላዊ ዝርው ተረኮቹን አስመልክቶ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ የሚረዳኝን መረጃ ለማግኘት አዘውትረው የስብከት ስርዓቶችን ከሚካፈሉ ምዕመናን ጋር ውይይት አካሂጃለሁ፡፡

---

* ከመስክ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ የሰበሰብኳቸው ተረኮች በአባሪ ሁለት ውስጥ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

## 1.8. የአጠናን ዘዴ

በዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ የዋሉ መረጃዎች (ቃላዊ ዝርው ተረኮች) ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች፤ ከሰባክያነ ወንጌል፤ በቀጥታ የተሰበሰቡ ሲሆን እነዚህን መረጃዎች ለማጠናከር የሚረዱ ተጨማሪ መረጃዎች ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች /ከቤተ ክርስቲያኗ ምዕመናን እና ባለሙያዎች/ ተሰብስበዋል። በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ስር ባሉ ቤተ ክርስቲያናት የሚሰብኩ መምህራን በቁጥር እጅግ በርካታና ስብጥራቸውም የተበታተነ በመሆኑ በትክክል ብዛታቸውን ማወቅ አዳጋች ሆኗል። ከዚህ ጎን ለጎን ከሰባክያነ ወንጌሉ ከፊሉ በንዑስ ርዕስ 1.6 ሥር በተጠቀሱ ምክንያቶች የጥናቱ መረጃ አቀባይ ለመሆን ፈቃደኛ ያልሆኑበት አጋጣሚ ነበር። በመሆኑም በዚህ ጥናት የመረጃ አቀባዮች የአመቺ ወይም የግኝት ናሙና አመራረጥ ዘዴን (convenience sampling) መሠረት በማድረግ ተመርጠዋል። ከመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች አይነታዊ (qualitative) ሲሆኑ፣ በመረጃዎቹ ላይ የተሰጠው ትንታኔ በአቀራረቡ ገላጭ (descriptive) ነው።

## ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ክለሳ ድርሳን

ይህ ምዕራፍ በስሩ ሁለት ንኡሳን ክፍሎችን ይዟል፡፡ ከንኡሳን ክፍሎቹ ቀዳሚው ከዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥናታዊ ሥራዎች የሚቃኙበት ነው፡፡ ቀጣዩ ንኡስ ክፍል ደግሞ ለጥናቱ ንድፈ ሐሳባዊ መሠረት ለመጣል የሚረዱ ፅሁፎች የሚዳሰሱበት ይሆናል፡፡

### 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ እንዲሁም በውጪ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ የትምህርት ክፍሎች የተሠሩና ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው አስራ ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች (ዲማፆች) እና ስምንት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ቲሲሶች ይቃኛሉ፡፡ በዚሁ መሰረት የቅኝቴን መነሻ ከዲማፆቹ አደርጋለሁ፡፡

በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ አምስት ያህል ዲማፆች በ1970ዎቹ ተሰርተው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ዲማፆች ያዕቆብ ወልደማርያም (1974) "የከፋ ተረቶች"፣ ደሀብ ተክሉ (1974) "የትግርኛ ተረቶች"፣ እንግዳ ወልደ ሰማያት (1974) "በጭላሎ አውራጃ በአማርኛ የሠማኒቸው ተረቶች"፣ አወቀ ውቤ (1975) "የወላይትኛ ተረቶች"፣ ሙልጌታ ነጋሳ (1976) "ከጅባትና ሜጫ አውራጃ የተሰበሰቡ የገበሬን ህይወት የሚያንፀባርቁ የኦሮምኛ ተረቶች" በሚል ርዕስ ያቀረቧቸው ጥናቶች ናቸው፡፡ ዲማፆቹ ትኩረታቸውን ይዘትና ቅርፃዊ ጥናት ላይ አድርገው ሲቀርቡ በተለይ ያዕቆብ (1974) እና እንግዳ (1974) ስብስብ ተረኮቻቸውን ገፀባህርያትን መሰረት አድርገው ሰውነክ፣ እንስሳነክ፣ ድብልቅ በማለት በዝርያቸው መድበዋል፡፡ በሌላ በኩል ደሀብ (1974) ስብስቦቿን በስድንባብ፣ በስድንባብና በግጥም እንዲሁም ግጥማዊና ድራማዊ ተረቶች በማለት መድባለች፡፡ እነዚህ አጥኚዎች ተረኮቻቸውን በዝርያ ለመመደብ ባደረጉት ጥረት የባህል ባለቤቶቹ አመዳደብ ምን ይመስላል የሚለውን አላሳዩም፡፡ ይህም አጥኚዎቹ ተረኮቻቸውን ለመመደብ የተገለገሉባቸው መንገዶች ምሉዕ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ዲማፆች በአጠቃላይ ሲታዩ ለአውዳዊ (contextual) መረጃ ትኩረት ሰጥተው የቀረቡ አይደሉም፡፡ ይሁን እንጂ ሙሉጌታ (1976) በአንፃራዊነት ሲታይ ከሌሎቹ ዲማፆች በተሻለ ለአውዳዊ መረጃ ትኩረት ሠጥቶ ቅኝት አድርጓል፡፡ አወቀ (1975) በሌላ በኩል ስለስነቃል ክዋኔ፣ ስለተራኪና አድማጭ ሚና ሰፊ ንድፈ ሀሳባዊ ማብራሪያ ሠጥቷል፡፡ ይሁን



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

እና አጥኚው ተጠኚ ተረቶች ላይ ትንታኔ ሲያደርግ ይህንን በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ያስቀመጠውን ሀሳብ ከተጠኚ ተረቶች ጋር ሳያዛምድና ምሳሌ እየሰጠ ሳያብራራ አልፏል፡፡

በዘርፉ በ1980ዎቹ ከተሰሩ ዲማፆች መካከል፣ አበበ ከበደ (1982) "በሰሳሌ አውራጃ የሚነገሩ የአማርኛ ተረቶች"፣ ጥሩነህ አበራ (1982) "የበኩቂኒ ኦሮምኛ ተረቶች"፣ ሰውነት መኮንን (1984) "በሞጣ አውራጃ የሚነገሩ የአማርኛ ተረታ ተረቶች" ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ ዲማጾች በ1970ዎቹ እንደተሰሩት ዲማፆች ሁሉ ትኩረታቸውን በይዘትና ቅርፃዊ ጥናት ላይ ያደረጉ ሲሆን ጥናቶቹ፣ በተለይ ጥሩነህ (1982)፣ ሰውነት (1984) በቀዳሚው ዘመን ከተሰሩ ዲማፆች በተሻለ ስፋት ለተረት ክዋኔ፤ ለአድማጭና ተራች ሚና እንዲሁም ለመከወኛ አውድ ትኩረት ሰጥተው ቀርበዋል፡፡

የዚነት አብዱልረሺድ (1991) "የሀረሪ ተረቶች ስብስብና ትንተና"፣ የተስፋዬ ሊሞሬ (1993) "የሀድይኛ ተረታ ተረቶች ይዘት"፣ የሙሉነህ ጉግሳ (1993) "የክስታኔ ተረቶች"፣ የሱሩር በድሩ (1995) "የስልጤ ተረቶች ይዘት ጥናት" ሌሎቹ በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ተሰርተው የቀረቡ ዲማፆች ናቸው፡፡ ተስፋዬ (1993) እና ሙሉነህ (1993) የየተረቶቹን ይዘትና ቅርፅ የተመለከቱ ሲሆን ዚነት (1991) እና ሱሩር (1995) ይዘትን በተናጠል ተመልክተዋል፡፡ ተስፋዬ (1993) ስለተረቶቹ ክዋኔና የመከወኛ አውድ መረጃን ከመስጠት አንፃር የተሻለ ሆኖ ታይቷል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ እነዚህ አስራ ሁለት ዲማፆች፣ ከቅርፅና ከይዘት አንፃር ለስብስብ ተረቶች ትንታኔ የተሰጠባቸው ናቸው፡፡ በተለይ ከይዘት አንጻር ተረቶች ላይ በተደረገ ትንታኔ አብዛኛዎቹ አጥኚዎች ተረቶች ከአንድ በላይ ይዘት ሊኖራቸው እንደሚችል መረዳታቸውን በየፅሁፎቻቸው ገልፀዋል፡፡ ይሁን እና የተረቶቹ ይዘቶች ናቸው ተብለው በጥናቶቻቸው የተጠቆሙት ነጥቦች በተረቶቹ ውስጥ ጎልተው የሚታዩት ወይም ዋነኛ ይዘቶች መሆናቸውን አጥኚዎቹ ጠቁመዋል፡፡ በዚህ መሰረት በአመዛኞቹ ጥናቶች ሞኝነት፣ ብልጠት ወይም ብልሀት፣ ትዳር፣ ትግግዝ፣ ኑዛዜ፣ የእንጀራ እናት ጭካኔ የሚሉ ነጥቦች በዋና ይዘትነት ተጠቅሰዋል፡፡

ቅኝታችንን ወደ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ቲሲሶች ስንመልስ አብዱልቃድር ሀጂ (1982) "Some Cultural Elements as Reflected in Somali Folktales" ተስፋዬ ገብረማርያም ሐይሉ (1990) "A Study of Major Theme in Jablawi Folktales" መላክነህ መንግስቱ (1990) "The Major Themes and Motifs of Southern Agew Folktales" ጥናቶችን እናገኛለን፡፡*
እነዚህ ጥናቶች ዋነኛ ትኩረታቸውን ጭብጣዊ ጥናት (thematic analysis) ላይ ያደረጉ

* በንኡስ ርእሱ ከተቃኙ ስምንት ያህል ቲሲሶች መካከል ከማንያለው አባተ ቲሲስ በስተቀር ቀሪዎቹ ሰባት ቴሲሶች የተሰሩበት አመተምህረት የተጠቀሰው የእ.ኤ.አ. መሰረት አድርጎ ነው፡፡

በመሆናቸው ከዚሁ ከትኩረት አቅጣጫቸው መመሳሰል አንፃር በአንድ ጎራ መድበን ልናያቸው እንችላለን፡፡ የሶስቱ ጥናታዊ ጽሑፎች ዋነኛ አላማዎች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡ አብዱልቃድር (1982) በተረቶቹ የሚንፀባረቁትን ባህላዊና ስነልቡናዊ ባህርያት (elements) በመግለፅ የባህል ባለቤቶቹን (የሶማሊያን ማህበረሰብ) መረዳት የሚል፤ ተስፋዬ (1990) በተጠኚ ተረቶች ዋና ዋና ጭብጥ ላይ በማተኮር የተጠኚውን ማህበረሰብ እምነት፣ ማህበራዊ እሴት፣ በአጠቃላይ የማህበረሰቡን ርዕዮተ ዓለም (world view) መረዳት የሚል፣ እንዲሁም መላክነህ (1990) የአገውን ተረቶች በመሰብሰብና ጭብጣዊ ጥናት በማድረግ የተረቶቹን ማህበረ-ባህላዊ ጠቀሜታ መግለጥ የሚል አላማን በአቢይነት አስቀምጠዋል፡፡

አብዱልቃድር (1982)፣ መላክነህ (1990) እና ተስፋዬ (1990) ጥናቶች ለአውዳዊ መረጃ ከሰጡት ትኩረት አንፃር ሲቃኙ ቀዳሚዎቹ ሁለቱ ጥናቶች ለዘርፉ ዋነኛ ትኩረት እንዳልሰጡ ይታይል፡፡ በተለይ አብዱልቃድር፡-

> *Story-telling naturally attracts listeners, and when I was taking down the tales there was always a group of people, children or some adults to laugh, comment, or just interrupt, to throw in their version, or just to snatch what was to come next from the informer's mouth. At times, this grew so intolerable that I and the informant had to sit shut in a hut for hours. (1982፣23)*

በማለት፣ መላክነህ *"Most of the tales were then recorded in cassettes for the sake of authenticity inside a closed room to avoid the crowd and extraneous sound"* (1990፣44) በሚል ያነሱት ሀሳብ አጥኚዎቹ በየጥናቶቻቸው ለተጠኚ ተረኮች ክዋኔ አውድ፣ ለተራኪና አድማጭ ማንነትና መስተጋብር አናሳ ትኩረት መስጠታቸውን በተጨባጭ የሚያሳይ ነው፡፡ ተስፋዬ (1990) በጥናቱ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አውዳዊ መረጃን አካቶ በመገኘቱ ከቀዳሚዎቹ ጥናቶች በዚህ ረገድ የተሻለ ሆኖ ታይቷል፡፡*

---

* ምንም እንኳን ተስፋዬ (1990) ለአውዳዊ መረጃ የተሻለ ትኩረት ሰጥቷል ቢባልም *Consequently previously told folktales were narrated and renarrated either in Oromo or in Amharic language. Meanwhile recording of folktales is done both in the open (directly) or indirectly, as condition permitted. For this purpose the researcher carried a very small tape recorder, that at times, it was possible to record some of the tales <u>without the speaker's notice</u>.*(ተስፋዬ 1990፣11-12፣) /አፅንኦቱ ከእኔ/

በሚል ያነሳው ሀሳብ Wm. Hugh Jansen, "Ethics and Folklorist" በተሰኘው ዕሁፍ፣ አንድ የፎክሎር ባለሙያ የመረጃ አቀባዩን ፍላጎትና ፍቃድ ሊያከብር ይገባል (ዓ.ም. ያልተጠቀሰ፣320-322) በሚል ካነሱት ሀሳብ ጋር የሚጋጭና የሙያውን ስነምግባር አሟልቶ ስለማክበሩ ጥያቄ የሚያስነሳበት ነው፡፡

ቀሪዎቹ አምስት ያህል ቲሲሶች ሳህሉ ኪዳኔ (1996) "Borana Oromo Prose Narratives: A Contextual Study", ይሄነው ጀምበር (1996) "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojam", ባይለየኝ ጣሰው (1999) "Anyuaa Oral Prose Narratives Ethnic Genres and Social Function", አብርሃም አለሙ(2000) "Jimma Oromo Oral Prose Narrative: A Preliminary Descriptive Analysis", እና ማንያስለው አባተ (1999) "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው" በሚል ርዕስ የቀረቡ ናቸው። ቲሲሶቹ ትኩረታቸውን ከቀዳሚዎቹ ሶስት ቲሲሶች በተለየ ከጭብጣዊ ጥናት ወደ አውዳዊ ጥናትና ስብስብ ተረኮችን በዘውግ (genre) ወደ መመደብ የመለሱ ናቸው። በዚህ መሰረት ሳህሉ (1996)፣ ባይለየኝ (1999)፣ አብርሃም (2000) እና ማንያስለው (1999) ለየጥናቶቻቸው መሰረት የሆኗቸውን ስብስብ ተረኮች እንደቅደም ተከተላቸው፤ Duri-duri, Mamakasa, Arga-ageti; Leere, Wae, Angade; Seenaa (Taarika), Oduu Duri, Qoosaa; ቶስ እና ኤሼሽ በማለት የባህል ባለቤቶቹን የአመዳደብ ስልትና ስያሜ መሠረት አድርገው በዝርያ መድበዋል። ይሄነው (1996) እንዲሁ የባህል ባለቤቶቹን መንገድ ተከትሎ ተረኮችን በዘር የመክፈል ተገቢነትን በፅሁፉ ጠቅሷል። ይሁን እና የባህል ባለቤቶቹ የአመዳደብ ዘዴ እንደ አካዳሚያዊው (analytical) ዘዴ ሁሉ ተረኮችን በየዘሮቻቸው በመክፈሉ ረገድ ያለበትን ችግር ጠቅሶ በጥናቱ ስብስብ ተረኮቹን አካዳሚያዊውን መንገድ ተከትሎ፤ folktale, legend, genealogies በማለት ከፋፍሏል።

ከዚህ ጎን ለጎን የተጠኚ ተረኮች ፈጣሪ ማህበረሰቦች ተረኮቻቸውን በየዝርያቸው ለመመደብ መሰረት ያደረጉት ምንን ነው የሚለው ሀሳብ በየቲሲሶቹ ተቃኝቷል። በዚህ መሰረት ለየምድቦቹ የተሰጡ ስያሜዎች መሰረታቸው፤ ባይለየኝ (1999) ባህላዊ ፍቺ፣ የተረኮቹ ይዘት፣ የከዋኝ እድሜ መሆኑን፤ አብርሃም (2000) እውነተኛና ፈጠራ መሆንና የሚተረቱበት አላማ መሆኑን፤ እንዲሁም ማንያስለው (1999) እውነተኛና እውነተኛነታቸው አጠራጣሪ መሆንና የመተረቻ ወቅት መሆኑን ገልፀዋል። በዚህ ረገድ ሳህሉ (1996) አካዳሚያዊውን መንገድ ተከትሎ ተረኮችን በዝርያ ለመክፈል እንደሚደረግ ሙከራ ሁሉ የባህል ባለቤቶቹ የመመደቢያ መንገድም የራሱ ችግር እንዳለው ገልጿል። አያይዞም የባህል ባለቤቶቹ እራሳቸው አንዳንዶቹን ተረኮች ከአንድ ጎራ ለመመደብ እንደሚቸገሩ በመጥቀስ መስፈርቶቹም አንድ ወጥ ሳይሆኑ አንዳንዴ መዋቅር (structure) ሌላ ጊዜ ማህበራዊ ጠባያት (social features) ሌላ ጊዜ ደግሞ ርዕስ ጉዳይ (subject matter) የሚሆኑበት አጋጣሚ እንዳለ ገልጿል። በተለያየ መጠንና ደረጃ ይሁን እንጂ

በእነዚህ አምስት ጥናታዊ ፅሁፎች አውዳዊ መረጃዎች ከቀዳሚዎቹ ጥናቶች በተሻለ ስፋትና አንዳንዴም በዋና ትኩረትነት (ለምሳሌ አብርሃም 2000) በየጥናቶቹ ተቃኝተዋል፡፡

እነዚህ ጥናቶች በጥቅሉ ሲታዩ ትኩረታቸውን በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ማድረጋቸው በፅሁፉ መነሻ ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ትኩረቱን በተመሳሳይ መልኩ በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ካደረገው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ያደርጋቸዋል፡፡ ይሁን እና ከላይ የተጠቀሱት የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎች፣ አንድን ዘር (ethnic) መሰረት አድርገው ፎክሎርን የፈጠሩ ቡድኖችን (ማህበረሰቦችን) ቃላዊ ዝርው ተረኮች ያጠኑ ናቸው፡፡ ይህ የእኔ ጥናት ከዘር በተለየ የፎክሎር ፈጣሪ ማህበሩ ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የእኔ ጥናት ሃይማኖትን የጋራ ጉዳያቸው አድርገው ቃላዊ ዝርው ተረኮችን የሚፈጥሩ ቡድኖች ላይ አትኩሮቱን አድርጓል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በተጠቃሾቹ ጥናታዊ ፅሁፎች በዋና ትኩረትነት ያልታየ አንድ የቃላዊ ዝርው ተረክ ገፅታ የሚያይ በመሆኑ የሚሞላው አንድ ክፍተት ያለው እንዲሆን ያስችለዋል፡፡

በአጠቃላይ በንኡስ ርዕሱ ስር የተቃኙ ጥናታዊ ጽሁፎች የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተቀርሰው እንዲቆዩ ከማድረግ አኳያ ጉልህ ድርሻ ያላቸው ናቸው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በተለይ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡት ፅሁፎች በመስኩ ጥናት ለሚያደርጉ የፎክሎር ተማሪዎች የተለያዩ የአጠናን መንገዶችን (approaches) ከማስተዋወቅና በዘርፉ ግንዛቤን ከማስጨበጥ አንፃር ከፍተኛ ግምት ሊሰጣቸው የሚገባቸው ሥራዎች ናቸው፡፡

## 2.2. ክለሳ ድርሳን

በምዕራፍ አንድ ውስጥ ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት አቢይ አላማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ክዋኔ፣ የክዋኔ አውድና ተረኮቹ በባህል ባለቤቶቹ ዘንድ ያላቸውን ተግባር በቅርበት ማጥናት ነው፡፡ ይህ ንኡስ ርዕስ በተረኮቹ ክዋኔ አውድ \context\ እና ተግባር \function\ ዙሪያ ለሚደረግ ቅኝት ንድፈ ሀሳባዊ መሠረት ለመጣል የሚያስችሉ ፅሁፎች የሚቃኙበት ይሆናል፡፡

### 2.2.1. አውዳዊ ጥናት (contextual analysis)

በፎክሎር ጥናት ከመስክ ለተሰበሰቡ ቴክስቶች ዋና ትኩረት ይሠጥ የነበረው የፎክሎር ጥናት አቅጣጫ ትኩረቱን ከቴክስት ወደ አውድ መመለስ የጀመረው፤ በአንድ የፎክሎር ቅርፅ ውስጥ የሚነሳው መልዕክት ወይም ሀሳብ በተግባር የሚታየው በቴክስቱ ውስጥ ሳይሆን ፎክሎራዊ

ሁነቱ በሚከወንበት ወይም በተግባቦታዊ ሂደቱ ውስጥ ነው፤ የሚለውን ሀሳብ የሚያራምዱ ወጣት የፎክሎር ባለሙያዎች (እነ Roger Abrahams, Dan Ben-Amos, Alan Dundes...) በ1960ዎቹ በተነሱበት ጊዜ እንደሆነ Dorson (2003, 251) ይጠቅሳሉ፡፡

Dan Ben-Amos እንደሚሉት የፎክሎር ቴክስት ትርጉም፣ ቴክስቱ በአውድ ውስጥ ያለው ትርጉም ነው፡፡ አንድን የፎክሎር ቴክስት ቀድሞ ከነበረበት አውድ ልዩ ወደሆነ አውድ ብንወስደው የቴክስቱ ትርጉም ወይም ፍቺ ቀድሞ ከነበረው ወደሌላ አዲስ ፍቺ ወይም ትርጉም ይለወጣል፡፡ ስለሆነም አንድን ቴክስት በተገቢው ሁኔታ ለመረዳት ቴክስቱ በአውድ ውስጥ ሊጠና ይገባል (1993፣ 210-211)፡፡

በአጠቃላይ በፎክሎር ጥናት በተለይ ደግሞ ተግባራዊ አንፃርን (functionalist approaches) መሠረት ባደረገ ትንተና፣ ስለፎክሎር ማህበራዊ አውድ (social context) ፤ ልዩ ልዩ የፎክሎር ቅርፆች ስለሚከወኑበት ቦታና ጊዜ፣ ስለከዋኞች ማንነትና ስለአከዋወን ስልታቸው፣ ስለታዳሚ ተሳትፎ ወዘተ. በበቂ ሁኔታ ገለፃ ሊሰጥ እንደሚገባ Bascom (1965፣ 281) ያስረዳሉ፡፡

በፎክሎር አውዳዊ ጥናት፣ አውድ የሚባለው የቱ ነው በሚለው ሀሳብ ዙሪያ የዘርፉ ባለሙያዎች ልዩ ልዩ ውይይቶችን አካሂደዋል፡፡ "The Notion of Context" በተሠኘው መጣጥፋቸው Katharine Young አንድ የፎክሎር ቅርፅ የሚከወንበትን አካባቢ በጥቅሉ ወይም ያለ ልዩነት የፎክሎር ቅርፁ አውድ አድርጎ መውሰድ ስህተት ነው፡፡ አንድን አውድ፣ አውድ የሚያስብለው የፎክሎር ቅርፁ ለሚከወንበት አካባቢ ያለው የቦታ ቀረቤታ ሣይሆን የተገቢነት ደረጃ ነው ብለዋል፡፡ Young ሁኔታውን ሲያብራሩም "Not only is not all of the surround[ing] context but also not all of the contexts are in the surround[ing]" (1995፣116) አንድ የፎክሎር ቅርፅ የሚከወንበት አካባቢ በጥቅሉ ብቻም አይደለም እንደ አውድ መቆጠር የሌለበት ሁሉም አውዶች የፎክሎር ቅርፁ በሚከወንበት አካባቢ ውስጥ ብቻ ተጠቃለው የሚገኙ አለመሆኑም ጭምር መታወቅ አለበት ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል Richard Bauman አውድን፣ ባህላዊ አውድ (cultural context) እና ማህበራዊ አውድ (social context) በማለት በሁለት መሠረታዊ ክፍሎች ከፍሎ ማየት እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡ እንደ Bauman ገለፃ ባህላዊ አውድ፣ አንድ የፎክሎር ቅርፅ ምን ሀሳብ ይገልፃል፣ በባህል ውስጥ ቦታው የት ነው፣ ከሌሎች የፎክሎር ቅርፆች ጋር እንዴት ይዛመዳል የሚለውን ሀሳብ ያካትታል፡፡ ማህበራዊ አውድ ደግሞ የባህል ባለቤቶቹ እነማን ናቸው፣ የፎክሎር ቅርፁ

በግለሠባዊ ህይወት ውስጥ ያለው ድርሻ ምንድነው፣ በማህብራዊ ሁኔታ ውስጥስ ያለው ጠቀሜታው ምን ይመስላል የሚለውን ሀሳብ የሚያካትት ነው። /ቀን ያልተጠቀሰ፣ 97/

Dan Ben-Amos እንዲሁ መሠረታዊና ሁሉን አቀፍ (inclusive) ናቸው ያሏቸውን የአውድ አይነቶች ባህላዊ አውድ (cultural context) እና አካባቢያዊ አውድ (situational context) በማለት በሁለት ክፍሎች መድበው አስቀምጠዋል። ባህላዊ አውድ እንደባለሙያው ገለፃ፣ የባህል ባለቤቶቹ የሚጋሩትን እውቀት፣ ስነ ምግባርን አስመልክቶ ያላቸውን የጋራ መግባባት፣ የእምነት ስርአትንና ስለታሪክ ያላቸውን ግንዛቤ ሞራላዊና ህጋዊ መመሪያቸውን ሁሉ ያካትታል። አካባቢያዊ አውድ ደግሞ እንደ Ben-Amos ገለፃ ከYoung (1985፣116) ተወስዶ ከላይ የተጠቀሰው የተገቢነት (relevance) ፅንሰ ሀሳብ ሊገልፀው ይችላል። ምንም እንኳን የተገቢነት ፅንሰ ሀሳብ እንደየባለሙያው የግል ስሜት የመወሰን አዝማሚያ (subjectivity) ቢታይበትም በአውዳዊ ጥናት ትግበራ ውስጥ ሊሰራበት ይችላል ብለዋል።

በአጠቃላይ የፎክሎር ጥናት መስክ፣ በዘርፉ በሚካሄድ ጥናት ትኩረት ተሠጥቶት ሊጠና የሚገባው ጉዳይ በአንድ በኩል ቴክስት በሌላ በኩል ደግሞ አውድ ነው በሚሉ ሁለት ፅንፈኛ አንፃሮች ዙሪያ ሲሽከረከር ቆይቷል። ይሁን እና Young እንደሚሉት ሁለቱም አንፃሮች የየራሳቸው የሆነ ውስንነት (limitations) አላቸው። አጠቃላይ ትኩረትን በቴክስት ላይ ብቻ መወሰን ፎክሎርን በብቃት ለመረዳት የማያስችለውን ያህል መላው ትኩረትን በአውድ ዙሪያ መገደብም የዛኑ ያህል የጥናት ውጤትን ትክክለኛነት ይጎዳል። በመሆኑም የፎክሎር ባለሙያው በአውድና በቴክስት ላይ የሚኖረው ትኩረት ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል /1985፣ 115-116/።

### 2.2.2. ተግባራዊ ጥናት (functionalist approaches)

በስነቃል ጥናት ከመስክ የተሠበሠቡ ልዩ ልዩ ስነቃላዊ ቅርፆችን ተንትኖ ለመረዳት የሚያስችሉ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች ባለፉት አስርት አመታት በመስኩ ባለሙያዎች ተዋውቀዋል። ተግባራዊ ጥናት ከነዚህ ንድፈ ሀሳቦች መካከል አንዱ ሲሆን በዚህ ጥናት በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ለሚደረግ ትንታኔ መሠረት ነው።

በፎክሎር ተግባራዊ ጥናት ዙሪያ ቅኝት ካደረጉ ባለሙያዎች መካከል እነ Simsም (2005) ተጠቃሽ ናቸው። ፎክሎር የፈጣሪው ማህበረሰብ ወይም ቡድን እምነትና ልዩ ልዩ መረጃዎች የሚተላለፍበት ቀጣይነት ያለው ሂደት መሆኑን እነ Sims ሲገልፁ፣ የፎክሎር ተግባራዊ ጥናት ለዘርፉ ባለሙያዎች፣ ሰዎችን ከሚፈጥሯቸው ልዩ ልዩ የፎክሎር ቅርፆች ጋር አዛምዶ ወይም

አገናዝቦ ለመረዳት የሚያስችል መንገድ እንደሚሰጣቸው ያስረዳሉ። አያይዘውም ባለሙያዎቹ፣ ፎክሎር ለሚፈጥረውና ለሚገለገልበት ማህበረሰብ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? ወይም ምን መልዕክትን ያደርሰዋል? የሚለው ነጥብ፣ ጥበቡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ተግባር ለማወቅ ወይም ለመረዳት በፎክሎር ባለሙያዎች ዘንድ በዋናነት የሚነሳ ጥያቄ መሆኑን ይገልፃሉ። /2005፣174/

ስለፎክሎር ተግባር ምንነት፣ ብያኔና ማብራሪያ ከሰጡ ባለሙያዎች መካከል Elliott Oring ሌላው ተጠቃሽ ባለሙያ ናቸው። Oring ስለፎክሎር ተግባር ምንነት፡-

> *Function is thus the contribution which a partial activity makes to the total activity of which it is a part. The particular social usage, therefore, is the contribution it makes to the continuity of the social structure, that is, the maintenance of the life process of the society. / 1976፣68/*
>
> ተግባር ስንል አጠቃላይ በሆነ እንቅስቃሴ ወይም ሁኔታ ውስጥ የታቀፈ አንድ ወይም ከፊል ሁነት፣ለአጠቃላዩ እንቅስቃሴ ወይም ሁነት የሚያበረክተው ድርሻ ነው። በዚህ መሰረት አንድ ማህበረሰብረ በቋንቋው አማካይነት የሚገልፀው ነገር ተግባር ሲባል የማህበረሰቡ፣ ማህበራዊ አደረጃጀት ወይም መዋቅር ባለበት ሁኔታ ተጠብቆ እንዲዘልቅ የሚያበረክተው ድርሻ ማለትም የማህበረሰቡን ህልውና በማስጠበቅ ረገድ ያለው ሚና ማለት ነው።

ብለዋል።

በፎክሎር ተግባራዊ ጥናት ልዩ ልዩ የፎክሎር ወይም የስነቃል ቅርፆች ለባህል ባለቤቶቹ ያላቸው ፋይዳ ወይም ተግባር ይህ ብቻ ነው ብሎ ወስኖ መናገር አዳጋች ይሆናል። ስነቃላዊ ቅርፆች፣ እንደየሚከወኑበት አውድና እንደየሚከወኑበት አላማ መለያየት ልዩ ልዩ ተግባር ሊኖራቸው ይችላል። ይሁን እና የስነቃል ቅርፆቹ ሊኖራቸው ከሚችል ዘርፈ ብዙ ተግባራት መካከል ጉልህና ተዘውታሪ ሆነው የሚወጡትን በመለየት ስነቃል በጥቅሉ ሊኖረው የሚችለውን ተግባር ማሣየት ይቻላል።

ተዝናኖትን መፍጠር የስነቃል አንዱ ተግባር መሆኑን Bascom (1965)፤ Okpehow (1982); ፊቃደ (1991) ይጠቅሳሉ። እንደባለሙያዎቹ ገለፃ በስነቃል አማካኝነት ተራቹ ማህበረሠብ አስደሳች ምናባዊ አለምን በመፍጠር የሠው ልጅ በዕለት ተዕለት ኑሮው ከሚያልፍበት



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አድካሚና አሠልቺ ህይወቱ ጊዜያዊ እፎይታንና ደስታን እንዲያገኝ ያስችሉታል፡፡ የተራቹን ማህበረሠብ ልዩ ልዩ እሴቶች ማስተማሪያ ሆኖ ማገልገል ሌላው የስነቃል ተግባር መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ባለሙያዎች ይጠቁማሉ፡፡ እንደባለሙያዎቹ ገለፃ ልዩ ልዩ የስነቃል ቅርፃች ለባህል ባለቤቶቹ ስነምግባርን፣ የአኗኗር ብልሃትን ወይም መርህን ማስተማሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

ተራቹ ማህበረሠብ ከሌላው ማህበረሠብ የሚለይበትን ገፅታ በማመልከት የራሱን ማንነት እንዲፈጥር፣ የራሱን ገፅታ በመገንባት ብሄራዊ ስሜት እንዲያጎለብት ማስቻል ሌላው የስነቃል ተግባር መሆኑን Okpehow (1982) ሲገልፁ፤ Bascom (1965)፤ ፈቃደ (1991) ደግሞ በስነቃል አማካኝነት ተራቹ ማህበረሠብ የእሴት ስርአቱን ተገቢነት ወይም ትክክለኛነት በመግለፅ አባላቱ ከእሴት ስርአቱ አፈንግጠው እንዳይወጡ ለመቆጣጠሪያነት እንደሚገለገልባቸው ይጠቅሳሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች ከፎክሎር ወይም ከስነቃል ዘርፌ ብዙ ተግባራት ከብዙ በጥቂቱ እንደማሳያ የሚሆኑ ሲሆን፣ እንደየፎክሎር ቅርፃቹ፣ እንደየተራቹ ማህበረሠብ፣ እንደየሚከወኑበት አውድ ወዘተ. መለያየት ጥበቡ ከዚህ የሠፋና የተለየ ፋይዳ ወይም ተግባር ሊኖረው እንደሚችል ከግንዛቤ ማስገባት ይገባል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረክ ዓይነቶች

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሚደረጉ የስብከት ስርዓቶች ወቅት በአካል በመገኘት (በተሳታፊ ተመልካችነት) እንዲሁም በቃለመጠይቅ በቁጥር ከስልሳ በላይ የሚሆኑ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ ስብስብ ተረኮቹ በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ የስብከት ስርዓቶች ወቅት ከሚነሱ ሀሳቦች ጋር በተዛምዶ የቀረቡ ቢሆኑም አንዳቸው ከሌላቸው፤ ከቅርፅ፣ ከመዋቅር፣ ከርዕሰ ጉዳይ ወዘተ. አንፃር የሚመሳሰሉበት እንዲሁም የሚለያዩበት የየራሳቸው ልዩ ልዩ ባህርያት ያሏቸው ናቸው፡፡ እነ Martha C. Sims, Barre Toelkenን ጠቅሰው፡-

> *Just as doctors do not talk about the body without knowing all the principal parts, just as a linguist cannot talk about language without a vocabulary of terms that describe words, sounds, and meaning, so the folklorist does not discuss folklore without a sound knowledge of its genres. . . .Without a generic terminology, we would have little hope of understanding each other.* (2005፣ 12)

ሲሉ ይህ የToelken ገለፃ፡-

> ዶክተሮች ዋና ዋናዎቹን የአካል ክፍሎች ጠንቅቀው ሳያውቁ ስለ አጠቃላዩ አካል እንደማይናገሩ፤ የስነልሳን ተመራማሪዎች ቃላትን፣ ድምፆችንና ትርጉምን (ፍቺን) የሚገልፅ የስያሜ ቃላት መድበል ሳይኖራቸው ስለቋንቋ መነጋገር እንደማይችሉ ሁሉ ፎክሎሪኞችም ስለፎክሎር ዘውግ በቂ ግንዛቤ ሳይኖራቸው ስለፎክሎር አይወያዩም…፡፡ስለፎክሎር ዘውጎች ስያሜ ቃል በሌለበት በዘርፉ ባለሙያዎች መካከል መግባባት ይኖራል ማለት የማይቻል ይሆናል፡፡ የሚል የአማርኛ ተቀራራቢ ፍቺን የሚይዝ ይሆናል፡፡

ይህ ምዕራፍ ይህን የእነ Simsን ሀሳብ አግባብነት ከግንዛቤ በማስገባት በስብስብ ተረኮች ላይ ቀጣይ ጥናት (ትንተና) ከመደረጉ አስቀድሞ ተረኮቹ ከየትኞቹ የፎክሎር ዘውጎች እንደሚመደቡ ለመለየት ጥረት ያደርጋል፡፡ የባህል ባለቤቶቹ ለየተረኮቻቸው የሚሰጧቸው እውቅና ወይም የአመዳደብ ስርአት (categorization system) እና ስያሜ መኖር አለመኖሩ ይመረምራል፡፡ ተረኮቹን ይበልጥ ሊያዛምዷቸው በሚችሉ ባህርያት ላይ በመመስረት በየዝርያቸው

(በአይነታቸው) ለመመደብና የምድብ ስርዓቱ ስለተመሰረተበት ባህርይ ገለፃ ለመስጠትም ይጥራል፡፡

የቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችን በአይነት ለመመደብ የሚያስችል አንድ ወጥ የሆነ፣ የሁሉን ባህል አቀፍ (universal) ስርዓት መዘርጋት አዳጋች እንደሚሆን (Finnegan፤1970፤320፣ Vansina፤1985፤82) ያስረዳሉ፡፡ የቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች ከየሚነገሩበት ማህበረሰብ ባህል ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው፣ የባህል ባለቤቶቹን ልዩ ልዩ እሴቶች በአጠቃላይ ለዓለም ያላቸውን አተያይ የሚያንፀባርቁ ቃላዊ ጥበቦች ናቸው፡፡ በመሆኑም ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በየዝርያቸው ለመመደብ በሚደረግ ጥረት የባህል ባለቤቶቹ ለየተረኮቻቸው የሚሰጧቸው እውቅና ወይም የአመዳደብ ስርአት እና ስያሜ መኖር አለመኖሩ ከወዲሁ ትኩረት ተሰጥቶት ሊመረመር እንደሚገባ የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡

በዚህ ጥናት ስብስብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በአይነታቸው ለመፈረጅ በተደረገ ጥረት በቀዳሚነት የተረኮቹ ተራች ማህበረሰብ (የባህል ባለቤቱ) ስለተረኮቹ ያለው አጠቃላይ ግንዛቤ ምን ይመስላል ለሚለው ሀሳብ ቅድሚያ በመስጠት ቅኝት ተደርጓል፡፡ በቅኝቱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና "ሙያተኞች" (ሰባክያነ ወንጌል፣ የስነ መለኮት ተማሪዎችና መምህራን እንዲሁም የአብያተ ክርስቲያናት የአስተዳደር ሰራተኞች) ተካተዋል፡፡ በዚህ መሰረትም በተለያየ የዕድሜ፣ የፆታና የስራ ሁኔታ ላይ ከሚገኙ የቤተ ክርስቲያኗ ምእመናን ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ተደርጓል፡፡ በውይይቱም በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በአብዛኛው በጅምላ "ታሪኮች" በሚል ስያሜ ከመጥራት በዘለቀ ምእመኑ ለቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የተለየ ስያሜም ሆነ የአመዳደብ ስርዓት እንዳልዘረጋላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ "ከሙያተኞች" ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ በአብያተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ተረኮች በባህል ባለቤቶቹ ዘንድ በአይነት ተለይተው የሚታወቁበት አንድ ቋሚ ስርዓትም ሆነ ስያሜ እንደሌላቸው የሚያሳይ መረጃ ተገኝቷል፡፡ ኢየሱስ ለገበሬዎች በዘር፣ ለሴቶች በቡኮ፣ ለአሳ አስጋሪዎች በመረብ እየመሰለ ከሚያስተምርበት ስርዓት የተወረሱ በመሆናቸው ተረኮቹ በአንዳዶች ዘንድ "ምሳሌዎች" በሚል የወል መጠሪያ እደሚታወቁ (በዕደማርያም፤29/8/2002፣ ቃለመጠይቅ ካሴት ተራ ቁ.2፤ገፅ* ለ፣ ሀብታሙ፤29/8/2002፤ቃለመጠይቅ ካሴት ተራ ቁ.2 ገፅ ሀ፣ ቀለመወርቅ፤16/09/2002፤ካሴት

* "ገፅ" የሚለው ቃል "side" ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ጋር አቻ ሆኖ የቃለመጠይቅ ካሴቶችን የ "ሀ" እና የ "ለ" ክፍል እንዲያመለክት (እንዲገልጽ) የገባ ነው፡፡

ተራ ቁ. 4፣ ገፅ ለ) ጠቅሰዋል፡፡ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የስብከት ስነ ዘዴ መምህርና የኮሌጁ የጥናትና ምርምር ክፍል ኃላፊ የሆኑት ቸሬ አበበ /ዲያቆን/ ተረኮቹ በአመዛኙ የቤተ ክርስቲያኗ ማህበረሰብ ዘንድ በአይነት ተለይተውና ስያሜ ተሰጥቷቸው አይታወቁ እንጂ በባለሙያ አይን ሲመዘኑ፤ ምሳሌያዊ፣ ታሪካዊ፣ ቅኔያዊ፣ አባባሎች፣ ራዕይ፣ መንፈሳዊ ልብወለድ በሚል ተፈርጀው ሊቀመጡ ይችላሉ የሚል ሀሳብ አለኝ የሚል አስተያየት ሰንዝረዋል (04/09/2002፣ ቃለመጠይቅ ካሴት ተራ ቁ. 3፣ገፅ ለ)፡፡

በአጠቃላይ ከቤተ ክርስቲያኗ ምዕመናንና ባለሙያዎች ጋር በተደረገ ውይይትና ቃለ ምልልስ የባህል ባለቤቱ ተረኮቹን፤ ወጥነት በሌለው መልኩ አንዳንዴ ምሳሌዎች፣ አንዳንዴ ታሪኮች ብሎ ከመጥራት በዘለቀ ለተጠኚ ቃላዊ ዘርው ተረኮች ይሁነኝ ብሎ (consciously) የዘረጋው አንድ ወጥ የአመዳደብ ስርአትም ሆነ ስያሜ አለመኖሩን ማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ቃላዊ ዘርው ተረኮችን በአይነት ለመከፋፈል የተደረገን ጥረት ሁለተኛ አማራጭ ወደመፈለግ መርቶታል፡፡ በዚህ መሰረትም ቃላዊ ዘርው ተረኮች በተፈጥሯዊ መቼት ውስጥ ሲከወኑ የተራቹንና የአድማጩን መስተጋብር ወይም የባህል ባለቤቶቹን አጠቃላይ ስሜት መመርመርንና የትንተና ዘዴን (analytical methodን) በጣምራ መጠቀምን ጥናቱ ስብስብ ተረኮችን በአይነት ለመመደብ እንደ ሁለተኛ አማራጭ ወስዶ ተገልግሏል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሚደረጉ ስብከቶች ወቅት የተሰበሰቡ ተረኮች በተፈጥሯዊ አውድ ውስጥ ሲከወኑ የተረኮቹ ከዋኞችና ታዳምያን በተናጠል እንዲሁም በጋራ ልዩ ልዩ ምግባራትን ሲሳዩና በርካታ ተግባራትን ሲፈፅሙ ይታያሉ፡፡ እነዚህ ተግባራትና ምግባራት የባህል ባለቤቶቹ ለየተረኮቹ ያላቸውን ዝንባሌ (attitude) እና ተረኮቹን የሚረዱበትን አኳኋን (manner) ያንፀባርቃሉ፡፡ የባህል ባለቤቶቹ በተረኮቹ ክዋኔ ወቅት ሲያንፀባርቁ የታየው ይህ ስሜት፣ ተራቹና አድማጩ ማህበረሰብ በግልጽ (explicitly) ባይሆንም በውስጠታዋቂነት (implicitly) ተረኮቹን እውነተኛ እና ፈጠራዊ በሚል እንደሚረዳቸው በዛው አግባብም የሚሰጣቸው ዋጋ (value) እንደሚለያይ እንደሚያሳይ እንደ አጥኚ ለማጤን ችያለሁ፡፡ በዚህ መሰረትም ከእኔ ከአጥኚዋ የግል ፍላጎት በመነጨ ስሜት ሳይሆን በተረኮቹ ተፈጥሯዊ የክዋኔ ሂደት ላይ በመገኘት ካጤንኩት ከዚህ እውነታ እንዲሁም ከራሳቸው ከተረኮቹ (ከቴክስቶቹ) ላይ ከሚታዩ መረጃዎች ላይ በመመስረት በአብያተ ክርስቲያናቱ በስብከት ስርዓት

ወቅት የሚነገሩ ስብስብ ተረኮች እውነተኛ እና ፈጠራዊ[*] በሚል ሁለት ክፍሎች ተለይተው ሊታዩ ይችላሉ ወደሚል መደምደሚያ ላይ ደርሻለሁ፡፡

በመሆኑም በዚህ ጥናት እውነተኛና ፈጠራዊ መሆን ተረኮቹን በአይነት ለመመደብ እንደ አንድ አቢይ መስፈርት ሆኖ ሲያገለግል፤ እውነተኛ እና ፈጠራዊ በሚሉ በየንኡሳን ክፍሎች የሚከፈሉ ተረኮች ምን አይነት ባህርይ የሚታይባቸው ናቸው? ተረኮቹን በዚህ መንገድ ለመፈረጅ መሰረት ሆኗል የተባለው የባህል ባለቤቶቹ አጠቃላይ ስሜትና የቴክስቶቹ አቀራረብስ ምን ይመስላል? የሚለው ጥያቄ በቀጣይ በየንኡሳን ክፍሎቹ እየተነሳ በዝርዝር ይቃኛል፡፡

### 3.1. እውነተኛ ቃላዊ ዝርው ተረኮች

እውነተኛ እና ምናባዊ በሚል መስፈርት ተረኮችን በምድብ (category) መፈረጅ በብዙ ማህበረሰቦች ዘንድ የተለመደ አሰራር መሆኑን (Bascom፣1965፣12) ያስረዳሉ፡፡ እውነተኛ በሚል በዚህ ንኡስ ርእስ ስር የሚቃኙ ተረኮች ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው እውነተኛ የሚያስብላቸው የአጥኚዋ ፈቃድ ወይም ፍላጎት ሳይሆን ተራቹና አድማጩ ማህበረሰብ ለተረኮቹ ያላቸው አመለካከት፤ ተረኮቹ በእውነት የተፈፀሙ ተግባራትን ያጋጠሙ ሁነቶችን የሚገልፁ ናቸው ብለው የሚቀበሏቸው መሆኑ ነው፡፡ ይህ ተራቹ ማህበረሰብ ለተረኮቹ ያለው አመለካከት በግልጽ ያልተገለፀ ነገር ግን በውስጠታዋቂነት የሚንፀባረቅና በራሳቸው በተረኮቹ (በ"ቴክስቶቹ") እንዲሁም ተረኮቹ በሚከወኑበት አኳኋን የሚገለፅ ነው፡፡ Finnegan እንደሚሉት አንዳንድ ጊዜ

---

[*] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚነገሩ ተረኮችን አድማጮችና ከዋኞች እውነተኛ ናቸው በሚል በውስጠ ታዋቂነት ይረዷቸዋል ስል ቃሉ (እውነተኛ) ሀሰተኛ ወይም የውሸት ከሚለው ቃል ጋር በተቃራኒ አቻነት እንደሚቆም በማሰብ አይደለም፡፡ በአንፃሩ እውነተኛ የሚለውን ቃል ስጠቀም፣ ቃሉ "Fact" እና "truth" የሚሉት የእንግሊዝኛ ቃላት የሚሰጡትን ፍቺ በተወሰነ ደረጃ በአንድ ጠቅልሎ እንዲወክልልኝ በማሰብ ነው፡፡
ለነዚህ ሁለት ቃላት The Oxford English Dictionary ሰፋ ያለ ብያኔ (definition) እና ማብራሪያ የሰጠ ቢሆንም እውነተኛ የሚለውን ቃል ለመግለፅ ያስፈልጉኛል ያልኳቸውን ብቻ በመምረጥ በሚከተለው መልኩ አቅርቤያለሁ፡፡
Fact – "something that has really occurred . . . a particular truth known by actual observation or authentic testimony" /1989; Vol. VIII/
truth – ". . . orthodoxy . . . , denoting a particular form of belief or teaching held by the speaker to be the truth one" |1989; Vol. XVIII|
እነዚህ ሁለት ብያኔዎች እንደቅደም ተከተላቸው፡-
- በእርግጥ የሆነ ወይም የተከሰተ አንድ ነገር፡፡ . . . በተጨባጭ ምልከታ ወይም ተአማኒነት ባለው ምስክር ወይም ማስረጃ የተረጋገጠ አንድ እውነታ፡፡ የሚልና፡-
- ቃሉ በጥቅሉ እውነት ነው ተብሎ ተቀባይነት የሚያገኝ ሀሳብን ወይም አመለካከትን እንዲሁም በአንድ ተናጋሪ የቀረበን ወይም የተያዘን እምነት ወይም አስተምህሮ በቁሙ እውነት እንደሆነ መቀበልን ይመለከታል፡፡ የሚል ተቀራራቢ የአማርኛ ፍቺን ይዘዋል፡፡

በዚህ መሰረትም እውነተኛ የሚለው ቃል በዚህ ጥናት እንደ አንድ የስብስብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች አይነት መግለጫነት ሲያገለግል ቃሉ አንድም በገሀዱ አለም በተጨባጭ የተፈፀመና በግለሰብ ወይም በማህበረሰቡ ገጠመኝ ላይ የተመሰረተ፤ እማኝ ሊጠቀስለት መረጃ ሊቀርብለት የሚችል የሚለውን ሀሳብ ይወክላል፡፡ በሌላ በኩልም ይህው ቃሉ ተጨባጭ መረጃ ወይም እማኝ ማቅረብ ሳያስፈልገው በአንድ ቡድን አባላት ዘንድ በጥቅሉ እውነት ስለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ወይም የሚሰጠው የሚለውን ሀሳብ የሚወክል ይሆናል፡፡
በተመሳሳይ ፈጠራዊ የሚለው ቃል "fictitious" ከሚለው እንግሊዝኛ ቃል ጋር በፍቺ አቻ ተደርጎ ሊታሰብ የሚችል ሲሆን ቃሉ በገሀዱ አለም በተግባር ያልተፈፀመ ነገር ግን ሊሆን ሊያጋጥም ይችላል በሚል ከአእምሮ በማፍለቅ የተነገረን በቁሙ ውሸት ተደርጎ የማይወሰድ ሀሳብ ወለድ ስራን የሚመለከት የሚለውን ሀሳብ ይዞ በዚህ ጥናት ውስጥ ያለግላል፡፡

አንዳድ የአፍሪካ ቃላዊ ዝርው ተረክ አይነቶች የባህል ባለቤቶቹ ልብ የማይሏቸው ወይም መኖራቸውን አምነው የማይቀበሏቸው ሆነው እንኳን አጥኚው በተረኮቹ መካከል ያለውን ልዩነት ሊመለከት ይችላል (1970,328) ፡፡

እውነተኛ በሚለው ንኡስ ርእስ ስር የተካተቱ ተረኮች በተደራሲያን ልቡና በውስጠ ታዋቂነት ለሚነሳ የእውነተኛነት ወይም በገሀድ ስለተፈጸሙ ተግባራት የእያወሱ ነው ወይ? ጥያቄ አወንታዊ መልስ በሚሠጡበት መልኩ ተራኪዎቻቸው በ1ኛ መደብ አንፃር (እኔ እያሉ) ስላዩዋቸው እና ስላጋጠሙዋቸው ሁነቶችና ድርጊቶች ወይም ስለግል ገጠመኞቻቸው የሚተርኩባቸው ተረኮች ናቸው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ተራኪዎች ስለሌሎች በቅርብ ስለሚያውቋቸው ሰዎች ገጠመኞች፣ የገጠመኞቹን ባለቤቶች በእማኝነት በመጥቀስ በ3ኛ መደብ አንፃር የሚያትቱዋቸው ተረኮችም በዚሁ ምድብ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እውነተኛ በሚለው ምድብ ስር በሚጠቃለሉ ተረኮች የትረካ ሂደት ተራቾች፣ ተረኮቹ በእውን የተፈፀሙ ድርጊቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው የሚል የጋራ መግባባት (common understanding) ላይ የሚያደርስ አንድምታን በሚያሰርጽ መልኩ ድርጊቶችና ሁነቶች ስለተፈጸሙበት ጊዜ እና/ወይም ቦታ እቅጫዊ መረጃን ይሰጣሉ፡፡ ተረክ 23፣24፣33 እና 47ን* ብንመለከት ተራኪዎች በታሪኩ ድርጊቶች ስለተፈፀሙበት ጊዜ እና/ወይም ቦታ ተጨባጭ መረጃን የሰጡባቸው ናቸው፡፡

ድርጊቶች በማን ተፈፅመዋል ለሚለው በእውነተኛ ተረኮች ከወል መጠሪያ ይልቅ ግለሰቦች በተናጠል በተፀውኦ ስም እየተጠቀሱ አንዳንዴም ግለሰቦቹ ተረኮቹ በሚነገሩበት ወቅት ስላሉበት ሁኔታ ጭምር ተጨማሪ ማብራሪያ እየተሰጠባቸው ይቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ በተረክ 9፣ 47 እና 64 ድርጊት ፈፃሚዎች ወይም ታሪኩ የሚነገርላቸው ሰዎች በስም ሲጠቀሱ ተረክ 9፣ 53 እና 55፤ "ታዋቂ ታላቅ . . (አሁን) በህይወት የሉም"፣ "ዱርዬ ነበር፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነበር በአንድ ወቅት" እና " ግብረገብ ያስተማሩኝ መምህሬ መንኩሰዋል አሁን" በሚል ግለሰቦቹን አስመልክቶ ተጨማሪ ማብራሪያ ተሰጧል፡፡ ይህ የተረኮቹ አቀራረብም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የተረኮቹን እውነተኛነት፤ ተረኮቹ በተጨባጭ ስለተፈፀሙ ወይም ስላጋጠሙ ሁነቶችና ድርጊቶች የሚያትቱ ናቸው ወይ? በሚል በተደራሲያን ልቡና በውስጠ ታዋቂነት ለሚቀሰቀስ ጥያቄ ምላሽ

---

* እነዚህ ተረኮችና በእውነተኛነት የተፈረጁ ሌሎች መሰል ተረኮች ምንም እንኳን እውነተኛ ገጠመኞችን የሚተርኩ ቢሆንም ተረኮቹ አንድም ተደጋግመው ከመነገራቸው የተነሳ፣ ከተራኪ ወደተራኪ ሲቀባበሉ እንደየግለሰቡ የአተራረክ ብቃት፣ እንደየሚተረኩበት አውድ መንፈስ (mood) እና አላማ ከመሰረታዊ የታሪክ አወቃቀራቸው ላይ በየጊዜው የሚያክሉት ባህርይ መኖሩ በቃላዊ ዝርው ተረክነት እንዲፈረጁ አንድ ምክንያት ሆኗል፡፡ ለዚህ አባባል በተለይ በተራ ቁ. 10 እና 24 ስር በአንድ ሴራ (plot) ላይ ተመስርተው በተለያዩ ተራኪዎች በተለያዩ አውዶች ላይ የቀረቡትን ተረኮች መመልከት ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡

እየሰጡ ስለተረኮቹ እውነታ ላይ መመስረት አድማጭ ተራቹን የጋራ መግባባት ላይ የሚያደርሱ ናቸው፡፡

እውነተኛ በሚለው ምድብ ስር የሚጠቃለሉ ተረኮች በአጠቃላይ ተራቾች የግል ወይም በቅርብ የሚያውቋቸውን ሰዎች ገጠመኞች እኔ በተጨባጭ እንዳየሁትና ከጉዳዩ ባለቤት እንደሰማሁት በሚል የሚያቀርቧቸው ናቸው፡፡ በታሪኩ የሚነሱ ድርጊቶችና ሁነቶች ስለተፈጸሙበት ጊዜና ቦታ ተጨባጭ መረጃ የሚሰጡባቸው ወይም ቢያንስ አድማጭና ተራቹ ማህበረሰብ ከሚኖሩበት የዘመን ክልል ያልራቁ መሆናቸውን የሚያመላክቱባቸውም ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም እነዚህ ተረኮች ታሪኩ የሚነገሩላቸውን ግለሰቦች በስም እየጠቀሱ የሚያቀርቡዋቸው ከመሆናቸው በመነጨ እውነተኛ ናቸው ተብለው በተራቹ ማህበረሰብ ዘንድ የታመነባቸው ናቸው፡፡

ይሁንና እውነተኛ በሚለው አቢይ ጥላ ስር የተጠቃለሉ ተረኮች ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ጊዜን፣ ቦታንና ባለታሪኮችን አስመልክቶ እቅጯዊ መረጃ የተሰጠባቸው ተረኮች ብቻ አይደሉም፡፡ ጊዜን ቦታንና ድርጊት ፈፃሚዎችን አስመልክቶ ተጨባጭ መረጃ ያልተሰጠባቸው ነገር ግን ከሃይማኖታዊ ጉዳይ ጋር ትስስር ያላቸው በመሆናቸው ከእምነት በመነጨ አድማጩና ተራቹ ማህበረሰብ እማኝ እንዲነቀስለት ሳይጠብቅ ሙሉ ተቀባይነትን የሚሰጣቸው ተረኮችም በዚህ ንኡስ ርእስ ስር የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡ በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ለሚጠቃለሉና ተጠቃሽ ባህርይ ላላቸው ተረኮች ማሳያነት በተራ ቁጥር 40፣57 እና 61 ስር የቀረቡ ተረኮችን በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ተራችና አድማጩ ማህበረሰብ የሚኖርበትን ነባራዊ ዓለም ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነልቡናዊ ሁኔታ ከተራች አድማጩ ማህበረሰብ የጋራ እሴት አንጻር የሚቃኙ ሂስ አዘል ተረኮችም በዚሁ እውነተኛ በሚለው ርዕስ ጥላ ስር የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡

በዚህ ንኡስ ርእስ ጥላ ስር የሚውሉ ተረኮችን እውነተኛ ናቸው ብሎ አድማጭና ተራቹ ማህበረሰብ የሚተርታቸውና የሚያደምጣቸው ናቸው ያስባላቸው ምክንያት እስከአሁን ባለው ሂደት እንደተመለከትነው በራሳቸው በተረኮቹ ("በቴክስቶቹ") ውስጥ በሚንፀባረቁ ባህርያት ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ በአንፃሩ ይህ የተረኮቹ መለያ ባህርይ ተረኮቹ በሚከወኑበት አኳኋን ጭምርም በዋናነት የሚገለፅ ነው፡፡ እውነተኛ ናቸው በሚል በሚቀርቡ ተረኮች፣ ተራቹ በተረኮቹ የትረካ ሂደት መካከል በተረኩ ስለተነሱ ድንቃድንቅ ወይም አሳዛኝ ተግባራት ታዳሚው ያለውን ስሜት እንዲገልጽ በመጠበቅም በማበረታታትም የሚያደርገው ቆምታ ድግግሞሹ የላቀ ፋታውም ፈጠራዊ በሚባሉ ተረኮች የክዋኔ ሂደት ላይ ከሚታው በአንፃራዊነት የተራዘመ ነው፡፡ ታዳሚው በበኩሉ እውነተኛ ናቸው በሚል ስሜት የቀረቡትን ተረኮች ሲያደምጥ በተረኩ

ለሚነሱ ስሜት ቀስቃሽ ሁኔታዎች (ለሚነገሩ ተአምራትና ገድላት፣ ለዜና ፊውሶችና መቅሰፍቶች ወዘተ.) የሚሠጠው ምላሽ (እልልታው፣ ጭብጨባው፣ ከንፈር መጠጣው ወዘተ.) ቸልተኛነት የማይስተዋልበት የላቀና ከጥልቅ ስሜት የመነጨ ነው፡፡ ይህ በላቀ መንፈስ የተገለፀ ስሜትም የሚበርድበት የጊዜ ርዝመት የተራዘመ ነው፡፡ በተረኮቹ የክዋኔ ሂደት የሚስተዋለው ይህ የተራችና አድማጩ ምግባር በአመዛኙ ከተራኪው አንፃር በእርግጥ (በእውን) ይህ ተደርጓል ወይም ተደርጎልናል የሚል አንድምታ ሲኖረው፤ የተደራሲው ምላሽ የናረና ከጥልቅ ስሜት የመነጨ እየሆነ እንዲሁ በአመዛኙ በእውነትም ሆኗል ደግሞም ይሁንልን ወይም ከዚህ ይጠብቀን የሚል አንድምታን የሚያሰርፅ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ እውነተኛ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሚለው አቢይ ጥላ ስር የሚመደቡ ተረኮች በአንድ በኩል በተረኩ የተነሱ ሁነቶችና ድርጊቶች ስለተፈፀሙበት ጊዜ፣ ቦታና ስለድርጊት ፈፃሚዎች ተጨባጭ መረጃን የሚሰጡና የተራኪውን የግል ወይም በቅርብ የሚያውቃቸውን ሰዎች ገጠመኞች የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ሃይማኖታዊ ጉዳይ በማንሳታቸው እማኝ ማቆም ሳያስፈልጋቸው ስለእውነተኛነታቸው በተራኪውና በአድማጩ ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኙ ተረኮችንም ንኡስ ርእሱ አካቶ የያዘ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በነባራዊው የተራች አድማጩ ማህበረሰብ፤ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነልቡናዊ ገፅታዎች ላይ የሚሰነዘሩ ሂሳዊ አስተያየቶችን የያዙ ተረኮችም በዚሁ ንኡስ ርእስ ስር የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡

በዚህ መሰረት ከስብስብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች መካከል ሃያ ሁለት ያህሉ ካላቸው ተጠቃሽ የወል ባህርያት የተነሳ እውነተኛ በሚለው አቢይ ጥላ ስር ተፈርጀዋል፡፡ ይሁን እና ተረኮቹ ካላቸው የወል ባህርይ ባሻገር ተጨማሪ ለዩ ባህርያትንም የተላበሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም እውነተኛ በሚለው ምድብ ስር በአንድ የተፈረጁት እነዚህ ተረኮች በተጨማሪ ትውስታዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች|Reminiscences|እና ሂሳዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሚል በሁለት ንኡሳን ክፍሎች ተፈርጀው ሊታዩ የሚችሉ ሲሆን የምድቦቹ ዝርዝር ባህርያት ከዚህ ቀጥሎ በቅደም ተከተል የሚታይ ይሆናል፡፡*

* እውነተኛ እና ፈጠራዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሚሉት አበይት ክፍሎች እንዲሁም በአበይት ክፍሎቹ ሥር በሚጠቃለሉት ንዑሳን ክፍሎች ስር የሚውሉ የተጠኚ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ዝርዝር ለይቶ የሚያሳይ ሰንጠረዥ በአባሪ ሦስት ስር ቀርቧል፡፡

### 3.1.1. ትውስታዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች /reminiscences/

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ለሚጠቃለሉ ዝርው ተረኮች "ትውስታዊ" የሚለውን ቃል በገላጭነት ስጠቀም በእንግሊዝኛ "Reminiscences" የሚለው ስያሜ ቃል እንደ አንድ የቃላዊ ዝርው ተረክ ንኡስ ክፍል ሆኖ ሲያገለግል ከሚሰጠው ፍቺ ጋር አቻ ሆኖ እንዲያገለግል በማሰብ ነው።

Reminiscences ለሚለው ቃል Oxford Advanced Learner's Dictionary *"a spoken or written description of sth that sb* remembers about their past life"* |1992; 2000| "ሰዎች ካለፈ ህይወታቸው በማስታወስ ስለአንድ ነገር በፅሁፍ ወይም በቃል የሚያቀርቡት ገለፃ (ነው)።" በማለት ፍቺ ሲሰጥ Bascom በአንፃሩ ቃሉ እንደ አንድ የቃላዊ ዝርው ተረክ ንኡስ ክፍል ሆኖ ሊወሰድ ይችላል በማለት ከዚሁ አንፃር ለቃሉ፡-

> *Reminiscences or anecdotes concern human characters that are known to the narrator or his audience, but apparently they may be retold frequently enough to acquire the style of verbal art and some may be retold after the characters are no longer known at first hand. They are accepted as truth, and can be considered as sub-type of the legend or a proto legend. (1965, 5)*

የሚል ብያኔ ሰተዋል። ይህ የBascom ብያኔ በአማርኛ፡-

> ትውስታዊ ተረኮች (Reminiscences) ወይም ወጎች፣ በተራኪውና በአድማጮች ዘንድ የሚታወቁ ሰው ገፀባህርያት ላይ የተመሰረቱ ነገር ግን ተደጋግመው ከመነገራቸው (ከመተረታቸው) የተነሳ የቃላዊ ጥበብ (verbal art) ስልትን የተላበሱ፤ አንዳንዶቹ ምናልባትም (ታሪኩ የሚነገርላቸው) ገፀባህርያት በአድማጩና ተራቹ ዘንድ በቀጥታ በማይታወቁበት (በማይታወሱበት) ሁኔታ ላይ ከደረሱ በኂላም የሚተረቱ (የሚነገሩ) (ተረኮች) ናቸው። እነዚህ ተረኮች (በአድማጭ ተራቹ ዘንድ) እውነተኛ ናቸው በሚል ተቀባይነት ያላቸውና የአፈ-ታሪክ (legend) ንኡስ ክፍል ወይም ዝርያ ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ (ተረኮች) ናቸው።

---

* "sth" "sb" የሚሉት ቃላት በOxford መዝገበ ቃላት ውስጥ something እና somebody ለሚሉት ቃላት ወካይ ሆነው በአፅርኦት የተቀመጡ ናቸው።

የሚል መንፈስ ይዞ ይገኛል፡፡ ከዚህ በመነሳት ትውስታዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሚል በዚህ ንኡስ ርዕስ ስር እውቅና የተሰጣቸው ተረኮች ተራኪው ከግል ገጠመኙ ወይም ከሌሎች ግለሰቦች ገጠመኞች ላይ በመነሳት እያስታወሰ የሚተርካቸው ተረኮች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተረኮቹ አድማጭ ተራቹ ማህበረሰብ እውነተኛ ናቸው ብሎ የሚቀበላቸውና ተደጋግመውና በቅብብሎሽ (በተለያዩ ተራቶች  በተለያየ ጊዜና ሁኔታ) ከመተረታቸው የተነሳ የቃላዊ ዝርው ተረክነት ስልትን የተላበሱ ናቸው፡፡

### 3.1.2. ሂሳዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች

ሂሳዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሚል በዚህ ንኡስ ርእስ ስር የወል ስያሜ የተሰጣቸው ተረኮች በባህርያቸው አንድ የተሟላ ታሪክን የማይተርኩ ወይም ጥብቅ ሴራ የሌላቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ተረኮች አትኩሮታቸውን በተራች አድማጩ ማህበረሰብ፤ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነልቡናዊ ገፅታዎች ላይ በማድረግ ለአድማጩ ልቦና ከታሪክነታቸው ይልቅ ሂሳዊነታቸው ጎልቶ በሚሰማበት መልኩ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ሂሳዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በማህበረሰቡ ተጨባጭ የህይወት ገጽታ ወይም በገሀድ እየተፈጸሙ ባሉ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው እውነተኛ የሚለውን እውቅና ሲያሰጣቸውና ከትውስታዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ጋር ሲያመሳስላቸው ተረኮቹ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ከሚተርኩት አንድ ታሪክ ይልቅ ሂሳዊነታቸው ጎልቶ የሚታይ መሆኑ ከትውስታዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የተለዩ ያደርጋቸዋል፡፡ በእነዚህ ሁለት የቃላዊ ዝርው ተረክ አይነቶች መካከል የተጠቀሰን የባህሪ አንድነትና ልዩነት ለማጤን ይረዳ ዘንድ በሂሳዊ ቃላዊ ዝርው ተረክነት የተፈረጀውን ተረክ 35ን እና በትውስታዊ ዝርው ተረክነት የተፈረጀውን ተረክ 55ን በምሳሌነት ወስደን እንመልከት፡፡

ተረክ 35

ይሄ አርቴፊሻል ሽጉጥ የሚላከው ወደ አፍሪካ ነው፡፡ ወገኔ እንደው የወጣችሁ ሰዎች ታዘቡኝ (ባህርማዶ ማለታቸው ነው) ሲውዲን ስድስት ወር ቆይቻለሁ፤ ብዙ መዋእለህፃናት ጎብኝቻለሁ እራሱ አሻንጉሊት የሚሸጥበት ሽጉጥ የለም ጭራሽ፡፡ እየው ሰማችሁኝ ሆነ ብለው እኮ ከህፃንነቱ ለምዶት እንዲያድግ ብለው ነው የሽጉጥ አርቴፊሻል አፍሪካ ውስጥ የሚልኩት የምንጣላው እኛ አይደለን?! የምንጣላው እኛ አይደለን?! ጦሩን መርዝ መትከል የሚችሉት እኛ ላይ አይደለም ሰው የለማ እኛ ቤት! ማሳውን የሚጠብቀው ሰው የለማ፡፡

ተረክ 55

ያኔ ዱሮ ዱሮ ግብረገብ ያስተማሩኝ መምህሬ መንኩሰዋል አሁን፡፡ ድሮ ነው ግብረገብ እንደ አንድ “ክሬዲት ሐወር” ይሰጥ ነበር፡፡ አስታውሳቸዋለሁ አንድ ቀን ትምህርት ቤቱ ውስጥ ከግብረገብ አስተማሪነት ሌላ ገንዘብ ያኘም ናቸው፡፡ ገንዘብ ያኙ መሆናቸውን ስለሚያውቅ

ቤታቸውን ሠርስሮ ገባ ሌባ፡፡ የት እያሉ? ትምህርት ቤት እያሉ እሳቸው፡፡ አሁን በዛን ሰዓት (ጊዜ) ካዝና አለ ግን ብዙም የለም [. . .] አሁን የሚገርማችሁ ልክ ሲሄዱ የቤታቸው በር ተሰብሯል አልደነገጡም አማተቡ፣ አማተቡና ገቡ፡፡ ልክ ሲገቡ አመናችሁኝም አላመናችሁኝም ሰውየው መሰርሰሪያውን እንደያዘ የተሟላ መሳሪያውን እንደያዘ ደርቋል፡፡ ልክ እንደሚያስቀድስ ሰው ቆሟል፡፡ መጥተው አጠገቡ ቆሙ አያይም ፊት ለፊት ነው የሚያየው፣ ወዲያና ወዲህ የለም፡፡ በጣም አስታውሳለሁ፣ አሁን በጣም ገርሟቸው፣ አንደኛ በሩ ተሰብሯል፣ እንደገና ሰውየው ቆሟል [. . .] አሁን ስተት ብለው ገቡ አዩ፡፡ ወዲያው ሌባ እንደሆነ አወቁ፡፡ ወደ ቤተክርስቲያን ሰው ላኩ ካህናት ተጠርተው ፀሎት ተደርጎ ሰውየው፣ ሌባው ዲዳ ሆነ (ሰውነቱን ግን) ለቀቀው፡፡ ሰውየው ራሱ አገልጋይ ሆነ አየው የእግዚአብሔርን ስራ፡፡ እኚህ አባት ብዙም አልቆዩ ከተወሰነ አመት በኋላ መንኩሰዋል፡፡ ለካስ ቤታቸው ውስጥ ስትገቡ ገብታችሁ እንዲህ ስትዞሩ (ፊቱን ወደቀኝ አዙሮ) ግድግዳው ላይ የስላሴ ስዕል አለ፡፡

በተራ ቁጥር 55 ስር በቀረበው ተረክ የተወሳው ታሪክ የተፈጸመው በተራቹ የታዳጊነት እድሜ ክልል መሆኑ፤ ድርጊቱ የተፈጸመበት ቦታም እንዲሁ የአድማጭና የተራቹ የጋራ መኖሪያ በሆነችው በኢትዮጵያ እንደሆነ በግልፅ ተጠቁሟል፡፡ በተረኩ ድርጊት ፈፃሚን አስመልክቶ “የግብረገብ መምህሬ” በሚል ተጨባጭ መረጃ ከመስጠት በዘለቀ “አሁን ገዳም ገብተዋል” በሚል ስለባለታሪኩ የወቅቱ ሁኔታ ተጨማሪ ማብራሪያ ቀርቧል፡፡ በተመሳሳይ በተረክ 35 እንዲሁ ከታሪኩ አጠቃላይ መንፈስ በመነሳት አድማጩ በቀላሉ በታሪኩ የተነሳው ድርጊት አሁን (አድማጭ ተራቹ እየኖረ ባለበት ዘመን) በአፍሪካና “በሰለጠነው ዓለም” በተጨባጭ እየተፈፀመ ያለ መሆኑን መገንዘብ ይችላል፡፡ ይህ የተረኮቹ አቀራረብ በአድማጩ ልቡና ለሚነሳ የእውነተኛነት ጥያቄ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አወንታዊ መልስ የሚሰጥ መሆኑ ሁለቱን ተጠቃሽ ተረኮች የሚያዛምዳቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል ተረክ 55ን ስንመለከት አድማጭ በቀላሉ ሊከተለው የሚችል የታሪክ ፍሰት ያለው በጥብቅ ሴራ ላይ የተመሰረተ ነው:: በአንፃሩ ከተረክ 35 አንጥረን ልናስቀምጠው የምንችለው አንድ አይነት የታሪክ ፍሰት የለም፡፡ ተረኩ ከታሪክነት ይልቅ “አፍሪካ ጠባቂ የሌላት ቤት ሆናለች” የሚል ሂሳዊ አስተያየት ገዝፎ በሚሰማበት መልኩ የቀረበ ነው፡፡

### 3.2. ፈጠራዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች

ፈጠራዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሚለው ንኡስ ርእስ ስር የተካተቱ ተረኮች እውነተኛ በሚለው ንኡስ ርእስ ስር ከሚጠቀሱ ተረኮች በተለየ ከተራቾች ምናብ እየፈለቁ፣ በገሀዱ አለም በተጨባጭ ስላልተፈፀሙ ተግባራትና ስላልተከሰቱ ሁነቶች የሚያትቱ ተረኮች ናቸው፡፡ ተራቹ

ማህበረሰብ ስለተረኮቹ ፈጠራዊነት በግልጽ አይናገር እንጂ ተረኮቹ ፈጠራዊ ስለመሆናቸው ያለው ግንዛቤ በራሳቸው በተረኮቹ (በ"ቴክስቶቹ") እንዲሁም ተረኮቹ በሚቀርቡበት አኳኋን በውስጠታዋቂነት ተንፀባርቆ የሚታይ ነው።

አብነቶች ከተረኮች (ከ"ቴክቶች") አንፃር ሲታዩ፤ በፈጠራዊ ዘርው ተረክነት በተፈረጁ ተረኮች በሚነገሩ ታሪኮች ድርጊቶችና ሁነቶች መቼና የት ተፈጽመዋል ወይም ተከስተዋል ለሚለው ጥያቄ ተጨባጭ መረጃ ተሰጥቶ ወይም ቀርቦ አይታይም። በሌላ አገላለጽ በፈጠራዊ ተረኮች ልዩ ልዩ ድርጊቶችና ሁነቶች ስለተፈጸሙበት ጊዜና ቦታ በተረክ 3፣ 4፣ 12፣ 14፣ 16፣ 17፣ 20፣ 29፣ 32 ላይ እንደምናየው ምንም አይነት ፍንጭ ሳይሰጥባቸው ይታለፋሉ። በተረኮቹ አልፎ አልፎ በተረክ 1፣ 5፣ 7፣ ላይ እንደሚታየው ድርጊቶችና ሁነቶች የተፈጸሙበት ጊዜ እና/ወይም ቦታ ተጠቅሶ በሚገኝበት አጋጣሚ እንኳን የጊዜ እና/ወይም የቦታ አጠቃቀሱ እውነተኛ ተብለው በሚቀርቡና በሚደመጡ ተረኮች ላይ ተዘውትሮ እንደሚታየው እቅጯዊ ያልሆነ አንድን የሩቅ ሀላፊ ጊዜ፤ አንድ ጊዜ፣ አንድ ቀን፣ ከእለታት አንድ ቀን በማለት በደፈናው ጠቁሞ ከማለፍ የማይዘልቅ ይሆናል። ፈጠራዊ ተረኮች ባለታሪኮችን (ድርጊት ፈፃሚዎችን) አስመልክቶ እንዲሁ ሴትየዋ፣ ሰውየው፣ ባል፣ አንድ ሰው በማለት በተራ ቁጥር 1፣ 37፣ 2፣ 36፣ 44 ስር እንደቀረቡት እና መሰል ተረኮች ለባለታሪኮች የወል መጠሪያ ከመስጠት በዘለቀ አንድም ጊዜ በተፀውዖ ስም አይጠሯቸውም፤ ገፀባህርያቱ ስላሉበት ሁኔታም ተጨማሪ ማብራሪያ አይሰጡም። በተረኮቹ የጊዜ፣ የቦታ፣ የባለታሪኮች መረጃ መጓደል ወይም እቅጯዊ አለመሆን፤ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ተረኮቹ በገሀዱ ዓለም በተጨባጭ ስለተፈፀሙ ድርጊቶች እና ሁነቶች የሚያወሱ አለመሆኑን ወይም ፈጠራዊነታቸውን ያንፀባርቃል። ይህም ተረኮቹ ከእውነተኛነት ይልቅ ፈጠራዊ ስለመሆናቸው በተራችና በአድማጩ ማህበረሰብ ዘንድ የጋራ መግባባት እንዲሰፍን የራሱን ድርሻ ያበረክታል።

እስከአሁን ከተጠቀሱትና በቃላዊ ዘርው ተረኮች "ቴክስቶች" ውስጥ ከሚንፀባረቁት ባህርያት ጎን ለጎን ቃላዊ ዘርው ተረኮቹ ፈጠራዊ ናቸው የሚለው የአድማጭና የተራቹ ማህበረሰብ ግንዛቤ በተረኮቹ ክዋኔ ሂደት በራሱ በአድማጩና በተራቹ ማህበረሰብ መስተጋብር ውስጥ በዋናነት ተንፀባርቆ የሚታይ ነው። ፈጠራዊ በሚለው ንኡስ ርእስ ስር የተካተቱ ተረኮች በተከወኑበት ተፈጥሯዊ አውድ የክዋኔ ሂደት ላይ ከዋኙ እውነተኛ ናቸው በሚል መንፈስ በሚያቀርባቸው ተረኮች የትረካ ሂደት ወቅት የሚያደርገውን ያህል በየመሀሉ በተደጋጋሚ ቆምታ አያደርግም። በሌላ አገላለፅ በተጠቃሽ ተረኮች የክዋኔ ሂደት ተራቹ በተረኮቹ ስለተነሱ ልዩ ልዩ ጉዳዮች (ስለተፈፀሙ ተአምራት፣ ስለአጋጠሙ መቅሰፍቶችና ድህነቶች ወዘተ.) አድማጩ ስሜቱን እንዲገልጽ ወይም ምስጋናውን እንዲያሰማ አዘውትሮ አይጋብዝም ወይም

አይጠብቅም። ከዚህ ጋር በተያያዘ በፈጠራዊ ተረኮች የትረካ ሂደት በታሪኩ ለሚነሱ ስሜት ነኪ ሁኔታዎች የታዳሚው ምላሽም ከእውነተኛ ተረኮች የክዋኔ ሂደት አንፃር ሲታይ ፍዝ ነው። ይህም ተራችና አድማጩ ማህበረሰብ ተረኮቹን የሚረዳበትን፣ እንዲሁም ለተረኮቹ የሚሰጠውን ዋጋ (value) መለያየት ከተረኮቹ ("ከቴክስቶቹ") አቀራረብ በተጨማሪ የሚያንፀባርቅበት ሌላው መንገድ ነው።

በፈጠራዊነት የተፈረጁ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን አስመልክቶ በእስከአሁኑ ሂደት የተነሱ ነጥቦችን በግልጽ ለመመልከት ይረዳን ዘንድ እንዲሁም ከእውነተኛ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ጋር ያላቸውን የባህርይ ልዩነት ለማጤን ያስችለን ዘንድ ንኡስ ርዕሱ ከመጠቃለሉ አስቀድሞ ከሁለቱ አበይት ጎራዎች የሚፈረጁ ተረኮችን በማስቀደም ፍሬ ነጥቦች የተጠቃለሉበት ሰንጠረዥ በማስከተል ይቀርባል። ከዚህ ቀጥሎ በምሳሌነት የተወሰዱት ሁለት ተረኮች በተለያዩ አውዶች ላይ ሲቀርቡ አድማጭና ተራቹ ማህበረሰብ ቀዳሚውን ፈጠራዊ ተከታዩን እውነተኛ ናቸው ብሎ በውስጠታዋቂነት የተቀበላቸው በዚህም ጥናት በዚሁ አግባብ የተፈረጁ ናቸው።

ተረክ 54

አንድ ቤት ሁለት ሌቦች ገቡ። ሁለት ሌቦች ሲገቡ ባልየው ብልጥ ነው፣ ብልጥ የመጨረሻው ዘመን ብልጥ (ነው)። ገብተው ሌቦቹ አንዱ በዚህ ጋ (ቀኙን እያሳየ) አንዱ በዚህ ጋ (ግራውን እያሳየ) እንደቆሙ አይቷቸዋል በጨለማ ጭላንጭሉች አሉ። ሚስትየው ተኝታለች ቀስ አለና በእግሩ ቢነካት ነቃች። ነቅታ ቀና ስትል አየቻቸው ምን የመሳሰለ ሰይፍ ይዘዋል፣ ቆመዋል "እንነቃለን ቢሉ ቆርጠን እንጥላለን" የሚሉ ናቸው። በኋላ "ወይኔ" ስትል "ምንድነው ዝምብለሽ ተኚ ምን አይነቷ ነች" (አለ) "እረ ይኸው አታይም" (ስትለው) "አይቻለሁ፤ ሚካኤልና ገብርኤል ሠይፍ ይዘው እየጠበቁን ነው ተኚ" አላት በኋላ እነዛ ሌቦች "ሚካኤል?! ገብርኤል?!" አሉና እንደሚካኤልና ገብርኤል አደረጋቸው ቀስ አሉና ሳይሰርቁ ወጡ።

ተረክ 24

ሰባ ስምንት አመተምህረት እዚህ ዊንጌት ጠዋት አንድ ሰአት ከምናምን ደርሼ (ለመድረስ) ወደዊንጌት የምሄድበት ጉዳይ ነበረኝ 28 ቁጥር ነበር የያዝኩት (አውቶብስ ለማለት ነው) ታክሲው ከፊቱ ሲገባ ፍሬኑን ሲይዝ በሙሉ የነበረው ሰው እንዳለ ተነጠፈ። እንዴት ያሉ አባት አዛውንት አንዲት ጥቁር ፀጉር በራሳቸው ላይ የለም። ተማሪዎች እላያቸው ላይ ወደቁ ቀና ብሎ አዩ (አብሮዋቸው የተሳፈሩትን ወጣቶች) "ልጆቼ ይቅርታ ይቅርታ" አሉ ተሣቀቁና። ብረቱን ይዘው ይወዛወዙ ነበር። አሮጊትና ሽማግሌዎች "ይቅርታ ይቅርታ" አሉ ቀና አሉ "ምናለ አሁን እንደ እናንተ ያለው ቢሞት" (አውቶብስ ውስጥ የነበረውን ወጣት ለማለት ነው) አላቸው። ሰባ ስምንት ዓመተ ምህረት በኋላ አባቶቼ መቼም እዚህ ሸበት ውስጥ ያለው እውቀት

አቤት እዚህ ሽበት ውስጥ ያለ ብልሀት [ኧረ ጉድ አዬ ዲግሪ አዬ ዶክትሬት ዶክ እሬት ዶክ-እሬት ንፁሆች ካላችሁ ይሄ አይነካም. . .] ከዛ በኋላ በዚህ በሽበት ውስጥ ያለ እውቀት "ውይ ልጆቼ እውነት ብላችኋል አልሆነልንም እንጂ ልጁ ወንበሩንም እንዳንቀመጥ ቀድማችሁ ያዛችሁት መቃብሩንም ቀድማችሁ ያዛችሁት ግራ ገብቶን ነው እኮ መቆማችንን የተያያዝነው" አሉዋቸው፡፡

| ተረክ ተራ ቁጥር | የድርጊት ፈፃሚዎች ማንነት | ድርጊቱ የተፈጸመበት ቦታ | ድርጊቱ የተፈጸመበት ጊዜ | የተራኪው አንፃር |
|---|---|---|---|---|
| 54 | በወል መጠሪያ የተገለፀ /ሁለት ሌቦች ባልየው/ | በውል የማይታወቅ /ያልተገለፀ/ | በውል የማይታወቅ /ያልተገለፀ/ | በውል የማይታወቅ /ያልተገለፀ/ |
| 24 | በወል መጠሪያ የተገለፀ /አንድ አዛውንት፣ ተማሪ/ | በተጨባጭ የተገለፀ /አ/አ ዊንጌት ትምህርት ቤት አካባቢ/ | በተጨባጭ የተገለፀ /በ1978 ዓ.ም ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ገደማ/ | በግልፅ የሰፈረ /አንደኛ ደረጃ ምስክር ወይም የአይን እማኝ/ |

ሠንጠረዥ 1

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ለማሳየት እንደተሞከረው በአጠቃላይ ፈጠራዊ ተረኮች ልዩ ልዩ ድርጊቶች ስለተፈፀሙበት ጊዜና ቦታ እንዲሁም ስለድርጊት ፈፃሚዎች ማንነት ምን ጊዜም ተጨባጭ መረጃን አይሰጡም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዝርው ተረኮቹ የክዋኔ ሂደት በተራኪውና በአድማጩ ዘንድ የሚታየው ስሜት በአንፃራዊነት ለዘብተኛነት የሚስተዋልበት ነው፡፡ በዚህ ንኡስ ርዕስ እነዚህን ዝርዝር ባህርያት የሚጋሩ አርባ ሁለት ያህል ተረኮች የተጠቃለሉ ሲሆን ተረኮቹ በአንድ ምድብ እንዲፈረጁ ካበቋቸው ተጠቃሽ የወል ባህርያት ባሻገር ተጨማሪ ለዩ ባህርያት ያሏቸውና በሁለት የተለያዩ የቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች፣ ተረቶች (folktales) እና ቀልዶ (jocks) ስር ተፈርጀው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡

### 3.2.1. ተረቶች /folktales/

በዚህ ጥናት "ተረቶች" የሚለው ስያሜ ቃል በእንግሊዝኛ "folktales" ከሚለው ቃል ጋር በፍቺ አቻ ሆኖ እንዲያገለግል የገባ ነው፡፡ ቃሉ በስሩ ለተፈረጁ የተረክ አይነቶች በወል መጠሪያነት በዚህ ጥናት እንዲያገለግል ሲሆን የሚሰጠው ፍቺ ሰፍቶ (in the broadest sense of the word) ቃላዊ ዝርው ተረክ ከሚለው ስያሜ ጋር አቻ በመሆን ሳይሆን የቃሉ ፍቺ ጠቦ (in the narrowest sense of the world) የገባ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም በንኡስ ርእሱ ተረት በሚል

የወል መጠሪያ (ስያሜ) የሚታወቁ ተረኮች (በዚህ ጥናት ከተሰበሰቡ ቃላዊ ዝርው ተረኮች መካከል 37 ያህሉ ተረቶች በሚለው ምድብ ስር የተካተቱ ሲሆን ዝርዝራቸው በአባሪ ሦስት ውስጥ ተጠቅሷል) በዝርው ቅርፅ የሚቀርቡ ፈጠራዊ ተረኮች ሲሆኑ ተረኮቹ የሚያነሷቸው ድርጊቶችና ሁነቶች መቼና የት ተፈፅመዋል ለሚለው ተጨባጭ መረጃን የማይሰጡ፤ ሰው፣ እንሰሳትንና ግኡዛንን በገፀባህርይነት የሚያሳትፉ ናቸው። በSacred Narrative, Readings in the Theory of Myth እንደሰፈረው

> *Folktales are prose narratives which are regarded as fiction. They are not considered as dogma or history; they may or may not have happened. Nevertheless, although it is often said that they are told only for amusement, they have other important functions, as the class of moral tales should have suggested. Folktales may be set in any time and place, and in this sense they are almost timeless and placeless. (Dundes፣ 1984፣8)*

ተረቶች ፈጠራዊ ናቸው ተብለው የሚወሰዱ ዝርው ተረኮች ሲሆኑ ቀኖና ወይም ታሪክ ናቸው ተብለው የማይታሰቡ፣ (በተጨባጭ) ስለተከሰቱም ስላልተከሰቱም ሁነቶችና ድርጊቶች ሊያትቱ የሚችሉ ናቸው። . . . ምንም እንኳን አዘውትሮ ተረቶች ለተዝናኖት ብቻ የሚነገሩ ናቸው ቢባልም እንኳን ሞራል ነክ ተረቶች እንዳላቸው ያለ ሌላ ጠቃሚ ፋይዳም ያላቸው ናቸው። የተረቶች (መቼት) በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሊመሰረት የሚችል፣ በዚህ ስሜትም የተረቶቹ (መቼት) ጊዜና ቦታ አልባ ነው ሊባል የሚችል ነው።

### 3.2.2. ቀልዶች /jokes/

ቀልዶች (jokes) በሚል የወል መጠሪያ በንኡስ ርእስ 3.2.2. ስር የሚውሉ ተረኮች ከቅርፅ አንፃር ዝርው መሆናቸው እንዲሁም ፈጠራዊነታቸው ከተረቶች ጋር የሚያመሳስላቸው ባህርይ ነው። ሆኖም ቀልዶች ከተረቶች የሚለያቸውና እንደ አንድ የቃላዊ ዝርው ተረክ አይነት (sub-type) ሆነው እንዲፈረጁ የሚያበቃቸው የራሳቸው ልዩ ባህርያት አሏቸው። የተረኮቹ ልዩ ባህርያትም በራሳቸው "በቴክስቶቹ" እንዲሁም በክዋኔ ሂደት ላይ የሚንፀባረቅ ነው።

ቅርፃዊ ልዩነት በተረቶችና በቀልዶች መካከል ከሚታየው የባህርይ ልዩነት አንዱ ነው። በዚህ ጥናት ቀልድ ተብለው የሚፈረጁ ተረኮች ከተረቶች በአንፃር እየቆሙ ሲመዘኑ አጭርና ቁጥብ

ናቸው። ከታሪክ ፍሰት አንፃር ሲመዘኑም እንዲሁ ተረቶች ከመነሻው ይዘውት የተነሱትን ታሪክ ከቀልዶች በተለየ አስፋፍተው በአንፃራዊነት ዘገምተኛ በሆነ አካሄድ ሲተርኩ፤ ቀልዶች በአንፃሩ በተፋጠነ አካሄድ አንድን ታሪክ እየተረኩ ወደ ታሪኩ መቋጫ ተቻኩለው ይደርሳሉ። ከሴራ አንፃር ተረቶች በአመዛኙ ከቀልዶቹ በላቀ በጥብቅ ሴራ ላይ ሲመሰረቱ አዘውትረው ወደ ተደራሲ የሚያደርሱት አንድ አስተምህሮ አላቸው። ቀልዶቹ በሌላ በኩል በታዳሚ ዘንድ ሳቅ ማጫርን ዋነኛ አላማቸው አድርገው በግልጽ የቀረበ አስተምህሮ ሳይኖራቸው የቀረቡ ናቸው።

ከዚህ ጎን ለጎን ተረቶች በአመዛኙ በአድማጭና በተራቹ ማህበረሰብ የጋራ እሴት ላይ ተመስርተው ተጠየቃዊ ሆነው ሲቀርቡ ቀልዶች ደግሞ አዘወትረው "ትርጉም የለሽ" ("senseless") አካሄድን እየተከተሉ ከአስተምህሮ ይልቅ ለተዝናኖት አፅንኦት ሰጥተው ይቀርባሉ። "ስለወንድ አረገዘ" እና "ስለየሞተብንን ፍየል መሰልከኝ" የተነገሩት ተረክ 45 እና 41 በተነገሩበት ተፈጥሯዊ አውድ የነበራቸው ስሜት ተገናዝቦ ሲታይ ከላይ ለጠቀስኩት የቀልዶች ባህርይ ማሳያ አብነት ይሆናሉ። በተረቶችና በቀልዶች መካከል ስላለው የባህርይ ልዩነት የተነሳውን ነጥብ Oring (1992) አጠቃላይ በቀልዶችና በተረቶች መካከል የሚታይን ልዩነት በንፅፅር ያሳዩበት ገለፃ የሚያጠናክረው ነው። የ Oring ገለፃ ከተቀራረበ የአማርኛ ፍቺው ጋር የሚከተለውን ይመስላል።

> *The tale is generally longer than the joke which, by comparison, is relatively brief. The world created in the tale emphasizes the normal, the typical, and the rational; the world of the joke invokes the abnormal, the bizarre, and non-sensical. There is a tendency for the tale to be explicitly didactic where as the joke seems to avoid any explicit moralization....*
> *The above distinctions are derived solely through textual comparison. Other distinctions that have been noted, however, attend the conditions of narration. For example, tales evoke smiles whereas jokes generate laughter. (81-82)*

ተረት በአጠቃላይ፣ በአንፃራዊነት ሲታይ ቁጥብ (እምቅ) ከሆነው ቀልድ የሚረዝም ነው። በተረት የሚፈጠረው ዓለም አፅንኦቱ በመደበኛው፣ በአይነተኛው እና በተጠየቃዊው (ዓለም) ላይ ሲሆን፤ የቀልድ ዓለም አፅንኦቱ እንግዳ በሆነው፣ ባልተለመደውና በትርጉም የለሹ ላይ ነው። ተረት በውስጠታዋቂነት ትምህርት አዘል

የመሆን ዝንባሌ ሲኖረው በሌላ በኩል ቀልድ በውስጠታዋቂነት የሚነገር ስነምግባራዊ አስተምህሮ የሌለው ይመስላል።…

ከላይ የተጠቀሱ ልዩነቶች "ቴክስቶችን" በማነፃር ብቻ የተደረሰባቸው ናቸው። ይሁንእና የትረካ ሁኔታን (ክዋኔን) በማጤን ሌሎች ልዩነቶችን ማየት ይቻላል። ለምሳሌ ተረቶች ፈገግታን ሲያጭሩ ቀልዶች በሌላ በኩል ሳቅን ይፈጥራሉ።

Oring ያነሱትን ንፅፅር ሲያጠቃልሉ ቀልዶችን ከተረቶች የሚለያቸው ዋናው ነጥብ የርዝመት የእጥረታቸው ጉዳይ አለመሆኑን አፅንኦት በመስጠት የሁለቱ ተረኮች መሰረታዊ ልዩነት ቀልዶች ሳቅን የሚያጭር የመቋጫ አረፍተ ነገር (punch-line) ያላቸው ከመሆኑ የሚመነጭ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ቀልዶች ተብለው በዚህ ጥናት የተፈረጁ ሰባት ያህል ተረኮች /የተረኮቹ ዝርዝር በአባሪ ሶስት ውስጥ ተካቷል/ በአመዛኙ ከላይ የተጠቀሰውን ባህርይ የሚጋሩ ናቸው። ይህን ንኡስ ርእስ ከማጠቃለሌ አስቀድሞ ቀልዶችን እንዲሁም በንኡስ ርዕስ 3.2.1. ስር ተረቶችን አስመልክቶ የቀረበውን ሀሳብ በተጨባጭ ለማሳየት ይቻል ዘንድ ከዚህ ቀጥሎ ከየምድቦቹ አንድ አንድ ምሳሌ በመውሰድ ሁኔታውን በዝርዝር ለማስቀመጥ እሞክራለሁ።

ተረክ 7

አንድ በድንግልና ፀንቶ የሚኖር ሰው ነበር። ከእለታት በአንድ ቀን ከሚፀልይበት በአት ወጣና ከባድ ፈተና ገጠመው። አንዲት ሴት አገኘችውና "አንተ ሰው" አለችው "አቤት" ሶስት ነገር አቀረበችለት። አንድ፤ አንድ ጠርሙስ አረቂ። ሁለት ህጻን ልጅ መናገር የሚችል። ሶስት በጣም የተሣለ ሠይፍ የሚያሥፈራ። ሶስቱን አቅርባ "አንተ ሰው" አለችው "አቤት" "ወይ ይሄንን አንድ ጠርሙስ አረቂ ጠጥተህ ጨርስ፤ ወይ በዚህ ሰይፍ የዚህን ህፃን አንገት ቁረጥ፤ ወይ ከእኔ ጋር ግንኙነት ፈጽም" አለችው። አስተውሉ ሶስቱም ኃጢአት ነው። የቱን ይፈጽም! ይሄ ሰው ጨነቀው። "አይ ዛሬ እንደው ከምፀልይበት በአት ባልወጣሁ አ. . .ዬ! ምን አይነት ፈተና ገጠመኝ" አለ። አዘነ፣ አሰበ፣ አሰበ አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ ለማንኛውም እስቲ ይሄንን አንድ ጠርሙስ አረቂ ቀስ እያልኩ ልጨርሰው ከዛ እራሴን ለማሸነፍ እሞክራለሁ" (አለና) ያን አንድ ጠርሙስ አረቂ ቀስ እያለ ሲጠጣ ይጨርሰዋል ይሰክራል። እራሱን መቆጣጠር ያቅተዋል። ከሴትየዋ ጋር ግንኙነት ይፈጽማል። ወዲያው ያንን ህፃን ልጅ ይናገርብኛል ብሎ በዚያ በሰይፍ አንገቱን ቆረጠው ይባላል።

ተረክ 45

ባል ታመመ ይባላል እየሰማችሁኝ ነው? ባል ታመመ ይባላል እና ላቦራቶሪ ሽንት አምጣ ይባላል። ምን አምጣ? ሽንት አምጣ ይባላል። ሽንት ጠፋ ከየት ይምጣ [አልገጠማችሁም

እንዲህ አይነት ነገር፡፡ ይጠፋል እኮ ላቦራቶሪ ብትታዘዙ ይጠፋል፡፡] ሽንቱ ጠፋ ባለቤቱን ጠራና "እባክሽ ተዋርጃለሁ እንደው ላቦራቶሪ ቴክኒሻኑ ይስቅብኛል እንደው ሽንትሽን አበድሪኝ" አላት "ኧረ ምን ችግር አለው" አለች "ውሰድ ምን ችግር አለው" ከዚያ ሽንቷን ስትሠጥ ሲመረመር የሶስት ወር እርጉዝ በስመ አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወንድ አረገዘ ተብሎ ላቦራቶሪ ቴክኒሻኑ ከመቀመጫው ወድቆ ነው የሞተው የተባለው፡፡

በዚህ ጥናት ተረክ 7 ተረት በሚለው ተረክ 45 ደግሞ ቀልድ በሚለው ምድብ ስር የተፈረጁ ናቸው፡፡ ሁለቱን ተረኮች ከቅርፅ አንፃር ስናያቸው ተረክ 45 በአንፃራዊነት አጭር ሲሆን ተረክ 7 ረዥም ነው፡፡ በተረክ 7 የተነሳው ታሪክ በአንፃራዊነት ሲታይ ተስፋፍቶ የተተረከ ሲሆን በተረክ 45 የቀረበው ታሪክ ከመነሻው እስከ መድረሻው ድረስ የተቻኮለ አካሄድ የሚታይበት ነው፡፡ ተረኮቹ በተከወኑበት ተፈጥሯዊ አውድ ውስጥ ከነበራቸው መንፈስ አንፃር ተገናዝበው ሲታዩ ተረክ 7፣ "መጠጥ የሰው ልጆችን ህይወት ወደሀጢያት ጎዳና የሚመራና ለውድቀትም የሚዳርግ ነው" የሚል በግልፅ የቀረበ አስተምህሮ ያለው ነው፡፡ ተረክ 45 በአንፃሩ ይህ ነው የሚባል አስተምህሮ ሳይኖረው በታዳምያን ዘንድ ሳቅን ለማጫር የቀረበ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ተረክ 45፣ በተረክ 7 ውስጥ የማናየውን ሳቅን የሚያጭር የመቋጫ ዐረፍተ ነገር /Punch-line/ ይዞ ቀርቧል፡፡

በአጠቃላይ በምዕራፉ የቀረበው ሀሳብ ተጠቃሎ ሲታይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት ለሚነገሩ ተረኮች ተራቹ ማህበረሰብ ይሁነኝ ብሎ የሚሰጣቸው ስያሜና በዝርያ ለይቶ የሚያውቅበት አንድ ስርዓት የለውም፡፡ ይሁን እና ተረኮቹ ከሚከውኑበት አኳኋን እንዲሁም ከራሳቸው ከተረኮቹ (ከ"ቴክስቶቹ") አቀራረብ አንፃር ሲታይ ተራቹ ማህበረሰብ በውስጠ ታዋቂነት ተረኮቹን እውነተኛ እና ፈጠራዊ በሚል እንደሚረዳቸው ለማጤን ተችሏል፡፡ ይህ ጥናትም ይህንኑ የባህል ባለቤቶቹ ለተረኮቹ ያላቸውን ግንዛቤ መሰረት አድርጎ እውነተኛና፣ ምናባዊ በማለት ተረኮቹን በሁለት ምድብ ከፍሏል፡፡ በእነዚህ ሁለት ምድቦች የተጠቃለሉ ተረኮችንም ተንታኝ ዘዴን (analytical methodን) በመከተል በአራት የቃላዊ ዝርው ተረክ አይነቶች፤ ትውስታዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች (Reminiscences)፣ ሂሳዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች፣ ተረቶችና ቀልዶች በማለት በአይነት መድቧል፡፡ በቀጣዩ ምዕራፍ ደግሞ እነዚህ ተረኮች የሚከወኑበትን አውድና ክዋኔን አስመልክቶ ቅኝት ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ክዋኔ /performance/

በቃላዊ ዝርው ተረኮች ጥናት የተረኮቹን ክዋኔና የክዋኔ አውድ በቅርበት ማጤን የተራቹን ማህበረሰብና የተረኮቹን መሰረታዊ ባህርይ ለመረዳት የሚያበረክተው ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ Finnegan እንደሚሉት በስነቃል፣ ክዋኔ መሰረታዊ ጉዳይ እንደመሆኑ ልዩ ልዩ የስነቃል ዘርፎችን በማጥናት ሂደት ለየስነቃሎቹ ክዋኔ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይገባል (1966፣66፤1970፣3-4)፡፡ እነM.C.Sims በተመሳሳ በፎክሎር ጥናት፣ ከሚጠናው አንድ ነገር ወይም ጉዳይ ባሻገር ነገሩ የተጠቃለለበት አውድ ጭምር ሊጠና የሚገባው መሆኑን በሚከተለው መልኩ ይገልጻሉ፡፡

> *When a folklorist enters the setting of a contemporary culture, she is likely to be interested in certain types of behaviors, beliefs or items that the members of the group practice or create. That doesn't mean, however, that she will overlook all the other existing elements of the culture to focus solely on the one that most interests her. Folklorist believe that in order to best understand the cultural expression in which they are interested, they must study it in context, considering the setting in which the item is found or used; in which the behavior is practiced; in which the belief is expressed; or in which the story is told. (2005፣ 20)*

አንድ የፎክሎር ባለሙያ በዘመነኛው ባህል ላይ ትኩረቷን ስታደርግ በአንድ ቡድን አባላት ዘንድ በሚተገበር ወይም በሚፈጠር ሁኔታ ዙሪያ ትኩረቷ ሊሳብ ይችላል፡፡ ይሁንእና ባለሙያዋ በአንድ ሁኔታ ተስባለች ማለት፣ ትኩረቷን ይበልጥ የሳበውን አንድ ጉዳይ በተናጠል በመመልከት በባህሉ ውስጥ ያሉትን ቀሪዎቹን ፀባያት ቸል ትላለች ማለት አይደለም፡፡ እንደፎክሎር ባለሙያዎች እምነት ትኩረታቸውን የሣበውን አንድ የባህል መገለጫ ወይም ገፅታ በሚገባ ለመረዳት የዘርፉ ባለሙያዎች፣ ሁኔታው የሚገኝበትን ወይም አገልግሎት ላይ የሚውልበትን መቼት፣ ባህሪው የሚተገበርበትን ሁኔታ፣ እምነቱ የሚገለፅበትን አኳኋን ወይም ታሪኩ የሚነገርበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

የተረኮችን ክዋኔና የክዋኔ አውድ መቃኘት የዚህ ጥናት አንዱና ዋነኛ ትኩረት ነው፡፡ በመሆኑም በምዕራፉ የተረኮቹ ከዋኞችና አድማጮች ማንነትና መስተጋብር እንዲሁም የክዋኔው ተፈጥሯዊ አውድና የአከዋወን ዘዴ (ስልት) ትኩረት ተሠጥቶት ይቃኛል፡፡ በተያዘው ምዕራፍ የተረኮቹን ክዋኔና የክዋኔ አውድ ከመቃኘት አስቀድሞ ቅኝቱን በማንበብ ሂደት ከወዲሁ ሊጤን የሚገባው ነጥብ አለ፡፡ ይኸውም ተረኮቹ በሚከወኑበት ተፈጥሯዊ አውድ ስለተረክነታቸው (for their own sake) የሚነገሩ ባለመሆናቸው የተረኮቹ ክዋኔ አጠቃላይ ገፅታ የሚቃኝ (oriented) መሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የተረኮቹ ተራቾች፣ ተረኮቹን መተረክን ተቀዳሚ አላማቸው አድርገው አይተርቷቸውም፤ ታዳምያኑም እንዲሁ ተረኮቹን ማድመጥን ዋነኛ አላማቸው አድርገው አይታደሙባቸውም ፡፡ ይህ መሆኑም ተረኮቹ የሚከወኑበትን አውድ ገጽታ፤ የተራቾች እና የአድማጮችን ማንነትና ሚና እንዲሁም የአከዋወን ስልትና ባህርይ ይወስናል፡፡ የተረኮቹ አጠቃላይ ገፅታ፣ ተረኮቹ ስለተረክነታቸው የሚነገሩ ባመሆናቸው እንዴት ይቃኛል የሚለው ሀሳብ በየንኡስ ርእሶች ስር እንደአስፈላጊነቱ እየተነሳ በዝርዝር ይታያል፡፡

### 4.1. የመከወኛ አውድ /context/

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ተረኮች መከወኛ አውድ፣ ተረኮቹ ተጠቃለው የሚገኙባቸው ስብከቶች በሚቀርቡባቸው ዋና ዋና ጊዜያቶችና ቦታዎች የተወሰነ ነው፡፡ ከጊዜ አንፃር ተረኮቹ በአመሻሽ የየአብያተ ክርስቲያን ጉባኤዎች፣ በንግስ ቀናት ታቦት በአውደ ምህረት ሲቆም፣ በጥዋት ቅዳሴ ማብቂያ ላይ፣ እንዲሁም በፆም ቀናት የቀትር ቅዳሴ ከመጀመሩ አስቀድሞ ባሉት ጊዜያቶች በሚደረጉ ስብከቶች ላይ ይነገራሉ፡፡ ከቦታ አንጻር ተረኮቹ በአውደምህረት፣ በመቅደስ ውስጥ፣ በፀበል መጠመቂያ ቦታና በአብያተ ክርስቲያን ደጃፍ ይከወናሉ፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ በዝርዝር የቀረቡ የስብከት ስርዓቶች የሚካሄዱባቸው ጊዜያቶችና ቦታዎች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ሲነገሩ የሚደመጥባቸው ቢሆንም የስብከት ስርዓቶች ተካሂደው ባለበት አጋጣሚ ተረኮቹ የማይነገሩበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የተረኮች መከወኛ ቦታዎችና ጊዜያቶች ናቸው ተብለው ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱ አውዶች ተዘውታሪ የተረኮች መከወኛ አውድ ከመሆን አንጻር አንዳቸው ከሌላቸው ጉልህ ልዩነት አላቸው፡፡ በዚህ ጥናት ከተፈጥሯዊ መቼት ከተሰበሰቡ ተረኮች መካከል 95 በመቶ ያህሉ በልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያን በተደረጉ የአመሻሽ የአውደምህረት ጉባኤዎች ላይ የተደመጡ ወይም የተቀረፁ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 5 በመቶ ያህሉ በአንጻሩ ከፆም ቀናት የቀትር ቅዳሴ መጀመር አስቀድሞ በመቅደስ ውስጥ ከተደረጉ ስብከቶች የተወሰዱ ናቸው፡፡ በመስክ በነበረኝ ቆይታ ከጥዋት ቅዳሴ መልስና በንግስ ቀናት በአውደ ምህረት፣ በፀበል ቦታና በቤተ ክርስቲያን ደጃፍ በሚደረጉ ስብከቶች ቅኝት ባደርግም ለዚህ ጥናት መሰረት የሆኑ ተረኮች



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሲነገሩ ያደመጥኩበት አጋጣሚ አልነበረም። ከላይ በዝርዝር በጠቀስኳቸው አውዶች ላይ ከሶስት ወራት በላይ ባደረኩት ቅኝት ተረኮቹ ሲነገሩ አለማድመጤ አውዶቹ የቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ተዘውታሪ መከወኛ ጊዜያቶችና ቦታዎች እንዳልሆኑ ያሳያል። ይሁንእና አጋጣሚው ከዚህ ባለፈ ተጠቃሽ አውዶች፣ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ፍፁም አይነገሩባቸውም ወደሚል መደምደሚያ አያደርስም። ለዚህ አባባል ድጋፍ የሚሆኑ ሁለት አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል። አንዱ አብነት ለዚህ ጥናታዊ ስራ የስብከት ስርዓቶችን መከታተል ከመጀመሬ አስቀድሞ በአውዶቹ በተገኘሁባቸው ጊዜያዎች ተረኮቹ ሲነገሩ የሰማሁባቸው ውሱን አጋጣሚዎች መኖራቸው ነው። ሁለተኛው አብነት የቤተ እምነቱ ምእመናን ከሆኑ ግለሰቦች ጋር ጉዳዩን አስመልክቶ ባደረግሁት ውይይት ተረኮቹ በአውዶቹ ላይ ዘወትር ባይሆንም በአንዳንድ አጋጣሚዎች ሲተረኩ የሚደመጡበት ሁኔታ መኖሩን ለማረጋገጥ መቻሌ ነው።

የአመሻሽ ጉባኤዎች ከቀሪዎቹ አውዶች እጅግ በላቀ ሁኔታ ተረኮቹ ተደጋግመው ሲከወኑባቸው መታየቱ፣ እንዲሁም በተቀሩት ጊዜያቶችና ቦታዎች ላይ ተረኮቹ የሚነገሩበት ሁኔታ ድግግሞሹ በቁጥር አናሳ መሆኑ በዋናነት ከሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች፤ ከጊዜና፣ ከስብከቱ አላማ፤ የሚመነጭ ነው ለማለት ይቻላል። የአመሻሽ ጉባኤዎች በዋናነት ለምእመናን የስብከት አገልግሎት ለመስጠት ተብለው የሚዘጋጁ በመሆናቸው በአንፃራዊነት ሰፊ ሊባል የሚችል የስብከት አገልግሎት ጊዜ አላቸው። በአዘቦት ቀናት በአመሻሽ ጉባኤዎች ላይ የሚካሄድ የስብከት አገልግሎት በአማካይ ከአንድ ሰአት እስከ አንድ ሰአት ከሰላሳ ለሚጠጋ ጊዜ ይዘልቃል። በክብረ በአላትና በልዩ ጉባኤዎች ዝግጅት ወቅት ደግሞ ስርዓቱ በአማካይ ከሁለት ከሰላሳ እስከ ሶስት ሰአት ድረስ ሊዘልቅና ከአንድ በላይ (ሁለት ወይም ሶስት) ሰባክያነ ወንጌልን ሊያሳትፍ ይችላል*። ይህም በአብዛኛው በአማካይ ከሰላሳ እስከ አርባ ደቂቃ ባለው ጊዜ ውስጥ ከሚጠናቀቁት፤ የቅዳሴ ስርአት መነሻና ፍፃሜ ላይ እንዲሁም በአውደምህረት በቆሙ ታቦቶች ፊት ከሚካሄዱ ስብከቶች አንፃር ሲታይ ሰፊ ጊዜ ነው። የጊዜው መስፋት ታዲያ ሰባክያነ ወንጌል የሚያነሷቸውን ሀይለቃላት በተለያዩ ተረኮች አስደግፈውና አስፋፍተው የሚያቀርቡበትን የተሻለ እድል ይሰጣቸዋል። የስብከት አገልግሎቱ ጊዜ መርዘም ሰባክያነ ወንጌል ተረኮቹን እንዲተርኩ ሰፊ እድል ከመስጠቱ ባሻገር አንዳንድ ጊዜ ተረኮቹ መተረታቸው የግድ አስፈላጊ የሚሆንበትን አጋጣሚ ይፈጥራል። ሁኔታውን ሰባኬ ወንጌል ሀብታሙ እንደሚከተለው ገልፀውታል።

---

* አዘቦትና ክብረበአላት በማለት ቀናትን ለይቼ ሳስቀምጥ ለምሳሌ እለቱ በአማንያኑ ዘንድ የቅድስት ማርያም ዕለት በመባል የሚታወቀው የወሩ ወይም የአመቱ ሃያ አንደኛ ቀን ከሆነ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያናትና ማርያም ድርብ አለች በሚባሉበት አብያተ ክርስቲያን ሁሉ ዕለቱ ክብረበአል ይሆንና የሚደረጉ የስብከት ስርአቶች በዚሁ በበአል መንፈስ የሚካሄዱ ይሆናሉ። ከዚህ ውጪ ባሉ ቤተ ክርስቲያናት በአንፃሩ በእለቱ የሚደረጉ የስብከት ስርአቶች በአዘቦት ቀን መንፈስ የሚካሄዱ ናቸው።

ምሳሌዎቹን መጠቀም ከሚገባው በላይ፣ በጣም ትልቅ ነገር ነው፡፡ አንደኛ ሰው ስልቹ ነው፣ ይሰለቻል፡፡ በአንድ መድረክ ላይ ደግሞ ቢያንስ አንድ ሰባኪ ከአርባ እስከ ስልሳ ደቂቃ ይቆያል፡፡ ከዛም በላይ ሊቆይ ይችላል፡፡ ያንን አርባና ስልሳ ደቂቃ ዝም ብሎ ያ ሰባኪ ደረቅ ቃል ብቻ የሚናገር ከሆነ ሰሚው ይሰለቻል፣ ሰሚው ሰውነቱ ይዝላል፣ ይደክማል፡፡ ስለዚህ አንድ አንድ ጊዜ ምሳሌዎቹን እያስገባሽ ስትነግሪያቸው እነዚያ ምሳሌዎች ሰዎችን ይስባሉ፣ ሰውየው ትኩረት እንዲያደርግ ያስችላሉ፡፡ (29/8/2002 ቃለ መጠይቅ ካሴት ተራ ቁ. 2፣ገፅ ሀ)

ከላይ እንደተገለፀው የተረኮች መተረቻ ዋነኛ ወይም ተዘውታሪ አውድ መሆን ከጊዜ መርዘምና ማጠር ባሻገር ስብከቱ ከተፈጠረበት አላማ አንጻር ጋርም የሚዛመድ ነው፡፡ የስብከቶቹን ባህርይ፤ የስብከት ስርአቶቹ የተፈጠሩበት አላማ መንፈስ ሲወስነው፤ የስብከቱ ባህርይ መወሰን ደግሞ በተረኮቹ መነገር ወይም አለመነገር ላይ የራሱን ተፅዕኖ ያሳርፋል፡፡ ለምሳሌ በቅዱስ ጊዮርጊስ ክብረበአል ላይ ለመስበክ በአውደ ምህረት የቆመ ሰባኬ ወንጌል አውዱ ሰማዕቱን ለመዘከር የተፈጠረ በመሆኑ የሰባኬ ወንጌሉ ትኩረት (የሚያነሳው ርዕስ ጉዳይ) በዛው አውዱ በተፈጠረበት አላማ ላይ የተወሰነ ይሆናል፡፡ በሌላ አገላለፅ ሰባኪው በእለቱ የቅዱስ ጊዮርጊስን እለተ በአል ከመዘከር በዘለቀ ሌሎች ሃይማኖታዊ እንዲሁም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በማንሳት የተስፋፋ ስብከት ለማድረግ የሚኖረው እድል ጠባብ ነው፡፡ በሌላ በኩል እለታዊ በሆነው የአመሻሽ ጉባኤ ላይ የሚገኘው ሰባኬ ወንጌል ከሚሰብክበት ርዕስ ጉዳይ ምርጫ አንፃር "ነፃ" ነው፡፡ ይህ የሰባኪው "ነፃነት" ስብከቱ ከሚሰጥበት ሰአት ሰፊ መሆን ጋር ተዳምሮ ከሃይማኖታዊ ጉዳይ በተጨማሪ ወይም ጎን ለጎን ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን እያነሳ በልዩ ልዩ ተረኮች (አንዳንድ ሰባክያነ ወንጌል እንደሚሏቸው በምሳሌዎች) እያስደገፈ ለመስበክ ሰፊ እድል ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ እስከአሁን ከነበረን ቆይታ ተረኮች ሲከወኑ የሚታዩባቸው አውዶች የትኞቹ እንደሆኑ ለማየት ችለናል፡፡ የአመሻሽ የአውደ ምህረት ጉባኤዎች ተረኮቹ በአንፃራዊነት በብዛት የሚከወኑባቸው አውዶች እንደሆኑም ተመልክተናል፡፡ በዚህ መሰረት፣ በሚከተሉት ንኡሳን ርእሶች ስር የተረኮችን ክዋኔና የክዋኔ አውድ አስመልክቶ የሚደረገው ቅኝት እነዚህን ዋነኛ መከወኛ አውዶች፤ መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡

የአመሻሽ ጉባኤዎች በአመዛኙ በአዘቦት ቀናት በ11:30 ላይ ተጀምረው እስከምሽቱ 1:00 ድረስ የሚዘልቁ ሲሆን፣ በበዐል ቀናት ከ10:30 እስከ ምሽቱ 2:00 እና 2:30 ድረስ የሚቆዩበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ተረኮቹን የሚያደምጡ ግለሰቦች ዋነኛ ታዳሚነታቸው ለስብከተ ወንጌሉ

ወይም ለሃይማኖታዊ ተልዕኮ እንደመሆኑ ብዛታቸው እንደየዕለቱ፤ በቁጥር በአማካይ ከ150 እስከ 2ሺ.ህ ድረስ ሊዘልቅ ይችላል፡፡ የታዳሚው ቁጥር መብዛትና ማነስ፣ ዕለቱ በአልና አዘቦት ከመሆኑ ባሻገር የስብከት አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቤተ ክርስቲያን መሀል ከተማ (በርካታ ኗሪዎች የሚገኙበት) አካባቢ ከመሆኑ አንፃርም ይወሰናል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ፤ አመዛኙ አማንያን በአሉ ለሚከበርለት መልዐክ ወይም ፃድቅ ወይም ሰማዕት ባላቸው የውዴታ ደረጃ መለያየትም እንዲሁ የታዳሚው ቁጥር ይወሰናል፡፡ በዕለቱ ትምህርቱን የሚሠጠው መምህር ያለው የታዋቂነት ደረጃም ለምዕመኑ ቁጥር መብዛትና ማነስ የሚያበረክተው የራሱ ድርሻ አለው፡፡ በነዚህ ምክንያቶች የተነሳ የታዳምያኑ ቁጥር መብዛትና ማነስ በአጠቃላይ በስብከት ስርአቱ በተለይ ደግሞ በስብከት ስርአቱ ውስጥ ተጠቃለው በሚነገሩ ተረኮች ላይ የሚያሳድረው ጉልህ ተፅዕኖ አለው፡፡ ተፅዕኖው ምን ይመስላል የሚለው በንኡስ ርእስ 4.3 ስር በስፋት የሚታይ ይሆናል፡፡

የአመሻሽ ጉባኤዎችን ለመካፈል በቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ምእመን በቅፅረ ግቢው ከቤተ ክርስቲያኑ ህንጻ ፊት ለፊት ለሰባክያነ ወንጌል ከሚዘጋጀው መቆሚያ መድረክ ትይዩ በአማካይ በአምስት ሜትር ርቀት ላይ በሚደረደሩ ወንበሮች ላይ ይቀመጣል፡፡* ከወንበሮቹ የሚተርፈው ምእመን ደግሞ በቅፅረ ግቢው በተሰሩ መጠለያዎች፣ ለመቀመጥ ምቹ በሚሆኑ ገላጣ ስፍራዎች ላይ ሁሉ ይቀመጣል፡፡ በተለይ ዕለቱ ክብረ በዓል ከሆነ ከወንበሮቹ የሚተርፈው አመዛኙ ምዕመን ሰባኬ ወንጌሉ ከቆመበት ጥቂት እርምጃዎች እራቅ ብሎ አንስቶ በመላው ቅፅረ ግቢው መሬት ላይ ይቀመጣል፡፡ የተቀረው ምእመን እንዲሁ መሬት ከተቀመጠው ምእመን በስተኋላ ይቆማል፡፡ ይህ የታዳምያኑ አቀማመጥ ተረኮቹ በሚከወኑበት አውድ በተራቹ እና በታዳሚው መካከል ለሚካሄድ የገፅ ለገፅ ተራክቦ /face–to–face communication/ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የምዕመናኑ አቀማመጥ ሴቶች ከመምህሩ አንፃር በስተግራ ነጠላቸውን በአመዛኙ በትዕምርተ መስቀል አጣፍተውና ተከናንበው ሲቀመጡ ወንዶቹ ከዘወትር የተለየ የአለባበስ ስርዓት ሳይከተሉ ከመምህሩ በስተቀኝ ይቀመጣሉ፡፡ የአለባበስ ስርዓቱን አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሰባክያነ ወንጌል፣ ቅዱስ ጳውሎስ ሴቶች ተከናንበው ይቀመጡ በሚል

* በአብያተ ክርስቲያን መምህራን ለስብከት አገልግሎት ሲቀርቡ የሰባኪነትም የተራችነትም ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በተመሳሳይ የተረኮቹ አዳማጮች በአውዶቹ ሲታደሙ ሚናቸው የምእመንነትም/የታዳሚነትም (የአዳማጭነትም) ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ፅሁፍ፤ ሰባኪ/ተራች(ከዋኝ) እና ምእመን/ታዳሚ የሚሉት መጠሪያዎች የባህል ባቤቶችን ለማመልከት እንደየሁኔታው ተተካኪ ሆነው በመግባት ያገለግላሉ፡፡

በመፅሀፍ ቅዱስ በተናገረው ቃል መሰረት ሴቶች  በቤተ ክርስቲያን ተከናንበው ይቀመጣሉ ብለዋል፡፡*

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በበአል ቀናት በሚካሄዱ ጉባኤዎች ወቅት በአብያተ ክርስቲያን የሚታደመው ህዝበ ክርስቲያን ቁጥር እጅግ በርካታ ነው፡፡ የህዝበ ክርስቲያኑ ቁጥር በርካታ መሆን ደግሞ በአጠቃላይ በአውዱ ላይ በሚካሄዱ ስብከቶች በተለይ ደግሞ በስብከት ስርዓት ውስጥ ተጠቃለው በሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ክዋኔ ሂደት ላይ የራሱ የሆነ አወንታዊም አሉታዊም ተፅእና ያሳድራል፡፡ ከአወንታዊ ተፅእኖው ልነሳ፡፡ የታዳምያኑ ቁጥር በበዛ መጠን በአውዱ ለሚነገረው ተረክ የሚሰጡት ምላሽ (እልልታው፣ ጭብጨባው፣ ከንፈር መጠጣው ወዘተ.) በዛው መጠን ጉልህ ይሆናል፡፡ የታዳምያኑ ተሳትፎ ጉልህ መሆን በአንፃሩ የተራቹን ስሜት ይበልጥ እየቀሰቀሰና እያነቃቃ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ተረኮቹን በጋለ ስሜትና በላቀ አቀራረብ እንዲከውናቸው ምክንያት ይሆናል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን እለቱ በዐል ሲሆን በአብያተ ክርስቲያን ከሚገኘው በቁጥር በርካታ ከሆነው ምእመን አመዛኙ ምሽቱ ለአይን ያዝ ማድረግ ሲጀምር ጧፎችን ያበራል፡፡ የተለኮሱት ጧፎች ቢጫማ ብርሃን ሲፈጥሩ፣ የጧፎቹ ብርሃን ከምሽቱ መጨለም፣ ችምችም ብለው ከሚታዩ ወንድ ምእመናን ጥቁር ራሶች እንዲሁም ሴት ምእመናን ከተከናነቧቸው ነጭ ነጠላዎች ጋር እየተነፃፀረ ለአይን ከሚፈጥረው ህብረ ቀለም ባሻገር የእለቱን ክብረ በአልነት እያመላከተ ወይም አፅንኦት እየሠጠ በከዋኙና በታዳሚው መስተጋብር ላይ ጉልህ የስሜት መነቃቃትን ይፈጥራል፡፡

* ሰባክያኑ ቅዱስ ጳውሎስ ሴቶች እንዲከናነቡ አዟል በማለት የጠቀሱት ሀሳብ በመፅሀፍ ቅዱስ፣ ቆሮንቶስ ፩ ፣ 11፤4-16 ድረስ የቀረበ ነው፡፡



ሴት ምዕመናን በማሕደረ ስብሃት ቅድስት ልደታ ለማርያምና ደብረ መድኃኒት
መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በአመሻሽ ጉባዔ ላይ /ምስል 1/

በሌላ በኩል በክብረ በአላት ዕለት በሚካሄዱ የአመሻሽ ጉባኤዎች ወቅት የምዕመኑ መብዛት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በተረኮቹ ክዋኔ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅእኖም አለው። በአዘቦት ቀናት በሚደረጉ የስብከት ስርዓቶች ወቅት አብያተ ክርስቲያኑን ለመሳለምና ፀሎት አድርሰው ለመመለስ ከሚንቀሳቀሱ ጥቂት ምእመናን እንዲሁም የስብከት ስርአቱን ለመከታተል የታደሙ ምዕመናንን ተከትለው ከሚመጡ አንድ አንድ ህፃናት ውርውርታ በስተቀር የታዳምያኑን ቀልብ ወይም ትኩረት የሚከፍል ጉልህ እንቅስቃሴ አይታይም። እለቱ ክብረ በዓል ሲሆን ግን የምዕመኑ ቁጥር እጅግ ከመብዛቱም በላይ የስብከት ስርዓቱን ለመከታተል ከሚታደመው ምዕመን ባሻገር እለተ ክብሩን በማሰብ ተሳልመው፣ ጸሎታቸውን ወይም ስዕለታቸውን አድርሰው ለመመለስ በየአብያተ ክርስቲያኑ የሚገኙ ምዕመናን እንቅስቃሴ ጉልህ ይሆናል። ከምእመናኑ እንቅስቃሴ ጎን ለጎን በዕለቱ ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ጋዜጦችን፣ መፅሄቶችንና ሲዲዎችን፣ እለቱ የተዘከረበትን ፀዲቅ (ዳቦ) ለምእመናን ለማድረስና ለማቅመስ የሚንቀሳቀሱ ወጣቶችና ታዳጊዎች እንዲሁም ከምእመናን ምፅዋት የሚጠይቁ ነዳያን እንቅስቃሴ የላቀ ነው። ይህ ጉልህ እንቅስቃሴ ታዲያ በተራቹ እና በታዳሚው መካከል ላለ መስተጋብር በተወሰነ ደረጃ መሰናክል (barrier) ይሆናል።

በበዐል ቀናት የሚታየው የላቀ እንቅስቃሴና እንቅስቃሴው የሚፈጥረው ድምጽ፣ ከፍተኛ ድምጽ በሚያወጣ ማጉያ እየታገዘ የሚካሄደው ስብከት እንዳይደመጥ አይገታም። ይሁን እና በአውዱ አልፎ አልፎ የተወሰኑ የንግግር ድምፆች በተለይ በዝቅተኛ ድምጽ የሚነገሩት የስብከት ወይም የተረክ ክፍሎች እንዳይደመጡ እንቅፋት ይሆናል። ታዳሚያን በዚህ እንቅፋት በተለይ በይበልጥ ሲታወኩ የሚታዩት ከአጠቃላይ የስብከት ስርዓቱ በላይ ተረኮቹ በሚነገሩበት ጊዜ ነው። በአንፃራዊነት ተረጋግተው ተቀምጠው የነበሩ ምዕመናን ተረኮቹ መነገር ሲጀምሩ በጥድፊያና "ትዕግስት በማጣት" እንቅስቃሴው የሚፈጥረውን ድምጽ ለማስቆም ጥረት ያደርጋሉ። ይህ የታዳምያኑ ተግባር በእለቱ የሚፈጠረው እንቅስቃሴ በትረካው ሂደት ያለውን አሉታዊ ተፅእኖ ከማሳየት ባሻገር ታዳምያን ለሚነገሩ ተረኮች ያላቸውን ስሜተ ስሱነትም (sensitivity) ያሳያል። ከዚህ ጎን ለጎን ታዳምያን ተረኮቹ መነገር ሲጀምሩ፣ ተረኮቹ መነገር ከመጀመራቸው በፊት ከነበራቸው ሁኔታ በተለየ እንቅስቃሴዎቹ እይታቸውን እንዳይጋርዱ አንገቶቻቸውን ወደግራና ወደ ቀኝ በማዝመም አንዳንዴ ወደላይ በመምዘዝ ለመሸሽ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። በዚህ መልኩ ታዳምያን ከተራቹ ጋር የነበራቸውን የገፅ ለገፅ ተራክቦ ለማስጠበቅ የሚያደርጉት ጥረት በቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የክዋኔ ሂደት የተራኪው አካላዊ እንቅስቃሴ እና የፊት ለውጥ በክዋኔው ተግባቦታዊ ሂደት ላይ ያለውን ጉልህ ድርሻ ያመላክታል።

### 4.2. ከዋኙ /performer/

Finnegan እንደሚሉት የስነቃል ህልውና በአንድ በተወሰነ አጋጣሚ በቃላት አቀናብረው በሚያቀርቧቸው ከዋኞች ላይ የተመሰረተ ነው (1970፣2)። የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሚነገሩበት ተፈጥሯዊ አውድ እንዲከወኑና ለታዳሚዎቻቸው እንዲደርሱ የከዋኞች ሚና ወሳኝነት አለው። በመሆኑም የተረኮቹ ተግባራዊነት ከከዋኞቻቸው ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። በዚህ መሰረት የዚህ ንኡስ ርዕስ ትኩረት በተረኮቹ ክዋኔ፣ የከዋንያንን ማንነትና ሚና መቃኘት ይሆናል።

በያዝነው ምዕራፍ መነሻ ላይ እንደተጠቀሰው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተቀዳሚ አላማቸውን ተረኮቹን መከወንን ባደረጉ ተራቾች የሚተረቱ አይደሉም። በመሆኑም ተረኮቹ በተራች እና በአድማጩ ማህበረሰብ ዘንድ ስለተረክ አተራረክ ክሂላቸው ልዩ ክብር ወይም እውቅና የሚሰጣቸው ባለሙያ (professional) ከዋኞች ወይም ተራቾች የሏቸውም።

በሌላ በኩል ቃላዊ ዝርው ተረኮች፣ ተጠቃለው የሚነገሩባቸው የስብከት ስርዓቶች ከሚተዳደሩበት የአብያተ ክርስቲያን ስርአትና ህግ ውጪ ባለመሆናቸው የከዋኞች ማንነትም

በዚሁ የስብከት ስርዓቱ በሚተዳደርበት ህግና ስርዓት ይወሰናል፡፡ ሴቶች በስብከት አገልግሎት እንዳይሳተፉ የአብያተ ክርስቲያን ስርአት ያግዳል፡፡* ይህ መሆኑም በቀጥታም ባይሆን በተያያዥ ሴቶች ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በተጠኑባቸው ተፈጥሯዊ አውዶች እንዳይከውኑ የአብያተ ክርስቲያኗ ህግና ስርዓት አቅቧቸዋል፡፡


አዋቂ ወንድ ሰባክያነ ወንጌል ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በተጠኑበት ተፈጥሯዊ አውድ ውስጥ የሚተርቱ ብቸኛ ከዋኞች ሲሆኑ ተራቾቹ ተረኮቹን የመተረክ ክሂልን በመደበኛ ትምህርት ቤት በመገኘት የቀሰሙ አይደሉም፡፡ ተራኪዎቹ፣ ተረኮቹን ከእናቶችና ከአባቶች ወግ ካደመጧቸው፣ በልዩ ልዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ባላቸው ተሳትፎ ካዩዋቸውና ከሰሟቸው፣ ከመገናኛ ብዙሀን ካነበቧቸውና ካደመጧቸው፣ በአጠቃላይ በእለት ተእለት ህይወታቸው ካስተዋሏቸው ሁነቶችና ድርጊቶች በመነሳት ይተርቷቸዋል፡፡ ሁኔታውን አስመልክቶ ለሰባክያነ ወንጌል በቀረበ ጥያቄ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት መስሪያቤት ዋና ስራ አስኪያጅ የሆኑት ሊቀማእምራን ፋንታሁን፡-

> አንድ ሰባኪ ትልቁ ነገሩ የተማረውን ብቻ ይዞ መቀመጡ አይደለም፡፡ ሚዲያዎችን መከታተል ይኖራል፣ ማንበብ ይኖራል፡፡ ማንበብ ሲባል ደግሞ ለማንበብ መጽሐፍ አይመረጥም ለእውቀት መንገድ ላይ ጋዜጣ ማንበብ ሊሆን ይችላል፣ እየሄድሽ ድንገት ሰዎችን ልትጠይቂ ትችያለሽ፤ ሰዎች ከሚያወሩት ከሚጫወቱት ልታገኚ ትችያለሽ፣ እናቶች ከሚያወሩት ልታገኚ ትችያለሽ፡፡(27/9/2002፣ ቃለ መጠይቅ ካሴት ተራ ቁ. 5፣ገፅ ለ)

በማለት ምላሽ ሲሰጡ ጥያቄው የቀረበላቸው ቀሪዎቹ ሰባክያነ ወንጌል የሰጡት ምላሽም ከሞላ ጎደል ከላይ ከቀረበው ገለፃ ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

---

* የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስርዓት ሴቶችን በስብከት አገልግሎት እንዳይሳተፉ የሚያግደው በመፅሐፍ ቅዱስ፣ በቆሮንቶስ ፩፣ 14፤34-36 እና ጢሞቴዎስ ፩፣ 2፤11-15 ውስጥ ቅዱስ ጳውሎስ ሴቶች በስብከት አገልግሎት እንዳይሰማሩ በማለት ባሰፈረው ቃል መሰረትነት መሆኑን ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ሰባክያነ ወንጌል ይጠቅሳሉ፡፡



መምህር ብርሃን አንለይ በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል በስብከተ ወንጌል አገልግሎት /ምስል 2/

ከዚህ ጋር በተያያዘ በዛ ያሉት ሰባክያነ ወንጌል እንደሚሉት ለስብከት አገልግሎት ወደ አውደ ምህረት ከመቅረባቸው ቀደም ብለው ለስብከት የሚሆናቸውን ርዕሰ ጉዳይ መርጠው ይዘጋጃሉ። በዚህ ጊዜ ከላይ በሊቀማእምራን ፋንታሁን ከተዘረዘሩትና ከሌሎች መሠል ምንጮች ካገኟቸው ተረኮች መካከል ከርእሰ ጉዳያቸው ጋር የሚሄዱትን ተረኮች አስቀድመው በመምረጥ ተዘጋጅተው ወደስብከት ይገባሉ። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ደግሞ ከያዙት ርእሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች ድንገት ወደ አእምሯቸው ሲመጡ በዛው ቅጽበት ይተርኳቸዋል እንጂ ቀደም ብለው የተዘጋጁባቸው አይሆኑም። አመዛኙ ሰባክያን እንደሚሉት ከስብከት ስርዓቱ በፊት ተዘጋጅተው ያቅርቧቸውም በስብከት ስርዓቱ ወቅት ድንገት በአእምሯቸው ሲከሰቱ ይተርኳቸው፣ በየትኛውም መንገድ ቢሆን ተረኮቹን የሚተርኳቸው ቀድመው ከሰሙበት ምንጭ እንዳሉ ቃል በቃል በመድገም አይደለም። ከተለያዩ ምንጮች ያገኟቸውን ተረኮች ይዘው ከተነሱት ርእሰ ጉዳይ፣ ተረኩን ከሚያቀርቡለት ታዳሚ ማንነት፣ ከራሳቸው ከሰባክያኑ ተመክሮ አንፃር አስማምተው ያቀርቧቸዋል። ሰባኬ ወንጌል ሀብታሙ ይህን ሁኔታ አስመልክተው፡-

አብዛኛዎቹን በራሴ አባባል ነው ምተረጉማቸው፤ በራሴ አካሄድ፡፡ ምክንያቱም ከትምህርቴ፣ ከርእሴ ጋር እንዲሄድ እያደረኩ እያጣጣምኩ ነው፡፡ ያን ለማድረግ ደግሞ ግዴታ ምሳሌዎቹን ሙሉ ለሙሉ አትወስጃቸውም...፡፡ በራሴ ቋንቋና በራሴ ጥበብ ነው ከርእሱ ጋር ይሄድልኛል መልዕክቱን ያስተላልፍልኛል በሚል ሁኔታ አስማምቼ ቃላቶችን አሳክቼ ነው የማቀርባቸው፡፡ (29/8/2002፣ቃለ መጠይቅ ካሴት ተራ. ቁ. 2፣ ገፅ ሀ)

ሊቀማእምራን ፋንታሁን በተመሳሳይ፡-

ስብከት ሁለት አይነት መንገድ ነው ያለው፡፡ አንደኛ ዝግጅት ይኖርሻል ከዝግጅት በተረፈ ደግሞ እዛ ሄደሽ (ወደ አውደምህረት ቀርበሽ ለማለት ነው) "ስለምትናገሩት ነገር አትጨነቁ መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ ያድራል፡፡ እሱ ይናገራል" ይላል ቅዱስ መፅሀፍ እና እዛ ደግሞ አማትበሽ አውደ ምህረት ላይ ቆመሽ ስትናገሪ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የሚያቀብልሽ ይኖራል፡፡ ከዝግጅቱ ጋር ተያይዞ ስለዚህ ያንን (ከተለያየ ምንጭ ያገኘሁትን ተረክ ለማለት ነው) እንዳለ ላላቀርበው እችላለሁ፡፡ አሁን ከእናቶች የሰማሁትን ቡና ሲጠጡ ሊሆን ይችላል እንዲሁ ሲጫወቱ ሀዘን ቤት ተቀምጠው ሌላም ያንን እንዳለ አላቀርበውም፡፡ አዋዝቼ ከራሴ ትምህርት ጋር እንዲያምር አድርጌ ላቀርበው እችላለሁ፡፡ (27/9/2002፣ቃለ መጠይቅ ካሴት ተራ. ቁ. 5፣ ገፅ ለ)

በማለት በሰባኬ ወንጌል ሀብታሙ የተነሳውን ነጥብ የሚያጠናክር ሃሳብ ሠንዝረዋል፡፡ አንድ ተራኪ ከሌላ ተራኪ ተረኮቹን በሚከወንበት መንገድ የሚኖረው ልዩነት ሁሉም ሰባክያነ ወንጌል እኩል ክሂል የሌላቸው ከመሆኑ የሚመነጭ መሆኑን መምህራኑ ሲገልፁ፤ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት የክህሎትም ብቻ ሳይሆን የመቀባት (የተሰጥኦ) ጉዳይ ጭምር እንደሆነ አክለው ይጠቅሳሉ፡፡ ከተለያዩ ምንጮች የሰሟቸው ተረኮች ከነባር ቅርፃቸው የመለወጣቸው ምክንያት ከታዳሚው፣ ከርእስ ጉዳዩ፣ ከሰባኬ ወንጌሉ ልምድ ጋር የማጣጣምና የክህሎት ጉዳይም ብቻ ሳይሆን እንደ ሰባክያነ ወንጌሉ እምነት በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት ከሚገኝ ሀይልም ጭምርም ነው፡፡

በቃል የሚነገር ነገር ሊዛነፍ ይችላል፡፡ ከሰው የሰማሁትን ሰውየው እንዳለው በቀጥታ ላላቀርበው እችላለሁ፡፡ ግን እኔ ሰውየው ካለው በላይ (ላቀርበው እችላለሁ) እንደችሎታ ነው፡፡ ምሳሌ የሚጠቀሙ መምህራን ብዙውን ጊዜ አንዱ አጣፍጦ፣ በጣም ሰውን አነቃቅቶ፣ ደስ አሰኝቶ፣ ሰው እንደው አንድ ስእት

ተቀምጦ አስር ደቂቃ የተቀመጠ እንዳይመስለው፣ እስከማይመስለው ድረስ ጥሩ አድርጎ የማቅረብ ችሎታ አለው። ደግሞ ፀጋው የሌለው ምሳሌውን የማያቀርብ ወንጌልን ብቻ የሚጠቀም አለ። ፀጋው ያላቸው ጥሩ አድርገው አጣፍጠው ያቀርቡታል። (አእምሮ፣8/8/2002፣ ቃለ መጠይቅ ካሴት ተራ ቁ. 1፣ ገፅ ለ)

በአጠቃላይ በያዝነው ንኡስ ርእስ በነበረን ቆይታ የቃላዊ ዝርው ተረኮች ከዋኞችን ማንነትና ሚና አስመልክቶ መረጃ ለመስጠት ተሞክሯል። በቀጣዩ ንኡስ ርእስ ደግሞ ታዳሚን አስመልክቶ ቅኝት ይደረጋል።

### 4.3. ታዳሚ /audience/

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ህልውና ከከዋኞቻቸው ጋር በጥብቅ የተቆራኘ እንደሆነ በቀዳሚው ንኡስ ርእስ ተጠቅሷል። በተመሳሳይ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ በተፈጥሯዊ አውድ ውስጥ እንዲከወኑ የታዳምያኑ መኖር የከዋኞቹን ያህል ወሳኝነት አለው። Okpewho፡- ታዳሚ፣ ቃላዊ ክዋኔ /oral performance/ ትርጉም ወይም ስሜት ኖሮት የሚፈጠርበት ብቸኛ አውድ ነው ይላሉ። አያይዘውም ባለሙያው በእርግጥ አድማጭ እንዲታደም የግድ የማይሆንባቸው አንዳንድ ክዋኔዎች ቢኖሩም በአመዛኙ ቃላዊ ክዋኔ በእውን ወይም በእርግጥ ተከስቷል የሚባለው የየከዋኙን ትኩረት ወይም አክብሮት ማግኘት የሚችልና ክዋኔውን በህሊናው ወይም በቴፕ ቀረፃ የሚያስቀር ታዳሚ ሲኖር ነው በማለት ያስረዳሉ (1992፤57)። የዚህ ንኡስ ርዕስ አላማም ለተረኮቹ መከወን አንድ መሰረት የሆኑትን ታዳምያን ማንነትና ሚና መቃኘት ይሆናል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርአት ወቅት የሚነገሩ ተረኮች ታዳሚዎች ማንነት በተረኮቹ መተረቻ አውዶች ላይ በአካል ታዳሚ ከመሆን እንዲሁም ከንቁ ተሳታፊነት (active participant) አንፃር በሶስት ደረጃ ተከፍሎ ሊታይ የሚችል ነው። ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሚነገሩባቸው የአብያተ ክርስቲያን ቅፅረ ግቢዎች ወንድ እና ሴት ህጻናት፣ ታዳጊና አዋቂ ወንድና ሴቶች በአንድነት በአካል ይታደማሉ። ከነዚህ በአካል ከሚታደሙ ህዝበ ክርስቲያናት መካከል እድሜያቸው ከአስር አመት በታች የሆኑ ህፃናት በቁጥር አናሳ ሲሆኑ በስርዓቱ ወቅት በታዳሚው መካከል ያለስጋት ወይም በነፃነት ከወዲያ ወዲህ የሚንቀሳቀሱ ታዳሚዎች ናቸው። ህፃናቱ ካላቸው አይነ ግቡነት እንዲሁም ካለማስተዋል ከሚያደርጉት አደጋ ሊያስከትልባቸው ከሚችል እንቅስቃሴ የቀሪውን ታዳሚ ቀልብ (ትኩረት) አዘውትረው

ይከፍላሉ፡፡ በዚህም በስብከት ስርዓቱ ሂደቱ ላይ አጉል ጫናን ከመፍጠር በዘለቀ ህፃናቱ በአውዱ በአካል በመታደማቸው በተረኮቹ ክዋኔ ሂደት ላይ የሚኖራቸው ተጠቃሽ ሚና የለም፡፡

ከአስር እስከ አስራ ስድስት አመት የሚሆናቸው ታዳጊ ወጣቶች በሁለተኛ ደረጃ ሊጠቀሱ የሚችሉ ታዳሚዎች ናቸው፡፡ በተጠቀሰው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ታዳጊ ወጣቶች ሴቶች ከሆኑ በአብዛኛው በአንገቶቻቸው ላይ በትእምርተ መስቀል የታሰረላቸውን ወይም በአንድ አቅጣጫ የተጣፋላቸውን ነጠላ ለብሰው፤ ወንዶች ከሆኑ ደግሞ እንደአዋቂ ወንዶች ሁሉ አብዛኞዎቹ በመደበኛ (በእለት ተዕለት) አለባበሳቸው ከአዋቂ ምዕመናን ጎን ለጎን በስርአቱ ላይ ይታደማሉ፡፡ በተጠቃሽ አውዶች ውስጥ ከሚታደሙት ታዳጊዎች ከፊሎቹ አዘውትረው ከተቀመጡባቸው ወንበሮች ላይ የተንጠለጠሉ እግሮቻቸውን ጉልህ በሆነ መንገድ ያወራጫሉ፡፡ አንገቶቻቸውን አሁንም አሁንም አንዴ ወደግራ አንዴ ወደቀኝ አንዳንዴም ወደኋላ ያሽከረክራሉ፡፡ የታዳጊ ታዳምያኑ ምግባራት ታዲያ በየአውዶቹ ውስጥ ታዳምያኑ በተከፈለ ልብ እየባከኑ ስለመሆናቸው የሚያሳስቡ ምልክቶች ናቸው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ታዳምያኑ ለወላጆቻቸው የሚያቀርቡት እንሂድ የማለት ጉትጎታ ታዳጊዎቹ በክዋኔ ሂደቱ ላይ ሙሉ ተሳታፊ እንዳልሆኑ የሚጠቁም ሌላው ሁኔታ ነው፡፡


በሌላ በኩል ከታዳጊ ወጣቶቹ ከፊሎቹ የአካባቢውን ስርአት በማክበር ወይም በተወሰነ ደረጃ በአውዱ ውስጥ ባለው ሁኔታ በመሳብ በእርጋታ ተቀምጠው ሂደቱን ይከታተላሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም አዋቂ ታዳምያን ለሚነገሩ ተረኮች ወይም ስብከቶች ስሜታቸውን የሚገልፁበትን መንገድ እየተከተሉ ስሜታቸውን ይገልፃሉ፡፡ ይህ ተግባር ታዳጊ ወጣቶቹ በታደሙበት አውድ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሚና እንዳላቸው የሚያሳይ አንድ ምሳሌ ሲሆን፣ ታዳጊዎቹ የአውዶቹ ተሳታፊዎች ስለመሆናቸው ፍንጭ የሚሠጡ ሌሎች አብነቶችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ በምዕራፍ አንድ በንኡስ ርዕስ 1.2. ውስጥ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ሲጠቀስ እንደተገለፀው፣ በአብያተ ክርስቲያን የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ለመጀመሪያ ጊዜ ቀልቤን በሳበ መልኩ የሰማሁት በአውዱ ላይ ተገኝቶ የሰማውን ተረክ ከቀናት በኋላ በማስታወስ ደግሞ ከተረከልኝ የ11 አመት ታዳጊ ወጣት ነው፡፡ የታዳጊ ወጣቱ ትረካ ኤሊ ድንጋይ እንዴት እንደለበሰች የሚያስረዳ ነበር፡፡ ተረኩ፣ እንደዛሬ ድንጋይ ያለበሰችው ኤሊ የዱር አራዊት ሁሉ በጠላትነት ሲነሱባት እምነቷን በአምላክ ላይ በመጣሏ ድንጋይ እንደለበሰችና በአምላክ ቸርነት ከጠላቶቿ ለማምለጥ እንደቻለች ያትታል፡፡ በተራኪው ይህ ተረክ ሲነገር በወቅቱ ተራኪው እምነታችሁ በእግዚአብሔር ላይ ይሁን የሚል ወይም መሰል ትምህርት ይዞ ተነስቶ ይህንኑ ለማጠናከር ተረኩን ያቀረበው እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡ ታዳጊ ወጣቱ በአንፃሩ ተረኩን


የተረዳበት ሁኔታ ወይም ከተረኩ የጨበጠው ዋና ነጥብ በእውን የሚያውቃት ኤሊ በእርግጥ ድንጋይ የለበሰችበት እውነተኛ አፍታና ገጠመኝ በተረኩ የተነገረው ሁኔታ መሆኑ ነው፡፡ ይህ የታዳጊው ግንዛቤና ተራኪው ወደታዳሚው ሊያደርሰው አስቦታል ተብሎ የሚገመተው ነጥብ መተላለፉ ታዳጊ ታዳሚዎች ተረኮቹ በሚነገሩባቸው አውዶች የእድሜ ደረጃቸው በሚፈቅደው የመረዳት መጠን ታዳሚዎች እንደሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

ሌላው አብነት ለዚሁ ጥናት የሚሆን መረጃ ለማሰባሰብ በ10/6/2002 በተለምዶ ቦሌ (ቴሌ) መድኃኔዓለም በሚል መጠሪያ በሚታወቀው ቤተ ክርስቲያን በተገኘሁበት ጊዜ የነበረኝ ገጠመኝ ነው፡፡ በዕለቱ ኢየሱስ ክርስቶስ አልአዛርን ከመቃብር ሲያስነሳው በተጠቀመበት “ፍቱትና ይሂድ”፤ በሚለው ቃል መሰረትነት ቀሲስ በላይ የዕለቱን ትምህርት ይሰጡ ነበር፡፡ ቄሱ ደግመው ደጋግመው “ፍቱትና ይሂድ” የሚለውን ቃል እየጠቀሱ ውስጣችሁ ያለውን አስሮ የያዛችሁን እኩይ ነገር ሁሉ ፍቱትና ይሂድ በማለት ሲሰብኩ ቆይተው ትምህርቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ምእመናንን መስቀል በማሳለም ያሰናብታሉ፡፡ እኔ ከጥናታዊ ስራዬ ጋር በተያያዘ ቀሲስ በላይን ለመተዋወቅ ቄሱ ምዕመናኑን ከሚያሳልሙበት ቦታ ፊንጠር ብዬ ቆሜ ተግባራቸውን እስኪጨርሱ እጠብቃለሁ፡፡ በዛ ሁኔታ ላይ እያለሁ በግምት አስራ ሁለት ወይም አስራ ሶስት አመት የሚሆነው ታዳጊ ወጣት ከምዕመናኑ መካከል እንደቆመ ለሁለተኛ ጊዜ ከቀሲስ በላይ እጅ መስቀል ሲሳለም ተመለከትኩት፡፡ በወቅቱ ገለል ብዬ ቆሜ በመታዘቤ ታዳጊ ወጣቱ ከመሳለም ባሻገር ቄሱን የማናገር ፍላጎት እንዳለው ለመረዳት ብችልም ካለው የምዕመናን ብዛት የተነሳ ቄስ በላይ ሁኔታውን አላጤኑትም ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ቄሱ ለሶስተኛ ጊዜ ልጁን አሳልመው ዞር ሲሉ እንዳላጤኑት የተረዳው ታዳጊ የቄሱን ጥቁር ሰማያዊ ካባ በእጁ ሣብ ሣብ አደረገ፡፡ በሁኔታው ታዳጊ ወጣቱ ሊያናግራቸው መፈለጉን ለመጀመሪያ ጊዜ ያጤኑት ቄስ አሻቅቦ ለሚያያቸው ልጅ ጎንበስ ብለው ጆሯቸውን ሰጡትና የሚለውን ካደመጡ በኋላ ወዲያው አጠር ያለ መልስ ሰጥተውት ቀና አሉ፡፡ ካለሁበት ርቀት ቄስ በላይ ከልጁ ጋር ምን እንደተነጋገሩ መስማት ባልችልም ከንግግራቸው በኋላ ቀደም ሲል በቄሱ ፊት ላይ ሰፍኖ የነበረው የመረጋጋት ስሜት እንደጠፋ ለመታዘብ ችዬ ነበር፡፡ በቄሱ ፊት ላይ በወቅቱ ይሄ ነው ለማለት ያልቻልኩት የመጨነቅ ስሜት እንደሰፈነ በፍጥነት ምእመናኑን ማሳለማቸውን ቀጥለው ሲጨርሱ ወደቢሮዋቸው ለመሄድ ፊታቸውን ወደእኔ አቅጣጫ መልሰው መራመድ ጀመሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ለምእመናኑ ጀርባቸውን የሰጡት ቀሲስ በላይ እጅግ መደበኛ (highly formal) በሆነው አውድ በምእመናኑ ፊት ላለመሳቅ ካደረጉት ትግል በፊታቸው ላይ ይታይ የነበረው ጭንቀት ተወግዶ (ይህን ጉዳይ ያገናዘብኩት በቆይታ ነው) ከራሳቸው ጋር እያጉረመረሙ በግልፅ መሳቅ ጀመሩ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ አጠገቤ ደርሰው ግጥምጥም ስንል ከፊታቸው ማንም እንደሌለ የገመቱት ቄስ ደንገጥና አፈር ብለው መስቀላቸውን እያሳለሙኝ አንድ ልጅ እንደ አስገረማቸው

ነገሩኝ። እኔም ልጁን ስከታተለው እንደነበር ምን እንዳላቸው ግን እንዳልሰማሁ፤ ሁኔታውን ለማወቅ ከነበረኝ ጉጉት በመነሳት ጠየቅኋቸው። "አባ አሁን ስጡትና ይሂድ ሲሉ የነበረው ምንድነው የሚሠጠው? ምንድነው የምንሰጠው?" ብሎ ነው የሚጠይቀኝ አሉ። ምንም እንኳን "ፍቱትና ይሂድ" የሚለው ቃል በስብከቱ ወቅት በተደጋጋሚ ሲነሳ የነበረና ከአጠቃላይ ስብከቱ ይዘት ጋርም ጥብቅ ቁርኝት ያለው ቢሆንም ታዳጊው በወቅቱ ሐረጉን ሊረዳው ወይም ትርጉም ሊሰጠው ወደሚችለው ሀረግ መልሶ አምጥቶታል። ይህ የታዳጊው ተግባር በአጠቃላይ በስብከት ስርዓቶች ላይ እንዲሁም በስርአቱ ወቅት በሚነገሩ ተረኮች ላይ ታዳጊ ወጣቶች እድሜያቸው በሚፈቅድላቸው የመረዳት ደረጃና መጠንም ቢሆን የአውዶቹ ታዳሚዎች ናቸው የሚለውን ነጥብ ለመረዳት እንድችል አግዞኛል። ከህፃናትና ከታዳጊ ወንድና ሴት ታዳምያን ጎን ለጎን ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አዋቂ ወንድና ሴት ምእመናን የአውዶቹ ዋነኛ ታዳሚዎች ናቸው።



ህፃናት ታዳምያን ከአዋቂ ሴት ምዕመናን ጋር በቦሌ ደብረሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል በአመሻሽ ጉባዔ ላይ /ምስል 3/



ህፃናት ታዳምያን ከአዋቂ ሴት ምዕመናን ጋር በማሕደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም እና ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በአመሻሽ ጉባዔ ላይ /ምስል 4/

አዋቂ ወንድና ሴት ምእመናን፣ ከህፃናትና ከታዳጊዎች በተለየ ተረኮቹ በሚነገሩበት አውድ በቁጥር ሰፊውን ድርሻ የሚይዙ ታዳሚዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ታዳሚዎች በንኡስ ርእስ 4.1. ስር ስለተረኮች መከወኛ አውድ በተደረገ ገለፃ በተጠቀሰው መልኩ የቤተ ክርስቲያኗ ስርዓት የሚፈቅደውን የአለባበስና የአቀማመጥ ስርአት በተለያየ ደረጃ በማሟላት በአውዱ ይታደማሉ፡፡ በአውዱ ውስጥ በሚኖራቸው ቆይታም ታዳምያኑ በአጠቃላይ በስብከት ስርዓቱ በተለይ ደግሞ በተረኮቹ የክዋኔ ሂደት ላይ ጉልህ ሚና አላቸው፡፡ ይህ የታዳምያኑ ሚና ተራኪዎች ስሜታቸውን (የታዳምያኑን) በማገናዘብ ተረኮቹን እንዲተርኩ ምክንያት ከመሆን ባለፈ ተረኮቹ የሚተረኩበት አኳኋን፣ ኪናዊ ደረጃቸው የላቀ እንዲሆን እስከማስቻል ድረስ የሚዘልቅ ሲሆን ሁኔታው ምን መልክ አለው የሚለውን በማስከተል በዝርዝር እንመልከት፡፡

አንድን ዘር ወይም ጎሳን (ethnic group) መሰረት አድርገው አንድን የፎክሎር ቅርጽ በሚፈጥሩ ማህበረሰቦች፤ የቃላዊ ዝርው ተረክ ክዋኔ ሂደት የታዳምያን ሚና የታሪኩን ሂደት ከማረምና የጎደለን ወይም የተረሳን ከማስታወስ የተራኪነት ሚና ነጥቆ እስከ መከወን ድረስ

ሊዘልቅ ይችላል፡፡* በሌላ በኩል ፎክሎር ፈጣሪው ማህበረሰብ ሃይማኖትን መሰረት ባደረገው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሚነገሩ ተረኮች ክዋኔ ሂደት ታዳምያን የታሪኩን ሂደት የማረምም ሆነ የጎደለን የመሙላትና የተረሳን የማስታወስ እንዲሁም የተራኪነት ድርሻን ወስዶ የመተረክ ሚና የላቸውም፡፡ ከነዚህ ተጠቃሽ ተግባራት አንፃር ሲታይ ተረኮቹ በሚነገሩበት አውድ የሚታደሙ ዋነኛ አድማጮች ይህ ነው የሚባል ሚና የላቸውም፡፡ ለምሳሌ በአንድ አውድ እየተነገረ ያለን ተረክ ታዳምያኑ፣ በራሱ በተራኪው ወይም በሌላ ተራኪ ቀደም ሲል ሲተረክ የሠሙት ቢሆን እንኳን ተረኩን ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሰሙት ሁሉ በፀጥታ ከመከታተል ባለፈ ከተራኪው አፍ በመንጠቅ አይከውኑም፡፡ ተራኪዎች በአንዳንድ አጋጣሚዎች የአተራረክ ሂደቱ በሚሳሳትባቸው ወይም በሚዘነጋቸው ጊዜና ማንኛውም ታዳሚ በቀላሉ ተጠየቅ (logic) ላይ ተመስርቶ ሊያርማቸው በሚችልበት አጋጣሚ እንኳን ታዳምያን፣ ከዋኞች እራሳቸውን አርመው ወደትረካው መስመር እስኪገቡ በዝምታ ወይም በትዕግስት ይጠብቃሉ እንጂ ጣልቃ አይገቡም፡፡ ታዳሚዎች በትረካ ወቅት ሀሳብ በመሰንዘር የተሣተፉባቸው ጥቂት አጋጣሚዎች ሲኖሩ፣ በነዚህ አጋጣሚዎች ታዳሚዎች ጣልቃ የገቡት ከዋኞች፣ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ካቀረቡላቸው ተደጋጋሚ ወይም ጠበቅ ያለ ግብዣ በኋላ ነው፡፡

በዚህ ረገድ የሚታየው የታዳምያን ሚና ፍዝነት አንድም ከአውዱ እጅግ መደበኛ መሆንና ከክርስቲያናዊ ስነምግባር የመነጨ ነው ወደሚል ሀሳብ ይመራል፡፡ በሌላ በኩልም ተረኮቹ ተጠቃለው በሚነገሩባቸው የስብከት ስርዓቶች መነሻ ላይ ተራኪው ወደ አውደ ምህረት ከመቅረቡ አስቀድሞ መድረኩን የሚመሩ ግለሰቦች (ካህናት ወይም ዲያቆናት) "የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል. . " የሚል አባባል አዘውትረው ይናገራሉ፡፡ በስብከት ስርአቱ ማብቂያ ላይም እንዲሁ "የሰበከን ያስተማረን ልዑል አምላክ ምስጋና ይግባው" የሚል አባባል ያሰማሉ፡፡ ይህ አባባል በአውደ ምህረት በሚቆመው ሰባኬ ወንጌል የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አድሮ ህዝቡን ያስተምራል ከሚለው በቃለ መጠይቅ ከተገኘው ሀሳብ ጋር የሚገናዘብ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሰባኪው ላይ ያድራል የሚለው ሀሳብ ታዲያ በተለያየ መጠንና ደረጃም ቢሆን በምዕመናን ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ ይኖረዋል፡፡ ታዳምያኑ በትረካ ሂደት ላይ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ የሚያሣዩት ጭምትነት (ቁጥብነት) ምናልባትም ለሰባክያነ ወንጌሉ ካላቸው አክብሮት ባሻገር በሰባክያነ ወንጌሉ አድሮ ለሚናገረው አምላክ ያላቸውን ትህትናና ፍርሀት የሚገልፁበት አንድ መንገድ ሊሆን ይችላል ወደሚል መላምት የሚመራ ነው፡፡

---

* የተረክ ፈጣሪው (የባህል ባለቤቱ) ቡድን መሰረት ያደረገው ጎሳን (ethnic) በሆነባቸው ተረኮች ክዋኔ ሂደት የታዳምያኑ ሚና የተሳሳተን ከማረም፣ የጎደለን ከመሙላት፣ የተረሳን ከማስታወስ የተራኪን ሚና እስከመንጠቅ የሚደርስ ነው ስል በOkepwho,1992, 57-63 የቀረቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

የተረኮች ዋነኛ ታዳምያን ተረኮቹን ከተራኪዎች ጋር ተቀባብሎ ከመተረክ አኳያ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ሚናቸው ፍዝ ይሁን እንጂ በተረኮቹ የሚነሱ ጉዳዮች የፈጠሩባቸውን ስሜት ከመግለፅ አንፃር የሚኖራቸው ሚና ጉልህ ነው፡፡ እልልታና ጭብጨባ ታዳምያን በትረካ አውዶች ስሜታቸውን ከሚገልፁባቸው መንገዶች ቀዳሚዎቹ ናቸው፡፡ የቃላዊ ዝርው ተረክ ተራኪው በአምላክ፣ በመላዕክት፣ በቅዱሳን ወይም በፃድቃን ስለተፈፀሙ በተረክ 18፣ 50፣ 55፣ 61፣ 63፣ 64 እንደቀረቡ ያሉ ተአምራትና ዜና ፊውሶችን ሲተርክ ታዳሚው፣ አንዳንዴ ተራኪው "ይህን ላደረገ አምላክ/ቅዱስ . . . ወሮታው (ክፍያው) ምንድነው?!" በሚል ስያሜ ቆም ሲል በሌላ አጋጣሚ ደግሞ ታዳሚው የተራኪውን ቆምታ ሳይጠብቅ ስሜቱን በሚያሰማው ጭብጨባና እልልታ ይገልፃል፡፡ ታዳምያን ከፍ ባለ ስሜት ሲያጨበጭቡና እልልታ ሲያሰሙ በከዋኙ ዘንድ የስሜት ተነሳሽነት ይፈጥራሉ፡፡ በዚህም ከዋኙ በተረኩ ለሚያነሳቸው ድንቃድንቅ ተግባራት ይበልጥ አፅንኦት እየሰጠ አጠንክሮና አጋኖ ሲገልፃቸው ይታያል፡፡ ይህ የተራኪው ተግባር ደግሞ የታዳሚውን ስሜት ይበልጥ እየነካ ይበልጥ ስሜቱን አጠንክሮ እንዲገልፅ ሲያነሳሳው ይታያል፡፡ በዚህ ሂደትም አንዳቸው ሌላቸውን (ተራኪው አድማጩን፤ አድማጩ ተራኪውን) እያነሳሱ የትረካውን ክዋኔ፣ የኪናዊነት ደረጃ የላቀ ያደርጉታል፡፡

ከእልልታና ጭብጨባ ጎን ለጎን ታዳምያን በክዋኔ ሂደት የተሠማቸውን ስሜት የሚገልጹባቸው ሌሎች መንገዶች ለዘብተኛ ፈገግታና ከንፈር መጠጣ ናቸው፡፡ በስብከት ስርዓት ወቅት ከሚነገሩ፣ ሳቅን ወይም ፈገግታን ሊያጭሩ ይችላሉ ተብሎ ከሚገመቱ ተረኮች መካከል ለይበልጡ የታዳምያኑ ምላሽ ደስታን ወይም መደነቅን ከሚገልፅ ሳቅ ይልቅ በከንፈር መጠጣ የታጀበ ለዘብተኛ የግርምት ወይም የትዝብት ፈገግታ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በተራ ቁጥር 4፣11፣19፣21፣36 እና 38 ስር የቀረቡ ተረኮች ምናልባት በሌላ አውድ ውስጥ ቢነገሩ ሳቅን ወይም ፈገግታን የሚያጭሩ ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ ተረኮቹ በተጠኑበት ተፈጥሯዊ አውድ ውስጥ ሲነገሩ ግን የታዳምያኑ አፀፋ (reaction) ከሳቅ ይልቅ ከንፈር መጠጣ ነበር፡፡ የታዳምያኑ ምግባር በዚህ መልኩ የተቃኘ እንዲሆን ተረኮቹ የሚነገሩባቸው አውዶች መደበኛ መሆን የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ከአውዱ መደበኛነት ጋር በተያያዘ ተራኪዎች ተረኮቹን የሚከውኑባቸው መንገዶች በአመዛኙ ሳቅ ከማጫር (ተዝናኖትን ከመጋበዝ) ይልቅ ታዳምያን የተረኮቹን መልዕክት በማጤን የራሳቸውን ምግባር እንዲፈትሹባቸው በሚጋብዝ መልኩ መሆኑና ታዳምያኑም በዛው መንገድ የሚረዷቸውና እራሳቸውን የሚፈትሹባቸው በመሆናቸው ነው፡፡

ሳቅን ሊያጭሩ ከሚችሉ ተረኮች ለአመዛኙ የታዳምያኑ አፀፋ ከሳቅ ይልቅ ከንፈር መጠጣ ወይም በከንፈር መጠጣ የታጀበ ለዘብተኛ ሳቅ ነው ቢባልም ታዳምያኑ በስብከት ስርአቶች

ወቅት በተነገሩ በየትኞቹም ተረኮች በነፃነት ሲስቁ አልታዩም ማለት አይደለም። ለምሳሌ እንደተረክ 41፣42፣44፣45፣46 ያሉ ተረኮች በተነገሩበት አውድ የታዳሚዎች አፀፋ ነፃ ሳቅ ነበር። እንዲህ ላለው ሳቅ፣ አንድም ከዋኙ ተረኮቹን ያቀረበበት መንገድ ተዝናኖትን የሚጋብዝ የነበረ መሆኑ፣ በሌላ በኩልም ተረኮቹ በባህሪያቸው ጥብቅ አስተምህሮ አዘል አለመሆናቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል።


በአጠቃላይ በንኡስ ርእሱ እንደተመለከተው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት በሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ዋነኛ ታዳምያን አዋቂ ወንዶችና ሴቶች ሲሆኑ፣ በትረካው ሂደት ታዳምያኑ ፍዝ ተመልካች ሳይሆኑ ንቁ ተሳታፊዎች ናቸው።



ሴት ምዕመናን በማሕደረ ስብሃት ቅድስት ልደታ ለማርያምና ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በአመሻሽ ጉባዔ ላይ /ምስል 5/



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY



ወንድ ምዕመናን በማሕደረ ስብሃት ቅድስት ልደታ ለማርያምና ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በአመሻሽ ጉባዔ ላይ /ምስል 6/

## 4.4. የአከዋወን ዘዴ (ስልት)

ቀደም ባሉት ንኡሳን ርእሶች ስለቃላዊ ዝርው ተረኮች ከዋኞችና ታዳሚዎች ማንነትና ሚና፣ እንዲሁም ተረኮቹ ስለሚከወኑበት አውድ ቅኝት ተደርጓል። በዚህ ንኡስ ርእስ ደግሞ በክዋኔ ሂደት የታዩ አበይት ስልቶች ይቃኛሉ።

### 4.4.1. ከትረካ መስመር መውጣት /digression/

"ከትረካ መስመር መውጣት" የሚለውን ሀረግ ለያዝኩት ንኡስ ርእስ መጠሪያ አድርጌ ስጠቀምበት "digression" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል Okpewho, African Oral Literature በሚለው መፅሐፋቸው ስለአፍሪካ ስነቃሎች አከዋወን ስልት ገለፃ ሲያደርጉ ከተጠቀሙበት ፍቺ እንዲሁም Ilhan Basgoz "Digression in Oral Narration; A Case Study of Individual Remarks by Turkish Romance Tellers" በተሠኘው መጣጥፋቸው ከተገለገሉበት ስሜት ጋር አቻ ሆኖ እንዲያገለግለኝ በማሰብ ነው። Okpewho ቃሉን፡-

*This is a device whereby the oral performer departs for a moment from the main line of the subject of a story or song either to address an object (or person) at the scene of performance or to comment on an issue which may be closely or remotely connected with the main subject.* (1992፣ 98)

በማለት ሲያብራሩ፣ ማብራሪያውም፡-

ቃላዊ ከዋኙ በክዋኔ ሂደቱ ላይ እያለ ስለአንድ ግለሰብ ወይም ከዋናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር የቅርብ ወይም የሩቅ ተዛምዶ ስላለው ሀሳብ አስተያየት ለመስጠት ለአፍታ ከዋናው የታሪኩ ወይም የዘፈኑ ርእሰ ጉዳይ የሚወጣበት ዘዴ ነው፡፡

የሚል ተቀራራቢ የአማርኛ ፍቺ ይኖረዋል፡፡

በተመሳሳይ Ilhan Basgoz ከላይ በተጠቀሰው መጣጥፋቸው በቃላዊ ዝርው ትረካ ወቅት ከትረካ መስመር የመውጣት ስልትን አስመልክተው ሰፋ ያለ ማብራሪ አስፍረዋል፡፡ Basgoz እንደሚሉት አንድ ከዋኝ በመድረክ ሲቆም እንደ አንድ ተዋናይ እራሱን ትቶ ወይም ደብቆ የወከለውን ገፀባህርይ፣ ባህርይ ተላብሶ አይደለም፡፡ በተረኩ ክዋኔ ወቅት ተራኪው በሚናገረው ታሪክ ውስጥ ምንም ያህል ራሱን ቢያስገዛም በመድረክ እንደቆመ ተዋናይ "ሙሉ ለሙሉ" ራሱን ትቶ አይደለም፡፡ ከዋኙ ለምሳሌ አንድን ተረክ ሲተርክ እንደግለሰብ፤ ያለው የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ያለው ፖለቲካዊ አቋምና ሀይማኖታዊ ዝንባሌ ወዘተ. የሚያላብሰውን ሰብእና በውስጡ እንደያዘ ነው፡፡ በተረኩ ክዋኔ ሂደት ላይ ታዲያ ተዳፍኖ የቆየው የከዋኙ ሰብእና ወይም እምነትና አመለካከቱ በድንገት በሚፈጠር ውስጣዊ ወይም ውጪያዊ ተፅእኖ ገንፍሎ የሚወጣበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ጊዜ ከዋኙ የተረኩን ዋና ጭብጥ በመተው ግላዊ አስተያየቱን ወይም እምነትና አመለካከቱን ይሰነዝራል፡፡ ይህም ነው እንግዲህ እንደ Basgoz ገለፃ ከትረካ መስመር መውጣት ሊባል የሚችለው፡፡

ከትረካ መስመር ስለመውጣት ስልት ምንነት በዚህ አይነት ገለፃ የሠጡት Basgoz፣ ስልቱ በአጠቃላይ በሶስት ምድብ ተከፍሎ ሊታይ እንደሚችል ጠቅሰው በሚከተለው መልኩ በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡

1. ገላጭና ትምህርታዊ /explanatory and instructional/በዚህ ምድብ የሚካተቱት፤ ተራኪዎች አድማጩ አይረዳቸውም ያሏቸውን ያረጁ ቃላትና አገላለፆች የሚያብራሩባቸው፣ ስለታሪክ፣ ስለስነ-መልክአምድር፣ ስለሃይማኖት፣ ስለሀገረሰባዊ

መድሀኒት ወይም ስለተለያዩ ወግና ልማዶችና ስለክብረ በአላት ተገቢነትና ኢተገቢነት የሚገልፁባቸው ናቸው።

2. ግላዊ አስተያየትና ትችት /opinion-related and commentative/ በዚህ ምድብ የሚካተቱት የተራኪው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ አቋም የሚንፀባረቅባቸው፣ ፍልስፍናው የሚገለፅባቸው፣ አስተያየቶች ናቸው።
3. ግለሂሳዊና "ኑዛዜያዊ" /self – reproaching and confessional/ በዚህ ምድብ የሚካተቱት ተራኪው ግላዊ ጉድለቱንና ችግሮቹን በአድማጩ ፊት በግልጽ የሚናገርባቸው ናቸው።

ከትረካ መስመር መውጣት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት በሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ክዋኔ ሂደት የሚሠራበት ዋነኛ ስልት ነው። በተረኮቹ ክዋኔ ሂደት ተራቾች ተረኮቻቸውን መተረክ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ በተረኩ የተነሳው ታሪክ መቋጫ ላይ እስኪደርስ ድረስ ከዋናው የታሪክ ፍሰት ሳይወጡ በአብዛኛው እስከመጨረሻው ድረስ አይዘልቁም። ተራኪዎች አብዛኛውን ጊዜ ከዋናው የትረካ መስመር እየወጡ ግላዊ አስተያየቶችን፣ ማብራሪያዎችንና ገለፃዎችን፣ ማጠናከሪያ ሀሳቦችን ወዘተ. ይሰነዝራሉ።

ከዋኞች ከትረካ መስመር በመውጣት የሚሠነዝሯቸው አስተያየቶች፣ ማብራሪያዎችና ገለፃዎች በአንድና በሁለት አረፍተ ነገሮች ሊጠቃለል ከሚችል ንግግር በብዙ መስመሮች ሊሰፍር እስከሚችል ረጅም ሀተታ ድረስ ይዘልቃል። ከዚህ ቀጥሎ ከሁለት የተለያዩ ተረኮች ተቆንፅለው የቀረቡት ምሳሌዎች ተራኪዎች በአንድና በሁለት አረፍተነገሮች ከትረካ መስመር የወጡበትን ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው።

ተረክ 61

…እኚህ እናት ተጨንቀዋል፣ በጣም ተጨንቀዋል አንድ ቀን ቁጭ ብለው ሲማሩ ሰባኪው ልባቸውን ነካው "የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ካላችሁ ድንጋዩን ተነስተህ ወይም ቃሉ እንደሚለው ተራራውን ተነስተህ ገደል ግባ ብትሉት ይገባል የሚሳናችሁ የለም" የሚለውን ቃል ሲሰሙ ደስ ብሏቸው አገልጋዩ ሲጨርስ ሄዱ። "ዛሬ በጣም ልብ የሚፈትሽ ቃል ተናግረኸኛል" (አሉት)። "እናታችን እኔ አይደለሁም የተናገርኩት እኔም ስማር ነበር እርሶም ሲማሩ ነበር። እኔ ቆሜ እርሶ ቁጭ ብለው"[ሲያስተምር የነበረው ማን ነው?(ምእመኑን) እግዚአብሔር] "ግን ቃሉ ምንድነው?" አላቸው። የሰናፍጭ እርሻ አለኝ በዚህ እርሻዬ ውስጥ እርሼ እንዳልጠቀም ግዙፍ ድንጋይ ተንከባሎ ቁጭ ብሏል አሁን እምነት ያላችሁ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት ካላችሁ ድንጋዩን ተነስተህ ገደል ግባ ብትሉት፣ ተራራውን ተነስተህ ወደ ገደል ግባ ብትሉት ይነሳል

ብለሀል አምኛለሁ! አምኛለሁ! እኔ በእርሻዬ መካከል ግዙፍ ድንጋይ አለ" አሉ፡፡ "እናታችን እግዚአብሔር እኮ በእኔ አድሮ የተናገረው ይሄን አይደለም የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት ካላችሁ ተራራውን ተነስተህ ገደል ግባ ብትሉት ይገባል ስል የእምነትን ታላቅነት ለማሳየት ነው" (አላቸው)፡፡ "ልጄ አሉት ተወደደም ተጠላም አምኛለሁ እግዚአብሔር እቤት ስራዬን እየሰራልኝ ነው ይሄን ጊዜ" አሉት፡፡ "እኔ እዚህ ነኝ እኔ በእውነት እዚህ ነኝ አላውቅም የድንግል ልጅ፣ አማኑኤል ቤቴ ምን እየሰራ እንደሆነ አላውቅም ግን ስራ እየሰራ ነው" አሉ፡፡ [ወገኖቼ እመኑ ባመናችሁ ጊዜ ለውጥ አለ] እኚህ እናት ልክ ሲሄዱ የሳቸው ቤት ተከቧል፡፡ (አጽንኦቱ ከእኔ ነው)

## ተረክ 56

አንድ ሰውዬ ለልጁ መጫወቻ የአለም ካርታ ገዛለትና ተጫወት ብሎታል፡፡ ይሄ ልጅ ለምዶታል በቃ (መጫወቻውን)፡፡ ከትምህርት ቤት ሲመጣ ሁልጊዜ ያቺን ካርታ የዓለም ናት፡፡ የአለም ካርታው ጀርባ ላይ የሰው መልክ አለ ሁሌ ግጥምጥ ያደርጋታል፡፡ አንድ ቀን አባት ከስራ በጊዜ መጣና ስራ ሲፈታ [ስራ የፈታ አእምሮ የሰይጣን ቢሮ ነው እንደበር እጁታ ያም ያም ይከፍተዋል]፡፡ አሁን እስቲ የልጄን መጫወቻ ልሞክር አለና አለምን ለማስተካከል አውስትራሊያን ሲያመጣ አፍሪካ ትወጣለች፤ አንዱን ወዲህ ሲያመጣ አንዱ ወዲያ ይወጣል፡፡ (አጽንኦቱ ከእኔ ነው)

በምሳሌነት በቀረቡት ሁለት ተረኮች አፅንኦት ያረፈባቸው ዐ.ነገሮች ተራኪዎች ከዋናው የትረካ መስመር የወጡበትን ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ከምሳሌዎቹ እንደሚታየው ተራኪዎች ከትረካ መስመር ወጥተው የሰነዘሯቸው ሀሳቦች ከመጠን አንፃር አናሳም ቢሆኑ በትረካው ሂደት ውስጥ ጉልህ ስልታዊ ፋይዳ ያላቸው ናቸው፡፡ በቀዳሚው ምሳሌ ተራኪው ከዋናው የትረካ መስመር ወጥቶ የሰነዘረው አንድ ዐ.ነገር አንድም በረጅሙ በቀረበው የትረካ ሂደት ታዳሚው ለተረኩ መነገር ዋነኛ ምክንያት የሆነውን አቢይ ጭብጥ እንዳይዘነጋ መለስ አድርጎ ለማስታወስ አግዞታል፡፡ በሌላ በኩልም ይኸው ዐ.ነገር "በእግዚአብሔር የጠበቀ እምነት ይኑራችሁ" ለሚለው የስብከቱ እንዲሁም የተረኩ ዋና ሀሳብ አፅንኦት ለመስጠት አስችሏል፡፡ በተመሳሳይ በቀጣይ የተጠቀሰው ምሳሌ ሰባኪው በዋናነት ይዞት ከተነሳው ዋና ሀሳብ ጎን ለጎን "ስራ ፈትነትን" አስመልክቶ ያለውን አቋም እንዲጠቁምና እግረ መንገዱን ለታዳሚው አንድ ትምህረት አስጨብጦ እንዲያልፍ አስችሎታል፡፡

ከዋኞች ከላይ እንደተጠቀሰው ከዋናው የትረካ መስመር ወጥተው በአንድ እና በሁለት አረፍተ ነገሮች ብቻ ሀሳባቸውን ገልፀው የማይመለሱባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው፡፡ በተረኮቹ

ክዋኔ፣ ከዋኞች አዘውትረው ከዋናው የትረካ መስመር በመውጣት ሰፊ ሐተታን ያሰማሉ። በዚህ ሰፊ ሀተታ ከዋኞቹ የሚያነሱዋቸው ጉዳዮች አንዳንዴ በየተረኮቹ ከሚነሱ ርእስ ጉዳዮች ጋር ተዛምዶ ያላቸው፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከርእስ ጉዳዮቹ ርቀው እየወጡ የሚሄዱ ይሆናሉ። ከዋኞች በየትኛውም መንገድ (በተዛምዶም ያለተዛምዶም) ከትረካ መስመር ሲወጡ፣ ከትረካው መስመር ወጥተው የሚያቀርቡት ሀተታ ለአጠቃላዩ የክዋኔ ሂደት አንድ ፋይዳ ያለው፤ በስብከቱ ወይም በተረኩ ለተነሳው አስተምህሮ እንደ ግብአት (input) የሚያገለግል ወይም የትረካውን ክዋኔ ኪናዊነት በማላቅ የታዳምያንን ስሜት የመያዝ ዋጋ (value) ያለው ይሆናል። ሁኔታውን ከስብስብ ተረኮች አብነት በመውሰድ እንመልከት

ምሳሌ አንድ

ተረክ 18

ምስካየህዙናን ቤተክርስቲያን ተሳልሜ ስወጣ በእድሜ ገፋ ያሉ ሽበት የቀላቀለባቸው አንድ ታላቅ አባት እንባ ይተናነቃቸው ነበር በሩ ላይ። አሳዘኑኝና "ምነው አባቴ አልኳቸው?" ጠጋ ብዬ "ልጄ ከውጪ ሀገር ተሰዳ ትኖር ነበር" አሉኝ ነገር ግን ይህቺ ልጅ እግዚአብሔርን ይዛ ነበር የተሰደደችው [ወገኖቻችሁ ብቻቸውን እንዲሰደዱ አትምከሯቸው እግዚአብሔርን ይዘው እንዲሰደዱ አስተምሯቸው። እግዚአብሔርን ይዞ ያልተሰደደ ክርስቲያን ቢሰደድም አያምርበትም ኑሮው አይስተካከልም፤ መንገዱ ሁሉ በእሾህ የታጠረ ይሆናል።] ይህቺ ሴት እግዚአብሔርን ይዛ ነው ለካ የተሰደደችው።. . . (አጽንኦቱ ከእኔ ነው)

ተረክ 21

ሴትየዋ ልጇን እንዲህ ትለው ነበር "ማሙሽ ወደምግብ ከመቅረብህ በፊት መጀመሪያ እግዚአብሔርን አመስግን" ትለዋለች "ከጨረስክም በኋላ እግዚአብሔርን አመስግን" [እንዲህ አይነት ቤተሰቦች አሉ። ለልጆቻቸው መልካም ትምህርት የሚያስተምሩ ለልጆቻቸው ሃይማኖትን የሚያስተምሩ ለልጆቻቸው በጎ ነገርን የሚያስተምሩ ወላጆች አሉ።] ይህቺ ሴት እንዲህ ነበር ትለው የነበረው "ወደ ማዕድ ስትቀርብ እግዚአብሔርን አመስግን" ትለዋለች "ከበላህም በኋላ እግዚአብሔርን አመስግን።". . . (አጽንኦቱ ከእኔ ነው)

ከላይ በምሳሌ አንድ ስር በቀረቡት ሁለት ተረኮች ውስጥ አፅንኦት ያረፈባቸው ሀተታዎች ከዋኞች ከትረካ መስመር የወጡበትን ሁኔታ የሚያሳዩ ሲሆኑ ሀተታዎቹ በየትረካዎቹ ከተነሱ ሀሳቦች ጋር ተዛምዶ ያላቸው ናቸው። ከሀተታዎቹ ቀዳሚው፤ በተረክ 18 ስር የተጠቀሰው፤ ከሀገራችሁ በተሰደዳችሁ ጊዜ ሀይማኖታችሁን ልትጠብቁ ይገባል የሚለውን ሀሳብ፤ ተከታዩ፤ በተረክ 21 ስር የተጠቀሰው ሀተታ፤ ወላጆች ልጆቻቸውን በክርስቲያናዊ ስነምግባር ሊያንፁ ይገባል የሚለውን በተረኩ የተነሳን ዋና ሀሳብ የማጉላት ፋይዳ ኖሯቸው ወይም ለአጠቃላዩ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የትረካ ሂደት በግብአትነት የሚያገለግሉ ሆነው የገቡ ናቸው። ከነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ጎን ለጎን በተረክ ተራ ቁጥር 5፣36 እና 53 ስር በቀረቡ ተረኮች ተራኪዎች ከትረካ መስመር መውጣታቸው ይታያል። በነዚህ ተረኮች ተራኪዎች ስልቱን በየስብከቶቹ (በየተረኮቹ) ለተነሱት ዋነኛ ጭብጦች አፅንኦት መስጫነት ተገልግለውበታል።

### ምሳሌ ሁለት

### ተረክ 3

ሰውየው ነው አሉ [ልንገራችሁ በዚሁ አጋጣሚ ደከማችሁ እንዴ?] ሰውየው ነው አሉ መንገድ ሲሄድ ሲሄድ መሸበት ገጠር አካባቢ መሽቶበት አሳድሩኝ አለ። ባልና ሚስቶች ደግሞ የሳር ቤት ናት ቤታቸው። በዛች ቤት ውስጥ መሀል ላይ የእንጨት ምሰሶ አለበት ቤቷን ቀጥ አድርጎ የያዘ፤ ከዛች ስር ደግሞ እሳት ያነዳሉ ከዛችው ቤታቸው "ቤት የእግዚአብሔር ነው ግባ" አሉና እንግዳውን አስገቡት፤ እራቱን አበሉት በሉ፤ እግሩን አጠቡት አስተናገዱት እና "በል እንግዲህ. . ." [መቼም የገጠር ባህል ምንድነው የምታደርጉት ሲበርዳችሁ? ከተማ ያላችሁ እብድ የሚያክል የደብረብርሃን ብርድልብስ መከናነብ አይደል? በገጠር ውስጥ ግን ብርድልብስ የለም ምን ያደርጋሉ ወደል ወደል የሚያክል ፍልጥ አስ ፈልጠው ያስቀምጣሉ፣ ያነዳሉ] የሚገርማችሁ ከምሰሶዋ ስር እሳት አለ ይነዳል፤ አነደዱና እንግዳውም በዚህ ቁጭ አለ፣ ሚስትም በዚህ ቁጭ አለች፣ ባልም በዛ ቁጭ አለ። . . (አጽንኦቱ ከእኔ ነው)

### ተረክ 22

አበምኔቱ በመንፈስ እግዚአብሔር የተቃኙ ስለነበሩ "ሥራ ስሩ የመመገቢያ ሰአት ሲደርስ ግን ደውል እንዲመታ አንፈልግም (አሉ)። [ልክ አስራ አንድ ሰዓት ሲደርስ በሚመገቡበት ሰዓት ሁሉም ምግቡን እየተቀበለ ወደበአቱ ይገባል በአንድ ላይ አይበሉም ለምንድነው ይሄ በየበኩላቸው የተሰጣቸውን መቁንን ለሌሎች እየሰጡ እነሱ ሶስት አራት ቀን ፆም እያደሩ የሚኖሩ መናንያን ስላሉ ነው። መመገብ አለመመገብ የራሳቸው ጉዳይ ነው።] "ደውል በሚደወልበት ሰአት ግን ሳትደውሉ ወደምግብ አዳራሽ ኑና መቁንናችሁን እየያዛችሁ ሂዱ" አሉ። . . (አጽንኦቱ ከእኔ ነው)

ከላይ በቀረቡት ሁለት ምሳሌዎች ተራኪዎች ከትረካ መስመር በመውጣት በጥቅሉ ሲታይ አንድ ሊባል የሚችል ተግባር ፈፅመዋል። ተራኪዎቹ ስልቱን መሰረት አድርገው አድማጭ ላያውቃቸው ይችላል ያሉትን አንድም የገጠር አኗኗርን፣ አንድም በገዳም ውስጥ ያለ የአመጋገብ ስርአትን አስመልክቶ መረጃን ለታዳሚው አድርሰዋል።

ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ምሳሌ ተራኪው ስልቱን መሰረት አድርጎ ያነሳው ሀሳብ በቀዳሚዎቹ ምሳሌዎች እንዳየነው ከስብከቱ ዋና ሀሳብ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ የለውም። ይሁን እና ተራኪው ስልቱን በመጠቀሙ ለትረካው ክዋኔ ሂደት ያስገኘው የራሱ የሆነ ፋይዳ አለው። ሁኔታውን ምሳሌውን በማስቀደም እንመልከት።

ምሳሌ ሦስት

ተረክ 55

. . . ልክ ሲገቡ አመናችሁኝም አላመናችሁኝም ሰውየው መሰርሰሪያውን እንደያዘ፣ የተሟላ መሳሪያውን እንደያዘ ደርቋል። ልክ እንደሚያስቀድስ ሰው ቆሟል። መጥተው አጠገቡ ቆሙ አያይም ፊት ለፊት ነው የሚያየው ወዲያና ወዲህ የለም። በጣም አስታውሳለሁ አሁን በጣም ገርሟቸው፤ አንደኛ በሩ ተሰብሯል፣ እንደገና ሰውየው ቆሟል [አሁን ጊዜ ቢሆን እንኳን በጣም ማለት ጊዜው ሩቅ ጊዜ ነው ግን አሁን አሁን አይታችኋል አንዳንድ ሱፐርማርኬቶች ጋር የሚቆም አሻንጉሊት አለ። ሰው መስሏችሁ የጠየቃችሁት ጊዜ የለም? ብዙ የቆሙ አሉ። እኔ አንዳንድ ጊዜ ሰው ይመስለኛል፤ ሳታስቡት። ያናገረው ሰው አለ ይባላል። እቃ መረጠ መረጠና “አይገርምም ውድ ነው አየህ” ምናምን ሲለው ዝም አሻንጉሊት ነው?! “ውድ እኮ ነው” ብሎ ዞር ሲል እራሱ ውድ ነው የሚሸጥ ነው።] አሁን ስተት ብለው ገቡ አዩ። ወዲያው ሌባ እንደሆነ አወቁ። . . . (አጽንኦቱ ከእኔ ነው)

በተረክ 55 ውስጥ አጽንኦት ያረፈበት ሀተታ ተረኩ በተነገረበት አውድ ተራኪው ይዞት ከተነሳው ዋነኛ ጭብጥ፤ በእግዚአብሔር የጠበቀ እምነት ይኑራችሁ፤ ጋር ተዛምዶ የለውም። ይህ ማለት ግን ሀተታው ለትረካው ሂደት መጎልበት ምንም ሚና የለውም ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም። ተራኪው ከዋናው የትረካ መስመር በመውጣት የዘመኑን አሻንጉሊቶች ሁኔታ በማተትና ለረጅም ደቂቃ መደበኛ በሆነው የስብከት ስርአት መንፈስ ተይዞ ለነበረው ታዳሚ የቅርብ ገጠመኝ የሆነውን የዘመኑን አሻንጉሊት ጉዳይ በማጋራት ታዳሚው በተሻለ መነሳሳት በተረኩ ክዋኔ እንዲሳተፍ አስችሎታል። (በስብከት ስርዓቱ ላይ ከተረኮቹ መተረክ አላማዎች አንዱም ይኸው ታዳምያኑ እንዲነቃቁ ማስቻል መሆኑን ልብ ይሏል)። በእስከ አሁኑ ቆይታ በቃላዊ ዝርው ተረኮች ክዋኔ ላይ ከትረካ መስመር የመውጣት ስልት ምን መልክ እንዳለው ተመልክተናል። በመቀጠል በተረኮቹ ክዋኔ ከትረካ መስመር መውጣት እንደስልት እንዲፈጠር ምክንያት የሆነው ምንድነው የሚለውን እናያለን።

በቃላዊ ዝርው ተረኮች የክዋኔ ሂደት ከትረካ መስመር መውጣት እንደስልት ጉልህ ሆኖ እንዲወጣ ተረኮች ስለተረክነታቸው /for their own sake/ የሚነገሩ አለመሆናቸው ጉልህ

አስተዋፅኦ አለው፡፡ ተረኮች ከሚነገሩባቸው አላማዎች አንዱና ዋነኛው ሰባኪ.ው ይዞት የተነሳውን ሀሳብ በተዛምዶ ግልጽ፣ ተጨባጭና አይረሴ ማድረግ መሆኑን (4/9/2002፣ቸሬ፣ቃለ መጠይቅ ካሴት ተራ ቁ. 3፣ ገፅ ሀ፤ 29/8/2002፣ ሀብታሙ፣ ቃለ መጠይቅ ካሴት ተራ ቁ. 2፣ ገፅ ሀ፤ 28/8/2002፣ አእምሮ፣ ቃለ መጠይቅ ካሴት ተራ ቁ. 1፣ ገፅ ለ) ይገልፃሉ፡፡ በዚህ መሰረት አንድን ተረክ ይዞት የተነሳውን ሀሳብ ይበልጥ ግልፅ፣ ይበልጥ ተጨባጭና አይረሴ ለማድረግ እያዛመደ የሚተርከው ከዋኝ በተረኩ ክዋኔ ሂደት ተረኩን ይዞ ከተነሳው ርእሰ ጉዳይ (እንዲገልፀው ከሚፈልገው ሀሳብ) ጋር የሚያዛምዱ ሌሎች አጋዥ ሀሳቦች ሲመጡለት ከትረካ መስመር በመውጣት ይዞት የተነሳውን ነጥብ በተዛምዶ ለማጉላት እንዲጥር በሚጋብዝ አንዳንዴም በሚያስገድድ ሁኔታ ውስጥ ይገባል፡፡ ይህ መሆኑም በስብከት ስርአት ወቅት በሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከትረካ መስመር መውጣት ተደጋግሞ እንዲታይና እንደስልትም እንዲፈጠር አንዱና ዋነኛው ምክንያት ይሆናል፡፡



መምህር መጋቤ ሐዲስ ቀለመወርቅ ታደሰ ቦሌ ደብረሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል በስብከተ ወንጌል አገልግሎት /ምስል 7/

### 4.4.2. ከፍተኛና ዝቅተኛ የድምጽ መጠንና ፍጥነት

በስብከት ስርአት ላይ የሚነገሩ ተረኮች ተራኪና ታዳሚ በአካል በተገኙበት በቃል እየተነገሩ የሚከወኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም የተራኪው የድምጽ አወጣጥ ሁኔታ ከታዳሚው ጋር በሚኖረው መስተጋብርም ሆነ የክዋኔ ሂደቱን ኪናዊ ደረጃ ከማላቅ አኳያ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ የስብከት ስርዓት ወቅት ተረኮች፣ ፈጣሪው ማህበረሰብ አንድ ጎሣ ወይም ዘር እንደሆነባቸው ተረኮች፣ በክዋኔ ሂደት ድራማዊ አቀራረብ ጉልህ ሆኖ የማይስተዋልባቸው፤ ተራኪዎቻቸው የገፀባህርያትን (የእንስሳትን፣ የሴቶችን፣ የህፃናትን ወዘተ.) ድምጽ አስመስለው ሲቀፅሉ የማይታዩባቸው ናቸው፡፡*

ይሁን እና በየትረካዎቻቸው የገፀባህርያትን አነጋገር የማይቀፅሉት ተራቾች በትረካ ሂደት የድምጻቸውን መጠን በእጅጉ ይቀያይራሉ፡፡ ተራኪዎቹ በቃላት ለሚናገሯቸው ጉዳዮች እየናረ ወደላይ በሚወጣ ከፍተኛና የሹክሹክታ ያህል ወደታች በሚወርድ ዝቅተኛ ድምፅ የተለያየ የትርጉም ወይም የፍቺ ደረጃን ይሰጣሉ፤ በተለያዩ ሁኔታዎች (በደስታ፣ በሀዘን፣ በስቃይ፣ በፍርሀት ወዘተ.) ውስጥ የገቡ ገፀባህርያትን ስሜት አጉልተው ያሳያሉ፡፡

ከፍተኛና ዝቅተኛ የድምፅ መጠን እንደስልት በተረኮቹ በአብዛኛው ብቻውን የሚቆም አይደለም፡፡ በትረካ ሂደት የገፀባህርያትን ስሜት (ፍርሀት፣ ደስታ፣ ሀዘን...)፤ ለመግለጽ ከዚህ ስልት ጎን ለጎን ከዋኙ የአነጋገር ፍጥነት መቀያየርን እንደስልት በተዛምዶ ይጠቀማል፡፡ አንድን ስሜት አጋኖ ወይም አጉልቶ ለማሳየት የድምፁን መጠን ወደላይ በማውጣት ጣራ ላይ በሚያደርስበት ሂደት ተራኪው ቃላትን ወይም ሐረጋትን የሚናገርበትን ፍጥነትም በአብዛኛው በዛው መጠን ይጨምራል፡፡ በከፍተኛ ድምጽ እና በከፍተኛ የአነጋገር ፍጥነት ሊገልፀው የፈለገውን ስሜት ገልፆ ሲያበቃና የድምፁን መጠን ወደታች ሲመልስ ተራኪው ቃላቱን የሚናገርበት ፍጥነት ዝግ ያለ ይሆናል፡፡ ሁኔታውን ከተረክ 53 በተቀነፀለ ምንባብ፣ ተረኩ በአውድ ሲነገር የነበረውን ተፈጥሯዊ የክዋኔ ሂደት መሠረት በማድረግ እንመልከት፡፡

ተረክ 53

ጉባኤውን ሊካፈል ይመጣል፤ አጫሽ ጠጪ በአለም ያሉትን የሀጢያት አይነቶች . . . ወገኖቼ በሀጢያት ጎዳና ሲጓዝ የነበረ አንድ ቀን መጣ፡፡ ቃለ እግዚአብሔር ሠማና ቀረ እዚሁ ጉባኤ ይከታተል ጀመር፡፡ አሁን ቃለ እግዚአብሔር ይከታተል ጀመረ፣ መንፈሳዊ ሆነ፡፡ በኋላ ምን መጣ ከባድ ህመም ጀመረው የጀርባ ህመም፡፡ ሄዶ ሲመረመር ኢትዮጵያ ውስጥ መዳን አትችልም፣ ውጪ ካልሆነ አትችልም አሉት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ መድሀኒቱ የለም አሉት፡፡

---

* የቃላዊ ዝርው ተረኮች ፈጣሪ ማህበረሰብ (folk group) አንድ ጎሣ ወይም ዘር (ethnic) የሆነባቸው ተረኮች ክዋኔያቸው ድራማዊ ነው ስል በ Finnegan, Limba Stories and Story-Telling ላይ የቀረቡ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

"መጥቼ ቁጭ ብዬ ጉባኤ ስከታተል አያመኝም" አለ "ስፀልይ አያመኝም፣ ሳስቀድስ አያመኝም" አለ። "አሁን ከኢትዮጵያ ውጪ ሄጄ ነው የምመረመረው?! በምንድነው?! አምላኬ/በአለም አደባባይ ሳለሁ ጤነኛ ነበርኩ። አለም ላይ እያለሁ ህመም አያውቀኝም ነበር አሁን አንተን ብዬ ሙጥኝ ብዬ ስመጣ ልሸከመው የማልችለው በሽታ ውስጥ ትከተኛለህ?! በአለም እያለሁ እኮ እኔ ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይቅላ ብዬ የምኖር ሰው ነኝ ለምን?! አልኩኝ"/ አለ በቃ "ግን መንፈሳዊ ህይወቴ እየጨመረ መጣ"። (አግድሞሽ መስመሩ (the slash) የእኔ ነው።)

ከተጠቀሰው ፅሁፍ መነሻ፣ የመጀመሪያው አግድሞሽ መስመር እስካረፈበት ድረስ ያለውን ንግግር ተራኪው፤ በትረካው ተፈጥሯዊ አውድ፤ መደበኛ ሊባል በሚችል የድምጽ ከፍታ (የጩኸት መጠን) እና ፍጥነት ሲናገር ይቆይና የመጀመሪያው አግድሞሽ መስመር ካረፈበት ሁለተኛው አግድሞሽ መስመር እስካረፈበት ድረስ ያለውን ንግግር የቀድሞውን የአነጋገር (የአተራረክ) ስልት በመቀየር እጅግ እየናረ በሚወጣ ከፍተኛ ድምጽ እና ከፍተኛ ፍጥነት ይዘልቀዋል። ይህ በከፍተኛ ፍጥነትና በከፍተኛ የድምጽ መጠን (ጩኸት) የተነገረ የታሪክ ክፍል ከመጀመሪያው አግድሞሽ መስመር በፊት ካለውና በመደበኛ ፍጥነትና የድምጽ መጠን ከሚነገረው ክፍል በተለየ ገፀባህሪው የገባበትን አደጋ የሚገልፅ፣ የተሰማውን ሀዘንና ምሬት የሚያሳይ ነው። ተራኪው በሁለቱ አግድሞሽ መስመሮች ተከቦ ያለውን ንግግር በከፍተኛ ድምጽና ፍጥነት በመናገሩ ወይም ተጠቃሽ ስልትን በተመጠቀሙ የገፀባህሪውን የምሬት ስሜት ለታዳምያን ይበልጥ አጉልቶና አጠንክሮ ለማሳየት አስችሎታል።

ከዚህ ባሻገር ተራኪው ከሁለተኛው አግድሞሽ በኋላ ያለውን የተረኩን ክፍል ቀደም ያለውን ንግግር ሲያደርግ የተጠቀመበትን ከፍተኛ የድምጽ መጠንና ፍጥነት በመተው ከመደበኛ አነጋገር በወረደ ወይም ዝግ ባለ ለስላሳ ንግግር ዘልቆታል። የተራኪው ዝግተኛና ለስላሳ ድምጽ ገፀባህሪው ህመሙ በፈጠረበት የሀዘን ስሜት ሳይበገር ምን ያህል እራሱን ለመንፈሳዊ ህይወት እንዳስገዛ ወይም ምንም ያህል አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ቢገባም በፅናትና በመረጋጋት መዝለቅ መቻሉን ገልጾ ለማሳየት በአጭሩ የገፀባህሪውን ገጠመኝ ጉልህ በሆነ መንገድ ለታዳሚው ለማጋራት አስችሎታል።

### 4.4.3. ቆምታ /pause/

በቃላዊ ዝርው ተረኮች የክዋኔ ሂደት፣ ከዋኞች ንግግራቸውን ለአፍታ ገታ እያደረጉ በዝምታ በመቆየት እንደገና ወደ ትረካው የሚመለሱበት አጋጣሚ በርካታ ነው። ይህ የከዋኞች ተግባር በክዋኔ ሂደት ተግባራዊ ፋይዳ (practical purpose) ያለው ነው። ተራኪዎች ቆምታን

እንደስልት እንደየሁኔታው ለተለያየ አገልግሎት ያውሉታል፡፡ አፅንኦት በቆምታ ስልት የሚገለፅ አንድ ገፅታ ነው፡፡ መደበኛ ሊባል በሚችል መንገድ አንድን ተረክ ሲተርክ የቆየ ከዋኝ አፅንኦት ለመስጠት የፈለገው ነጥብ ጋ ሲደርስ እና/ወይም ነጥቡን ከተናገረ በኋላ ወደሚቀጥለው ንግግር ከመዝለቁ በፊት ለአፍታ ቆም በማለት ለተናገረው ነጥብ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን በማሳየት አጽንኦት ሰጥቶ ያልፋል፡፡ አፅንኦት ለመስጫነት ከማዋል ጎን ለጎን ተራኪዎች፣ ታዳሚን በተረኩ ሂደት ተሳታፊ ለማድረግ ቆምታን እንደስልት ይጠቀሙበታል፡፡ በአንድ ተረክ የክዋኔ ሂደት በተለይ የተነሳው ጉዳይ፣ በአምላክ፣ በመላዕክት በቅዱሳን ወይም በፃድቃን የተሰሩ ተአምራትን የሚያትት ሲሆን ከዋኙ "ስለተደረገው ተአምር ደስ ሊላችሁና ልታመሰግኑ ይገባል" የሚል አንድምታን ባዘለ መልኩ ቆም እያለ ታዳሚዎች በእልልታ፣ በጭብጨባ፣ በከንፈር መጠጣ ወዘተ. ስሜታቸውን እንዲገልፁ እየጠየቀም እየጋበዘም ታዳሚዎች በክዋኔ ሂደቱ የሚሣተፉበትን መንገድ ምቹ ያደርጋል፡፡

ቀደም ባለው ንኡስ ርዕስ እንዳየነው ሁሉ የቆምታ ስልትም በአብዛኛው በተናጠል የሚቆም አይደለም፡፡ በተለይ ተራኪዎች ሊገልፁት የፈለጉትን ሃሳብ ወይም ስሜት በብቃት ለመግለፅ የቆምታ ስልትን በአብዛኛው ከንግግር ፍጥነት እና ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በአንድ አስተባብረው ይጠቀሙበታል፡፡ ለምሳሌ አንድ ተራኪ አፅንኦት ለመስጠት ለፈለገው ጉዳይ ቆምታን እንደ ስልት ተጠቅሞ ሲገልፅ በተያያዥ አፅንኦት የሚሰጠውን ነጥብ (ከአፍታ ቆምታ በፊት ወይም በኋላ የሚያነሳውን ነጥብ) በከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ፍጥነት ይናገረዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዥነትም ተራኪው ከድምጽ ማጉሊያ ነፃ የሆነውን እጁን (በአብዛኛው የቀኝ እጅ ነው ነፃ የሚሆነው) ወደላይ ወደሰማይ በመዘርጋትና ለአፍታ በዛው ሁኔታ በማቆየት አጽንኦት ለመስጠቱ ሂደት ተጨማሪ ገላጭ ባህሪን ያክላል፡፡ በዚህ መልኩ ተራኪዎች ሶስቱን የቆምታን የፍጥነትን እና የአካላዊ እንቅስቃሴ ስልትን በአንድ አስተባብረው በመጠቀም ለማስተላለፍ የፈለጉትን ሀሳብ ወይም ስሜት በብቃት ከግብ ያደርሳሉ፡፡



መምህር ዜና ጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በማሕደረ ስብሃት ቅድስት ልደታ ለማርያምና ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በስብከተ ወንጌል አገልግሎት /ምስል 8/

### 4.4.4. ድግግሞሽ /repetition/

የቃላዊ ዝርው ተረኮች ከዋኞች ለተለያዩ አገልግሎቶች ለማዋል በክዋኔ ሂደት ላይ ድግግሞሽን እንደ አንድ ስልት ይጠቀማሉ፡፡ ተራኪዎች ቃላትን፣ ሐረጋትን ወይም አረፍተ ነገሮችን በክዋኔ ሂደት ደጋግመው በመናገር ከድግግሞሹ አፅንኦት የመስጠትን፤ አንድ ሁነት ወይም ድርጊት የተፈፀመበትን የድግግሞሽ መጠን የመግለጽን፣ የገፀባህርያትን የስሜት ደረጃ (መጠን) የማሳየትን ፋይዳ ያዘምራሉ፡፡ ሁኔታውን ከስብስብ ተረኮች አብነቶችን በመውሰድ እንመልከት፡፡

## ተረክ 29

ሰውየው በሬ ሊገዛ ወደገበያ ይሄዳል፡፡ ታዲያ መንገድ ላይ ጓደኛው አገኘውና "ወዴት ትሄዳለህ" አለው "በሬ ልገዛ ወደገበያ እየወጣሁ ነው" አለው፡፡ ጓደኛውም መለሰና "እግዚአብሔር ከፈቀደልህ" አለው፡፡ "እንዴ ገንዘቡ እኮ ኪሴ ውስጥ አለ የእግዚአብሔር ፍቃድ ለምን ያስፈልጋል" አለ፡፡ ጥቂት ኪሎ ሜትር እንደተጓዘ ወንበዴዎች ቅጥቅጥ አድርገው ልብሱን ገፈው ገንዘቡን ዘርፈውት ሄዱ፡፡ ቆስሎ፣ ተደብድቦ፣ ገንዘቡ ተዘርፎ ሲመለስ ጠዋት ያገኘው ጓደኛው "እንደምን ዋልክ" አለው፡ ሳይለው (አባባሉን ለማረም ነው) "ወዴት እየሄድክ ነው" አለው፡፡ መጀመሪያ ምን ነበር ያለው "ወደከተማ እየወጣሁ" "ምን ልታደርግ" "በሬ ልገዛ" ሲለው "እግዚአብሔር ከፈቀደልህ" ሲለው "አይ ኪሴ ውስጥ እኮ ገንዘብ አለኝ የእግዚአብሔር ፍቃድ ምን ያስፈልጋል" ነበር ያለው፡ ተደብድቦና ቆስሎ ገንዘቡንም አጥቶ ገንዘቡንም ተዘረፎ እርሱም አካሉን አጥቶ ሲመለስ ግን ጠዋት ያገኘው ጓደኛ "ወዴት እየሄድክ ነው" አለው "እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደቤቴ እየሄድኩ ነው" አለ፡ "እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደቤቴ እየሄድኩ" አለ፡፡

ከላይ በቀረበው ተረክ ማብቂያ ላይ "እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደቤቴ እየሄድኩ ነው፡፡" የሚለው አረፍተ ነገር ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ የአረፍተ ነገሩ መደጋገም ከመነሻው ላይ እግዚአብሔር በህይወቱ ውስጥ ድርሻ እንዳለው ያልተረዳው ገፀባህርይ በሂደት በወንበዴዎች ተደብድቦ ከተዘረፈ በኋላ የአምላክን ድርሻ ምን ያህል እንደተገነዘበ (ምን ያህል ሁኔታው ወደልቡናው እንደሰረፀ) ድግግሞሹ አጉልቶ ያሣያል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ድግግሞሹ እግዚአብሔር በአጠቃላይ በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ ያለውን ጉልህ ድርሻ በአውዱ በዋናነት ለማሳየት ለተነሳው ተራኪ ላነሳው ሀሳብ አፅንኦት የመስጠት ስልታዊ ጠቀሜታን አስገኝቶለታል፡፡

## ተረክ 19

ሰውየው ንስሀ ሊይዝ ወደ አባቱ (የንስሀ) ይመጣል፡፡ "<u>አባቴ ሀጥያት ሰርቼ</u> ንስሀ ይስጡኝ" "አይ ልጄ ደስ ይላል ሰው ሆኖ የማይበድል እንጨት ሆኖ የማይጨስ የለም ትልቁ ነገር መመለስህ ነው እንኳን ደህና መጣህ ልጄ <u>የሠራኸው ሃጢአት ምንድነው</u>" ይሉታል፡፡ "<u>ገመድ ሰርቄ</u> ይላቸዋል፣ <u>ገመድ ሰርቄ ነው</u>"፡፡ "እንዴ ይሄስ ቀላል ነው" ብለው ንስሀ ይሰጡታል፡፡ ከወራት በኋላ ደግሞ ይመጣል "<u>አባቴ ሀጢአት ሰርቼ</u>" "ምንም ችግር የለም ወድቆ መቅረት ነው እግዚአብሔርን የሚያሳዝነው በሀጢአት መውደቅ ሳይሆን ወድቆ መቅረት ነው (ክፉው) አንተ ግን በቃ እንደወደክ አልቀረኽም ትልቁ ነገር የሚፈለገው መምጣትህ ነው ሀጢአትህን አምነህ፡፡ ምንም ችግር የለም <u>የሰራኸው ሀጢአት ምንድነው?</u>" "<u>ገመድ ሰርቄ</u>" ይላቸዋል፡፡ እሺ እሰጥሀለሁ ብለው ንስሀ ይሰጡታል፡፡ አሁንም ከወራት በኋላ ደግሞ ለሶስተኛ ጊዜ ይመጣል፡፡ "<u>አባቴ ሀጢያት ሰርቼ</u>" ይላቸዋል "አይ ልጄ ምን ችግር አለ እግዚአብሔር ባለብዙ ምህረት ነው፣

ባለብዙ ይቅርታ ነው ትልቁ ነገር አንተ እኮ አምነህ እየመጣህ ነው፡፡ አምላክ ይቅር ባይ መሀሪ መሆኑን ተረድተሀል እኮ፡፡ የሰራኸው ሀጢአት ምንድነው?" ይሉታል፡፡ "ገመድ ሰርቄ" ለሶስተኛ ጊዜ "አንተ ልጅ በገመድ ተለክፈሀል እንዴ ገመድ ገመድ ትላለህ እሳ?! የቸገረኽ ገመድ ከሆነ እኔ ሙሉ ገመድ እሰጥሃለሁ" አሉት፡፡ እኚህ አባት የሚፈልገውን ያህል ገመድ ሰጡት፡፡ ጥቂት እንደተጓዘ የአባቱ ደግነት እሩህሩህነት ማፅናናታቸው ተሰማው ልቡን ነካው "እስከመቼስ እግዚአብሔርን እዋሸዋለሁኝ፡፡ አባቴንስ ለምን አታልላለሁኝ እውነቱን ለምን አልናገርም" አለና ተመልሶ መጣ፡፡ "አንዱ ገመድ አነሰህ እንዴ? አልበቃህም እንዴ?" ይሉታል፡፡ "አይ እኔ እንደው አባቴ እንዲህ አይደለም እኮ ነገሩ እንደው ገመድ ሳይሆን ገመዱ ጫፍ ላይ በሬ አለ" አለ፡፡ ለካ ይህ ሰው የሰረቀው ገመድ ሳይሆን በሬ ኖሯል፡፡ (አጽንኦቶቹ ከእኔ ናቸው)

ከላይ በቀረበው ተረክ ውስጥ አፅንኦት ያረፈባቸው ሀረጋት በተወሰነ ርቀት ደግመው ደጋግመው እየመጡ በተረኩ ክዋኔ ሂደት ይህ ነው ሊባል የሚችል ተግባር ፈፅመዋል፡፡ "አባቴ ሀጥያት ሰርቼ" የሚለውን ሀረግ ከዋኙ ደግሞ ደጋግሞ በመግለፅ "የሰው ልጅ ከሀጢያት ጋር የሚኖር በመሆኑ እውነተኛ ንስሀ ያስፈልገዋል" በሚለውና በአጠቃላይ ለተረኩ መነገር ምክንያት በሆነው የስብከቱ ዋና ሀሳብ ውስጥ ጠንክሮ ለሚነሳው "የሰው ልጅ ከሀጢያት የማይለይ ነው" ለሚለው ሀሳብ አፅንኦት ይሰጣል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን "አባቴ ገመድ ሰርቄ" ለሚለው ገፀባህርይ ደግሞ ደጋግሞ "የሰራኸው ሀጢያት ምንድነው?" የሚለው ጥያቄ መነሳቱና "ገመድ ሰርቄ" የሚለው መልስ በተደጋጋሚ መሰጠቱ በተረኩ ክዋኔ ሂደት ታዳሚው፣ ከዋኙ "አሁን ይህን ጥያቄ አንስቶ ቀጥሎ ይሄንን መልስ ሊል ነው" ብሎ ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅ ያስችለዋል፡፡ በሌላ አገላለፅ ታዳሚው የታሪኩን ፍሰት በመልመድ የገጸባህርያቱን ተደጋጋሚ ንግግር በልቡናውም ቢሆን ከከዋኙ ጋር እየተናገረ እንዲዘልቅ ያነሳሳዋል፡፡ ይህም በተረኩ ክዋኔ ሂደት ታዳሚው ቤተኛነት እንዲሰማው፣ የታዳሚነት ብቻም ሳይሆን "የከዋኝነት" ሚናም እንዲኖረው ያስችለዋል፡፡

ተረክ 50

ሁለት እ. . . በጫካ ውስጥ ብዙ አውሬዎች ይኖራሉ መቼም ጫካ ያው የአውሬዎች መኖሪያ ነው፡፡ በዛ ጫካ ውስጥ የሚኖሩ አንበሳና ድኩላ ነበሩ፡፡ አንበሳው "እራበኝ እራበኝ፣ እራበኝ" ይላል "እራበኝ" ሲል አንድ ድኩላ ይመለከታል፡፡ ድኩላዋ ደግሞ አንበሳውን ስትመለከት አንበሳው ከያዘ እንደማይለቃት ስለምታውቅ "አውጣኝ፣ አውጣኝ፣ አውጣኝ" ማለት ጀመረች፡፡ አንበሳው አብላኝ ይላል ድኩላ አውጣኝ ትላለች፡፡ በዚህን ሰዓት ያቺን ድኩላ ባየ ጊዜ አንበሳው፣ ድኩላዋን ለመያዝ ሲሮጥ ድኩላዋም ደግሞ ላለመያዝ ስትሮጥ ድንገት ከሜዳ ላይ አሳማ ተኝቷል፡፡ ያ አንበሳ ድኩሏዋን መያዝ ስላልቻለ አሳማው ተኝቶ ባገኘ ጊዜ ያንን አሳማ ይዞ ጨፍልቆ በላው፡፡ እንግዲህ አውጣኝ ያለም ወጣ፣ አብላኝ ያለም በላ፣ ተኝቶ የተገኘ አሳማ ተበላ በማለት አባቶቻችን ይናገራሉ፡፡ (አጽንኦቶቹ ከእኔ ናቸው)

በዚህ ተረክ ውስጥ "አንበሳው ኧራበኝ! እራበኝ! እራበኝ' ይላል። . . . ድኩላዋ ደግሞ አንበሳውን ስትመለከት ከያዛት እንደማይለቃት ስለምታውቅ 'አውጣኝ! አውጣኝ! አውጣኝ!' ማለት ጀመረች" የሚሉት ቃላት በድግግሞሽ ስልት ቀርበዋል። የቃላቱ መደጋገም የገፀባህርያቱን የመሻት ደረጃ፤ የአንበሳን የእራብ መጠንና የመብላት ፍላጎት፣ የድኩላን የፍርሀትና በህይወት የማምለጥ ጉጉት፤ አጋኖና አጉልቶ ለማሳየት ተራኪውን አስችሎታል። በአባሪ ሁለት ውስጥ በተካተተው ተረክ 59 ስር እንዲሁ "ደብድባ! ደብድባ! ደብድባ!" የሚለውና "ስትሮጥ! ስትሮጥ! ስትሮጥ! ስትሮጥ! ስትሮጥ!" የሚሉት ቃላት በተጠቀሰው መልኩ መደጋገማቸው በተረኩ ድርጊት ፈፃሚ የሆነችው ሚዳቋ ድርጊቱን የፈፀመችበትን መጠን ከፍተኛነት በማሳየት ታዳሚያን የገፀባህርይዋን እልህ አስጨራሽ ትግል በተጨባጭ እንዲያዩት የማስቻል ስልታዊ ጠቀሜታን አስገኝቷል።

### 4.4.5. ወደረኛ ቅንብር /parallelism/

ወደረኛ ቅንብር ቀደም ሲል በቀረቡት ንኡሳን ርእሶች ከተጠቀሱት ስልቶች ጎን ለጎን በተረኮች ክዋኔ ሂደት የሚታይ ሌላው ስልት ነው። ወደረኛ ቅንብር በአንድ የፅሁፍ መዋቅር ውስጥ ያሉ ቃላት ሀረጋት፣ ዐ.ነገሮች፣ አንቀፆች ተመጣጣኝ ሆነው የሚዋቀሩበት ሂደት መሆኑን Dictionary of Literary Terms በሚከተለው መልኩ ይገልፃል *"Arrangement of the parts of a composition so that elements (parts) of equal importance are balanced in similar constructions. Such structural order applies to words, phrases, clauses, sentences, paragraphs, and complete units of compositions."* (1972፣ 275)

በቃላዊ ዝርው ተረኮች ክዋኔ፣ ከዋኞች አንድ አይነት ቃላትን፣ ሐረጋትን ወይም አረፍተ ነገሮችን ከመደጋገም ባሻገር፣ በድግግሞሹ ውስጥ በመጠን፣ በፍቺ፣ በቅላፄ ተመሳሳይነት ወይም ተመጣጣኝነት ያላቸውን ቃላት ወይም ሐረጋት ወይም አረፍተ ነገሮች በማምጣት አንድ ተግባራዊ ወይም ኪነውበታዊ ፋይዳ የሚያስገኙበትን የወደረኛ ቅንብር ስልትን ይጠቀማሉ። የወደረኛ ቅንብር ስልት እንደ ድግግሞሽ ስልት ሁሉ ተራኪው አጠንክሮ ሊገልፀው ለሚፈልገው ሀሳብ አፅንኦት ከመስጠት ባሻገር ለተረኩ ዜማዊነትን የማስገኘት ስልታዊ ፋይዳ አለው። ሁኔታውን ከስብስብ ተረኮች በተቆነፀሉ ምሳሌዎች ማሳያነት መመልከት ይቻላል።

በተረክ 3 ". . . እንግዳውም በዚህ ቁጭ አለ፣ ሚስትም በዚህ ቁጭ አለች፣ ባልም በዛ ቁጭ አለ።" በማለት በቀረበው አገላለፅ በሶስቱ አቻነት ባላቸው ሀረጋት መድረሻ ላይ "በዚህ ቁጭ አለ/ አለች" የሚሉት ሀረጋት ተደጋግመው በመምጣታቸው ለዐ.ነገሩ ወደረኛነት አስገኝተዋል። ተራኪው ይህን ስልት በመጠቀሙ ታሪኩ ቀደም ሲል ይነገርበት የነበረውን በአንፃራዊነት አንድ

አይነት የሆነ ድምጸት (monotonous tone) በመስበር የአድማጩን ጆሮ ሊይዝ የሚችል ዜማን አስገኝቷል፡፡ በተመሳሳይ በተረክ 18 “. . . ስትፀልይ፣ ስትዘምር፣ ስትሰግድ . . .” የሚለው፤ በተረክ 21 “ለልጆቻቸው መልካም ትምህርትን የሚያስተምሩ፣ ለልጆቻቸው ሃይማኖትን የሚያስተምሩ ለልጆቻቸው በጎ ነገርን የሚያስተምሩ . . .” የሚለው በተረክ 47 “. . . ፎቃችን አይደለም፤ የመንገዳችንም ጉዳይ አይደለም፣ የስልጣኔያችንም ጉዳይ አይደለም” የሚለው እና “ኩሩ ህዝብ መሆናችን፣ ታሪኩን ወዳድ መሆናችን፣ ለነፃነት ታጋይ መሆናችን…” የሚሉት፤ እንደቅደም ተከተላቸው፤ “ስት . . .”፣ “ለልጆቻቸው . . . የሚያስተምሩ”፣ “አይደለም” “መሆናቸው” የሚሉት ቃላት በየሀረጋቱ ውስጥ ተደጋግመው በመምጣት ለዐ.ነገሮቹ ወደረኛነትን አስገኝተዋል፡፡ ተራኪዎቹ በየተረኮቹ የወደረኛ ቅንብር ስልትን በመጠቀማቸው ለየተረኮቹ ክዋኔ ሂደት ዜማዊነትን ከማስገኘት ባሻገር በትረካዎቹ የተነሱትን ነጥቦች አፅንኦት የመስጠት ስልታዊ ፋይዳን አስገኝተዋል፡፡

በአጠቃላይ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሚካሄዱ የስብከት ስርዓቶች ወቅት በሚነገሩ ተረኮች ከዋኞች በእለት ተእለት የመግባቢያ ቋንቋ ነገር ግን የተረኮቹን ክዋኔ ከእለት ተእለት ተግባቦታዊ ሂደት ልዩ በሚያደርጉ ስልቶች ላይ በመመስረት ይተርካሉ፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተግባራትን /functions/ መሠረት ያደረገ ትንታኔ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርአት ወቅት ስለሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች መከወኛ አውድ፣ ስለከዋችና ስለታዳምያን ማንነት፣ ሚናና መስተጋብር እንዲሁም ስለአከዋወን ስልት በምዕራፍ አራት ዝርዝር መረጃ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህኛው ምዕራፍ ደግሞ ተረኮቹን መሰረት ያደረገ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

በስነቃል ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ልዩ ልዩ የስነቃል ቅርፆች ለተዝናኖት ወይም/እና አንድን ቁምነገር ለማስጨበጥ በሚል አላማ ይነገራሉ፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ከሆኑት ተረኮች መካከል ይበልጡ በሚከወኑበት ተፈጥሯዊ አውድ አድማጮችን ለማዝናናት ዓላማ አይነገሩም፡፡ ተረኮቹ በቀዳሚነት አንድን ተግባር እንዲፈፅሙ የሚነገሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ ተረኮቹ አንድ ሙያ ያላቸው መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት በስነቃል ጥናት አገልግሎት ላይ ከሚውሉ ልዩ ልዩ ንድፈ ሀሳቦች መካከል ተግባራዊ አንፃርን (functionalist approaches) መሠረት ያደረገ ትንታኔ ለመስጠት ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ወደትንታኔ ከመዝለቄ አስቀድሞ ግን በትንታኔ ሂደት የሚነሱ ሐሳቦች ከምን አንፃር የቀረቡ እንደሆኑ ለመረዳት አጋዥ የሚሆኑ ሁለት መሰረታዊ ነጥቦችን እጠቅሳለሁ፡፡

የመጀመሪያው ነጥብ የዝርው ተረኮቹ ተግባራት በዝርዝር ሲጠቀሱ ተግባራቱ በየትኛውም ቦታና ጊዜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ተረክ ተግባራትን አጠቃለው ይገልፃሉ ወይም ሁሉንአቀፍ (universal) ናቸው ከሚል ስሜት አለመሆኑ ነው፡፡ በየንኡስ ርዕሶቹ ስር ተግባራቱን ስጠቅስ የተጠቀሱት ተግባራት ወካይ ሆነው ተረኮቹ የሚኖራቸውን አበይት ተግባራት በጥቅሉ ሊያሳዩ ይችላሉ ከሚል እምነት ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የተረኮቹን ተግባራት ስጠቅስ ተግባራቱ የማይለወጡ ወይም ቋሚ (static) ናቸው ከሚል እሳቤ ሳይሆን በጊዜ ቆይታ የተራቹና የአድማጩ ማህበረሰቡ ቡድናዊ ልማድ፣ እምነት፣ እሴት ሊገጥመው ከሚችል ለውጥ አንፃር የተረኮቹ ተግባራትም ለለውጥ ሊጋዙ የሚችሉበት አጋጣሚ እንደሚፈጠር ከግንዛቤ በማስገባትም ነው፡፡

ሁለተኛው ነጥብ፣ በትንታኔ ሂደት የስብከት ስርዓት ወቅት ተረኮች ተግባራትን በተጨባጭ ለማሳየት ከስብስብ ተረኮች መካከል የተወሰኑት ተረኮች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ተረኮች እነዚህ እነዚህን ተግባራት ይፈፅማሉ ስል፣ ተግባራቱ ተረኮቹ በተጠኑበት

ወይም በተሰበሰቡበት ተፈጥሯዊ አውድ* ላይ የነበረውን የክዋኔ ሂደት መሠረት ያደረጉ ሲሆን ምናልባት ተረኮቹ በሌላ አውድ ላይ ቢነገሩ ሌላ ተግባር ሊኖራው እንደሚችል ሳልዘነጋ ነው።

## 5.1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እሴት የማስተማር ተግባር

ፎክሎር በአጠቃላይ በየትኛውም በተለይ ደግሞ የፅሁፍ ቋንቋ ባልዳበረበት ማህበረሰብ ዘንድ ጉልህ የማስተማር ድርሻ አለው። ፎክሎር ፈጣሪው ማህበረሰብ ልዩ ልዩ የስነቃል ቅርፆቹን፤ የታዳጊ ህፃናትን አእምሮ በትምህርት ለማጎልበት፣ ወጣቶችን በስነምግባር ለማነፅ በአጠቃላይ የማህበረሰቡን እሴት በአባላቱ ዘንድ ለማስረፅ ይጠቀምበታል። (Bascom፣ 1965፣293-294)። በተመሳሳይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የቤተ እምነቱን እሴት* ማስተማሪያ ሆነው ያገለግላሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደአንድ ሃይማኖታዊ ተቋም ህልውናዋን ጠብቃ ለመዝለቅ የሚያስችሏት እሴቶች ወይም አስተምህሮዎች አሏት። በየአብያተ ክርስቲያን በስብከት ስርአት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች አንዱና ዋነኛ ተግባርም ይህን የቤተ ክርስቲያኗን እሴት ወደ ምዕመኑ ልቡና ማስረፅ ወይም ማስተማር ነው። ይህ የተረኮቹ ተግባር ምን ይመስላል የሚለውን በምሳሌ በማስደገፍ በሚከተለው መልኩ መመልከት ይቻላል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በመፅሀፍ ቅዱስ ወይም በወንጌል ውስጥ በሰፈረ ቃል ላይ የተመሰረተ ነው። በተቋሙ በስብከት ስርአት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ለተራው ምዕመን ጠናን እና ረቂቅ የሆነውን የወንጌል ቃል ምዕመኑ በቀላሉ ሊረዳው ወደሚችልበት ደረጃ በማምጣት ለገጠመኙ ቅርብ ያደርጋሉ። በዚህም ጠናኑን ሀሳብ ግልጽ ረቂቁን ተጨባጭና አይረሴ እያደረጉ የወንጌሉን ቃል በምዕመኑ ልቦና ያሰርፃሉ፣ ያስተምራሉ።

---

* በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ተረኮች አውድ በሁለት መንገድ ሊታይ የሚችል ነው። አንደኛው የተረኮቹ መከወኛ አውድ የአብያተ ክርስቲያኑ ቅርፅ ግቢን፣ ተራቾችን፣ አድማጮችን፣ አለባበሳቸውን፣ አቀማመጣቸውን፣ መስተጋብራቸውን በአጠቃላይ አካላዊና ባህላዊ መቼቱን የሚመለከት ነው። ሌላው የተረኮቹ አውድ ደግሞ ተረኮቹ ተጠቃለው የሚነገሩበት ስብከት ሲሆን፣ እነዚህ ሁለት አውዶች በተረኮቹ የክዋኔ ሂደት እና በሚያስተላልፉት መልዕክት ላይ የየራሳቸውን ተፅእኖ ያሳድራሉ።

* የቤተ እምነቱን እሴት ስል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች የክርስትና እምነት ተከታይ ተቋማት የምትለይበት የራሷ የሆነ እሴት ወይም አስተምህሮ እንዳላት ከግንዛቤ በማስገባት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ከሌሎች የክርስትና እምነት ተከታይ ተቋማት የምትለይበት ምክንያት አንድ ወይም ነጠላ አይደለም። ይሁን እና ከልዩ ልዩ ምክንያቶች መካከል አንዱ "ተዋሕዶ" በሚለው ቃል ከሚገለፀው ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር የተያያዘ ነው። እንደ ቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ልደት አለው። የመጀመሪያው ልደት ቅድመ ዓለም ከአብ መወለዱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከ5 ሺህ ዓመት በኋላ ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለወንድ ዘር በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና በሰው አምሳል መወለዱ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከ5 ሺህ ዓመት በኋላ ከቅድስት ድንግል ማርያም በሰው አምሳል ቢወለድም መለኮት አልተለየውም። ተዋሕዶ የሚለው ቃል ይህን የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮትና ትስብዕት (ሰውነት) መዋሀድን የሚያሳይ ሲሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለወንድ ዘር የተገኘና መለኮት ያልተለየው ስለመሆኑም የእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድመወሊድ፣ በወሊድ ጊዜ፣ ከወሊድ በኋላ ድንግልና እብነት ነው (ይህን መረጃ ያገኘሁት ከአማካሪዬ ከዶ/ር ዮናስ ነው)።

በተራ ቁጥር አምስት ውስጥ የቀረበውን ታሪክ በአብነት በመውሰድ ሁኔታውን እንመልከት፡፡ ተረኩ አንድ እግዚአብሔርን ወዳድ የሆነ ሰው በቤቱ የሰባ አመት አዛውንት ሲያስተናግድ የፈፀመውን ተግባር ያሳያል፡፡ በታሪኩ ሰውየው፣ በእንግድነት ቤቱ የመጣው አዛውንት "በእግዚአብሔር መኖር አላምንም፣ እግዚአብሔር መኖሩን አላውቅም ስላለ ከቤቱ እንዳባረረው ተገልጿል፡፡ ከዚህ ጋርም ተያይዞ ሰውየው እንግዳው እግዚአብሔርን አልወድም በማለቱ ከቤቱ እንዳባረረው እግዚአብሔር ይህን ሲሰማ በሰውየው ተግባር ማዘኑና እሱ (እግዚአብሔር) የጉዳዩ ባለቤት ሆኖ አላውቅህም ያለውን ሰው ለሰባ አመታት ሲታገሰው ሰውየው ለአንድ ቀን አዳር መታገስ ባለመቻሉ እንደወቀሰው ታሪኩ ያትታል፡፡ የታሪኩ መንፈስ ሁሉን ሊያደርግ፤ ሊሾም ሊሽር፣ ሊቀጣ ሊክስ፣ ሊኮንን ሊያፀድቅ…፤ የሚችል ፈጣሪ አምላክ በፍጡሩ ህልውናው ሲካድ ለሰባ አመት ያህል ሊታገስና ይቅር ሊል ከቻለ እኛ ደካማ የሆንን ፍጡራን እርስ በእርሳችን ይቅር ልንባባልና ታጋሽነት ልናሳይ ሊያቅተን አይገባም በሚል አንድምታ የቀረበ ነው፡፡ ይህ በተረኩ የቀረበው አስተምህሮ በሰባኬ ወንጌሉ በተፈጥሯዊ የተረኩ መከወኛ አውድ ላይ በቀጥታ አይጠቀስ እንጂ፡-

> "ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማይ ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁን መርቁ፣ ለሚጠሉአችሁም ጸልዩ. . . የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁን ብቻ እጅ ብትነሱ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ አህዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን፤ እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍፁም እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ፡፡ (ማቴዎስ፤5÷43-48)

የሚለውና እርስ በእርስ መዋደድንና ይቅር መባባልን የሚሰብከውንና መሰል መፅሀፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን በአንድ ጠቅልሎ ወደምዕመኑ የሚያሰርፅ ነው፡፡

በተራ ቁጥር 16 ስር የቀረበው ተረክ በተመሳሳይ በተከወነበት ተፈጥሯዊ አውድ ጉልህ የማስተማር ድርሻ አለው፡፡ በዚህ ተረክ ገፀባህርያቱ እንስሳ ናቸው፡፡ ይሁን እና ተረኩ በእንስሳት ገፀባህርያቱ አማካይነት እያነሳ የሚሄሰው የሰው ልጆችን ምግባር ነው፡፡ Fennigan እንደሚሉት በተረቶች እንሰሳት በገፀባህርይነት ቢሳሉም በገፀባህርያቱ አማካይነት የሚነሳው ጉዳይ በሰው ልጅ ባህርያት ላይ ያነጣጠረ አስተያየት እና ምፀት (satire) ነው፡፡ የተረቱ ከዋኝም ስለ እንሰሳ ገፀባህርያቱ ድርጊትና ጠባይ ሲተርክ የሚገልፀው ሀሳብ የሰው ልጆችን ህፀፅና ምግባር የሚያሳይ ነው (351፣1970) ፡፡ በተራ ቁጥር 16 ስር በቀረበው ተረክ ውስጥ በዋና ገፀባህርይነት የተቀረፁት ጦጣና ዝንጀሮዎች ይሁኑ እንጂ የታሪኩ ዋና ጉዳይ የሰው ልጅን

አንድ ባህርይ እየሄሰ ተገቢ ያለውን አስተምህሮ በታዳምያኑ ልቡና ማስረፅ ነው፡፡ በታሪኩ የየራሱን መላጣ (ሙሽልቅ) "ቂጥ" ማየት ያልቻለውና አንዱ በአንዱ ሙሽልቅ "ቂጥ" እየሳቀ የሚኖረው የዝንጀሮ ማህበር አዘውትሮ የራሱን ህፀፅ፣ ጉድለት፣ ሀጢአት ማየት ይሳነዋል ለሚባለው የሰው ልጅ ፀባይ ማሳያነት በተምሳሌትነት የቆመ ነው፡፡ በዚህ ተምሳሌታዊ አቀራረብ ተራኪው ምዕመናን፣ እኔን ሰባኪውን ጨምሮ አንዳችን ከአንዳችን የማንለይ ሁላችንም ከበደል፣ ሁላችንም ከሀጢያት ያልፀዳን ሆነን ሳለን ወደሌሎች ህፀፅ ጣታችንን እንጠቁማለን የሚል ሀሳብ ያቀነቅናል፡፡

ተረኩ በተከወነበት ተፈጥሯዊ አውድ ተራኪው በቀጥታ፡- "በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፣ በአይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለምን አትመለከትም? ወይም ወንድምህን ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆ በአይንህ ምሰሶ አለ፡፡ አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከአይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያ በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፍ ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ" (ማቴዎስ፤7፣3-5) የሚለውን ጥቅስ አልጠቀሰም፡፡ ይሁን እና በዚህ ተረክ ተምሳሌታዊ አቀራረብ መሰረትነት ተራኪው ይህንና መሰል መፅሀፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች በአንድ ጠቅልሎ ወደምዕመኑ ልቡና ያሰርፃል፡፡

በአብያተ ክርስቲያናቱ በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ተረኮች የወንጌሉን ቃል ለምእመናን ገጠመኝ ቅርብና ተጨባጭ በማድረግ ከማስተማር ተግባር ጎን ለጎን ቀድሞ ያውቃቸዋል የሚባሉ ነገር ግን አጠቃላይ መልዕክታቸውን በአግባቡ እንዳልጨበጣቸው የሚታሰቡ የቤተ እምነቱን ስርዓቶች ወይም እሴቶች ወደታዳምያን እያቃኑ የማድረስን ወይም የማስተማር ተግባርን ይፈጽማሉ፡፡ በተለይ በተረክ 19 እና 51 ውስጥ የቀረቡት ተረኮች ለተነሳው ነጥብ ተጨባጭ ማሳያ ሲሆኑ ተረኮቹን እንደቅደም ተከተላቸው በምሳሌነት ወስደን ሁኔታውን በዝርዝር እንመልከት፡፡

የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ከሰራውና ከሚሰራው ሀጢያት እግዚአብሔር አምላኩ ይቅር ይለው ዘንድ ሊፀፀትና፣ ንስሀ ሊገባ ይገባል የሚለው ሀሳብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዋናነት ከሚነሱ አስተምህሮዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያኗ ለንስሀ አባት ሀጢያትን የመናዘዝ ተገቢነት ሲሰበክ እስከምን ደረጃ በሚደርስ ግልፅነት እንደሆነ ምዕመኑ ይረዳ ዘንድ ተረክ 19 በማስተማሪያነት ቀርቧል፡፡ ተረኩ በሬን ያህል ነገር ደግሞ ደጋግሞ እየሰረቀ ገመድ ሰርቂ እያለ በተደጋጋሚ ንስሀ የሚገባ ሌባ ገፀባህርይ ታሪክን ይዞ ቀርቧል፡፡ በተረኩ የገፀባህሪው ድርጊት "ከባድ" ሀጢያት ሰርቶ ሳለ "ቀላሉን" (ገብስ ገብሱን) ለንስሀ አባቱ ከሚናገረው ምዕመን ምግባር ጋር ትይዩ ሆኖ የቀረበ ነው፡፡ ተረኩ፣ ሌባው

በተደጋጋሚ በሬ እየሰረቀ ገመድ ሰርቂ እያለ ሲናዘዝ ቆይቶ በስተመጨረሻ መፀፀቱና ትክክለኛውን ሀጢያቱን፤ ገመዱ ጫፍ ላይ በሬ አለ፤ በማለት የሰረቀው በሬ መሆኑን ገልፆ ንስሀ መግባቱን ያሳያል፡፡ በዚህ የገፀባህሪው ድርጊት ማሄጃነትም ሰባኪው፤ ምዕመኑ ንስሀ መግባት ያለበት እውነተኛ ሀጢያቱን ገልፆ መሆኑን እያስተማረ፣ ለለውጥ ያዘጋጃል፡፡

በሌላ በኩል በተረክ 51 ስር የቀረበው ታሪክ በእርሻ ቦታው ላይ እያለ ጠላቱን የተመለከተ ገበሬ ወደቤቱ ሄዶ መሳሪያውን ይዞ ሲወጣ ጠላቱን ለመግደል መሆኑን ያላጤነች ሚስቱ በጥዋት "አፍህን ሳትገድፍ" እህል ሳትቀምስ ከቤት አትውጣ ብላ ስትይዘው ያሳያል፡፡ ታሪኩ አያይዞም ጠላቱን ሊገድል የሚሄደው ባል እለቱ አርብ (የፆም ቀን) መሆኑን በመጥቀስ እህል በአፌ አልቀምስም ማለቱን ያትታል፡፡ በታሪኩ በበፆም ቀን እህል የመቅመስ እና ሰውን የመግደል የኃጢአትነት ደረጃ ጉልህ ሆኖ እንዲታይ በአንፃር ተቀምጧል፡፡ የንፅፅሩ መኖር በታሪኩ የሚኖረው ዋነኛ ፋይዳ ታዲያ ምዕመናን ከራስ ተመክሮ፤ ነጋዴው ስለሃይማኖቱ ብሎ እየፆመ ከሚዛን ላይ ይሸቅብ (ያጎድል) እንደሆነ፣ አለቃ ስለፅድቅ ብሎ በፆመበት አፉ ምንዝሩን ይዘልፍ እንደሆነ ወዘተ.፤ ጋር እያገናዘበ እራሱን እንዲፈትሽም እንዲሄስም ማነሳሳት ነው፡፡ በሂደቱም ተረኩ በቤተ ክርስቲያኗ ፆም ሲሰበክ ከእህል ከውሃ በዘለቀ ከክፉ ምግባራት ሁሉ መታቀብ መሆኑን ያላጤነ ምዕመን እንዲያጤን፤ ያልተገነዘበም ቢኖር እንዲረዳ ያስተምራል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን በተራ ቁጥር 32 እና 48 ስር የቀረቡት ተረኮች በተከወኑበት ተፈጥሯዊ አውድ በቤተ ክርስቲያኗ አዘውትሮ የሚነሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት አጉልቶ በማሳየት፣ በምዕመናን ልቡና የማስረፅና እንዳይረሳ አድርጎ የመክተብ ተግባር አላቸው፡፡ ተረኮቹ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ቤዛ መሆኑን በየራሳቸው መንገድ የሚያሳዩ ሲሆን፣ ተረኮቹን በተናጠል በመውሰድ ይዞታቸውን እንመልከት፡፡

በተረክ 32 የሚፈለገውን ተክል ከገደል ውስጥ በማውጣት ገንዘብ እንዲከፈለው ከአንድ የስነ እፅዋት ተመራማሪ ጋር ውል የተዋዋለ ልጅ ታሪክ ቀርቧል፡፡ ልጁ ወደገደሉ ሲወርድ ወገቡ የሚታሰርበትን ገመድ ብክብድህ ትጥለኛለህ በማለት ተመራማሪው እንዳይዝ አግዶታል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ይህው ልጅ የወለደኝ ስለሆነ አባቴ ብክብደውም አይጥለኝም በማለት አባቱን ጠርቼ ልምጣ ያለበት ሁኔታ ተገልጿል፡፡ ይህ የልጁ ምግባርና አጠቃላይ የታሪኩ አቀራረብ፣ ተረኩ ከተነገረበት አውድ አንፃር ተገናዝቦ ሲታይ ተምሳሌታዊ ነው፡፡ በታሪኩ ልጅ ገፀባህሪው ለቤተ እምነቱ ምእመናን፤ የወለደኝ አባቴ የተባለው ለኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ አምላክነት፤ እንዲሁም ገደሉ ለሞት ለጥፋት ማሳያነት ተምሳሌት ሆነው ቀርበዋል፡፡ በዚህ ተምሳሌታዊ አቀራረብ ተረኩ በልጁ የተመሠለው ምዕመን በህይወቱ ከሚገጥመው አደጋ (በገደሉ ከተመሰለው ሞትና

ጥፋት) ቤዛው በምንም ሁኔታ የማይተወው ፈጣሪ አምላኩ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ይገልፃል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ተረኩ ምእመናን "ለህይወታቸው ብቸኛ ቤዛ" ለኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጡትን ዋጋ (value) ከፍ እንዲያደርጉ የማትጋት ተግባርን ይጫወታል፡፡

በተረክ ተራ ቁጥር 48 ስር የቀረበው ታሪክ በአንፃሩ ላይ ላዩን ሲነበብ ስለልጇ ፍቅር ስትል የራሷን ውበት፣ ደምግባት ለእሳት ቃጠሎ አሳልፋ የሰጠች እናትንና እሱን ከእሳት ለማዳን ስትል በቃጠሎ ውበቷን ማጣቷን ለማጤን ተስኖት በጓደኞቹ ዘንድ ሲያቀርባት ሲያፍር የቆየን ልጅ ታሪክ ያትታል፡፡ ተረኩ በዚህ ደረጃ (በዝርው (literal) ቅርጹ) የሚያትተው ታሪክ ለታዳምያኑ ገጠመኝ ቅርብ ነው፡፡ ማለትም የእናትና ልጁ ገጠመኝ ከምዕመኑ የህይወት ተመክሮ እምብዛም የማይርቅ ሲሆን ይህም ተራኪው እናት የከፈለችውን መስዋእትነትም ሆነ የልጁን አላዋቂነት ወይም ውለታቢስነት በታዳምያን ልቡና በቀላሉም አጠንክሮም ለማስረፅ የሚያስችለው ነው፡፡ ይሁንእና የታሪኩ የመጨረሻ ወይም ታላሚ ግብ በዚህ በእናትና ልጁ ታሪክ ዙሪያ የተወሰነ አይደለም፡፡ የታሪኩ ታላሚ ግብ ታዳምያንን ለገጠመኛቸው ቅርብ በሆነው የእናትና ልጁ ታሪክ ተምሳሌትነት ይዞት ወደተነሳው ዋነኛ ነጥብ ማዝለቅ ነው፡፡ የታሪኩ ዋነኛ ነጥብ ወይም በዝርው በተነገረው ታሪክ ተምሳሌትነት ነጥሮ የሚወጣው መሰረታዊ አንድምታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሲል የከፈለውን ዋጋ፤ ህማሙን፣ ስቃይ፣ መከራና እንግልቱን በአጠቃላይ ቤዛነቱን ገልፆ ማሳየትና ማስተማር ነው፡፡

በአጠቃላይ ተረኮቹ ያላቸውን የማስተማር ተግባር ለማሳየት ከላይ በአብነት እየተጠቀሱ ትንታኔ ከተሰጠባቸው ተረኮች ጎን ለጎን በተራ ቁጥር 11፣20፣22፣36 እና 59 ስር የቀረቡት ተረኮችም እንዲሁ ምእመናንን የማስተማር ተግባር ያላቸው ናቸው፡፡

## 5.2. የመቆጣጠር እና የመግታት ተግባር

ፎክሎር የፈጣሪውን ማህበረሰብ ወይም ቡድን እሴት ማስተማሪያ ሆኖ ከማገልገል በዘለቀ ከማህበረሰቡ እምነትና አመለካከት ወይም ስምምነት (social convention) የሚያፈነግጡ ግለሰቦች ላይ ጫና ለማሳደሪያነትና ለመቆጣጠሪያነትም እንደሚያገለግል (Bascom፣ 1965፣ 294) ይገልፃሉ፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተግባርም ምዕመናኑን በማስተማር፤ በቀዳሚው ንኡስ ርእስ ስር እንደተገለፀው ባለ መልኩ አንድን ጥሬ መረጃ ወደታዳሚው በማድረስ ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ በስርዓቱ ወቅት የሚነገሩ ተረኮች፤ ገፀባህርያት ክርስቲያናዊውን ስነምግባር ተከትለው ሲኖሩና ለስኬት ሲበቁ፤ እንዲሁም ከክርስቲያናዊው ስነ ምግባር አፈንግጠው

ሲወጡና መጨረሻቸው ውድቀት ሲሆን እያሳዩ አባላቱ ከቤተ እምነቱ የእሴት ስርዓት አፈንግጠው እንዳይወጡ ከወዲሁ ይቆጣጠራሉ፣ ይገታሉ፡፡ በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ከምናያቸው ተረኮች አመዛኙ አቀራረባቸው ማስጠንቀቂያ አዘል ሆኖ ምእመናን የቤተ እምነቱን ስርአት እንዳይጥሱ ጫና ያሳድራሉ፡፡ በዚህም ተረኮቹ የተቋሙ የእሴት ስርዓት ሳይናጋ፣ ህልውናው ተጠብቆ እንዲዘልቅ የማድረግ ሚናን ይጫወታሉ፡፡ የተረኮቹን ተጠቃሽ ተግባር በተጨባጭ ለማሳየት ይቻል ዘንድ ከተረኮቹ መካከል ምሳሌ በመጥቀስ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

በተራ ቁጥር 29 ስር የቀረበው ተረክ ምዕመናን የቤተ እምነቱን አንድ እሴት ጠንቅቀው እንዲያውቁና ከእሴት ስርአቱ አፈንግጠው እንዳይወጡ የመቆጣጠር/የመግታት ተግባር አለው፡፡ ተረኩ ይህንን ተግባር እንዴት ይፈጽማል የሚለውን ለማየት በቅድሚያ አጠቃላይ የታሪኩን ይዘት በአጭሩ ላስቀምጥ፡፡

አንድ ሰው በሬ ሊገዛ ወደገበያ ሲሄድ ጓደኛው መንገድ ላይ ያገኘውና "ወዴት ትሄዳለህ?" ይለዋል፡፡ ሰውየው "በሬ ልገዛ ወደ ገበያ እየወጣሁ ነው" ይላል፡፡ ጓደኛውም መልሶ "እግዚአብሔር ከፈቀደልህ" ይለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውየው "እንዴ ገንዘቡ እኮ ኪሴ ውስጥ አለ የእግዚአብሔር ፍቃድ ለምን ያስፈልጋል፡፡" |አፅንኦት 1| ይላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ጓደኛሞቹ ተለያይተው፣ ያ ሰው ጥቂት እንደተጓዘ ወንበዴዎች ደብድበውትና ገንዘቡን ዘርፈውት ቆስሎ ይመለሳል፡፡ |አፅንኦት 2| ሰውየው በሚመለስበት ጊዜ ከበፊቱ ጓደኛው ጋር እንደገና ይገናኛሉ፡፡ ጓደኛውም እንደገና ደግሞ "ወዴት እየሄድክ ነው" ይለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የተደበደበውና የተዘረፈው ሰው "እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደቤቴ እየሄድኩ ነው" |አፅንኦት 3| ብሎ ይመልሳል፡፡

ይህን ተረክ ይዘነው የተነሳነውን ሀሳብ ግልፅ ለማድረግ ይረዳን ዘንድ በሶስት መሰረታዊ ክፍሎች ከፋፍለን እንመልከት፡፡ የታሪኩ የመጀመሪያ ክፍል ተረኩ በተከወነበት ተፈጥሯዊ አውድ የሰው ልጅ ህይወት በእግዚአብሔር ፈቃድ ታድራለች ወይም የሰው ልጅን እጣ ፈንታ ወሳኙ እግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነው የሚለው የቤተ እምነቱ አንድ አቢይ አስተምህሮ የተቀነቀነበት ነው፡፡ ይህ የታሪኩ ክፍል እያንዳንዱ ምእመን ይህንን እውነታ በየልቡናው ከትቦ ሊይዝ ይገባል በሚል አንድምታ የቀረበ ነው፡፡

የታሪኩ ሁለተኛ ክፍል በአንፃሩ ይህ ተጠቃሽ እሴት ሲጣስ (አፅንኦት አንድን ይመልከቱ) እንዲሁም ጥሰቱን የፈፀመው ግለሰብ ለውድቀት ሲዳረግ (አፅንኦት ሁለትን ይመልከቱ) የሚታይበት ነው፡፡ በዚህ ክፍል የቤተ እምነቱን እሴት የጣሰው ገፀባህርይ ያጋጠመው

ውድቀት፣ ንብረት ከማጣት እስከ አካል ጉዳት ድረስ የሚዘልቅ ሆኖ አቀራረቡ ማስጠንቀቂያ አዘል ነው፡፡ ታዲያ በታሪኩ ማስጠንቀቂያ አዘል አቀራረብ የሚገለፀው ሀሳብ ህይወቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደምትተዳደር ያላወቀ አለበለዚያ ደግሞ ቸል ያለ ምዕመን ቢኖር እውነታውን ከራሱ ውድቀት ይማረዋል የሚል አንድምታ ያለው ነው፡፡ ይህም በተለይ በታሪኩ ሶስተኛ ክፍል የእግዚአብሔርን ድርሻ ማየት የተሳነው ገፀባህርይ ከውድቀቱ በህይወቱ እግዚአብሔር ያለውን ድርሻ እንዴት እንደተገነዘበ በተገለፀበት ከኳኊን (አፅንኦት ሶስትን ይመልከቱ) ተንፀባርቋል፡፡ በአጠቃላይ ታሪኩ የእግዚአብሔርን ድርሻ ከወዲሁ መገንዘብ የተሳነው ወይም ያልፈለገና ህይወቴን በራሴ ፍቃድ እመራለሁ ብሎ በተአብዮ የሚያስብ ምዕመን ቢኖር ውድቀቱ የከፋ ይሆናል በማለትና በማስጠንቀቅ ምዕመናን ከዚህ የቤተእምነቱ አንድ አስተምህሮ በተአብዮ እንዳያፈነግጡ ይቆጣጠራል/ይገታል፡፡

ተግቶ የመፀለይ ተገቢነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተደጋግሞ የሚነሳ አስተምህሮ ነው፡፡ "ለምኑ፥ይሰጣችኋል፤ፈልጉ፥ታገኙማላችሁ፤መዝጊያ አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል፡፡"(ማቴዎስ፤7፤7) በሚለውና በመሰል መፅሀፍ ቅዱሳዊ ቃል ላይ ተመስርቶ የሚቀነቀነው የመፀለይ ተገቢነት በተራ ቁጥር 50 እና 63 ስር የቀረቡት ተረኮች ዋነኛ ማጠንጠኛ ነጥብ ነው፡፡ አስተምህሮው እንዴት በተረኮቹ እንደተቀነቀነ ተረኮቹን በተናጠል በማምጣት እንመለከታለን፡፡

ተረክ 50

በጫካ ውስጥ ብዙ አውሬዎች ይኖራሉ መቼም ጫካ ያው የአውሬዎች መኖሪያ ነው፡፡ በዛ ጫካ ውስጥ የሚኖሩ አንበሳና ድኩላ ነበሩ፡፡ አንበሳው "እራበኝ፣ እራበኝ፣ እራበኝ" ይላል "እራበኝ" ሲል አንድ ድኩላ ይመለከታል፡፡ ድኩላዋ ደግሞ አንበሳውን ስትመለከት አንበሳው ከያዘ እንደማይለቃት ስለምታውቅ "አውጣኝ፣ አውጣኝ፣ አውጣኝ" ማለት ጀመረች፡፡ አንበሳው አብላኝ ይላል ድኩላ አውጣኝ ትላለች፡፡ በዚህን ሰዓት ያቺን ድኩላ ባየ ጊዜ አንበሳው፣ ድኩላዋን ለመያዝ ሲሮጥ ድኩላዋም ደግሞ ላለመያዝ ስትሮጥ ድንገት ከሜዳ ላይ አሳማ ተኝቷል፡፡ ያ አንበሳ ድኩሏዋን መያዝ ስላልቻለ አሳማው ተኝቶ ባገኘ ጊዜ ያንን አሳማ ይዞ ጨፍልቆ በላው፡፡ እንግዲህ አውጣኝ ያለም ወጣ አብላኝ ያለም በላ ተኝቶ የተገኘ አሳማ ተበላ በማለት አባቶቻችን ይናገራሉ፡፡

በዚህ ተረክ ውስጥ የቀረቡት ገፀባህርያት እንስሳት ይሁኑ እንጂ ተረክ አስራ ስድስትን አስመልክቶ ትንታኔ ሲሰጥ ለመግለፅ እንደተሞከረው የታሪኩ ዋና ጉዳይ የሰው ልጅ ነው፡፡ በታሪኩ በእንስሳት ገፀባህርያት አማካይነት ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በፆም በፀሎት ሊተጋ ይገባል የሚለው የአብያተ ክርስቲያናት አንድ ጥብቅ የእሴት ስርአት ተንፀባርቋል፡፡ በጥቅሉ ሲታይ

የታሪኩ አቀራረብ ተምሳሌታዊ ነው፡፡ ከላይ በተረክ 50 ስር ከቀረበው ታሪክ ለማየት እንደሚቻለው አንበሳ ደጋግሞ "እራበኝ፣ እራበኝ፣ እራበኝ" ይላል፡፡ ይህ የአንበሳው የእራበኝ ጥያቄ በዝርው ፍቺው እንደምናየው፤ የአንድን የዱር እንስሳ የመብላት ፍላጎት ለማሳየት የገባ አይደለም፡፡ ይልቁን የአንበሳው የመብላት ፍላጎትና የአብላኝ ተማፅኖ የሰው ልጅ ከሚኖረው ልዩ ልዩ ፍላጎትና ያን ፍላጎት ለማሟላት ወደፈጣሪው ተማፅኖውን ሲያቀርብ፣ ሲፀልይ ይገባል ከሚለው ሀሳብ ጋር ትይዩነት ያለው ነው፡፡ በተመሳሳይ በተረኩ የዱኩላዋ የአውጣኝ ተማፅኖ ሲነሳ፣ ተማፅኖው የአንድን እንስሳ በህይወት የመቆየት ፍላጎት ለማሳየት የገባ ሳይሆን አሁንም በታሪኩ በዋናነት የተነሳውን ነጥብ፤ የሰው ልጅ በፀሎት ሊተጋ ይገባል የሚለውን አስተምህሮ ለማጠናከር የገባ ነው፡፡ ታዲያ በታሪኩ ወደፈጣሪ የተሰነዘረውና ተምሳሌታዊ ነው ያልነው የአንበሳው የራበኝ ጥያቄና የድኩላው የአውጣኝ ተማፅኖ እንደየፍላጎታቸው ይፈታል ፡፡ ይህ የታሪኩ አጨራረስ በተመሳሳይ ትእምርታዊነትን  የተከተለ ሲሆን የሰው ልጅ ዘርፈ ብዙ መሻቶች፣ ፍላጎቶች፣ ፈተናዎችና ስጋቶች ተግቶ በመፀለይ መልስ ያገኛሉ፣ ይፈታሉና ተግታችሁ ፀልዩ የሚል አንድምታን ወደታዳሚው ያደርሳል፡፡

አንበሳና ድኩላ "አብላኝ፣ አውጣኝ" እያሉ ድምፃቸውን ወደፈጣሪ ሲያሰሙ ያለህሳብ ተኝቶ የነበረው አሳማ በሌላ በኩል ተምሳሌታዊነቱ በጸሎት ለማይተጋው ምዕመን ነው፡፡ በታሪኩ በፀሎት ያልተጋው አሳማ መጨረሻው ውድቀት መሆኑ፣ በፀሎት የማይተጋው ምዕመን በፈተናው ወራት ምን ሊገጥመው እንደሚችል ከወዲሁ እያሳየ ምእመናን በዕለት ተዕለት ህይወታቸው በጸሎት እንዲተጉ ያነሳሳል፣ እንዳይዘናጉም ይቆጣጠራል፡፡

በተመሳሳይ በመፀለይ ተገቢነት ዙሪያ የሚያጠነጥነው ተረክ 63 አንድም ቀን ፀሎት አድርሶ የማያውቅ መድሀኒት ሻጭ (ፋርማሲስት) ገጠመኝን ይዞ ቀርቧል፡፡ ከታሪኩ እንደምናየው ከእለታት በአንደኛው ቀን አንድ እናቱ የታመሙበት ልጅ በሌሊት የፋርማሲስቱን ሱቅ አስከፍቶ መድሀኒት ገዝቶ ይሄዳል፡፡ መድሀኒቱን በእንቅልፍ ልቡ የሸጠው ፋርማሲስት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ልቡናው ሲመለስ ከትእዛዝ ውጪ መድሀኒት መሸጡንና ያም ታማሚዋን ሊገላቸው እንደሚችል ይረዳል፡፡ ፋርማሲስቱ ከዚህ ቀደም ወደ አምላኩ ፀልዮ አያውቅም በዛ ቅፅበት ግን በህይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በሱ ምክንያት የሴትየዋ ህይወት እንዳይጠፋ ለአምላክ ፀሎት ያደርሳል፡፡ ፀሎቱ ተሰምቶም ከጥቂት ደቂቃ በኋላ መድሀኒት የገዛው ልጅ ወደሱቁ ተመልሶ በችኮላ ሲሮጥ የመድሀኒቱ ብልቃት ስለተሰበረበት ሌላ እንዲሰጠው ይጠይቀዋል፡፡ ይህ ተረክ ምዕመናን ከተለያዩ ፈተናዎች የሚወጡት በፀሎት ነው የሚል ሀሳብ ለመግለፅ የቀረበ ቢሆንም ተረኩ ይዞት የተነሳውን አስተምህሮ ወደምዕመናን የሚያደርስበት መንገድ ተረክ 50 ካቀረበበት መንገድ የተለየ ነው፡፡ ቀዳሚው ተረክ በፀሎት ተግቶ ያልተገኘውን አሳማ መጨረሻ ውድቀት

በማድረግ ተረኩ ምዕመናን ሀሳቡን እንዲቀበሉ ጫናን ያሳድራል፡፡ ተረክ 63 በሌላ በኩል ተገቢ ነው የተባለውን ክርስቲያናዊ ስነምግባር የተከተለው ገፀባህርይ ከፈተና በድል ሲወጣ እያሳየ ታዳምያን ከአስተምህሮው እንዳይወጡ እያበረታታና፣ እያጀገነ ይቆጣጠራል፡፡

በንኡስ ርእሱ ስር ያነሳነውን ሀሳብ ከማጠቃለላችን በፊት በተራ ቁጥር 37 ስር የቀረበውን ተረክ በተጨማሪ ምሳሌነት እንመልከት፡፡ በሌሎች ላይ ግፍ አለመዋል፣ የሌሎችን ሀቅ አለመመኘት፣ በአጠቃላይ ከሀጢያት መራቅ በቤተ ክርስቲያኗ የሚነሳ ሌላው አስተምህሮ ሲሆን በተራ ቁጥር 37 ስር የቀረበው ተረክም ዋነኛ ማጠንጠኛ ነጥብ ነው፡፡ በተረኩ ንፁህ ነው እያሉ ውሀ እየቀላቀሉ ወተት የሚሸጡ ሴት ታሪክ ቀርቧል፡፡ ሴትየዋ ለብዙ ጊዜያት ይህን ተግባር ሲፈፅሙ ይኖራሉ፡፡ በአንድ ወቅት ግን ወተት የምትሰጣቸውን ብቸኛ ላማቸውን ውሃ ለማጠጣት ወንዝ ይዞ የወረደው ልጃቸው ላሚን ሳይዝ ብቻውን ይመለሳል፡፡ ሴትየዋ ላማቸውን ሲጠይቁትም "እማማ ላሚን ያኔ አንቺ ወተት ውስጥ የጨመርሽው ውሀ ጎርፍ ሆኖ ወሰዳት" ሲላቸው ተረኩ ይጠናቀቃል፡፡ በተረኩ ማብቂያ ላይም ተራኪው "አንዳንድ ጊዜ የምናጠራቅመው ሀጢያት፣ የምናጠራቅመው በደል፣ የምናጠራቅመው ጥፋት ጎርፍ ሆኖ እንዳይወስደን፣ እንዳያጠፋን ልንጠነቀቅ ይገባል" የሚል አስተያየት ይሰነዝራሉ፡፡ ከዚህ በተራኪው ከተሰነዘረው አስተያየት ጋር ተገናዝቦ ሲታይ፣ በተረኩ ሴትየዋ ወተት ውስጥ ሲጨምሩት የኖሩት ውሃና ላሚን የወሰዳት ጎርፍ፣ የሰው ልጆች በህይወት ዘመናቸው በሚፈጽሙት ተደጋጋሚ ሀጢያት መጨረሻቸው ውድቀት ይሆናል የሚል አንድምታን የሚያሰርፅ ይሆናል፡፡ በዚህ አንድምታም ተረኩ ምዕመናን በሚሰሩት ሀጢያት ለውድቀት እንዳይዳረጉ እያስጠነቀቀ፣ ክርስቲያናዊውን ስነምግባር ጠብቀው፣ ከሀጢያት ርቀው እንዲኖሩ ከወዲሁ ይቆጣጠራል፡፡

### 5.3. ስነልቡናዊ እፎይታን የማስገኘት/የመስጠት ተግባር

ቀደም ባሉት ሁለት ንኡሳን ርዕሶች የተመለከትናቸው የቃላዊ ዝርው ተረኮች ተግባራት በ Bascom ከተጠቀሱት የፎክሎር ተግባራት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው፡፡ በንኡስ ርዕስ 5.3 ስር የምናየው የቃላዊ ዝርው ተረኮች ተግባር በሌላ በኩል በ Bascom ከተጠቀሱት ተግባራት ጋር ተመሳሳይ ያልሆነ ነገር ግን በስብከት ስርአት ወቅት ተረኮች ውስጥ ጉልህ ሆኖ የሚታይ ተግባር ሲሆን ሁኔታውን በማስከተል በዝርዝር እንመልከት፡፡

የሰው ልጅ በሚኖርበት ዓለም እንደምኞቱና እንደፍላጎቱ ህይወቱን እንዳይመራ የሚገድቡ ወይም የሚያቅቡ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ መሰናክሎችና ስጋቶች (threats) አሉበት፡፡ እነዚህ መሰናክሎችና ስጋቶች እንደስራ ወይም ትዳር አጥነት፤ ከፍቅረኛ፣ ከጓደኛ፣ ከቤተሰብ ወዘተ.

ጋር እንደአለመግባባት ወይም ከትምህርት እንደመሰናከል ያሉና ዕለታዊ ወይም ተራ (ordinary) ሊባሉ የሚችሉ ችግሮች ሊሆኑ ይችላሉ። በሌላ በኩል እንዲሁ መሰናክሎቹና ስጋቶቹ እንደመሬት መንቀጥቀጥ፣ እንደጎርፍና እንደአውሎነፋስ ያሉ የተፈጥሮ አደጋዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እንደካንሰር እና ኤች. አይ. ቪ. ባሉ መድሀኒት አልባ በሽታዎች እንደመለከፍና፤ እንደጦርነትና እንደስደት ስጋት ያሉና በአጠቃላይ ውስብስብና በቀላሉ የማይፈቱ ችግሮችም ሊሆኑ ይችላሉ። ታዲያ የሰው ልጅ ተጠቃሽና መሰል ዕለታዊ ችግሮቹን ለመፍታት አለመቻሉ ወይም አንዱን ችግሩን ሲፈታ ሌላው የሚተካ መሆኑ በኑሮው ከችግሮቹ ጋር አብሮ እንዲዘልቅ የግድ ይሆንበታል። ይህም ህይወቱን በተለያየ መጠንና ደረጃም ቢሆን በውጥረት የተሞላ ያደርገዋል። ምንም ያህል በቴክኖሎጂ ቢራቀቅም ውስብስብ ችግሮቹን ሊፈታ፤ ልዩ ልዩ ተፈጥሯዊ አደጋዎችን ሊገታ፤ ፈውስ ለሌላቸው በሽታዎች መፍትሄ ሊያገኝላቸው ወዘተ.፤ አለመቻሉም እንዲሁ የሰውን ልጅ ኑሮ አዘውትሮ ከውጥረት ነፃ ያልሆነ ያደርገዋል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርአት ወቅት የሚነገሩ ተረኮች ታዳምያንም ከላይ በተጠቀሱት መሰናክሎችና ስጋቶች በሚፈጠር ውጥረት በተለያየ ጊዜና ሁኔታ በተለያየ ደረጃም ቢሆን ለስነልቡናዊ ጫና ይጋለጣሉ። በቤተ ክርስቲያኗ በስብከት ስርአት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ታዲያ እነዚህ ስጋቶችና መሰናክሎች በታዳምያን ልቡና ላይ የሚፈጥሩትን ጫና የሚያቀሉ ሆነው ይቀርባሉ፤ ወይም ለታዳምያኑ ስነልቡናዊ እፎይታን የማስገኘት ተግባርን ይፈፅማሉ። ተረኮቹ በምን ሁኔታ ለታዳምያኑ ስነልቡናዊ እፎይታን ያስገኛሉ የሚለውን ለመረዳት ከስብስብ ተረኮች አብነቶችን በመውሰድ በዝርዝር እንመልከት።

በተራ ቁጥር 53 ስር የቀረበው ተረክ በቀላሉ ፈውስ ለማግኘት በማይችል ህመም የተለከፈ ወጣት ታሪክ የቀረበበት ነው። ባለታሪኩ ወጣት ከዩኒቨርሲቲ ትምህርት የመባረር፣ የእናት ሞት፣ ለጎዳና ሕይወት መዳረግ እና መሰል መከራዎች የደረሱበት ነው። በዓለም እየኖረም* ይህ ወጣት በርካታ ኃጢአቶችንም ሲፈጽም ኖሯል። ይሁን እና በአንድ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማታ የስብከት ፕሮግራም ከተካፈለ በኋላ ባለታሪኩ በእግዚአብሔር ፍቅር ተስቦ እራሱን ለመንፈሳዊ ህይወት ያስገዛል። በዚህ ወቅት ታዲያ ይህ ወጣት በድንገተኛ የጀርባ ህመም ይጠቃና ወደ ሀኪም ዘንድ ይሄዳል። ሀኪሙ የወጣቱ ህመም ከባድና በሀገር ውስጥ ህክምና መፍትሄ ሊያገኝ የማይችል መሆኑን ቢገልጽም በወቅቱ ወጣቱ

---

* በዓለም እየኖረ የሚለው ቃል ተራኪው ተረኩን ሲተርክ ከተጠቀመበት ቃል በቀጥታ የተወሰደ ሲሆን፣ ቃሉ ታሪኩ የሚነገርለት ወጣት እግዚአብሔን ሳያውቅ፣ መንፈሳዊ ህይወት ሳይኖረው በፊት የሚለውን ሀሳብ እንዲገልጽ የገባ ነው።

ወደባህር ማዶ ዘልቆ ህክምና ሊያደርግ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ አቅም አልነበረውም። በሌላ በኩል ደግሞ ህመሙ እለት በእለት እየበረታ የሚሄድ ሲሆን በቆይታ ልጁ ስቃዩን መቋቋም ከማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ እንደ ታሪኩ ገለፃ ወጣቱ የፃድቁ ገብረመንፈስ ቅዱስን ፀበል ሲጠመቅ ከህመሙ ፈውስ የሚያገኘው።

የዚህ ተረክ አቀራረብ በተነገረበት ተፈጥሯዊ አውድ ታዳምያን በባለታሪኩ ገጠመኝ አማካይነት የየራሳቸውን ግላዊ ህይወት እንዲያስቡ የሚገፋፋ ነው። በታሪኩ ሂደት ምዕመናኑ አንድም የየራሳቸውን የጤናና መሰል ችግሮች በተዛምዶ ያስባሉ። በሌላ በኩልም የቱንም ያህል ዓለም በቴክኖሎጂ ቢራቀቅም አሁንም የሰው ልጅ በቀላሉ ሊፈታቸው ካልቻላቸው እንቆቅልሾቹ ወይም ከመፍትሄ አልባ ደዌዎቹ ጋር ህይወቱን በአንድ እያጓዘ ያለ ስለመሆኑ ያስታውሳሉ። ምዕመናን እነዚህን ሁኔታዎች እያሰቡ እንዲጓዙ የሚያደርገው ታሪክ በተለይ መቋጫው የወጣቱ ህመም በፃድቁ ፀበል ፈውስ አግኝቶ የሚጠቃለል መሆኑ ተረኩ በተነገረበት ተፈጥሯዊ አውድ ምዕመናን በተዛምዶ ለሚያስቧቸው የየግል ችግሮቻቸው መፍትሄ የሚሰጥ አንድ ከእነሱ በላይ የሆነ አካል መኖሩን እንዲያውቁ ወይም እንዲያስታውሱና አምነው እንዲቀበሉ የሚያነሳሳ ነው። በዚህም ተረኩ ምዕመናን በውስጣቸው ላሉ ስጋቶች መልስ እንዲያገኙ፣ ከነሱ በላይ የሆነ ሁሉን ሊያደርግ የሚችል አንድ አካል እንዳለላቸው እንዲያስቡ ወይም አምነው እንዲቀበሉ በማድረግ ከየውጥረቶቻቸው ፋታን ይሰጣቸዋል፣ ስነልቡናዊ እፎይታን የሚያገኙበትን መንገድም ያቀናላቸዋል።

በተራ ቁጥር 55 ስር የቀረበው ተረክ ከላይ ከቀረበው ተረክ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ በተነገረበት ተፈጥሯዊ አውድ ለታዳምያን ስነልቡናዊ እፎይታን የመስጠት ተግባርን ይዞ የቀረበ ነው። ተረኩን በማስቀደም ሁኔታውን በዝርዝር እንመልከት።

ተረክ 55

ያኔ ዱሮ ዱሮ ግብረገብ ያስተማሩኝ መምህሬ መንኩሰዋል አሁን። ድሮ ነው ግብረገብ እንደ አንድ "ክሬዲት ሐወር" ይሰጥ ነበር። አስታውሳቸዋለሁ አንድ ቀን ትምህርት ቤቱ ውስጥ ከግብረገብ አስተማሪነት ሌላ ገንዘብ ያዥም ናቸው። ገንዘብ ያዥ መሆናቸውን ስለሚያውቅ ቤታቸውን ሠርስሮ ገባ ሌባ። የት እያሉ? ትምህርት ቤት እያሉ። እሳቸው አሁን በዛን ሰዓት (ጊዜ) ካዝና አለ ግን ብዙም የለም [. . .] አሁን የሚገርማችሁ ልክ ሲሄዱ የቤታቸው በር ተሰብሯል አልደነገጡም አማተቡ፣ አማተቡና ገቡ። ልክ ሲገቡ አመናችሁኝም አላመናችሁኝም ሰውየው መሰርሰሪያውን እንደያዘ የተሟላ መሳሪያውን እንደያዘ ደርቋል። ልክ እንደሚያስቀድስ ሰው ቆሟል። መጥተው አጠገቡ ቆሙ አያይም ፊት ለፊት ነው የሚያየው። በጣም

አስታውሳለሁ አሁን በጣም ገርሟቸው፣ አንደኛ በሩ ተሰብሯል፣ እንደገና ሰውየው ቆሟል [. . .] አሁን ሰተት ብለው ገቡ አዩ። ወዲያው ሌባ እንደሆነ አወቁ። ወደ ቤተክርስቲያን ሰው ላኩ ካህናት ተጠርተው ፀሎት ተደርጎ ሰውየው፣ ሌባው ዲዳ ሆነ (ሰውነቱን ግን) ለቀቀው። ሰውየው ራሱ አገልጋይ ሆነ አየው የእግዚአብሔርን ስራ። እኚህ አባት ብዙም አልቆዩ ከተወሰነ አመት በኋላ መንኩሰዋል። ለካስ ቤታቸው ውስጥ ስትገቡ ገብታችሁ እንዲህ ስትዞሩ (ፊቱን ወደቀኝ አዙሮ) ግድግዳው ላይ የስላሴ ስዕል አለ።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የሰው ልጅ የቱንም ያህል በቴክኖሎጂ መራቀቁ ህይወቱን በሚፈልገውና ይመቸኛል በሚለው መንገድ ብቻ ለመምራት የሚችልበት ደረጃ ላይ ለመድረስ አላበቃውም። እንዲያውም ከቴክኖሎጂው መራቀቅ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወይም የጎንዮሽ ችግሮች መፈጠራቸው በኑሮው ራስ ምታት ሲሆንበት ይታያል። የሰው ልጅ ደህንነቱን ለመጠበቅ በሩ ላይ ከሚሰቅለው ብረት ምጣድ አንስቶ እስከ አደገኛ አጥር እና የአደጋ ጊዜ አንቂ መጥሪያ (siren) ድረስ የሰጠው ቴክኖሎጂ ለተቃራኒው ወገንም የዛኑ ያህል የተራቀቀ የስርቆሽ "ጥበብ" እና መሳሪያ አጎናፅፎታል። ይህን ሁኔታ ታዲያ አጠቃላዩ የሰው ልጅ ወይም በዚህ ጥናት አውድ የተረኮቹ ታዳምያን የሚረዱት ሲሆን፤ ሁኔታውን መረዳታቸውም በታዳምያኑ ላይ በተለያየ መጠንና ደረጃም ቢሆን የሚያሳድርባቸው ስጋት ወይም ውጥረት ይኖራል። ከላይ በቀረበው ተረክ ያለምንም ካዝና፣ ያለምንም ጥበቃ የተራኪው ግብረገብ መምህር በቤታቸው ያለን ንብረት በአንድ ግድግዳ ላይ በሰቀሉት "የስላሴ ስዕል" ማትረፍ ችለዋል መባሉ ተረኩ በተነገረበት ተፈጥሯዊ አውድ ዋነኛ ፋይዳው የአማልክቱን ተራዳኢነት ከመግለፅ የሚዘልቅ ነው። በተረኩ የግብረገብ መምህሩ ለደህንነታቸው አገኙት የተባለው ዋስትና የላቀው ቴክኖሎጂ ስለደህንነቱ ጨርሶ ዋስትና ሊሰጠው ላልቻለው ታዳሚ አንድ ሌላ ከሁሉም የላቀ ተአማኒና ምሉዕ የሆነ ዋስትና እንዳለ በማሳየት ክፍተቱን ይሞላለታል። በዚህም ተረኩ ታዳምያን በእለት ተእለት ህይወታቸው ይዘውት ከሚጓዙት ልዩ ልዩ የደህንነት ስጋት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ነጻ እንዲወጡና ስነልቡናዊ እፎይታን እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። በበርካታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች አንገት ላይ የሚንጠለጠሉ መስቀሎችን፣ በየቤታቸው የሚሰቀሉ የመላዕክት ምስሎችን በየበሮቻቸው ላይ የሚንጠለጠሉ የተቋጠሩ እምነቶችንና የኮዳ ውስጥ ፀበሎችን ከዚህ ሁኔታ ጋር አዛምዶ ማሰብ ይቻላል።

በሰናፍጭ እርሻቸው ላይ ትልቅ ቋጥኝ ተንከባሎ ወድቆ ማሳቸውን አርሰው እንዳይበሉ ስላገዳቸው አንድ እናት ታሪክ የሚተርከው በተራ ቁጥር 61 ስር የቀረበው ተረክ በተመሳሳይ በተነገረበት ተፈጥሯዊ አውድ ስነልቡናዊ እፎይታን የማስገኘት/የመስጠት ተግባር አለው። ታሪኩ በአጭሩ የሚከተለውን መልክ የያዘ ነው። ቋጥኙ ማሳቸውን አርሰው እንዳይጠቀሙ

ያገዳቸው እናት በአንድ አጋጣሚ በቤተ ክርስቲያን የስብከት ፕሮግራም ላይ ተገኝተው የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ቢኖራችሁ ተራራውን ተነስተህ ገደል ግባ ብትሉት ይገባል ብሎ አንድ ሰባኬ ወንጌል ሲያስተምር ይሰማሉ፡፡ የሰባኪው ቃል ወደልቡናቸው የዘለቀው እናትም ቃሉን ከራሳቸው ችግር ጋር በማዛመድ እኔ እዚህ (ቤተ ክርስቲያን) እያለሁ የማርያም ልጅ አማኑኤል ቤቴ ስራዬን ይሰራልኛል፣ ችግሬን ይፈታልኛል ብለው በልቡናቸው እምነት ያሳድራሉ፡፡ እኚህ እናት ቤታቸው ሲሄዱ ታዲያ እንደእምነታቸው ችግራቸው ተፈትቶ፤ ከፍለውት የሚያነሳላቸውን አካል ያላገኙለት ቋጥን ተከፍሏቸው እንዲነሳላቸው ሁኔታዎች ተመቻችቶ ይደርሳሉ፡፡

በዚህ ተረክ የቀረበው ታሪክ ከላይ እንደተጠቀሱት ሁለት ተረኮች ሁሉ በተነገረበት ተፈጥሯዊ አውድ ችግር የገጠማቸውን እናት አንድ ነጠላ ገጠመኝ አሳይቶ በማለፍ ላይ ብቻ ያነጣጠረ አይደለም፡፡ የታሪኩ አጠቃላይ አቀራረብ ታዳምያን በታሪኩ ሂደት እንደየቢጤያቸው የየግል ችግሮቻቸውን ስንክሳሮቻቸውን፤ ትዳር፣ ስራ፣ ሰላም አጥነት ቁሳዊ ፍላጎት አለመሟላት ወዘተ.፤ እንዲያስቡ በሚጋብዝ ወይም በሚያነሳሳ መልኩ የቀረበ ነው፡፡ የታሪኩ መቋጫም እንዲሁ በእግዚአብሔር እምነታቸውን የጣሉ እናት ለችግራቸው መፍትሄ እንዳገኙ ሁሉ የእናንተም ችግር እመኑ በእግዚአብሔር ይፈታል የሚልና አፅናኝም በተለያዩ ግላዊ ችግሮቻቸው ውጥረት ውስጥ ላሉ ታዳምያን ስነልቡናዊ እፎይታን የሚሰጥም ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት ተረኮች ጎን ለጎን ከስብስብ ተረኮች መካከል በተራ ቁጥር 18፣ 58፣62 ስር የቀረቡ ተረኮችም እንዲሁ በየራሳቸው መንገድ ለታዳምያን ስነልቡናዊ እፎይታን የመስጠት ተግባርን ይዘው የቀረቡ ናቸው፡፡ ተረኮቹ እንደቅደም ተከተላቸው በስደት እያላችሁ እንኳን የማይጥላችሁ አምላክ ከጎናችሁ አለ፤ የምታጡት ነገር ለእናንተ ያልተባለውን ብቻ ነው፤ መከራችሁ ቢበዛም ከታገሳችሁ ዋጋችሁ ከፍ ያለ ይሆናል በሚል ለታዳምያን መፅናኛ የሚሆኑ ነጥቦችን ይዘው የቀረቡና ስነልቡናዊ እፎይታን የሚሰጡም ጭምር ናቸው፡፡

## 5.4. የማህበራዊ እሴቶችን ተገቢነት ወይም ጠቀሜታ ከፍ የማድረግ ተግባር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከት ስርዓት ወቅት የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች አጠቃላይ ትኩረት በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ በተረኮቹ የሚነሱ ጉዳዮች ወሰን ከሃይማኖት ጋር የቀጥታ ወይም የቅርብ ተዛምዶ ካላቸውና፤ እንደፅድቅና ኩነኔ፣ ፆምና ፀሎት፣ ፈውስና መቅሰፍት፤ ካሉና ከመሰል ጉዳዮች ቅንብብ ዘልቆ የሚወጣ ነው፡፡ ተረኮቹ ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ባሻገር የአድማጭና የተራቹን ማህበረሰብ፣

ማህበራዊ ህይወት ይቃኛሉ። የተረኮቹ ቅኝት መሰረት በአመዛኙ የአድማጪንና የተራቹን ማህበረሰቡ፣ ማህበራዊ እሴት ተገቢነት ወይም ጠቀሜታ የሚገልፅና ሂሳዊ ሆኖ የሚቀርብ ነው። Bascom እንደሚሉት ፎክሎር የተራቹንና የአድማጩን ማህበረሰብ ባህል ጠቃሚነት የመግለፅ፤ የተቋማቱንና የመንፈሳዊ ስርዓቶቹን ተገቢነት የማረጋገጥ ተግባርን ይጫወታል (1965፣292)። በዚህ መሰረት በተያዘው ንኡስ ርእስ ይህ የተረኮቹ ተግባር በዝርዝር የሚታይ ይሆናል።

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር የሚነሱ ተረኮች በተከወኑበት ተፈጥሯዊ አውድ በተለይ ነባር (ቀደምት) የሆኑ ማህበራዊ እሴቶችን ተገቢነት በመግለፅ እሴቶቹ በተያዘውና በቀጣዩ ዘመን ያላቸውን ዋጋ (value) ጠብቀው እንዲዘልቁ የማስቻል ተግባርን የሚከውኑ ናቸው። በተራ ቁጥር 10 እና 24 ስር የቀረቡ ተረኮች ተጠቃሽ ተግባርን ከሚከውኑ ተረኮች መካከል የሚፈረጁ ሲሆን፣ ተረኮቹ በተለያዩ አውዶች በተለያዩ ከዋኞች ይነገሩ እንጂ የሚያነሱት ጉዳይ ተመሳሳይነት ያለው ነው። በመሆኑም በመጠን አናሳ ከመሆን አንፃር በቦታው ለመጥቀስ ምቹ የሆነውን ተረክ አስርን ከዚህ ቀጥሎ በማስፈር እንዴት የማህበራዊ እሴት ተገቢነትን ከፍ ያደርጋል የሚለውን ነጥብ በዝርዝር ለመመልከት እንሞክራለን።

ተረክ 10

አንድ ወጣት አውቶብስ ላይ ወንበር ይዞ ተቀምጦ ተዝናንቶ ሲሄድ አንድ አረጋዊ ሽማግሌ፣ አንጋፋ አባት ደግሞ አጠገቡ ቆመዋል። አውቶብሱ እየሄደ ነው። ልጁ ተቀምጦም አፉ አያርፍም "አንተ አባት" ይላቸዋል "አቤት" "እናንተ የእድሜ ባለፀጋ የሆናችሁ ሽማግሌዎች እያላችሁ ሞቱ የፀናው በእኛ በወጣቶቹ ላይ ነው ይሄ እንዴት ነው?" አላቸው እሳቸው ደግሞ "እዬ ልጄ ጥሩ ብለህል እግዚአብሔር ወደኛ ሲመጣ በእኛ ወንበር ላይ እናንተ ተቀምጣችሁ ስላየ እናንተን እየወሰደ ነው" (አሉት)።

ይህ ተረክ በኢትዮጵያውያን ባህል ውስጥ ረጅም ዘመን ባስቆጠረውና በእድሜ ለሚበልጧቸው ሁሉ ታናናሾች በአክብሮት መቀመጫ ሊለቁላቸው የተገባ ነው በሚለው ማህበራዊ እሴት ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው። በተረኩ ለአዛውንቱ መቀመጫ ያለቀቀው ወጣት አዛውንቶች እያሉ ለምን ሞት በወጣቱ ላይ እንደፀና ሲጠይቅ በአዛውንቱ የተሰጠው መልስ ቀልድ አዘል ቢመስልም አካሄዱ መራር ትችት ሆኖ ወጣቱ ነባሩን ማህበራዊ እሴት አለመጠበቁን የሚሄስ ነው። ከዚህም ባሻገር የአዛውንቱ መልስ ማስጠንቀቂያ አዘል በሆነ አቀራረብ፤ ለታላላቆች አክብሮት መንፈግ የሚያስከትለውን መቅሰፍት በመጠቆም፤ የማህበራዊ እሴቱን ተገቢነት በሚያረጋግጥና በሚያፀና መልኩ የቀረበ ነው።

የሰላምታ ልውውጥ ስርዓት እንደ አንድ ማህበራዊ እሴት በተረክ ተራ ቁጥር 26 ውስጥ የተነሳ ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ ተረኩ በቅርብ ጊዜ በተለይ በወጣቶች ዘንድ እየጎለበተ የመጣን በትከሻ የመገጫጨት የሰላምታ አሰጣጥ ዘይቤን ይተቻል፡፡ በተረኩ ዘመነኛው የሰላምታ አሰጣጥ ዘይቤ ከወዳጅነት ስሜት ይልቅ አቅም መፈታተሻነት (መገማመቻነት)፣ የጠብ መንጃነት መሆኑ እየተጠቆመ ኢተገቢነቱ ይገለፃል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የእጅ ለእጅ መጨባበጥ ሰላምታ አሰጣጥ ዘይቤም በተረኩ ተሂሷል፡፡ ተረኩ፣ የሰላምታ አሰጣጥ ዘይቤው አንድም ትእምርቱ ተሸንፌያለሁ፣ ተማርኬያለሁ ማለት ነው፤ በሌላ በኩልም ምግባሩ ከጣሊያን የተወረሰ መጤ ልማድ ነው በማለት ይተቸዋል፡፡ በአንጻሩ የትከሻ ለትከሻ መሳሳም ልማድን ነባርነት (ቀደምትነት) ተረኩ እያወሳ የማህበራዊ እሴቱን ተገቢነት ያፀድቃል፡፡

በተመሳሳይ በተራ ቁጥር 34 ስር የቀረበው ተረክ በተነገረበት ተፈጥሯዊ አውድ እርስ በእርስ የመረዳዳትን ተገቢነት ወይም ጠቀሜታ ከፍ የማድረግ ተግባር አለው፡፡ ተረኩ በተለይ በአንድ የስራ ሂደት ላይ በግለሰቦች መካከል ሊኖር ስለሚገባ የመረዳዳት መንፈስ ይገልፃል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ቀደም ባሉት ዘመናት የነበረው የመረዳዳት መንፈስ ከፍተኛ እንደነበር ያትታል፡፡ ከሀተታው መቋጫ ላይ "ዛሬ ዳማከሴ ያወቀ እንደሆነ ሶስቴ ዞሮ ነው የሚቆርጣት ሰው እንዳያውቅ! ዳማከሴ ያወቀ እንደሆነ አያድርስ ነው" |አፅንኦቱ የእኔ ነው| የሚል አባባል ሰፍሯል፡፡ አባባሉ ባለፈው ዘመን የነበረው የመረዳዳት ስሜት በአሁኑ ጊዜ ምን ያህል እንደመከነ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በተለይ ተራኪው እውቀቱን ለደበቀው ገፀባህርይ ያላበሱት እውቀት (ጥበብ) የተራቀቀ የባህል መድሀኒት አዋቂ መሆን እንኳን ሳይጠይቅ ማንኛውም ተራ ግለሰብ የሚያውቀውን ዝቅተኛ (Minor) የሆነውን የዳማከሴ ፈዋሽነትን እውቀት ነው፡፡ በተረኩ ሲደበቅ የሚታየው ተራው የዳማከሴ እውቀት መሆኑ፣ በተረኩ የተነሳን የመረዳዳት ስሜት ጠፍቷል አቤቱታ የደረጃ ልቀት ጉልህ ሆኖ እንዲታይ አስችሎታል፡፡ ከዚህም ባሻገር የተረኩ አቀራረብ እያንዳንዱ ግለሰብ እያጎለበተው ያለውን የአዲሱን ማህበራዊ እሴት፣ የግለኝነትንና የመረዳዳት ስሜት መጥፋትን "ኢተገቢነት" ከተደበቀው እውቀት (ጥበብ) "ተራነት" ጋር በትይዩነት በማምጣት አጉልቶ እያሳየ የቀደምቱን እሴት የተገቢነት/የጠቀሜታ ደረጃን ከፍ የማድረግ ተግባርን ተጫውቷል፡፡

በአጠቃላይ በእስከአሁኑ ቆይታ ከተጠቀሱት ተረኮች ጎን ለጎን ከስብስብ ተረኮች መካከል በተራ ቁጥር 8፣28፣30፣33 እና 44 ስር የቀረቡት ተረኮችም እንዲሁ በተከወኑበት ተፈጥሯዊ አውድ የማህበራዊ እሴትን ጠቀሜታ ወይም ተገቢነት ከፍ የማድረግ ተግባር አላቸው፡፡

## 5.5. የማህበራዊ እሴት ተገቢነት ላይ ጥያቄ የማንሳት ተግባር

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር የሚቃኙ ተረኮች በንኡስ ርእስ 5.4. ስር እንደተጠቀሱ ተረኮች ሁሉ ማህበራዊ እሴትን የመሄስ ተግባር አላቸው፡፡ ይሁን እና በተያዘው ንኡስ ርእስ ስር የቀረቡት ተረኮች በቀዳሚው ንኡስ ርእስ ስር እንደተጠቀሱት ተረኮች የማህበራዊ እሴትን ተገቢነት ከፍ ከማድረግ አኳያ አልቀረቡም፡፡ በንኡስ ርእሱ ስር የሚቃኙ ተረኮች በተለይ ነባር ወይም ቀደምት የሆኑ ማህበራዊ እሴቶች ተገቢነት ላይ ጥያቄ የሚያነሱ ናቸው፡፡ ሁኔታውን በተጨባጭ ለመመልከት የሚያስችሉ አብነቶች በመሆናቸው በተራ ቁጥር 23 እና 27 ስር የቀረቡ ተረኮችን ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

በተራ ቁጥር 23 ስር የቀረበው ተረክ፣ ተረኩ በተከወነበት ተፈጥሯዊ አውድ በተራችና በአድማጩ ማህበረሰብ ዘንድ ለሴቶች በሚሰጥ ቦታ ተገቢነት ላይ ጥያቄ የሚያነሳ ነው፡፡ የተረኩ መቼት ከጊዜ አንፃር ዘመነ ደርግ ነው፡፡ ይሁን እና የተረኩ አቀራረብ በታሪኩ በሴት ገፀባህርይዋ ላይ ሲፈፀም የሚታየው ተግባር አሁንም በተራችና በአድማጩ ማህበረሰብ ዘንድ በተጨባጭ እየተፈፀመ የዘለቀ ድርጊት መሆኑን ያሳያል፡፡ ተረኩ ባሏ ለረጅም አመታት ሁለት መቶ ብር ናት ደመወዜ እያለ የሚሰጣትን ብር ተቀብላ ከስምንት ልጆቿ ጋር ጎመንና ዘንጋዳ እየተቃመሰች የኖረችን ሴት ታሪክ ያትታል፡፡ ይህች ሴት፣ ባሏ በአንድ አጋጣሚ ደርግ ወደኤርትራ ካዘመተው ሰራዊት አንዱ ለመሆን ሲገደድ እሷ በአንፃሩ ደመወዙን ለመቀበል ትቀርባለች፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ ሁለት መቶ ብር ነው ሲባል የኖረው የባሏ ደመወዝ ዘጠኝ መቶ ብር ሆኖ ታገኘዋለች፡፡ በታሪኩ መቋጫ ላይ ተራኪው በባሏ ስትታለል የኖረችው ሴት "... ሰውየው ወደጦር ሜዳ ሄዷል ይህች ሴት መልሰው ብላ ነው የምትፀልየው?! ... " ብለው የሰነዘሩት ጥያቄ ለበስ አስተያየት በባሏ ድርጊት የገጸባህሪዋ የምሬት ደረጃ ምን ያህል የላቀ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ የተራኪው አስተያየት የገፀባህሪዋን ምሬት ከመግለፅ በላይም በተራችና በአድማጩ ማህበረሰብ ዘንድ ለሴቶች የሚሠጠውን ደረጃ በመተቸት በማህበራዊ እሴቱ ላይ ለውጥ እንዲመጣ ይጠይቃል፡፡

በተመሳሳይ በተራ ቁጥር 27 ስር የቀረበው ተረክ መሰረቱ ፆታዊ ጉዳይ ሲሆን ዋና አትኩሮቱ በሴቶች ላይ ጫና የሚያሳድረውን የአድማጭና የተራቹን ማህበረሰብ ፆታን መሠረት ያደረገ የስራ ክፍፍል መሄስ ነው፡፡ ተረኩ በአንድ ጎን "የሴትና የወንድ ስራ የሚል የለም፣ በመጽሐፋችን ያዕቆብ፣ ወንድሙ አድኖ ሲመጣ . . . የምስር ወጥ ይሰራ ነበር፡፡" በማለት ከመፅሐፍ ቅዱስ እማኝ ይጠቅሳል፡፡ ከቅዱስ መፅሀፉ በጠቀሰው ታሪክ እማኝነትም ተረኩ፣ የወንድና የሴት ስራ በሚል ማህበረሰብ የደነገገው ፆታን መሠረት ያደረገ የሥራ ክፍፍል ሀይማኖታዊ መሰረት እንደሌለው ለታዳምያን ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል ይኸው ተረክ "ዛሬ ድስቷን

ጣድ አድርጋ ወይ ልብስ ልታሰጣ ወይ ዘይት ልትገዛ ወደሱቅ ስትሄድ ከሰሉ ላይ የጣደችው ድስት ሲገነፍል "እረ ገነፈለልሽ" ይላል ያ ከንቱ ንብረቱ ገደል ሲገባ" የሚለውን አባባል ይሰነዝራል። በዚህም ወጡ ሲፈስ ዝምብሎ በሚያየው አባወራ አይረቤ ምግባር መረማመጃነት በመዝለቅ ተረኩ ወንድ የሴት ስራ አይሰራም በሚለው የማህበረሰቡ ነባር እሴት ላይ እየተሳለቀ ታዳምያንም በራሱ እሴት ከንቱነት ላይ እንዲሳለቅ (እንዲዘባበት) ይጋብዛል። የነባሩን ማህበራዊ እሴት ኢ-ተገቢነት እየገለፀም አግባብነት አለው ያለውን "አዲስ" እሴት (የወንድና የሴት የሚልባል ስራ የለምን) የማስረፅ ተግባርን ይጫወታል።

በአጠቃላይ በምዕራፍ አምስት ውስጥ ካደረግነው ቅኝት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከት ወቅት ተረኮች አምስት ዋና ዋና ተግባራት እንዳላቸው ተመልክተናል። ይሁን እና የተረኮቹ ተግባራት በእነዚህ አምስት ተግባራት ብቻ አይወሰንም። ተረኮቹ ከነዚህ ጉልህ ተግባራት በተጨማሪ ሌሎች ጉልህ ሆነው ያልወጡ ተግባራትም አላቸው። በመሆኑም ምዕራፉን ከማጠቃለሌ አስቀድሞ ጉልህ ሆኖ ላልወጡ የተረኮቹ ተግባራት ማሳያ ይሆን ዘንድ ተረኮቹ ባላቸው የፖለቲካ ስርዓትን የማሄስ ተግባር ዙሪያ ቅኝት አደርጋለሁ።

በተራ ቁጥር 35 ስር የቀረበው ተረክ በአጠቃላይ በአፍሪካ ውስጥ የሚታይ ስር የሰደደ ጦርነትን ወይም የእርስ በእርስ ግጭትን፣ እንዲሁም ምዕራባውያን ሀገራት ሁኔታውን በማባባስ ረገድ ያላቸውን ድርሻ ተችቷል። በተረኩ በአውሮፓ ውስጥ የጦር መሳሪያ በአሻንጉሊትነት ተመርቶ ለልጆች መጫወቻነት እንደማይውል ተጠቅሷል። ሆኖም ሆነ ተብሎ አሻንጉሊቱ እየተመረተ ለአፍሪካ ህፃናት እንደሚላክ በተረኩ ተገልጿል። የአውሮፓውያኑን ምግባር በዚህ መልኩ የሚገልፀው ተረክ፣ የምእራባውያኑ የፖለቲካ ስርአት በአፍሪካ ያለውን ችግር በማባባስ ረገድ ያለውን ድርሻ በተጨባጭ የሚገልፅና ሁኔታውን የሚተቸም ነው። በሌላ በኩል ተረኩ አፍሪካን ጠባቂ በሌለው ማሳ እየመሰለ አህጉሪቱ እራሷን ለጦርነት ያጋለጠችበትን ፖለቲካዊ ስርአት አይረቤነት ይሄሳል።

## ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሚደረጉ የስብከት ስርዓቶች ላይ ልዩ ልዩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ይነገራሉ፡፡ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ በባህል ባለቤቶቹ ወይም በቤተ ክርስቲያኗ ማህበረሰብ ዘንድ በጥቅሉ ምሳሌዎች ወይም ታሪኮች በሚል መጠሪያ ይታወቃሉ፡፡ ከዚህ በዘለቀ የባህል ባለቤቶቹ ለቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የሚሰጧቸው አንድ ወጥ ስያሜም ሆነ ተረኮቹን በዝርያ ከፋፍለው የሚለዩበት አንድ አይነት ስርዓት የላቸውም፡፡ ይሁን እና በተረኮቹ የክዋኔ ሂደት ላይ ተራኪውና አድማጩ ማህበረሰብ ከሚፈፅሙት ልዩ ልዩ ምግባራትና በውስጠ ታዋቂነት ከሚያንፀባርቁት አመለካከት በመነሳት ተረኮቹ እውነተኛ እና ፈጠራዊ በሚሉ ሁለት አበይት ክፍሎች ተከፍለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ አካዳሚያዊውን መንገድ በመከተል፣ ትውስታዊ እና ሂሳዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እንዲሁም ተረቶችና ቀልዶች በሚሉ ንኡሳን ክፍሎች ተፈርጀዋል፡፡

እነዚህ ተረኮች፣ ተረኮቹን መተረክንም ሆነ ማድመጥን ዋነኛ ዓላማቸው ያደረጉ ተራቾችና ታዳሚዎች የሏቸውም፡፡ ተረኮቹ በሚከወኑበት ተፈጥሯዊ አውድ ውስጥ በዋናነት በስብከት ስርዓቶች ወቅት የሚነሳ አስተምህሮን ወደታዳምያን ልቡና፣ በቀላሉና በማይረሳ መንገድ ለማስረፅ ይነገራሉ፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የተረኮቹ ክዋኔ፤ የከዋኝና አድማጭ ማንነት፣መስተጋብ፣ በአጠቃላይ ተረኮቹ የሚከወኑበት አውድ ባህርይ ተረኮቹ ተጠቃለው በሚነገሩበት የስብከት ባህርይ ይወሰናል፡፡ በዚህ መሰረት የቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ብቸኛ ከዋኞች አዋቂ ወንድ ሰባክያነ ወንጌል ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አዋቂ ሴቶችን በአውደ ምህረት ላይ እንዳይሰብኩ የሚያግደው ስርዓት ተረኮቹን በተፈጥሯዊ የመከወኛ አውድ ላይ እንዳይከውኑ ያግዳቸዋል፡፡

ከመከወኛ ጊዜና ቦታ አንፃር የአመሻሽ ላይ የአውደ ምህረት ጉባኤዎች የተረኮቹ ዋነኛ መከወኛ አውዶች ሲሆኑ፣ አዋቂ ወንድና ሴት ምዕመናን የአውዶቹ ዋነኛ ታዳሚዎች ናቸው፡፡ ታዳምያኑ በአውዱ በሚኖራቸው ቆይታ፣ በተረኮቹ የክዋኔ ሂደት ላይ ፍዝ ተመልካቾች ሳይሆኑ ንቁ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

የቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ከዋኞች ተረኮቹን የመተረክ ክሂልን በመደበኛ ትምርህት ያገኙ አይደሉም፡፡ ተራኪዎቹ ተረኮቹን ከእናቶችና ከአባቶች ወግ፣ ከመገናኛብዙሃን፣ ከመጽሃፍት ወዘተ. ያገኟቸዋል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች ያገኟቸውን ተረኮች፣ ከዋኞቹ ይዘውት ከተነሱት አስተምህሮ፣ ከምዕመናኑ ማንነትና ከራሳቸው ልምድ ወዘተ. ጋር እያዛመዱ በራሳቸው መንገድ ይተርካሉ፡፡

እነዚህን ከተለያዩ ምንጮች ያገኟቸውን ተረኮች፣ ከዋኞች የዕለት ተዕለት የመግባቢያ ቋንቋን በመጠቀም፤ ነገር ግን ከዕለት ተዕለት የተግባቦት ሂደት የተለየ ደረጃን ሊያስጣቸው በሚችል የአከዋወን ዘዴ (ስልት) ላይ ተመስርተው ይከወናሉ። ከዋኞቹ በዋናነት ተረኮቹን አምስት ያህል ስልቶችን መሰረት አድርገው ይከወናሉ። ከእነዚህ የክዋኔ ስልቶች መካከል አንዱ ከትረካ መስመር መውጣት ነው። ተራኪዎች ስልቱን በመጠቀም ይዘውት ለተነሱት አስተምህሮ አፅንኦት ይሰጣሉ፤ ለምዕመኑ እንግዳ ናቸው ለሚሏቸው ጉዳዮች ማብራሪያ ይሰጣሉ፤ የግል አስተያየቶቻቸውን ይሰነዝራሉ። ድግግሞሽና ወደረኛ ቅንብር ተራኪዎች በክዋኔ ሂደት የተገለገሉባቸው ሌሎች ስልቶች ናቸው። ስልቶቹ ተራኪው ይዞት ለተነሳው ሀሳብ አፅንኦት መስጫነት ከማገልገል ጎን ለጎን አንድ ዓይነት ሆኖ የዘለቀውን የትረካ ድምፀት የመቀየርና ለተረኩ ዜማዊነት የማስገኘት ፋይዳ አላቸው። ከነዚህ ስልቶች ጎን ለጎን፤ ከፍተኛና ዝቅተኛ የድምፅ መጠን፣ አካላዊ እንቅስቃሴና ቆምታ እንደስልት በቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ክዋኔ ወቅት ታይተዋል።

በሌላ በኩል በአብያተ ክርስቲያናት የሚነገሩ ተረኮች ካላቸው ተግባር አንፃር በጥናቱ ሲመዘኑ በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ አምስት ያህል ተግባራት እንዳሏቸው ለማጤን ተችሏል። የቤተ እምነቱን እሴት ለምዕመኑ ማስተማሪያ ሆኖ ማገልገል የተረኮቹ አንዱ ተግባር ሲሆን፣ ከዋኞች በተረኮቹ አማካይነት ጠናኑን መፅሀፍ ቅዱሳዊ ቃል አለዝበውና ለምዕመኑ ገጠመኝ ቅርብ አድርገው ያቀርባሉ። ከማስተማር ተግባር ጎን ለጎን ተረኮቹ ምዕመናን ከቤተ እምነቱ እሴት ስርዓት አፈንግጠው እንዳይወጡ መቆጣጠሪያና መግቺያ ሆነው ያገለግላሉ። የአብያተ ክርስቲያን ምዕመናን እንደሰው ባላቸው አቅም መፍትሄ ሊሰጧቸው ላልቻሏቸው ችግሮቻቸው ወይም ስጋቶቻቸው መልስ ሊሰጥ የሚችል ከነሱ በላይ የሆነ አንድ አካል እንዳለ አምነው እንዲቀበሉ በማድረግ ስነልቡናዊ እፎይታን ማስገኘትም የተረኮቹ ሌላ ተግባር ነው።

በጥናቱ ሂደት ለማየት እንደተቻለው የስብከት ስርዓት ወቅት ተረኮች በሃይማኖታዊ ጉዳይ ዙሪያ ብቻ የተቀነበቡ አይደሉም። ተረኮቹ ከሃይማኖታዊው ቅንብብ ዘልቀው በመውጣት አንድም የተራችና የአድማጩን ማህበረሰብ ማህበራዊ እሴት ተገቢነት ይገልፃሉ። በሌላ በኩልም ተረኮቹ ስህተት ነው ያሉት ማህበራዊ እሴት ላይ ጥያቄ በማንሳት ለውጥን ይሰብካሉ።

በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያናት የሚነገሩ ተረኮች እነዚህን ተግባራት መሰረት አድርገው ቤተ ክርስቲያናት እንደ አንድ ሃይማኖታዊ ተቋም ህልውናዋን ጠብቃ እንድትዘልቅ የራሳቸውን ድርሻ ያበረክታሉ።

## ዋቢ ጽሑፎች

ከዚህ በታች በሀገር ውስጥና በውጭ ቋንቋ የተፃፉ መጻሕፍትና ጥናታዊ ጽሑፎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ ከዝርዝሮቹ ከፊሎቹ በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ በቀጥታ ሀሳብ በመውሰድ የተገለገልኩባቸው ናቸው፡፡ ከፊሎቹ ደግሞ ከጥናታዊ ጽሑፉ ጋር ተዛምዶ ያላቸው በመሆናቸው ቅኝት ያደረኩባቸው ናቸው፡፡


ሀብታሙ ከበደ ፡፡ ቃለ መጠይቅ፡፡ ካሴት ተራ ቁ. 2፣ ገፅ ሀ፣ 29/8/2002 ዓ.ም.፡፡

ሙሉነህ ጉግሳ፡፡ "የክስታኔ ተረቶች"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993 ዓ.ም.፡፡

ሙሉጌታ ነጋሳ፡፡ "በጅባትና ሜጫ አውራጃ የተሰበሰቡ የገበሬ ህይወትን የሚያንፀባርቁ የኦሮምኛ ተረቶች"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1976 ዓ.ም.፡፡

ማንያለው አባተ፡፡ "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው"፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ለኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999 ዓ.ም.፡፡

ሰውነት መኮንን፡፡ "በሞጣ አውራጃ የሚነገሩ የአማርኛ ተረት ተረቶች"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1984 ዓ.ም.፡፡

ሱፋር በድሩ፡፡ "የስልጤ ተረቶች ይዘት ጥናት"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1995 ዓ.ም.፡፡

ቀለመወርቅ ታደሰ ፡፡ ቃለ መጠይቅ፡፡ ካሴት ተራ ቁ. 4፣ ገፅ ለ፣ 16/9/2002 ዓ.ም.፡፡

በዕደማርያም ይትባረክ፡፡ ቃለ መጠይቅ፡፡ ካሴት ተራ ቁ. 2፣ ገፅ ለ፣ 29/8/2002 ዓ.ም.፡፡

ተስፋዬ ሊሞሬ፡፡ "የሀድይኛ ተረታ ተረቶች ይዘት"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993 ዓ.ም.፡፡

ቸሬ አበበ ፡፡ ቃለ መጠይቅ፡፡ ካሴት ተራ ቁ. 3፣ ገፅ ለ፣ 4/9/2002 ዓ.ም.፡፡

አበበ ከበደ፡፡ "በሰላሌ አውራጃ የሚነገሩ የአማርኛ ተረቶች"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1982 ዓ.ም.፡፡

አእምሮ አሰፋ ፡፡ ቃለ መጠይቅ፡፡ ካሴት ተራ ቁ. 1፣ ገፅ ለ፣ 8/8/2002 ዓ.ም.፡፡

አወቀ ውቤ፡፡ "የወላይትኛ ተረቶች"፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1975 ዓ.ም.፡፡

እንግዳ ወልደሰማያት። "በጭላሎ አውራጃ በአማርኛ የሰማኊቸው ተረቶች"። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974 ዓ.ም.።

ዚነት አብዱልረሺድ። "የሐረሪ ተረቶች ስብስብና ትንተና"። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1991 ዓ.ም.።

ደሀብ ተክሉ። "የትግሪኛ ተረቶች"። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974 ዓ.ም.።

ጥሩነህ አበራ። "የበኩቁኒ ኦሮምኛ ተረቶች"። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1982 ዓ.ም.።

የኢትዮጵያ መፅሐፍ ቅዱስ ማኅበር። መጽሐፍ ቅዱስ። ዩናይትድ ባይብል ሶሳይቲ፣ ናይሮቢ፣ 1980 ዓ.ም.።

ያዕቆብ ወልደማርያም። "የከፋ ተረቶች"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974 ዓ.ም.።

ፈቃደ አዘዘ። የስነቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች፣ 1991 ዓ.ም.።

________። "የሥነቃል ትምህርትና ምርምር ፋይዳ በኢትዮጵያ"። The Ethiopian Journal of Education። Vol. XVI፣ No.2፣ 1996 እ.ኤ.አ.፣ ገፅ 54-77።

ፋንታሁን ሙጩ ። ቃለ መጠይቅ። ካሴት ተራ ቁ. 5፣ ገፅ ለ፣ 27/9/2002 ዓ.ም.።

Abdulkadir Haji Jima. "Some Cultural Elements as Reflected in Somali Folktales." M.A. Thesis, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1982.

Abreham Alemu. "Jimma Oromo Oral Prose Narrative: A Preliminary Descriptive Analysis." M.A. Thesis, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 2000.

Bascom, William. "The Forms of Folklore: Prose Narratives." The Journal of American Folklore, Vol.78 No.307 (Jan-Mar., 1965), 3-20; American Folklore Society; http://www.jstor.org/stable/538099

________. "Four Functions of Folklore". In Dundes, A. [Ed.]. The Study of Folklore. Englewood Cliffs, N.J: Prentice-Hall, Inc, 1965, 279-298.

Basgoz, Ilhan. "Digression in Oral Narrative: A Case Study of Individual Remarks by Turkish Romance Tellers". The Journal of American

Folklore, Vol.99, No.391 5-23 (Jan.-mar.,1986) http://www.jstor.org/stable/540851.

Bauman, Richard. "The Filed Study of Folklore in Context". Folklore and Printed Sources (Comp. Fekade Azeze). Undated, pp. 92-99

Bayileyegn Tasew. "Anyuaa Oral Prose Narratives: Ethnic Genres and Social Functions" M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1999.

Ben-Amos, Dan. " 'Context' in Context". Western States Folklore Society, Vol. 52, No. 2/4, (Apr. – Oct., 1993) pp. 209-226 http://www.jstor.org/stable/150087.

Bowman, Marion. "Vernacular Religion and Nature: The 'Bible of the Folk' Tradition in New Found land". Vol.114, No.3, 285-295, Taylor and Francis, Ltd, (Dec., 2003) http://www.jstor.org/ stable/30035119.

Burchfield, R.W. (Ed.) The Oxford English Dictionary (2th ed.). Oxford: Clarendon Press Oxford; 1989.

Danielson, Larry. "Religious Folklore." Readers for EtLi 621:Folklore, (Comp. Fekade Azeze), 2003, pp.407-522.

Dorson, Richard M. (Ed.). Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Dundes, Alan (Ed.). Sacred Narrative: Readings in the Theory of Myth. Berkeley and Los Angeles: University of California Press, 1984.

Finnegan, Ruth. Limba Stories and Story-Telling. United States of America: Oxford University press, 1967.

__________. Oral Literature in Africa. Oxford: Clarendon Press, 1970.

Harry, Show. Dictionary of Literary Terms. New York: McGraw Hill Inc., 1992.

Janson, Wm. Hugh. "Ethics and Folklorist." Folklore and Printed Sources. (Comp. Fekade Azeze). Undated, pp 319-326.

Melakneh Mengstu. "The Major Themes and Motifs of Southern Agew Folktales." M.A. Thesis, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1990.

Okepwho, Isidore. African Oral Literature. Bloomington and Indianapolis: Indiana University Press, 1992.

Oring, Elliot. "Three Functions of Folklore: Traditional Functionalism as Explanation in Folkloristic". The Journal of American Folklore, Vol.89, No.351 (Jan.-mar.,1976) pp.67-80 http://www.jstor.org/stable/539547.

———————. Jokes and their Relations. Lexington: University Press of Kentuky: 1992.

Sahilu Kidane. "Borana Oromo Prose Narratives: A Contextual Study." M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1996.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions. Logan, Utah: Utah State University Press, 2005.

Tesfaye G. Mariam. "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales." M.A. Thesis, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1990.

Vansina, Jan. Oral Tradition as History. Madison, Wisconsin: University of Wisconsin Press, 1985.

Wehmeier, Sally (Ed.) Oxford Advanced Learner's Dictionary (6th Ed). New York: Oxford University Press, 1992.

Yihenew Jembere. "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojam." M.A. Thesis, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1996.

Young, Katharine. "The Notion of Context". Western States Folklore Society, Vol. 44, No. 2 (Apr., 1985) pp. 115-122 http://www.jstor.org/stable/1499556.

## አባሪ አንድ

## የስብስብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የንባብ መምሪያ

የዚህ ጥናት መሰረት የሆኑ ስብስብ ተረኮች በቃል እየተነገሩ ሲደመጡ፤ ከተናጋሪው ልዩ ልዩ አካላዊ እንቅስቃሴና ከድምፀቱ (ከአንድምታው) በመነሳት አድማጭና ተራቹ ያለችግር መግባባት ይችላሉ። ነገር ግን ተረኮቹ ከተፈጥሯዊ አውድ ውጪ በፅሁፍ እንደወረዱ እንዲሰፍሩ ሲደረጉ በአንድ አንድ አጋጣሚ አንባቢው በቀላሉ ሊረዳቸው የሚቸገርባቸው ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። ይህንን ሁኔታ ለማቅለል በየተረኮቹ መሀል ልዩ ልዩ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅሜያለሁ። አንባብያን ስርዓተ ነጥቦቹ ከምን አንፃር እንደገቡ ተረድተው ተረኮቹን ያለችግር ያነቡ ዘንድ ይህ "የስብስብ ተረኮች የንባብ መምሪያ" በጥናቱ እንዲካተት ሆኗል።

1. ‹‹ ›› ይህ የጥቅስ ምልክት የተራኪውን ንግግር ከገፀባህሪው ንግግር ለመለየት የገባ ነው።
2. ? ይህ የጥያቄ ምልክት ተራኪው ጥያቄ አዘል ንግግሮችን በሰነዘረባቸው አረፍተ ነገሮች መጨረሻ ላይ የገባ ነው።
3. ?! እነዚህ የጥያቄና የቃለአጋኖ ምልክቶች በአንድ ላይ ሲመጡ ተራኪው ባነሳው ጥያቄ አዘል መሰል ንግግር ውስጥ የአረጋጋጭነት (assurance) አንድምታ ጎልቶ እንደሚደመጥ ለማመልከት የገባ ነው።
4. ( ) ይህ የቅንፍ ምልክት ተራኪው በትረካ ሂደት ወቅት በግልጽ ያልተናገራቸው፣ ነገር ግን አድማጩ መኖራቸውን ከአጠቃላይ የትረካው አካሄድ የሚገነዘባቸውና ተረኮቹ በፅሁፍ ሲሰፍሩ እነዚህ የተገደፉ ቃላት ወይም ሐረጋት ካልታከሉ አንባቢው ፅሁፉን ለመረዳት አዳጋች ሊሆንበት ወይም የፅሁፉን ስሜት ሊያጣ ይችላል በሚል እኔ፣ ከራሱ ከትረካው ሂደት ካገኘሁት ስሜት በመነሳት፤ ያከልኳቸው ቃላትና ሐረጋት የተጠቃለሉበት ነው።
5. … ይህ ሶስት ነጥብ ተራኪው የተረኩን አንድ ክፍል መናገር ከጀመረ በኋላ በሌላ ሀሳብ ተነጥቆ የጀመረውን አረፍተ ነገር ሳይጨርስ በእንጥልጥል መተዉን ለማመላከት የገባ ነው።
6. [ . . . ][*] ይህ ሶስት ነጥብ ተቀንፎ ሲቀመጥ ተራኪው መናገር የጀመረውን ታሪክ ወደጎን ብሎ (ለጊዜው) በመሀሉ ከተረኩ ጋር ቀጥታ ተዛምዶ የሌለው ሰፊ ሀተታ ማድረጉን ለማመልከት ገብቷል።

---

[*] [ . . . ] ይህ ተራኪው በተረኩ መካከል ከዋናው ተረክ የተለየ ሰፊ ሀተታ ማድረጉን የሚያሳይ ስርዓተ ነጥብ በስብስብ ተረኮቹ መካከል በተደጋጋሚ ሰፍሮ ይገኛል። የዚህ ምክንያት ከምን የመነጨ ነው ለሚለው በምዕራፍ አራት በንኡስ ርእስ 4.4.1. ውስጥ ዝርዝር ማብራሪያ ተሰጥቷል።

7. [ፅሁፍ . . . ] ተቀንፎ የተቀመጠ ሶስት ነጥብ ከፊቱ ማንኛውንም ፅሁፍ ሲያስቀድም ተራኪው መናገር የጀመረውን ከተረኩ ጋር ተዛማጅነት ያለውን ሀሳብ ወደጎን ብሎ በመሀል ከተረኩ ጋር ቀጥታ ተዛምዶ የሌለው ሰፊ ሀተታ ማድረጉን ለማልከት ገብቷል።
8. *[*] በአባሪ ሁለት ውስጥ በተጠቃለሉ ተረኮች መነሻ ላይ የተራኪዎች ማንነት እንዲገለፅ ተደርጓል። ይህ የኮከብ ምልክት ይህን የተራኪውን ማንነት ተክቶ ሲቀመጥ ማንነታቸው በግልጽ እንዳይጠቀስ የፈለጉ አንድ የመረጃ አቀባይን የሚያመላክት ይሆናል።

---

[*] በዚህ የኮከብ ምልክት የተወከሉ የመረጃ አቀባይ አንጋፋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባት ናቸው። እኚህ አባት በልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት የሚያደርጓቸውን ስብከቶች እንድከታተልና መረጃዎችን እንድጠቀም ቢፈቅዱልኝም የሚያደርጉትን ስብከት በመቅረፀ ድምጽ እንዳስቀርም ሆነ ስማቸውን በግልጽ እንድጠቅስ አልፈቀዱልኝም። እኔም ይህን ፈቃዳቸውን አክብሬያለሁ። ከእኚህ አባት ጋር በ11/9/2002 በስራ ቦታቸው በመገኘት ከመቅረፀ ድምጽ ውጪ ባደረግነው ቃለ ምልልስ ይህ አቋማቸው ከምን የመነጨ እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው መልኩ ቃል በቃል አፅፈውኛል።

> የእግዚአብሔርን ቃል ለመናገር በአውደምህረት፣ በምህረት አደባባይ የሚቆም ሰው እራሱን ለእግዚአብሔር ማስረከብ አለበት። ይህንንም ስል በስጋ ህይወቱ በተማረው ትምህርት ላይ ተመርኩዞ፣ በእውቀቱ እየታበየ አውደምህረቱ ላይ እንዳይቆም። እራሱን ባዶ አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት መቆም አለበት። ባዶን የሚሞላ እግዚአብሔር ስለሆነ በእንዲህ አይነት ባዶ ውስጥ ወዲያውኑ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሰው አድሮ እርቦኛል ጠምቶኛል ብሎ በእግዚአብሔር ፊት የቀረበውን ህዝብ ምን መመገብ እንዳለበት (ምን አይነት ትምህርት እንደሚያስፈልገው) የሚያውቀው መንፈስ ቅዱስ በዚህ እራሱን ባዶ ባደረገው ሰውዬ ላይ አድሮ ህዝቡን የሚያንፀውን ትምህርት እንደሚገባው አድርጎ ያስተምራል።
>
> በአውደምህረት ላይ የሚቆም ሰው ምንጊዜም እግዚአብሔር አምላኩን ከፍ አድርጎ እራሱን ዝቅ አድርጎ በትህትና የታነፀ ሰውነት ይዞ መቆም አለበት። እኔ በአደባባይ ቆሜ የማስተምራቸው ቃሎች በሙሉ የእግዚአብሔር ስለሆኑ በዚህ ምክንያት ስሜ አይጠቀስም። እኔ ተናገርኩ ብዬ መናገሬ ውዳሴ ከንቱ ያመጣል፤ ውዳሴ ከንቱ ደግሞ ከሀጢያት የበለጠ ሰው ይጥላል። ሀጢያት በንስሀ ይታደሳል ውዳሴ ከንቱ በንስሀ አይፀዳም። በዚህ ምክንያት ስሜ አይነሳም።

## አባሪ ሁለት

በዚህ አባሪ ስር ከየካቲት 8, 2002 እስከ ግንቦት 16,2002 ድረስ ባሉት አራት ወራት በተደረገ የመስክ ቆይታ የተሰበሰቡ 66 ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተካተዋል፡፡ ተረኮቹ ሲነገሩ በተገኙበት (በተደመጡበት) የጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት የሰፈሩ ሲሆን ለእያንዳንዳቸው ተረኮች፣ ስለተራኪዎቻቸው ማንነት፣ ስለተተረኩበት ጊዜና ቦታ የተሟላ መረጃ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡ ይሁን እና በተረኮቹ መተረቻ ጊዜነት የተቀመጡ ሰዓታት ተረኮቹ የተነገሩባቸው ስብከቶች መሰበክ የጀመሩበትን ጊዜ የሚያመላክቱ እንጂ ተረኮቹ በስብከቶቹ ውስጥ ሲነገሩ የተደመጡበትን እቅጫዊ ሰአት የሚያመላክቱ አለመሆኑን ከወዲሁ ለማሳወቅ እወዳለሁ፡፡

### ተረክ 1

ከመምህር (ዲ/ን) አእምሮ አሰፋ በ20/6/2002 በ11፡30

ቀበና ምስራቀ ፀሐይ መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን

ጠንቋይ ቤት የሚሄዱ ሰዎች… አንድ ጊዜ ሴትየዋ ሁለት ቁና ዱቄት ጠፋባት ሁለት ቁና ምን ጠፋባት? ሁለት ቁና ዱቄት ጠፋባት ከዛ ሁለቱን ቁና ዱቄት የወሰደባትን ሰው እንዲነግራት አራት ቁና ዱቄት ይዛ ሄደች ይባላል፡፡ እዳዋ ጨመረ እንጂ አልቀነሰም፡፡

### ተረክ 2

ከመምህር (ዲ/ን) አእምሮ አሰፋ በ20/6/2002 በ11፡30

ቀበና ምስራቀ ፀሐይ መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን

ሰውየው [እውነትሽን ነው ትዝ አለኝ አንድ ነገር (ለምእመን የተሰነዘ ሀሳብ ነው)] ሰውየው እንዲሁ የዛን ቀን እኮ ነው(የጾም ቀን ለማለት ነው) ሰዎች ሲሰጡት ሲበላ ሲበላ መቼም ፆሙ ሊገባ ስለሆነ ይህን ስጋ መጨረስ አለብኝ ብሎ ተነሳ፡፡ ሰው ቤት ሄዶ ክትፎው ምኑ ቀረበ፡፡[ ምራቃችሁን እንዳትወጡ እሺ. ፆም ነው] ሲበላ አሁን ደግሞ ሴትየዋም ብዙ ነገር ነው መቼም ፆም ሊገባ ስለሆነ ብዙ ስጋ ነው ያለው "ይሄ ማለቅ አለበት ዛሬ" ተባለ ነገ ፆሙ ሊገባ ስለሆነ ዛሬ ማለቅ አለበት ይበላሻል [ሥጋው ይበላሻል ተብሎ ሰው መበላሸት አለበት እንዴ?!] "ይበላሻል መጨረስ አለበት" እያለች ሴትየዋ እያለቃቀሰች ትጨምርለታለች "ይበላሻል አይደል?" እያለ እሱም ይጨምራል፣ ሲጨምር አንገቱ ደረሰ እንግዲህ ጎንበስ ሲል እንዳይፈስበት ቀና አለ፡፡ አሁንም ቀና እንዳለ እዛው ላይ ይጨምራል አሁን ሴትየዋ "እባቴ ከአደረ እኮ ይበላሽብናል ኧረ እባኮትን" አሁንም አንድ አገር ስጋ ስትጨምርለት አሁንም ይበላሻል እያለ ይጨምራል መጨረሻ ላይ ቢለው አላልቅ አለ፡፡ ሊያልቅ ሲል ስትጨምርበት መጨረሻ ላይ አፉ ጋር ደረሰ

ከመጠን በላይ ሆነ መጨረሻ ላይ "ኧረ ይበላሻል ስትላቸው" አይ ልጄ ይበላሻል እያልሽ እኔ ተበላሽቼ ላርፍ ነው" አሏት መጨረሻ ላይ።

## ተረክ 3

ከመምህር (ዲ/ን) አእምሮ አሰፋ በ20/6/2002 በ11:30

ቀበና ምስራቀ ፀሐይ መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን

ሰውየው ነው አሉ [ልንገራችሁ በዚሁ አጋጣሚ ደከማችሁ እንዴ?] ሰውየው ነው አሉ መንገድ ሲሄድ ሲሄድ መሸበት ገጠር አካባቢ መሸቶበት አሳድሩኝ አለ። ባልና ሚስቶች ደግሞ የሳር ቤት ናት ቤታቸው። በዛች ቤት ውስጥ መሀል ላይ የእንጨት ምሰሶ አለበት ቤቷን ቀጥ አድርጎ የያዘ፤ ከዛች ስር ደግሞ እሳት ያነዳሉ ከዛችው ቤታቸው "ቤት የእግዚአብሔር ነው ግባ" አሉና እንግዳውን አስገቡት፤ እራቱን አበሉት በሉ፤ እግሩን አጠቡት አስተናገዱት እና "በል እንግዲህ. . ." [መቼም የገጠር ባህል ምንድነው የምታደርጉት ሲበርዳችሁ? ከተማ ያላችሁ እብድ የሚያክል የደብረብርሃን ብርድልብስ መከናነብ አይደል? በገጠር ውስጥ ግን ብርድልብስ የለም ምን ያደርጋሉ ወደል ወደል የሚያክል ፍልጥ አለ ፈልጠው ያስቀምጣሉ፣ ያነዳሉ] የሚገርማችሁ ከምሰሶዋ ስር እሳት አለ ይነዳል፤ አነደዱና እንግዳውም በዚህ ቁጭ አለ፣ ሚስትም በዚህ ቁጭ አለች፣ ባልም በዛ ቁጭ አለ ። እየሞቁ ነው እየሞቁ ሳለ መቼም ሰይጣን የማይገባበት የለም በባልና ሚስቶቹ መካከል የጠብ እንክርዳድ ዘራ፤ ሰይጣን። ከዛ እንግዳው እያለ ተጣሉ አንድ አንድ ሲነጋገሩ ቃላት ሲወራወሩ ባል መቼም ወንድ ነውና ፍልጥ አንስቶ "በዚህ ነው ጭንቅላትሽን የምልሽ" ይላታል። ሚስትም "እስቲ ወንድ ነህ እኔም አልልህም"አለች እሷም ፍልጧን መዘዘች። እንግዳው ብቻ ቀረ እሱም በዛው በኩል እብድ የሚያክል ፍልጥ መዘዘ ሶስቱም ፍልጥ ያዙ። ባልየው ገረመውና "አንተ፣ እኔ እና እሷ ባልና ሚስት ነን ሁልጊዜም እንጣላለን እንታረቃለን። አብረን ነው የምንኖረው። አንተ ለዛሬ አሳድሩኝ ብለህ መጥተህ ፍልጥ ማንሳትህ ምንድነው? ኧረ ምን ፈልገኽ ነው?" አለው "የቤቱ አመል መስሎኝ ነው!" አለው።

## ተረክ 4

ከመምህር ብርሃን አንለይ በ22/6/2002 በ11:30

በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል

አዛውንቷ እግዚአብሔርን አንድ ፀሎት ስትፀልይ ሁልጊዜ ትጠይቀው ነበር። በእድሜዋ የእድሜ ጣራ ላይ የደረሰች ሰባ ሰማንያ አካባቢ ይሆናታል። ነገር ግን ሁልጊዜ ፀሎቷን ስትጀምርም ሆነ ስትጨርስ ወደ እግዚአብሔር የምታመለክተው ነገር አለ "እባክህ አምላኬ በበጋ አትውሰደኝ ትለዋለች" መቼ አትውሰደኝ? በበጋ አትውሰደኝ። በጋ ሲመጣ እንዲህ ትላለች። የበጋው ወራት ሲያልፍ ደግሞ "እባክህ አምላኬ በክረምት አትውሰደኝ ትላለች።" እንዲህ እያለች ሰማንያ አመት

ሞላት መጨረሻ ላይ ከእለታት አንድ ቀን እራሱ ክርስቶስ ተገለጠ ምን አላት "መቼ እንድወስድሽ ነው የምትፈልጊው?" አላት፡፡ መቼ ትል ይመስላችኋል? "እንግዲህ በበጋ አትውሰደኝ በበጋ ይቺ ባልቴት ፀሀይ አስበላችን ብሎ ሰው እንዳያመናጭቀኝ" ከሞተች በኋላ ስለሰው እኮ ነው የምትጨነቀው፡፡ "ይቺ ባልቴት እንዲህ አድርጋ በፀሀይ አስበላችን እንዳይል በክረምት አትውሰደኝ በጭቃው በዝናቡ በውጣ ውረዱ ሰው ይቺ ባልቴት እንደው ሀጢአተኛ ናት ብሎ እንዳይለኝ በክረምትም በበጋም አትውሰደኝ?" [ታዲያ መቼ ይውሰዳት ሁለቱንም አትውሰደኝ ብላለች መቼ እንዲወስዳት ፈልጋ ነው፡፡] ተገለጠና መድኃኒዓለም ክርስቶስ "መቼ አንድወስድሽ ነው የምትፈልጊው?" ብሎ ጠየቃት መልሷ ምንድነው? አዎ "ምናለ እኔን እስከመጨረሻው ብትረሳኝስ" ነው ያለችው፡፡

## ተረክ 5

ከመምህር መጋቤ ሀዲስ ቀለመወርቅ ታደሰ በ26/6/2002 5፡15 ጥዋት
በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ
አረጋዊ ካቴድራል

አንድ የሰባ አመት ሽማግሌ ነበር፡፡ አንድ ቀን መሸበትና አውሬ ከሚበላኝ ወይም ዱርዬ ከሚቀጠቅጠኝ ለምን ፤ ለምን ከሰው ቤት አልጠጋም አለና በር አንኳኳ፡፡ እንግዳ መቀበል የሚወድ፣ እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ተቀበለው፡፡ በስርአት አስተናገደው፡፡ እራት ከተበላ በኋላ ያም እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ለዚህ ሽማግሌ ስለ እግዚአብሔር ማዳን ስለቸርነቱ ያወጋው ነበር፡፡ እግዚአብሔር የሚለውን ድምጽ ሲሰማ ሽማግሌው ደነገጠ የሰባ አመት ሽማግሌ ነው፡፡ በጣም ደነገጠ የእግዚአብሔር ስም ሲጠራ ግራ ገባው፡፡ "እኔ እኮ፣ እኔ እኮ በእግዚአብሔር መኖር አላምንም!" አለ፡፡ ሽማግሌው የሰባ ዓመት ሽማግሌ ነው "በእግዚአብሔር አላምንም! እግዚአብሔር መኖሩን አላውቅም!" አለ፡፡ ደነገጠ "አንተ የሰባ አመት ሽማግሌ ሆነህ እስከአሁን እግዚአብሔርን የማታውቅ በል ውጣልኝ" ብሎ ከቤቱ አባረረው፡፡ መልካም ነገር የሰራ መስሎት ደስ (አለው)፡፡ (ያ ሰው) ፀሎት ቤት ገብቶ "እግዚአብሔር ሆይ የአንተ ባሪያ የአንተ አገልጋይ! አንተን የማይወድ ሰው ቤቴ ውስጥ ቢመጣ አባረርኩት"[አንድ አንድ ጊዜ አንዳንዶቻችን ስለ እግዚአብሔር ብለን እንጣላለን፡፡ ስለ እግዚአብሔር ብለን እንሳደባለን፡፡ ሰዎችን መጥላት ተገቢ አይደለም ስህተታቸውን ነው መጥላት፡፡ ስህተታቸውን ነው ልንጠላ የሚያስፈልገው ክርስቲያኖች እኛ] "እኔ ያንተ ባሪያ አባረርኩት እኮ" አለው፡፡ እግዚአብሔርም "እኔ ሰባ አመት ሙሉ የታገስኩትን አንተ አንድ ቀን መታገስ አቃተህ?! እኔ ሰባ አመት የተሸከምኩትን አንተ ለአንድ ቀንና ሌሊት መታገስ አቃተህ?!" አለው፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## ተረክ 6

ከመምህር ላዕከ ወንጌል በዕደማርያም ይትባረክ በ26/6/02 በ11.30
በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና
አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

ሌሊት ነው ሁለት አህዮች መንገድ ላይ ቆመዋል፡፡ አንዷ አህያ ፊቷን ወደዚህ አዙራ (ቀኙን እያመላከተ) ወደዚህ ትሄዳለች፡፡ አንዷ አህያ ፊቷን ወደዚህ አዙሯ (ግራውን እያመላከተ) ትሄዳለች፡፡ ጅቡ እርቦታል መሀል ላይ ቆሞ ሁለቱንም አህዮች በአይኑ ቃኛቸው፡፡ "ዛሬ በጣም እርቦኛል ግን አጋጥሞኛል፡፡ ሁለት አህዮች አጋጥመውኛል ግን" አለ "የትኛዋን ልብላ ይቺኛዋን ልብላ ወይስ ይቺኛዋን" ይቺንም ያያል ይቺንም ያያል፡፡ "ቆይ እስቲ ለማንኛውም ይቺኛዋን ልሞክር" አለና ወደዚህችኛዋ አህያ ትንሽ እንደሄደ "አይ! አይ! አይ! ይቺኛዋ ታመልጠኛለች" አለ፡፡ አሁንም ወደዚህችኛዋ አህያ ትንሽ እንደሄደ "አይ! አይ! አይ! ይቺኛዋ ታመልጠኛለች" አለ፡፡ አንድ ጊዜ ወደዚህችኛዋ አህያ አንድ ጊዜ ወደዚህችኛዋ አህያ ሲሄድ የአህዮቹ ባለቤት መጥቶ ጅቡን ቀጥቅጦ ገደለው፡፡ ለምን ሁለት ልብ ስለሆነ፡፡

## ተረክ 7

ከመምህር ላዕከ ወንጌል በዕደማርያም ይትባረክ በ26/6/02 በ11.30
በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና
አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

አንድ በድንግልና ፀንቶ የሚኖር ሰው ነበር፡፡ ከእለታት በአንድ ቀን ከሚፀልይበት በአት ወጣና ከባድ ፈተና ገጠመው፡፡ አንዲት ሴት አገኘችውና "አንተ ሰው" አለችው "አቤት" ሶስት ነገር አቀረበችለት፡፡ አንድ፤ አንድ ጠርሙስ አረቂ፡፡ ሁለት ህጻን ልጅ መናገር የሚችል፡፡ ሶስት በጣም የተሣለ ሠይፍ የሚያሥፈራ፡፡ ሶስቱን አቅርባ "አንተ ሰው" አለችው "አቤት" "ወይ ይሄንን አንድ ጠርሙስ አረቂ ጠጥተህ ጨርስ፤ ወይ በዚህ ሰይፍ የዚህን ህፃን አንገት ቁረጥ፤ ወይ ከእኔ ጋር ግንኙነት ፈጽም" አለችው፡፡ አስተውሉ ሶስቱም ኃጢአት ነው፡፡ የቱን ይፈጽም! ይሄ ሰው ጨነቀው፡፡ "አይ ዛሬ እንደው ከምፀልይበት በአት ባልወጣሁ አ. . .ዬ! ምን አይነት ፈተና ገጠመኝ" አለ፡፡ አዘነ፣ አሰበ፣ አሰበ አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ ለማንኛውም እስቲ ይሄንን አንድ ጠርሙስ አረቂ ቀስ እያልኩ ልጨርሰው ከዛ እራሴን ለማሸነፍ እሞክራለሁ" (አለና) ያን አንድ ጠርሙስ አረቂ ቀስ እያለ ሲጠጣ ይጨርሰዋል ይሰክራል፡፡ እራሱን መቆጣጠር ያቅተዋል፡፡ ከሴትየዋ ጋር ግንኙነት ይፈጽማል፡፡ ወዲያው ያንን ህፃን ልጅ ይናገርብኛል ብሎ በዚያ በሰይፍ አንገቱን ቆረጠው ይባላል፡፡

## ተረክ 11

ከመምህር ሊቀ ማእማራን ፋንታሁን ሙጬ በ28/6/02 በ1:30

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና

አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

እንዲሁ በአለማዊ ኑሮ ውስጥ የነበሩ ሁለት ወጣቶች የቤተክርስቲያኑ አገልግሎት ደስ ያሰኛቸውና ወደ ቤተክርስቲያን ይመጣሉ፡፡ በአጋጣሚ ፆመ እየሱስ ይደርሳል፡፡ ንስሀ አባት ይዘዋልና "አባቴ ልንፆም ፈልገን ነበር እንፁም" አሏቸው፡፡ "እሰየው ልጆቼ ፁሙ ነገር ግን የወጣት የጀማሪ ፆም ሌላ ነው ደግሞ የዛሬ አመት ስትደርሱ ከፍ ታደርጋላችሁ፣ ደግሞ ስትሄዱ ደግሞ እንደገና እየጨመራችሁ ትሄዳላችሁ፡፡ የመጀመሪያው ፆማችሁ እስከ ስድስት ሰአት ቢሆንስ" አሏቸው፡፡ "ኧረ እኛ እስከዘጠኝ ሰአትም እንፆማለን ግዴለም አባታችን ድሮም እኮ ቢሆን ስናገኝ እንበላለን ሳናገኝ ጦማችንን እናድራለን፡፡" [ያኔ መቼም ረሀብ የሚመጣው መፆም ሲጀመር ነው] "ግዴለም ልጆቼ እስቲ እስከ ስድስት ጀምሩት" አሏቸውና "እስቲ እንጀምር እኛ ግን እስከዘጠኝ እናደርገዋለን እስከቅዳሴ መውጫ" ብለው ይጀምራሉ፡፡ ገና ፆሙ ሰኞ ነው እንግዲህ የሚጀምረው እሁድ በጣም ተበልቷል አላለቀም፡፡ ከዛ በጠዋት ያስነሳቸዋል ያ አጅሬ አለ አይደለም? እስከ ሁለት እሰከ ሶስት ሰአት ያስተኛ የነበረው፣ ፆም መጣ ቀደም አድርጎ ይሄዳል (ሊያስነሳቸው)፡፡ ቢያዩት ሰአቱ አይሄድም ሆድ ውስጥ የሚጮኸው ሌላ ነው "ዱዱ ዱዱ" ይላል፡፡ "አንተ ስድስት ሠዓት አልደረሰም" "ኧረ ገና ነው ባክህ" "ታዲያ ምን ይሻለናል?" "እኔ እንጃ!"፡፡ ሲሉ ሲሉ ሶስት ሰዓት አስጠጉት "ሰዓት ስንት ሆነ?" "ሶስት ሰዓት" "እንግዲያ የአንተ ሶስት ሰዓት የእኔ ሶስት ሰዓት ሲደመር ስድስት ሰዓት ነው ሁለታንም አብረን እንብላ" (ሳቅ)

## ተረክ 12

* በ29/6/02 በ11፡.30

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ

ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

ሰውየው እናቱ ሞተው የቤተክርስቲያን መጎናጸፊያ ተደርቦላቸው እየተለቀሰ ሲሄዱ ምን እያለ ያለቅሳል "ተመለሽ ቢሏት ይቺ ሰው መቼ ተመልሳ

ኧረ ኮርታለች እሷ የሰው ጃኖ ለብሳ" አለ አስከሬኑን ሲሸኝ፡፡

## ተረክ 13

* በ29/6/02 በ11፡.30

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ

ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

አንድ ሰው ክፉ ሲሰራ ባልእንጀራው ማን ነው ይባላል፡፡ አንድ ባልንጀራ ይላሉ "የአንተ እከሌ አንተ ጠባዩን ታውቃለህ እንዴ ምን ይመስላል ጠባዩ?" ብለው ጠየቁት ይላሉ፡፡ ሲጠይቁት "ጫካ

## ተረክ 11

ከመምህር ሊቀ ማእማራን ፋንታሁን ሙጬ በ28/6/02 በ1:30

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና

አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

እንዲሁ በአለማዊ ኑሮ ውስጥ የነበሩ ሁለት ወጣቶች የቤተክርስቲያኑ አገልግሎት ደስ ያሰኛቸውና ወደ ቤተክርስቲያን ይመጣሉ፡፡ በአጋጣሚ ፆመ እየሱስ ይደርሳል፡፡ ንስሀ አባት ይዘዋልና "አባቴ ልንፆም ፈልገን ነበር እንፁም" አሏቸው፡፡ "እሰየው ልጆቼ ፁሙ ነገር ግን የወጣት የጀማሪ ፆም ሌላ ነው ደግሞ የዛሬ አመት ስትደርሱ ከፍ ታደርጋላችሁ፣ ደግሞ ስትሄዱ ደግሞ እንደገና እየጨመራችሁ ትሄዳላችሁ፡፡ የመጀመሪያው ፆማችሁ እስከ ስድስት ሰአት ቢሆንስ" አሏቸው፡፡ "እረ እኛ እስከዘጠኝ ሰአትም እንፆማለን ግዴለም አባታችን ድሮም እኮ ቢሆን ስናገኝ እንበላለን ሳናገኝ ጦማችንን እናድራለን፡፡" [ያኔ መቼም ረሀብ የሚመጣው መፆም ሲጀመር ነው] "ግዴለም ልጆቼ እስቲ እስከ ስድስት ጀምሩት" አሏቸውና "እስቲ እንጀምር እኛ ግን እስከዘጠኝ እናደርገዋለን እስከቅዳሴ መውጫ" ብለው ይጀምራሉ፡፡ ገና ፆሙ ሰኞ ነው እንግዲህ የሚጀምረው እሁድ በጣም ተበልቷል አላለቀም፡፡ ከዛ በጠዋት ያስነሳቸዋል ያ አጅሬ አለ አይደለም? እስከ ሁለት እስከ ሶስት ሰአት ያስተኛ የነበረው፣ ፆም መጣ ቀደም አድርጎ ይሄዳል (ሊያስነሳቸው)፡፡ ቢያዩት ሰአቱ አይሄድም ሆድ ውስጥ የሚጮኸው ሌላ ነው "ዱዱ ዱዱ" ይላል፡፡ "አንተ ስድስት ሠዓት አልደረሰም" "እረ ገና ነው ባክህ" "ታዲያ ምን ይሻለናል?" "እኔ እንጃ!"፡፡ ሲሉ ሲሉ ሶስት ሰዓት አስጠጉት "ሰዓት ስንት ሆነ?" "ሶስት ሰዓት" "እንግዲያ የአንተ ሶስት ሰዓት የእኔ ሶስት ሰዓት ሲደመር ስድስት ሰዓት ነው ሁለታንም አብረን እንብላ" (ሳቅ)

## ተረክ 12

* በ29/6/02 በ11፡.30

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ

ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

ሰውየው እናቱ ሞተው የቤተክርስቲያን መኅናጸፊያ ተደርቦላቸው እየተለቀሰ ሲሄዱ ምን እያለ ያለቅሳል "ተመለሽ ቢሏት ይቺ ሰው መቼ ተመልሳ

እረ ኮርታለች እሷ የሰው ጃኖ ለብሳ" አለ አስከሬኑን ሲሸኝ፡፡

## ተረክ 13

* በ29/6/02 በ11፡.30

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ

ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

አንድ ሰው ክፉ ሲሰራ ባልእንጀራው ማን ነው ይባላል፡፡ አንድ ባልንጀራ ይላሉ "የአንተ እከሌ አንተ ጠባዩን ታውቃለህ እንዴ ምን ይመስላል ጠባዩ?" ብለው ጠየቁት ይላሉ፡፡ ሲጠይቁት "ጫካ

ሲወርድ አፋፍ ወርደህ ጠብቀው ይዞ የሚመጣውን እንጨት ተመልከተው አሉ ይባላል፡፡ [እየሰማችሁኝ ነው ከእኔ ጋር ናችሁ?] ይህ ሰው እጫካ ወርዶ ይዞ የሚመጣውን እንጨት እየው አመሉን ለማወቅ አሉ ይባላል፡፡ [ምን ለማለት ነው ንገሩኝ እስቲ የገባው?] እጫካ ወርዶ ጠማማውን ይዞ ከመጣ ምንድነው ማለት ነው ሰውየው? (ሳቅ) መለል መለል ያለውን ይዞ ከመጣ ምንድነው ማለት ነው? (ሳቅ) ይኸውልህ ጠማማውን ይዞ ከመጣ አመለ ብልሹ ነው እንደማለት፡፡

## ተረክ 14

* በ29/6/02 በ11፡30

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ

ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

ያልሰባ በሬ ገበያ ይዞ ይወጣል? ይወጣል? ነግሬያችኋለሁ ከአሁን በፊት (ተረቱን ለማለት ነው) በሬውን ጭድ አብልቶ ቸግሮት ሲያርስ ክስት ብሎብታል ለበሬው ጨው አርከፈከፈና ጭድ ሰጠው፡፡ እንኳን ጨው ተጨምሮበት፣ ያን አገኘ ያ በሬ አጋበሰ አጋበሰ፤ እንደገና ጨው ጨመረና ሰጠው ያን ጠጣና ጥርዝ አለ ያ በሬ፡፡ ያንን ገበያ ነድቶት ወጣ፡፡ ሆዱ መቼም ነጋሪት አክሏል፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ ገበያ ወጣና ገበሬዎች መሀል ከገበያ ቀየጠና ፈንጠር ብሎ ያያል (የበሬው ባለቤት)፡፡ አሁን አንድ ሰውዬ ሆዱ ተነርቶ ሲያይ (የበሬው) "እንዴ ይህንንማ መግዛት አለብኝ" ብሎ ጠጋ ብሎ ፍርምባውን ቢያይ ምንም የለም ከኋላው ያለውን አለና፤ ታላቅ ነው ታናሽ ነው የሚባለው? ዞሮ ቢያይ ምንም የለም፡፡ ሻኛው ጋ ሲያይ ይቺን ነው (እጃቸውን አኮስሰው በመጨበጥ እያሳዩ) የምታክለው በኋላ "ኧረ" አለ አወቀና በቀጭን ዘንግ በሬውን ጠንቆሎ (ሆዱን የመንካት ምልክት እያሳዩ) "ባለጭድ አለው?" ሆዱን ነካ፣ ነካ እያደረገ "ባለጭድ" አለ ባለቤት እንደሆነ "ለጠንቋይ አይሸጥም" (አለ)፡፡

## ተረክ 15

መምህር (ዲ/ን) አእምሮ አሰፋ በ2/7/2002 በ12፡00

በቦሌ ደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን

በአንድ ወቅት ልጅቷ ውጪ ሀገር ትኖራለች [የት ትኖራለች? ... ለገንዘብ ተብሎ እንጂ እግዚአብሔር ተፈልጎ ውጪ ሀገር እንደማይኬድ ታውቃላችሁ! ዛሬማ ተረቱ ምንድነው ዙሮ ዙሮ ከቤት ኑሮ ኑሮ ምንድነው የሚባለው እ. . . ከሞት አይደለም የሚባለው እሱ ተለውጦ ዛሬማ ኑሮ ኑሮ ከሞት ዞሮ ዞሮ ከአሜሪካ አይቀርም ተብሏል፣ ተለውጧል፡፡. . .] ውጪ ሀገር ትሄዳለች ልጅቷ፡፡ ምን ፈልጋ? ገንዘብ! እናት፤ ኢትዮጵያ ምድር ቀየች እሷ ከሄደችበት ሰዓት ጀምሮ ብቻቸውን የዚህች ልጅ እናት እቤት ውስጥ ሲኖሩ አንድም ሰው ገብቶ "እንዴት ሆኑ?!

አይዞት” ብሎ ያፅናና ሰው አልነበረም ለካስ እኚህ እናት አንዲት ብቻ ስትወጣና ስትገባ የሚበሉትን የሚጠጡትን እያዘጋጀች የምትሰጥ አይዞሽ እማዬ ብላ የምታንተርስ አይዞሽ እማዬ ብላ የምታጎርስ (አንዲት ልጅ ብቻ ነበረች ያለቻቸው) ለገንዘብ ስትል ወደ ውጪ ሄዳለች፡፡ ከብዙ አመታት በኋላ ስትመጣ የሚገርመው የሰው ልጅ በረሀብ አይሞትም [እግዚአብሔር ሙት ካላለው የሰው ልጅ አይሞትም፡፡ እመንገድ ላይ ያም እያደሩ የሚኖሩ ሰዎች አሉ አይደል እንዴ? ደግሞ እንደልባቸው እየበሉ የሚሞቱ አሉ፡፡] ስለዚህ ያም እያደሩ እናቷ ልጅቷ እስክትመጣ ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን ሰውነታቸው ተጎሳቅሏል ተርበዋል እና ተጠምተዋል እና ከስተው ሰውነታቸው ደርቆ አጥንታቸው ብቻ ቀርቶ ሥጋቸውና አጥንታቸው ተጣብቆ ተጎሳቁለው በቃ ስትመለስ አገኘቻቸው፡፡ እናቷን “እማዬ እንደዚህ ተጎዳሽ ወይ እናቴ ሆይ! ስለዚህ ወደልብስ መሸጫ ሱቅ ልውሰድሽና ባይሆን የድሮ መልክሽን ማምጣት መለወጥ ባልችል ልብስ ገዝቼልሽ ላሳምርሽ፣ በልብስ ላሽቆጥቁጥሽ በልብስ ላስጊጥሽ” አለችና እናትዋን ይዛ ከውጭ ሀገር የመጣችው ልጅ ወደሱቅ ሄደች፡፡ እዛ የልብስ መሸጫ ሱቅ በር ላይ ደግሞ ይሄንን የቤተክርስቲያን በር የሚያክል ትልቅ መስታወት ቁሟል፡፡ እኚህ እናት የፊት መስታወት እንኳን አይተው አያውቁም እንኳን የቁም መስታወት፡፡ በዚህ ሰአት ያንን መስታወት ሲመለከቱ ከእግራቸው ጥፍር እስከ እራሳቸው ፀጉር የራሳቸውን መልክ ተመለከቱ ይላል፡፡ መልካቸውን ባዩ ጊዜ እኚህ እናት ገረማቸው፡፡ አዩ አዩ እና መጨረሻ ላይ “ልጄ” አሉ እኚህ እናት “አቤት እማዬ” “ይህቺ አስቀያሚ ሴትዮ የማን ናት” አሉ ይባላል፡፡ [ማንን ነው ያሉት እራሳቸውን ነዋ!] “ይቺ አስቀያሚ ሴት የማናት” ሲሉ ልጅቷ ደግሞ “እማዬ አንቺ እኮ ነሽ” አለቻቸው ይባላል፡፡ [... ] (በኋላ)”ምነው እማዬ ዝም አልሽ ደነገጥሽ ወይ” ብትላቸው “አይ ልጄ እኔ ዝም ያልኩት የራሴን መልክ ካየሁ በኋላ ታዘብኩትና ከሁሉም በላይ የደነቀኝና ዝም ያስኘኝ ነገር ቢኖር አባትሽ እኔን አግብቶ መኖሩ ነው አሉ ይባላል፡፡

## ተረክ 16

መምህር (ዲ/ን) አእምሮ አሰፋ በ2/7/2002 በ12፡00

በቦሌ ደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን

በጫካ ውስጥ የሚኖሩ እንሰሳት የጦጣ ማሂበርና የጅንጀሮ ማሂበር አለ፡፡ ጦጣ ዛፍ ላይ ሆኖ ጅንጀሮዎችን ዘቅዝቃ፣ ትመለከት ነበር፡፡ ዝንጀሮ አንዱ የአንዱን ቂጥ እያየ ይስቃል፡፡ መላጣ ስለሆነ ማለት ነው፡፡ ጦጣ ደግሞ ታዘበችና ዛፍ ላይ ሆና “ዝምበይ እየአንዳንድሽ ባታይው ነው እንጂ ሁልህሽም ሙሽልቅ ነህ(ሽ)” አለች አሉ፡፡

## ተረክ 17

ከመምህር መጋቤ ሀዲስ ቀለመወርቅ ታደሰ በ3/7/2002 5፡45 ጥዋት
በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ
አረጋዊ ካቴድራል

ሰውየው በባህር ላይ መዝናናት ፈለገና ጀልባ ተከራይቶ መንዝ ጀመረ፡፡ ቀዛፊውም እየቀዘፈ ይጓዟሉ፡፡ ማዕከለ ባህር ሲደርሱ ቀና ብሎ ሲመለከት ከዋክብትን አየ "አንተ ቀዛፊ፤ አንተ ባለጀልባ ስለክዋክብት ተምረሀል" አለው፡፡ "አይ ጌታዬ" (አለ) ይህ ሰው ደነገጠ ይሄንን ሲሰማ እንኳን ሊማር ቀርቶ ስያሜውንም በራሱ አያውቀውም "ጌታዬ እኔ የማውቀው ጀልባ መቅዘፍ ብቻ ነው ከዚህ በቀር ሌላ ሞያ የለኝም አላውቅም" አለ፡፡ ትንሽ እራቅ እንዳለ ደግሞ አሁንም በባህር አካባቢ ያሉ እፅዋትን ተመለከተና መጀመሪያ ስለ ከዋክብት ተምረሀል ሲለው አላውቅም ሲለው በቃ ከህይወትህ እሩቡን ያህል አጥተሀል! ጥቂት እንደተጓዘ በባህር አካባቢ ያለውን እፅዋት ተመለከተና "አንተ ሰው ስለ ስነእፅዋት ተምረሀል ስለአበቦች የምታውቀው ነገር አለ?" አለው "ጌታዬ ነገርኮት እኮ እኔ የማውቀው ጀልባ መቅዘፍ ብቻ ነው ከዚህ በቀር የማውቀው አንዳች ነገር የለም" አለ "አሁንም ከህይወትህ ሌላ እሩቡን ያልህ አጥንተሃል" አለው፡፡ ጥቂት እንደተጓዙ ማዕበል ተነሳ ታንኳዋ መስጠም ጀመረች፡፡ ውሀው ከታንኳዋ ላይ ሲሞላ ባለ ጀልባው ዞር ብሎ ምሁሩን ሲመለከት ውሀ በአፉ በአፍንጫው እየገባ እየተፋ ነው "ጌታዬ ውሀ ዋና ያውቃሉ? ውሀ ዋና ያውቃሉ?" አለው፡፡ "አይ አላውቅም እኔ የተማርኩት ሌላ ነው ውሀ ዋና አላውቅም?" አለው "ከአሁኑ ሰአት ጀምሮ ሙሉ ህይወቶን አጥተዋል" አለና እየዋኘ እየዋኘ እሱ ተሻገረ ሰውየው ግን ምሁር ነኝ የሚለው ሰጥሞ ቀረ፡፡

## ተረክ 18

ከመምህር መጋቤ ሀዲስ ቀለመወርቅ ታደሰ በ3/7/2002 5፡45 ጥዋት
በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ
አረጋዊ ካቴድራል

ምስካየህዙናን ቤተክርስቲያን ተሳልሜ ስወጣ በእድሜ ገፋ ያሉ ሽበት የቀላቀለባቸው አንድ ታላቅ አባት እንባ ይተናነቃቸው ነበር በሩ ላይ፡፡ አሳዘኑኝና "ምነው አባቴ አልኳቸው?" ጠጋ ብዬ "ልጄ ከውጪ ሀገር ተሰዳ ትኖር ነበር" አሉኝ ነገር ግን ይህቺ ልጅ እግዚአብሔርን ይዛ ነበር የተሰደደችው [ወገኖቻችሁ ብቻቸውን እንዲሰደዱ አትምከሯቸው እግዚአብሔርን ይዘው እንዲሰደዱ አስተምሯቸው፡፡ እግዚአብሔርን ይዞ ያልተሰደደ ክርስቲያን ቢሰደድም አያምርበትም ኑሮው አይስተካከልም፤ መንገዱ ሁሉ በእሾህ የታጠረ ይሆናል፡፡] ይህቺ ሴት እግዚአብሔርን ይዛ ነው ለካ የተሰደደችው የቅድስት አርሴማ የገድሏን መፅሐፍና የቅዱስ ጎርጎሪዮስን ፀበሉን

እና እመቱን ይዞ ወደ አህዛብ አገር ተሰደደች፡፡ በአህዛብ ሀገር ስትሰራ ጠዋት ከእንቅልፏ ስትነሳ ትፀልያለች፡፡ እጆቿን ለፀሎት ትዘረጋለች፡፡ ውዳሴ ማርያም ታደርሳለች፤ ትሰግዳለች፤ የቅድስት አርሴማን የገድሏን መፅሐፍ ታነባለች፣ ውሀ በጠርሙስ አስቀምጣ ከፊት ለፊት ላይ ማለት ነው የቅድስት አርሴማን መጽሐፍ ታነባለች ስትጨርስ ግማሹን ትጠጣለች ግማሹን ደግሞ ትጠመቅበታለች በዛ ቤት ፀሎት ሲደረግ እግዚአብሔር ሲመለክ፣ የቅዱሳን ስም ሲጠራ ዘንዶው ተቆጣ፡፡ በዛች ላይ (በልጅቷ አሰሪ ላይ ለማለት ነው) ያደረ እርኩስ መንፈስ በልጅቷ ላይ ክፉ የሞት እርምጃ እንድትወስድ አሳሰባት፡፡ ክፉኛ የሆነ ጭካኔ በልጅቷ ላይ እንድትፈጽም በሷ ላይ ያደረው እርኩስ መንፈስ ሴትየዋን፣ ያቺን አህዛባዊት ሴት አሳሰባት፡፡ ለካስ በመስታወት ሆና ትመለከታት ነበር ስትፀልይ፣ ስትዘምር፣ ስትሰግድ ለአምልኮት እጆቿን ስትዘረጋ ስዕለ ማርያምን ከጎኗ አስቀምጣ ስትሰግድ ስትንበረከክ ታያት ነበር፡፡ ብልጭ አለባት፣ አልቻለችም፡፡ ሰይፍ ይዛ ልታርዳት መጣች "አንቺ ሴት ከአሁን ሰዓት ጀምሮ ቤቴ ውስጥ የምትፈጽሚውን አምልኮት ታቆሚያለሽ የማታቆሚ ከሆነ አንገትሽን በሰይፍ አርድሻለሁ" ብላ ዝታባት ሄደች፡፡ [ምን ማድረግ ነበረባት አሁን ይህቺ ሴት እንደሰው ሠውኛው እኔ የመጣሁት ኑሮን ለማሸነፍ ችግሬን ለመቅረፍ ቤተሰብ ለመርዳት ነው፡፡ ሁኔታዎች እስኪመቻቹ ድረስ አንገቴን ደፍቼ አኖራለሁ እውነቱን ሀሰት፤ ሀሰቱን እውነት ብዬ ልኑር እኔ ወደ ሀገሬ መግባት እፈልጋለሁ ገንዘብ ሽክፌ ማለት ነበረባት ግን በፍጹም አላደረገችውም] "ከሃይማኖቴ የሚበልጥ አንዳች ነገር የለም አለች" በቃ "ከእምነቴ የሚበልጥ አንዳች ነገር የለም" የአባቶቿን ታሪክ አስታወሰች፡፡ አባቶቻችን ለሃይማኖት ሲሉ መስዋዕትነት እንደከፈሉ፣ ዋጋ እንደከፈሉ፣ እራሳቸውን ትተው ሃይማኖታቸውን እንደወደዱ፣ ለሃይማኖታቸው ሲሉ ህይወታቸውን እንዳጡ፣ እነሱ እየቆሰሉ ለአለም ፈውስ እንደሆኑ፣ እነሱ እንደሰም እየቀለጡ ለአለም ብርሃን እንደሆኑ እራሳቸውን እየጎዱ ሌላውን እንደጠቀሙ የአባቶቿን ታሪክ በአይነህሊናዋ ተመለከተችው ያኔ አስታወሰች፡፡ "ስለዚህ እኔ የአባቶቼን ፅዋ እጎነጫለሁ እዚህ ጋር እኔ ደሜ ቢፈስ ብሞት ለክርስቲያኖች ታሪክ! ነው ድል ነው! ማተቤን አልበጥስም ከአምልኮቴ አልለይም! ከሃይማኖቴ አልለይም! ለፈጣሪ እምበረከካለሁ! ለጣዖት አልሰግድም!" ብላ ወሰነች፣ የመጣው ቢመጣ እቀበላለሁ ብላ ወሰነች፡፡ ይባስ ጠዋት ተነስታ ጮክ ብላ ትፀልይ ጀመር፡፡ ሃይማኖታዊ ቅናት አደረባት ጠዋት ተነስታ ስትፀልይ ሴትየዋ አልቻለችም፡፡ ሰይፍ ይዛ ልታርዳት መጣች፡፡ "አንቺ ሴት ትናንትና ነገርኩሽ ማቆም አልቻልሽም መሞት ትፈልጊያለሽ!" አለቻት፡፡ "አዎ እኔ በአምላኬ ስም እሰዋለሁ ህይወቴን እሰጣለሁ በሱ ዘንድ ሙሉ ህይወት አለኝና ምንም ችግር የለብኝም የመጣውን መከራ እቀበላለሁ" አለቻት፡፡ አንገቷን ልታርዳት ሰይፏን ከአንገቷ ላይ ጣል አደረገችው ያቺ አህዛባዊ ሴት፡፡ በልጅቷ ታላቅ እምነት በእግዚአብሔር ጠብቆት፣ በቅድስት አርሴማ ምልጃና ፀሎት ሰይፉ መሬት ላይ ወደቀ ይላል፡፡ ስሙ የተመሰገነ ይሁን መሬት ላይ ወደቀ፡፡ አልገባትም ይቺ ሴት

ምናልባት አጥብቄ ስላልያዝኩት ሊሆን ይችላል ብላ በሁለት እጇ አጥብቃ ይዛ እንደገና አንገቷ ላይ አሳረፈችው አሁንም መሬት ላይ ወደቀ፡፡ ለሶስተኛ (ጊዜ) አንገቷ ላይ አሳረፈችው አሁንም ወደቀ ግራ ገባት ከንፈሯን መጠጠች እራሷን ነቀነቀች እጆቿን በአፏ ላይ ጭና "በእውነት የክርስቲያኖች አምላክ ገናና አምላክ ነው" አለች፡፡ ልትመሰክር ቀረበች አህዛባዊት ሴት እግዚአብሄርን የማታውቅ ከነብይ ያነሰ ነብይ ነው ብላ የምታምን ሴት "የክርስቲያኖች አምላክ ገናና አምላክ ነው አሸናፊ አምላክ ነው በተሰደዱበት አብሯቸው ይሰደዳል በተሰደዱበት ቦታ ግርማ ሞገስ ሆኖ ክርስቲያኖችን ይጠብቃል፡፡ በእውነት ያንቺ አምላክ ገናና አምላክ ነው እምነትሽም ትልቅ እምነት ነው ከአሁኑ ሰአት በኋላ ቤቴ ውስጥ የምትፈልጊውን የአምልኮ ስርአት በነፃነት ማራመድ ትችያለሽ ብላ ፈቀደችላት" ይላል፡፡

ተረክ 19

ከመምህር መጋቤ ሀዲስ ቀለመወርቅ ታደሰ በ3/7/2002 5:45 ጥዋት
በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ
አረጋዊ ካቴድራል

ሰውየው ንስሀ ሊይዝ ወደ አባቱ (የንስሀ) ይመጣል፡፡ "አባቴ ሀጥያት ሰርቼ ንስሀ ይስጡኝ" "አይ ልጄ ደስ ይላል ሰው ሆኖ የማይበድል እንጨት ሆኖ የማይጨስ የለም ትልቁ ነገር መመለስህ ነው እንኳን ደህና መጣህ ልጄ የሠራኸው ሃጢአት ምንድነው" ይሉታል፡፡ "ገመድ ሰርቄ ይላቸዋል፣ ገመድ ሰርቄ ነው"፡፡ "እንዴ ይሄስ ቀላል ነው" ብለው ንስሀ ይሰጡታል፡፡ ከወራት በኋላ ደግሞ ይመጣል "አባቴ ሀጢአት ሰርቼ" "ምንም ችግር የለም ወድቆ መቅረት ነው እግዚአብሔርን የሚያሳዝነው በሀጢአት መውደቅ ሳይሆን ወድቆ መቅረት ነው (ክፉው) አንተ ግን በቃ እንደወደክ አልቀረኽም ትልቁ ነገር የሚፈለገው መምጣትህ ነው ሀጢአትህን አምነህ፡፡ ምንም ችግር የለም የሰራኸው ሀጢአት ምንድነው?" "ገመድ ሰርቄ" ይላቸዋል፡፡ እሺ እሰጥሀለሁ ብለው ንስሀ ይሰጡታል፡፡ አሁንም ከወራት በኋላ ደግሞ ለሶስተኛ ጊዜ ይመጣል፡፡ "አባቴ ሀጢያት ሰርቼ" ይላቸዋል "አይ ልጄ ምን ችግር አለ እግዚአብሔር ባለብዙ ምህረት ነው፣ ባለብዙ ይቅርታ ነው ትልቁ ነገር አንተ እኮ አምነህ እየመጣህ ነው፡፡ አምላክ ይቅር ባይ መሆኑን ተረድተሀል እኮ፡፡ የሰራኸው ሀጢአት ምንድነው?" ይሉታል፡፡ "ገመድ ሰርቄ" ለሶስተኛ ጊዜ "አንተ ልጅ በገመድ ተለክፈሀል እንዴ ገመድ ገመድ ትላለህ እሳ?! የቸገረኸ ገመድ ከሆነ እኔ ሙሉ ገመድ እሰጥሃለሁ" አሉት፡፡ እኚህ አባት የሚፈልገውን ያህል ገመድ ሰጡት፡፡ ጥቂት እንደተጓዘ የአባቱ ደግነት እሩህሩህነት ማፅናናታቸው ተሰማው ልቡን ነካው "እስከመቼስ እግዚአብሔርን እዋሸዋለሁኝ፡፡ አባቴንስ ለምን አታልላለሁኝ እውነቱን ለምን አልናገርም" አለና ተመልሶ መጣ፡፡ "አንዱ ገመድ አነሰህ እንዴ? አልበቃህም እንዴ?" ይሉታል፡፡ "አይ እኔ እንደው አባቴ እንዲህ አይደለም እኮ ነገሩ እንደው ገመድ ሳይሆን ገመዱ ጫፍ ላይ በሬ አለ" አለ፡፡ ለካ ይህ ሰው የሰረቀው ገመድ ሳይሆን በሬ ኖሯል፡፡

አባሪ ሁለት

## ተረክ 20

ከመምህር ሀብታሙ ከበደ በ3/7/2002 በ11፡00

ታእካ ነገስት በአታ ለማርያም ቤተክርስትያን

ንጉስ እንዲህ አደረጉ። ፀሎት ወደሚያደርጉ ሰዎች ቀረቡና እንዲህ አሏቸው "ምን እያደረጋችሁ ነው?" "አይ ንጉስ ሆይ ፀሎት እያደረግን ነው" "ፀሎት እያደረጋችሁ ነው?" "አዎ" "አይ መልካም እስኪ ከእናንተ ውስጥ አባታችን ሆይ የሚለውን ፀሎት በትክክል ጀምሮ እስከመጨረሻው ድረስ የሚጨርስልኝ ካለ እኔ ፈረሴን እሰጠዋለሁ" አሉ። እነዚያ ፀሎት የሚያደርሱ ሰዎች እኔ! እኔ! እኔ! አሉ። ከመካከላቸው አንዱን መረጡና "በል አንተን መርጨሀለሁ በል አንተ ፀሎቱን ጀምር" አሉት እሺ አለና ያ ሰው ጀመረ።

አባታችን ሆይ
በሰማያት የምትኖር
ስምህ ይቀደስ
መንግስትህ ትምጣ
ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን
የእለት እንጀራችንን ስጠን . . . አለና ትዝ አለው

ንጉስ ሆይ ፈረሱን የሚሰጡኝ ብቻውን ነው ወይስ ከኮርቻው አለ።

## ተረክ 21

ከመምህር ሀብታሙ ከበደ በ3/7/2002 በ11፡00

ታእካ ነገስት በአታ ለማርያም ቤተክርስትያን

ሴትየዋ ልጇን እንዲህ ትለው ነበር "ማሙሽ ወደምግብ ከመቅረብህ በፊት መጀመሪያ እግዚአብሔርን አመስግን" ትለዋለች "ከጨረስክም በኋላ እግዚአብሔርን አመስግን" [እንዲህ አይነት ቤተሰቦች አሉ። ለልጆቻቸው መልካም ትምህርት የሚያስተምሩ፣ ለልጆቻቸው ሃይማኖትን የሚያስተምሩ፣ ለልጆቻቸው በጎ ነገርን የሚያስተምሩ ወላጆች አሉ።] ይህቺ ሴት እንዲህ ነበር ትለው የነበረው "ወደ ማዕድ ስትቀርብ እግዚአብሔርን አመስግን" ትለዋለች "ከበላህም በኋላ እግዚአብሔርን አመስግን።" በዚህ አይነት ሁኔታ እሷን እየፈራ ከምግብ በፊት እግዚአብሔርን ያመሰግናል ከምግብም በኋላ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። አንድ ቀን እሷ እንጀራ ስትጋግር አጠገቧ ቁጭ ብሎ ይጫወታል አንዲት ውሻ ነበረችና ያቺ ውሻ ስትጮህ ያቺ ሴት ትጋግረው ከነበረው እንጀራ በጨቅ አደረገችና ለውሻዋ ሰጠች። ውሻዋ ልትበላ ስትል ልጁ ጫማ አንስቶ ውሻዋን ካልገደልኩ አለ። "እንዴ ምን አደረገች"(አለችው)። "እንዴት ዝም ብለሽ ታያለሽ ከመብላትህ በፊት እግዚአብሔርን አመስግን ከበላህም በኋላ እግዚአብሔርን አመስግን

ብለሺኝ የለም" "አዎ" "ይቺ ውሻ እኮ ሳታመሰግን ልትበላ ነው" "አይ እሷ እኮ እንሰሳ ናት ተዋት ምስጋና የሚጠበቀው ከኛ ነው እሷን ተዋት" አለችው፡፡ ከእለታት አንድ ቀን አንድ እንግዳ እቤት ይመጣል፡፡ እንግዳው ከሩቅ ሀገር ከብዙ ዘመን በኋላ የመጣ ስለነበር በመጣ ጊዜ ከዚህም ከዚያ ብላ ማስተናገጃ ማዕድ አቀረበችለት፡፡ ያ ህፃን ቁጭ ብሎ ይመለከት ነበር፡፡ ያም እንግዳ የቀረበለትን ማዕድ እግዚአብሔርን ሳያመሰግን ሲበላ ህፃኑ ትኩር ብሎ ያየዋል የህፃኑን አመለካከት ባየ ጊዜ "እንዴ እንዴት ነው የሚያየኝ?! አቡሽ ታውቀኛለህ እንዴ?" አለው "አዎ አውቅሀለሁ የቡቺ ወንድም ነህ" ይህን ያለው እግዚአብሔርን ሳያመሰግን ስለበላ ነው፡፡

## ተረክ 22

በመምህር ብርሃን አንለይ በ8/7/2002 በ11፡30

በቅዱስ ባለእግዚአብሔር እና ባለወልድ ቤተክርስቲያን

አንድ ሰነፍ? ባህታዊ ወደ አንድ ትልቅ ገዳም ይሄዱና የገዳሙ መነኮሳት በሙሉ በስራ ላይ ናቸው፡፡ [. . .] እኚህ ሰነፍ ባህታዊ ምን አሉ ይባላል እንዲህ አሉ "እናንተ ስትወርዱ ስትወጡ ስትቆፍሩ ገዳማውያን እግዚአብሔር የሠጠውን ነገር ይበላል" አሉ፡፡ "ጌታ እኮ የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ ብሏል፡፡ እናንተ እኮ ከስጋውያ በምን ትለያላችሁ፤ ስታርሱ ስትቆፍሩ ስትደክሙ ነው የማያችሁ"፡፡ አዎ ይህ ነገር ከመነኮሳቱ አልፎ ወደገዳሙ አስተዳዳሪ ደረሰ (መነኮሳቱ) እንዲህ እየወቀሱን ነው "እናንተ ከአለማውያን ምንም የተሻለ ሥራ የላችሁም፣ ኑሮ የላችሁም፣ አለማውያንም ይሰራሉ እናንተም ትሰራላችሁ ጌታችን የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ ብሏል እያሉ እየወቀሱን ነው ምን ይሻላል" ብለው ገዳማውያኑ የገዳሙን አስተዳዳሪ ጠየቁ፡፡ የገዳሙ አስተዳዳሪ "እኚህ ሰው እኮ በክርስትና ህይወት ውስጥ ከገዳም ገዳም እየተዘዋወሩ 15 ቀን አንዱ ገዳም 15 ቀን አንዱ ገዳም እየዞሩ ኑሯቸውን ነው የሚገፉት ስራም አይሰሩም ጸሎትም (አያደርሱም) በአንድ ቦታ ፀንቶ በመገኘት ነው እግዚአብሔር የሚገኘው በቤተክርስቲያን ፀንተን ስንቀመጥ ነው እግዚአብሔር ዋጋ ሊሠጠን የሚችለው፡፡ ወደቃልቻውም ወደጣኦቱም ወደምኑም መዛወር ከጀመርን እግዚአብሔርን ማግኘት አንችልም በገዳም ውስጥ ያለው ባሕል ይህ ነው በገዳም ውስጥ ፀንቶ መኖር ነው" (አሉ)፡፡ አበምኔቱ በመንፈሰ እግዚአብሔር የተቃኙ ስለነበሩ "ሥራ ስሩ የመመገቢያ ሰአት ሲደርስ ግን ደውል እንዲመታ አንፈልግም (አሉ)፡፡ [ልክ አስራ አንድ ሰዓት ሲደርስ በሚመገቡበት ሰዓት ሁሉም ምግቡን እየተቀበለ ወደበአቱ ይገባል በአንድ ላይ አይበሉም ለምንድነው ይሄ በየበኩላቸው የተሰጣቸውን መቁንን ለሌሎች እየሰጡ እነሱ ሶስት አራት ቀን ፆም እያደሩ የሚኖሩ መናንያን ስላሉ ነው፡፡ መመገብ አለመመገብ የራሳቸው ጉዳይ ነው]፡፡ "ደውል በሚደወልበት ሰአት ግን ሳትደውሉ ወደምግብ አዳራሽ ኑና መቁንናችሁን እየያዛችሁ ሂዱ" አሉ፡፡ የገዳሙ አስተዳዳሪ ናቸው ሁሉም

መነኮሳት በዛን ቀን ደወል ሳይደውሉ መቁነናቸውን ይዘው ወደየበአታቸው ገቡ። እኛ ይተቿቸው የነበሩት መነኩሴ ቀና ብለው ሲያዩ ጥላቸውን ሲለኩ የመመገቢያቸው ሰዓት አልፏል። "እንዴ እኚህ መነኮሳት እኔን ሳይጠሩኝ ተመገቡ እንዴ?" እያሉ ጥያቄ ማንሳት ጀመሩ። ጠየቋቸው ምግብ ተመግባችኋል ወይ አሏቸው "አዎ አባታችን እኛማ ተመግበናል"(አሉ)። "ምነው ጌታኮ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝም ብሎ ተናግሯል" አሉ። መነኮሳቱ ምን እንዳሏቸው እኚህን መነኩሴ "አባታችን" አሏቸው በነገር ነካ አረጓቸው "እኛ አለማውያን ነን እርሶ ግን መንፈሳዊ ነዎትና ምግብ እያስፈልጎትም ብለን ነው ሳንነግሮት የተመገብነው" ብለው አሏቸው ይባላል።

## ተረክ 23

* በ12/7/2002 በ11፡30

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን

በደርግ ጊዜ ወደ ኤርትራ የመንግስት ሰራተኛ ሁሉ ይዝመት ተባለ። [አልተባለም? የለም አንዴ ሰው ሁሉ (ምእመኑን መልስ እንዲሰጣቸው በመጠባበቅ) የሊቀመላኩ ያለህ ምነው ከበዳችሁ?! አልተባለም ወይ? ውሸት ተናገረ እንዳይሉኝ ብዬ ነው ትናንት የተወለዱ ካሉ]። ከዚያ በኋላ ይቺው ናት ደሞዜ ሁለት መቶ ብር ናት እያለ የስምንቶች እናት ሴትዮ ሁለት መቶ ብር ይሰጣታል። ያቺን አቆናቁና መከራዋን አይታ ልጆቿን መከራዋን አይታ ዘንጋዳውን ኀመኑን እያለች ታሳድጋለች። ከዚያ በኋላ ግድ መጣ ሚስቶቻችሁን አምጡ ተባለ። ሚስት ፈረመች በወሩ፣ በሄደ በወሩ ደመወዝ ልትቀበል ሄደች "የአቶ እገሌ ሚስት" "አቤት" "አንድ ሁለት ሶስት አራት . . ." ዘጠኝ መቶ ብር ተቀበለች እና ዞር ብላ ብትቆጥረው ዘጠኝ መቶ ብር! ብትቆጥረው ዘጠኝ መቶ ብር! እንዴ ይህ ሰውዬ ተሳስቷል አለች። "እስኪ እንካ ቁጠረው" አጠገቧ ያለው ሰውዬ ቆጠረው "ዘጠኝ መቶ ብር ነው" አላት "አንተ ሰውዬ" አለች ደመወዝ ከፋዩን "ይሄን ብር ቁጠረው። "እስቲ ምነው የአቶ እገሌ ባለቤት አይደሉ እንዴ?! ተሳሳትኩ እንዴ?! ደሞዙ እኮ ቋሚ ደመወዙ ሺህ ምናምን የእናት ሀገር ጥሪ፣ የሚኒሻ የመንገድ ይሄ ይሄ ተቆርጦ የተጣራ ደመወዙ ዘጠኝ መቶ ብር ነው" አላት "ለመሆኑ ከመቼ ጀምሮ ነው ሺህ ብር ይበላ የነበረው" "እንዴ ስንት አመቱ!" (ምዕመኑን ነው) [ይቺ ሴትዮ... ሰውየው ጦር ሜዳ ሄዷል ይህቺ ሴትዮ መልሰው ብላ ነው የምትፀልየው እዛው ድፋው ብላ ነው የምትጸልየው አሁን ምን ብላ ትፀልይ ይህቺ ሴት እንደው በመድኃኒአለም ፍረዱኝ ምን ብላ ትፀልይ ይቺ ሴትዮ ንገሩኝ?!]

## ተረክ 24

* በ12/7/2002 በ11፡.30

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

ሰባ ስምንት አመተምህረት እዚህ ዊንጌት ጠዋት አንድ ሰአት ከምናምን ደርሼ (ለመድረስ) ወደዊንጌት የምሄድበት ጉዳይ ነበረኝ 28 ቁጥር ነበር የያዝኩት (አውቶብስ ለማለት ነው) ታክሲው ከፊቱ ሲገባ ፍሬኑን ሲይዝ በሙሉ የነበረው ሰው እንዳለ ተነጠፈ። እንዴት ያሉ አባት አዛውንት አንዲት ጥቁር ፀጉር በራሳቸው ላይ የለም። ተማሪዎች እላያቸው ላይ ወደቁ ቀና ብለው አዬ (አብረዋቸው የተሳፈሩትን ወጣቶች) "ልጆቼ ይቅርታ ይቅርታ" አሉ ተሟቀቁና። ብረቱን ይዘው ይወዛወዙ ነበር። አሮጊትና ሽማግሌዎች "ይቅርታ ይቅርታ" አሉ ቀና አሉ። "ምናለ አሁን እንደ እናንተ ያለው ቢሞት" (አውቶብስ ውስጥ የነበረውን ወጣት ለማለት ነው) አላቸው። ሰባ ስምንት ዓመተ ምህረት በኂላ አባቶቼ መቼም እዚህ ሸበት ውስጥ ያለው እውቀት አቤት እዚህ ሸበት ውስጥ ያለ ብልሀት [ኧረ ጉድ አዬ ዲግሪ አዬ ዶክትሬት ዶክ እሬት ዶክ- እሬት ንፁሆች ካላችሁ ይሄ አይነካም. . .] ከዛ በኂላ በዚህ በሸበት ውስጥ ያለ እውቀት "ውይ ልጆቼ እውነት ብላችኂል አልሆነልንም እንጂ ልጆ ወንበሩንም እንዳንቀመጥ ቀድማችሁ ያዛችሁት መቃብሩንም ቀድማችሁ ያዛችሁት ግራ ገብቶን ነው እኮ መቆማችንን የተያያዝነው" አሉዋቸው።

## ተረክ 25

* በ12/7/2002 በ11፡.30

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

እስቲ ወደቦሀቃው አንድ አፍታ ልውሰዳችሁ ነጭ የተባለ የተመረጠ ጤፍ ጋግራችሁ፤ ምጣዱ ላይ ልዩ ነው ንጣቱ ጠዋት መሶቡ ሲከፈት ነጭ ነው? አመድማነው ጤፉ? ምን ሆኖ ነው የምታገኙት? አመድማ ወየት ሄደ ንጣቱ? ምን ወሰደው መልኩን ምን ቀየረው እኔና እናንተ እየተቀያየርን ግፍና ሀጢአት እንደምንሰራ ቦሀቃው እየመሰከረብን ነው ይኸው ነው በረከቱ ተወስዷል።

## ተረክ 26

* በ12/7/2002 በ11፡.30

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

አባቶቻችን ልጅ ሆነን "የአክስትህ ልጅ ናት ሳማት። ይህ ዘመዳችን ነው የአያት የቅድመ አያትህ ልጅ ነው ዘራችን አንድ ነው እስቲ ሳሚው ሳማት" ይባል ነበር። እጅ መጨበጥ እኮ የጣሊያን ቅርስ ነው መጤ ነው ሀገር የለውም እኮ። እጅ መጨበጥ ተማርኬያለሁ ማለት እኮ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ እኮ ተማርኮ አያውቅም። የኛ ትክሻ መሳሳም ነው መልኩን ቀይሮ አሁን ገና

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሲያገኘው ይለትመዋል (የዘመኑን ትክሻ በትክሻ በመገጫጨት ሰላምታ መለዋወጥን ለማለት ነው)፡፡ ከወዲያውም እየፈተሸው ነው፡፡ መሸት ያለለታ (ያለ ዕለት) ብዙ ጨዋታ አለ፡፡

## ተረክ 27

* በ12/7/2002 በ11፡30

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

የሴትና የወንድ ስራ የሚል የለም በመፅሀፋችን ያዕቆብ ወንድሙ አድኖ ሲመጣ ምን ይሰራ ነበር? የምስር ወጥ ይሰራ ነበር፡፡ የሴት ስራ አምጦ መውለድ ብቻ ነው፡፡ ሌላ የሴት ስራ የሚባል የለም፡፡ዛሬ ድስቷን ጣድ አድርጋ ወይ ልብስ ልታሰጣ ወይም ዘይት ልትገዛ ወደሱቅ ስትሄድ ከሰሉ ላይ የተጣደው ድስት ሲገነፍል "አረ ገነፈለልሽ" ይላል ያ ከንቱ ንብረቱ ገደል ሲገባ፡፡ አዩ ወንድ ተሁኖ ተሙቷል ስሪውን እንደሁ ሁሉም ታጥቆታል ወንዱ ማነው? ሴቱ ማነው?

## ተረክ 28

ከመምህር መጋቤ ሀዲስ ቀለመወርቅ ታደሰ በ13/7/2002 በ12፡00

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ

አረጋዊ ካቴድራል

የኳስ ነገር እኛን (ሰባኬ ወንጌል) አገልጋዮቹን ሁሉ ሳይቀር ፈትኖናል፡፡ አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ ሰውየው አንድ ጉባኤ ላይ ተጠርቶ ይጓዛል በአንድ ቦታ ላይ ታላቅ ጉባኤ ይዘጋጅና ሁለት መምህራን ናቸው የተጋበዙት፡፡ አሁን ሁለተኛ እንዲያስተምር የተጋበዘው መምህር አስቀድሜ እኔ ማስተማር አለብኝ ይላል ፕሮግራም መሪውን ጠርቶ፡፡ እንዴ አንተ እኮ የተጋበከው ሁለተኛውን ክፍለ ትምህርት አንድታስተምር ነው ለምን ቸኮልክ ይለዋል፡፡ አይ እኔ አስቀድሜ መስበክ አለብኝ ማንቼስተር ግጥሚያ ስላለው ቶሎ ሰብኬ ልሂድ ብዬ ነው አለ፡፡

## ተረክ 29

ከመምህር መጋቤ ሀዲስ ቀለመወርቅ ታደሰ በ13/7/2002 በ12፡00

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ

አረጋዊ ካቴድራል

ሰውየው በሬ ሊገዛ ወደገበያ ይሄዳል፡፡ ታዲያ መንገድ ላይ ጓደኛው አገኘውና "ወዴት ትሄዳለህ" አለው "በሬ ልገዛ ወደገበያ እየወጣሁ ነው" አለው፡፡ ጓደኛውም መለሰና "እግዚአብሔር ከፈቀደልህ" አለው፡፡ "እንዴ ገንዘቡ እኮ ኪሴ ውስጥ አለ የእግዚአብሔር ፍቃድ ለምን ያስፈልጋል" አለ፡፡ ጥቂት ኪሎ ሜትር እንደተጓዘ ወንበዴዎች ቅጥቅጥ አድርገው ልብሱን ገፈው ገንዘቡን ዘርፈውት ሄዱ፡፡ ቆስሎ፣ ተደብድቦ፣ ገንዘቡ ተዘርፎ ሲመለስ ጠዋት ያገኘው ጓደኛው "እንደምን ዋልክ" አለው፡፡ ሳይለው (አባባሉን ለማረም ነው) "ወዴት እየሄድክ ነው" አለው፡፡

መጀመሪያ ምን ነበር ያለው "ወደከተማ እየወጣሁ" "ምን ልታደርግ" "በሬ ልገዛ" ሲለው "እግዚአብሔር ከፈቀደልህ" ሲለው "አይ ኪሴ ውስጥ እኮ ገንዘብ አለኝ የእግዚአብሔር ፍቃድ ምን ያስፈልጋል" ነበር ያለው፡፡ ተደብድቦና ቆስሎ ገንዘቡንም አጥቶ ገንዘቡንም ተዘረፎ እርሱም አካሉን አጥቶ ሲመለስ ግን ጠዋት ያገኘው ጓደኛ "ወዴት እየሄድክ ነው" አለው "እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደቤቴ እየሄድኩ ነው" አለ፣ "እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደቤቴ እየሄድኩ" አለ፡፡

## ተረክ 30

ከመምህር መጋቤ ሀዲስ ቀለመወርቅ ታደሰ በ13/7/2002 በ12፡00

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

ሴትየዋ ወደ ሆስፒታል ትሄዳለች [ማህበራዊ ኑሮውንም እየዳሰስኩ ነው ጎንለጎን] ወደ ሆስፒታል ትሄዳለች፡፡ ነፍሰጡር ሆና ወደመንግስት ሆስፒታል ስትሄድ ምን እዳደረገች ታውቃላችሁ ሀኪሙ፣ ዶክተሩ አመናጭቆ ይልካታል፡፡ ከሀኪሞች የሚጠበቀው ትእግስትና ትህትና ሲጠፉ ግራ ገብቷት እያዘነች ገንዘቤ ካለምናለ ግል ሆስፒታል ሄጄ እታከማለሁ ብላ እራሷን አፅናንታ ወደግል ሆስፒታል ሄደች፡፡ እዛ የተቀበላት ሀኪም ልዩ ነበር፡፡ በሚያጽናና ትህትናና ፍቅርን በተላበሱ ቃላት "አይዞሽ የእኔ ቆንጆ ፊትሽ ላይ ሀዘን ትካዜ ብስጭት ይነበባል ነገሩ ምንድነው" እያለ ያፅናናት ጀመር እሷም "አይ አንቺ አለም ክፉውም ደጉም ይኖርብሻል ሀኪሞቹን ጨርሼ እንዳላመሠግን እንደጥዋቱ አይነት ሀኪም አለ፡፡ ጨርሼ ደግሞ እንዳላማ እንደዚህ አይነት የተባረከ ሀኪም አለ" ብላ ቀና ብላ ስትመለከት ለካስ እያባበላት ያለው ጠዋት አመናጭቆ የላካት ዶ/ር ነበር [ሀሳቡ ገብቷችኋል ክርስቲያኖች መንግስት ሆስፒታል ላይ የሚከፈለው ገንዘብ አነስተኛ ስለሆነ አመናጭቆ ላካት የሚፈልገው ምን ስለሆነ ነው ብር ነዋ ሰው እራሱን ለብር ሸጧል፡፡]

## ተረክ 31

ከመምህር (ቀሲስ) አስቻለው መሐሪ በ17/7/2002 በ12፡30

በመንበረ መንግስት ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን

[ነግሬያችሁ ሊሆን ይችላል] ማንን ትወዳለህ ሲሉት አንድ ፈላስፋ ልብስ ሰፊዬን አለ፡፡ ለምንድነው ልብስ ሰፊህን የምትወደው ሲባል ያለው ነገር ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? አምና በለካኝ ልክ ዘንድሮ አይሰፋልኝም ሁልጊዜ በመጣሁ ቁጥር እየለካ ነው የሚሰፋልኝ አለ፡፡

## ተረክ 32

ከመምህር (ቀሲስ) አስቻለው መሐሪ በ17/7/2002 በ12፡30

በመንበረ መንግስት ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን

አንድ የሥነ እፅዋት ተመራማሪ የሚፈልገውን ተክል ገደል ውስጥ ይመለከታል:: ከዚያ በአካባቢው ከሚጫወቱት ልጆች መካከል አንዱን ጠርቶ እባክህ እዚያ ገደል ውስጥ የምፈልገው ተክል አለና ወርደህ አምጣልኝ ይለዋል፡፡ ልጁም እሺ በጄ ይላል የሚሠጠውን ብር ተመልክቶ:: ወገቡ ላይ ገመድ ታሰረ ወደገደሉ ለመውረድ፡፡ ከዚያ በኋላ ገደሉን ወደታች ሲመለከት በጣም ጥልቅ ነው፡፡ አሁን "አባቴን ጠርቼ ልምጣ" አለ "ለምንድነው አባትህን ጠርተህ የምትመጣው እኔ ገንዘብ እሰጥሀለሁ ገመዱ ገመገም ላይ ታስሮ እኔ ገመዱን እይዛለሁ ወደታች ትወርዳለህ የሚፈለገውን ይዘህ ትመጣለህ ከዛ ገንዘቡን እሰጥሀለሁ"(አለው)፡፡ "አይ አንተ ስላልወለድኸኝ ብከብድህ ትጥለኛለህ አባቴ ግን የወለደኝ ስለሆነ ብከብደውም አይጥለኝም" አለ፡፡

## ተረክ 33

* በ11/8/2002 በ11፡.30

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ

ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

ወገኖች በወተቱ ውሀ በጤፉ አሸዋ የሚገርማችሁ አንድ በርሜል ዘይት ግማሽ ወገቡን ውሃ ይሞላና ከላይ ዘይት ገዝቶ ይሄዳል፤ ክፍለሀገር ጭኖ ይሄዳል፡፡ እዛ ሲሄድ ሲቀዳው ከላይ ዘይቱ ያልቅና ከስር ምኑ ይመጣል?!. . . ባለፈው አም አሁን ሰኔ ሲመጣ ይሆን? ህዳር ሲመጣ አመቱ (እራሳቸውን በመጠየቅ) አንድ ጀሪካን ሀያ ሊትር ገዝተን ቤንዚን ሄድን፡፡ ሄድንና እኛ ዝም ብለን እናንቆረቁራለን (በቤተክርስቲያን የሌሊት ቅዳሴ ላይ ለመብራት በሚጠቀሙበት ጀነሬተር ውስጥ ለማለት ነው) መጨረሻ ከ9 ሠዓት በኋላ ወደ 12 ሰዓት የሚያደርሰንን ስንሞላው ና ተነስ ሞተር አባቴ ይሙት፣ ወዲያ ብንለው ወዲህ ብንለው "ምንድነው ነገሩ?" በኋላ አይ ምናልባት በጣም ምልቶ ሊሆን ይችላል ብለን፤ ትንሽ ጎደል አድርጉት ይላል መመሪያው፤ በኋላ ትንሽ እናጉድለው አልንና ስንቀዳው የቀዳነውን እንዲህ አድርገን (እጃቸውን ወደላይ ከፍ በማድረግ እያዩ) እናየዋለን ሁለት ነገር ነው፡፡ ከስር ውሀ ከላይ ቤንዚን ነው፡፡ ጠቅላላ ጀሪካኑን አምጥተን እንዲህ ከፍ አድርገን ወደብርሀን እናየዋለን ግማሹ ሙሉ በሙሉ እንዳለ ውሀ ነው፡፡ ምን እናድርገው ሌሊቱ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ማህሌቱ ሄደ ከዚያ ያንን ሁሉ ውሀ ተሸክመን ሄደን ጀኔሬተር ተከራይተን፣ ሞንታሮ ተከራይተን ሄደን ተመልሰን ትተን መጥተን አስረክበናል፡፡ ወገኖቼ ጉድ ነው የሚሰራው ፍረዱ እስቲ ምን አድርገው በምን ፍጥነት ያንን ግማሽ ውሀ እንዳደረጉት አናውቅም፡፡

## ተረክ 34

* በ11/8/2002 በ11፡30

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ

ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

በፍቅር በትህትና በየዋህነት ሆነን እንደብርሀን ልጆች በፍቅር እንመላለስ፡፡ በትህትና ስራውን ሳሰራው ይሄ አልገባኝም ቢል ማመናጨቅ አይደለም የእናቴ ልጅ “ይሄ አልገባህም? እስቲ ና እንዲህ አድርገን እንሞክረው እንዲህ አድርገን እንሞክረው” እራሳችንን አዋቂ አድርገን አንቀርብም፡፡ “እስቲ አብረን እንሞክረው እስቲ እንዲህ አድርገን እንሞክረው እንዲህ እንዲህ አድርገን እንስራው” ነው እንጂ “ይህን አድርገህ አትሰራም” (በማመናጨቅ ድምጸት) ስትለው ይደነግጥና ይጠፋበታል ይደነግጣል፡፡ ቀስ ብሎ በትህትና አይዞህ እኔም ተምሬ እኮ ነው አብረን እንስራው ምን ቁም ነገር አለው ነበር እንዲህ አድርገን ነበር የምናውቃትን ነገር (የምናካፍለው)፡፡ ዛሬ ዳማከሴ ያወቀ እንደሆነ ሶስቴ ዞሮ ነው የሚቆርጣት፡፡ ሰው እንዳያውቅ! ዳማከሴ ያወቀ እንደሆነ አያድርስ ነው!

## ተረክ 35

* በ11/8/2002 በ11፡.30

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ

ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

ይሄ አርቴፊሻል ሽጉጥ የሚላከው ወደ አፍሪካ ነው፡፡ ወገኔ እንደው የወጣችሁ ሰዎች ታዘቡኝ (ባህርማዶ ማለታቸው ነው) ሲውዲን ስድስት ወር ቆይቻለሁ፤ ብዙ መዋእለህፃናት ጎብኝቻለሁ እራሱ አሻንጉሊት የሚሸጥበት ሽጉጥ የለም ጭራሽ፡፡ እየው ሰማችሁኝ ሆነ ብለው እኮ ከህፃንነቱ ለምዶት እንዲያድግ ብለው ነው የሽጉጥ አርቴፊሻል አፍሪካ ውስጥ የሚልኩት የምንጣላው እኛ አይደለን?! የምንጣላው እኛ አይደለን?! ጦሩን መርዝ መትከል የሚችሉት እኛ ላይ አይደለም ሰው የለማ እኛ ቤት! ማሳውን የሚጠብቀው ሰው የለማ፡፡

## ተረክ 36

በመምህር (ቀሲስ) ይግዛው መኮንን በ14/8/2002 በ11፡45

በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ

ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል

ሰውየው ትልቅ ባህር ውስጥ ገባ ባህር ውስጥ ገብቶ ባህሩ ይዞት ሲሄድ አድነኝ እያለ መጮኽ ጀመረ ወደ እግዚአብሔር፡፡ “አድነኝ! አድነኝ! አድነኝ!” ሲል አንድ ጉቶ አገኘ እዛው ውስጥ ማለት ነው፡፡ ለቀም አድርጎ ይዞ “አድነኝ!” አለ ጮኸ [እግዚአብሔር የሚጮሁትን ድምጽ ይሰማል አይሰማም? ይሰማል? ፈጣሪ ይሰማል ጩኹ ዝም ብላችሁ ወደ እግዚአብሔር ይሰማል

መከራ ሲወድቅባችሁ ጩሁ እሱ እኮ አስተዋይ ነው አይደለም እንዴ?!. . .] ጉቶውን ይዞ "አድነኝ!" ይላል "አድነኝ!" ብሎ ሲጮኽ ጩኸቱን ሰማውና ድምጹን አሰማው "መጣሁ" አለው፡፡ "በል ላድንህ ስለሆነ ጉቶውን ልቀቀው" አለው ፈራ ጉቶውን ብለቀው ይሄ ውሃ ይዞኝ ሊሄድ ነው አለና "አይ እንደው ጉቶውንም አለቅም አንተም አድነኝ" አለ፡፡

## ተረክ 37

በመምህር (ቀሲስ) መጋቤ ሐዲስ ኪዳኔ በ16/8/2002 በ11፡00

በደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን

ሴትየዋ እንዲህ አሉ አሉ፡፡ አንዲት ላም ነበረቻቸው ያቺን ላም በጣም ነበር የሚመኩባት ላሚ በቃ የእለት ጉርሳቸው መመኪያቸው እንጀራቸው ነበረች ያቺ ላም፡፡ የዛችን የላም ወተት እያለቡ ውሀ ትንሽ ቀልቀል አድርገው ንፁህ ነው እያሉ ያንን ወተት ይሸጡ ነበር፡፡ ህዝብን እያታለሉ ማለት ነው ያለአግባብ፡፡ ንፁህ ወተት ነው እያሉ ውሀውን እየጨመሩ ከወተቱ ጋር እየቀላቀሉ ይሸጡ ነበር፡፡ እንደዛ ሲኖሩ አንድ ወንድ ልጅ ነበራቸው ሲኖሩ ሲኖሩ ይሄንን እስቲ ይሄንን ወስደህ (ላሚን ለማለት ነው) ውሃ አጠጣት ወደወንዝ ብለው አሉት አሉ፡፡ ያ ልጅ ይሄድና የእናቱን ትዕዛዝ ለመፈጸም ላሚን ይዞ ወደወንዝ መሄድ፡፡ ላሚቷ ወራጅ ወንዝ አለ አፋፉ ላይ ቆማ ውሃውን ስትጠጣ ያልታሰበ ደራሽ ጎርፍ መጣና ላሚን ይዟት ጥርግ አለ፡፡ ልጁ እንግዴህ የእኛ እናት መመኪያቸው እንጀራቸው ተስፋቸው አለኝታቸው ማን ነች? ማን ነች? ላሚ ነበረች፡፡ አሁን እንዴት ይሁን ጨነቀው እያለቀሰ ወደቤት ሄደ እናት ከአሁን ከአሁን ቀረ ብለው (ጠብቀው ሲመጣ) አንተ የታለች ላሚ (ሲሉት) "እማማ ላሚን ያኔ አንቺ እዛ ወተቱ ውስጥ የጨመርሽው ያጠራቀምሽው ውሀ ጎርፍ ሆኖ ወሰዳት አላቸው አሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የምናጠራቅመው ሀጢአት የምናጠራቅመው በደል የምናጠራቅመው ጥፋት ጎርፍ ሆኖ እንዳይወስደን እንዳያጠፋን ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡

## ተረክ 38

በመምህር (ቀሲስ) መጋቤ ሐዲስ ኪዳኔ በ16/8/2002 በ11፡45

በደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን

አንድ አባት እንዲህ አሉ አሉ፡፡ አጋንንት የሚስብ አንድ ደብተራ ነበር አሉ፡፡ አጋንንት ሲስብ ሲስብ ተያዘ መጨረሻ ላይ "እስቲ ልጄ እባክህ አሁን እንኳን እክደከ ሰይጣን በልና ሙት" አሉት አሉ፡፡ ንስሀ አባቱ እክደከ ሰይጣን፤ ሰይጣን ክጄሀለሁ ብለህ ሙት አሉት፡፡ "አባቴ ይተው እንጂ" አለ "እስከዛሬ እየጎተተኩ ስጠቀምበት ቆይቼ በአለቀ ሰዓት ክጄሀለሁ ማለት ትርፉ ጠላት ማብዛት ነው" አለ፣ አሉ፡፡

## ተረክ 39

በመምህር (ቀሲስ) ይግዛው መኮንን በ17/8/2002 በ12፡30

በደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ካቴድራል

እኔ እዚህ ጋር የምነግራችሁ አንድ ታላቅ እናት አሉ ስራቸው ሁልጊዜ ማብላት እንግዳ መቀበል እንግዳ ማስተናገድ (ነበር)። ታዲያ ይሄ እኔንና እናንተን የነካካው የኑሮ ውድነት እንዲያው ነካ ሲያደርጋቸው ጊዜ ምን እንዳሉ ታውቃላችሁ "አሁንስ እንኳን መብላት ማብላትም ቀረ" ነው ያሉት "እንኳን መብላት ማብላትም ቀረ" እሳቸው የሚያስቀድሙት ማብላትን ነው።

## ተረክ 40

በመምህር (ቀሲስ) ይግዛው መኮንን በ17/8/2002 በ12፡30

በደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ካቴድራል

አንድ ጊዜ አለም እንደተፈጠረ እግዚአብሔር አምላክ በእለተ እሁድ መላእክትን ፈጥሯል ከመቶው ነገድ አንድ ነገድ ሳጥናኤል ወድቋል በተለይ በእለተ አርብ [ሳሳጥረውና ታሪኩን ጊዜ ስለሌለ የሆነውን ነገር ልንገራችሁ] እግዚአብሔር አምላክ ሶስት ፍጥረታትን ፈጠረ እረቡ ዕለት እሁድ ጀምሮ ማለት ነው እነዚህ ሶስት ፍጥረታት ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ነበሩ። ምድር በብርሀን ስትሞላ ጨለማ ተገፎ ብርሃን ሲሆን ቅዱሳን አመሰገኑ እግዚአብሔርን ብርሀንን የሚሠጥ ብለው "ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ!" ብለው አመሰገኑት ከዛ ሣጥናኤል "አንተ እግዚአብሔርን አመስግን" አሉት። ምን ብሎ እንዳላቸው ታውቃላችሁ "እኔስ አላመሰግንም ቢቻላችሁ እኔን አራተኛ አድርጋችሁ አመስግኑኝ አለ" ደፋር አይደል? በዚህ ሰአት እግዚአብሔር ወደ አንጦሮጦስ አወረደው። እግዚአብሔር በስልጣኑ ሲመጡበት ቀናተኛ አምላክ ነው። [. . . ]ምስጋና ለኔ ይገባኛል ሲል ወደ እንጦሮጦስ አወረደው። የሚገርማችሁ ነገር ዲያብሎስ እየወረደ እየወረደ እየራቀ ሲሄድ ከሰማይ እየራቀ እየራቀ ወደታች እየወረደ ሲሄድ ምን አለ ወደሰማይ ተመለከተና "አምላክ ሰራዊቱን ስልጣኑን ሁሉ ጠቅልሎ እኔን እየሸሸ ነው አዎ እየሄደ ነው ተመልከቱ" አለ።

## ተረክ 41

በአባ ሰላማ ብርሃኑ በ19/8/2002 በ01፡00

በመንበረ መንግስት ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን

አንድ አባት ናቸው ይባላል ሲያስተምሩ አንዲት እናት ከመድረክ ስር ተቀምጠው ያለቅሳሉ በጣም ያለቅሳሉ እና (መምህሩ) ስብከቱ ስለገባቸው መሠላቸውና "እናቴ እርሶ የሚያለቅሱት ቃለ እግዚአብሔር ሰለገባም ይመስለኛል ስለዚህ ስብከቴን አሳጥሬ የወረድኩት ንስሀ ልሰጦት ነው" አሉና ወርደው "ስለዚህ ንስሀ ልስጦት" ሲሉ "አይ አባቴ እርሶ ከተናገሩት ምንም የጨበጥኩት

አንድም ነገር የለም እኔን የሚያስለቅሰኝ ልክ እርሶን የሚመስል ፂማም ፍየል ሞቶብኝ ነው" አሉ ይባላል፡፡

## ተረክ 42

በአባ ሰላማ ብርሃኑ በ19/8/2002 በ1፡00

በመንበረ መንግስት ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን

አንድ አባት ነው ይባላል ሂደህ ሙዝ ግዛ ብሎ ልጁን ላከው [እየሰማችሁኝ ነው?] ሙዝ ለመግዛት ሄዶ (ልጁ) ሶስት ኪሎ ሙዝ ነው እንዲገዛ የተላከው ልጁ ግን ስንት ኪሎ ሙዝ ይዞ መጣ ሁለት ኪሎ፡፡ አንድ ኪሎ ቀንሶ ማለት ነው፡፡ አባቱ ተናደደ "ሶስት ኪሎ አይደል እንዴ የላኩህ?" "አዎ አባቴ እሱ የሠጠኝ ሁለት ኪሎ ነው፡፡ ሁለት ኪሎ ብቻ ነው" (አለው)፡፡ መልእክት እንደገና ላከ፣ "ስማ?" ሙዝ ለሸጠው ሰው "ለምንድነው ብሬን ወስደህ ሁለት ኪሎ ሙዝ ብቻ የላከው" "አይ እኔ የላኩት ሶስት ኪሎ ሙዝ ነው እንግዲህ ልጅህን መዝን" ማንን መዝን? ልጅህን፡፡ ልጁ አስራ ሰባት ኪሎ ነበር ሲመዘን አስራ ስምንት ኪሎ ሆነ አንድ ጨመረ፡፡

## ተረክ 43

በአባ ሰላማ ብርሃኑ በ19/8/2002 በ1፡00

በመንበረ መንግስት ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን

አንድ አባት ናቸው አሁንም የኤቲክስ መምህር ናቸው ልጃቸውን አስነሱና ማነው? (የተሳሳተን በማረም) ተማሪያቸው ናት አስነሱና "አባትሽ እራት ከበላ በኋላ ምን ብሎ ነው እግዚአብሔርን የሚያመሰግነው" (አሏት) "አይ አባቴ እራት ከበላ በኋላ አንድ ጊዜ ያገሳና አምላኬ ሆይ ልፈነዳ ነው ይላል"

## ተረክ 44

በአባ ሰላማ ብርሃኑ በ19/8/2002 በ1፡00

በመንበረ መንግስት ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን

አንድ ሰው ሰርግ ቤት ሄደ ይባላል፡፡ ሰርግ ቤት ሄዶ እንግዲህ የሰርግ ምግብ ሁላችሁም ታውቃላችሁ ሰሞኑን የሰርግ ሰሞን ነው ሁላችሁም ታውቃላችሁ እና ሰርግ ቤት ሄዶ እሱ እንዲህ ምግብ ተደርድሯል ሞልቷል አንድ ክትፎ ብቻ አነሳ፡፡ ምን ብቻ አነሳ? አንዷን ክትፎ ብቻ አነሳ፡፡ የሱ ጓደኛ ደግሞ ሰሀኑ እስኪሰበር ድረስ ከየአይነቱ እንዲህ (በእጃቸው የሳህንና የመቆለል ምልክት በማሳየት) (አነሳ) ከዛ ያ አንድ ያነሳው ምን አለ መሰላችሁ አየውና ደንቆት "አንተ እንዴት እሱን ሁሉ አነሳህ አለው" ዝም አለው መጨረሻ "Choose the best" አለው (አንድ አይነት ያነሳው) ያ ሁሉን ያነሳው "All of the above" አለው ይባላል፣ ሁሉም መልስ ነው፡፡

### ተረክ 45

በአባ ሰላማ ብርሃኑ በ19/8/2002 በ1፡00

በመንበረ መንግስት ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን

ባል ታመመ ይባላል እየሰማችሁኝ ነው? ባል ታመመ ይባላል እና ላቦራቶሪ ሽንት አምጣ ይባላል። ምን አምጣ? ሽንት አምጣ ይባላል። ሽንት ጠፋ ከየት ይምጣ [አልገጠማችሁም እንዲህ አይነት ነገር። ይጠፋል እኮ ላቦራቶሪ ብትታዘዙ ይጠፋል።] ሽንቱ ጠፋ ባለቤቱን ጠራና “እባክሽ ተዋርጃለሁ እንደው ላቦራቶሪ ቴክኒሻኑ ይስቅብኛል እንደው ሽንትሽን አበድሪኝ” አላት “እረ ምን ችግር አለው” አለች “ውሰድ ምን ችግር አለው” ከዚያ ሽንቷን ስትሠጥ ሲመረመር የሶስት ወር እርጉዝ በስመ አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወንድ አረገዘ ተብሎ ላቦራቶሪ ቴክኒሻኑ ከመቀመጫው ወድቆ ነው የሞተው የተባለው።

### ተረክ 46

በአባ ሰላማ ብርሃኑ በ19/8/2002 በ1፡00

በመንበረ መንግስት ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን

በነገራችን ላይ የስካር አይነቶችን ታውቃላችሁ። የአንበሳ ስካር የሚባል አለ ይባላል። የአንበሳ ስካር የሰከረ ሰው ካለ መንገድ መልቀቅ ብቻ ነው ያለባችሁ ያደቃችኋል ካገኛችሁ። “ጋሼ” ብትሉት እራሱ አያናግራችሁም። እንደገና የበግ ስካር የሰከረ ሰው ደግሞ ያለሱ ሰው የለም ኩሩ ነው ይኮራል ይዝናናል። የፍየል ስካር የሰከረ ሰው ደግሞ ይቁነጠነጣል። ይሄ ዝሙት የሚያሰራው ይሄ የሚያስጨፍረው የሚያስደንሰው የፍየል ስካር የሰከሩ ናቸው። የጦጣ ስካር የሰከረ ሰው ደግሞ መዝለል ነው ዝምብለው የሚዘሉ ሰዎች አሉ። እ… የሴቶች ስካር አለ ይባላል። አትስማሙም? ሴቶች ሲሰክሩ ይስቃሉ ይባላል እኔ አልሰማሁም ይሄንን።

### ተረክ 47

መምህር (ዲያቆን) ደረጀ ጅማ በ27/8/2002 በ12፡40

በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም

አንድ ታሪክ ልንገራችሁ ብፁዕ አባታችን አቡነ ልቃስ ከረጅም አመታት በፊት ለሥነመለኮት ትምህርት ወደዚህ ወደ ሩቅ ምስራቅ ሄደው ነበር። ያኔ ታዲያ በተማሪነቴ አሉ ፈረንጆችን መቼም የኢትዮጵያ ነገር እጅግ ስለሚማርካቸው ገና እንዳገኙኝ ጥያቄ ሊጠይቁኝ መጡ አሉ። ጥያቄው ግን እሚገርም ነበር መቼም ፈረንጆቹ የኢትዮጵያ ነገር የሚገርማቸው መቼም ፎቃችን አይደለም፣ የመንገዳችንም ጉዳይ አይደለም፣ የስልጣኔያችንም ጉዳይ አይደለም እነሱን የሚደንቃቸው ግን አንድ ነገር አለ ኩሩ ህዝብ መሆናችን፣ ታሪኩን ወዳድ መሆናችን፣ ለነፃነት ታጋይ መሆናችን [. . .] እና ጥያቄ ጠየቁኝ አሉ። ምንድነው ጥያቄው “እስቲ እባኮት

ኢትዮጵያውያን በጣም የሚማርክ ዜማ አላቸውና ያንን ዜማ አዚሙልን ግን አንድ ነገር እንንገሮት ከዚህ በፊት አንድ ኢትዮጵያዊ መጥቶ አዚሞልናል የሚጣፍጥ ዜማ የያሬድ ነው ብሎ እና እርሶም ያዚሙልን፡፡" "አይ ለምን መጀመሪያ የሱን የተቀረፀውን ዜማ አታመጡልኝምና አልሰማውም" አሉ፡፡ "እሺ" ተከፈተ ለካ ይሄ ሰው እስቲ ከያሬድ ዜማዎች ከቤተክርስቲያን ዜማዎች አንዱን አዚም ሲባል ግራ ገብቶታል በዛ እግዚአብሔር የለም በሚለው ዘመን ለትምህርት የወጣ ነው አልችልም እንዳይል ሊዋረድ ነው፤ እችላለሁ እንዳይል ምንም የለም ምን ያድርግ እ. . .? በደንብ አድርጎ አዜመላቸው ፈረንጆቹ "ፐ...ፐ...ፐ...! እያሉ እያደነቁ አስቀምጠውታል፡፡ ለእኚህ አባት ከፈቱት ሲከፈት ምን እንደሚል ታውቃላችሁ "ችቦ አይሞላም ወገቧ፣ ችቦ አይሞላም ወገቧ ማርእሸት ነው ቀለቧ" የሚለውን ዘፈን አዝማቹንም ስንኙንም ዘፍኖ ይሄ ነው የያሬድ ዜማ ብሏቸው ሄዷል፡፡ "አፈርኩ" አሉ "ምንም አላልኩም በሉ ላዚምላችሁ ይሄ የብሉይ ኪዳን ዜማ ነው ሰውየው እንዳያፍር ይሄ ተሸሯል ሰውየውን ላለማዋረድ ብዬ እንደገና የቤተክርስቲያን ዜማዎች አዜምኩላቸው ደስ አላቸው" አሉ፡፡

## ተረክ 48

መምህር (ዲያቆን) ደረጀ ጅማ በ27/8/2002 በ12፡40

በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም

አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡፡ አንዲት እናት አንድ ልጅ ነበራቸው በጣም ይወዱታል፡፡ እና ባህር ማዶ ተምሮ መጥቶ የሚኖረው ከእናቱ ጋር ነው፡፡ አንድ ቀን ጓደኞቹን እንደሚጠራ ለእናቱ ነገራቸው፡፡ "እሺ ምን ላድርግ ታዲያ" "ጥሩ ምሳ አዘጋጂ መመገቢያ "ቴብሉ" ላይ ወጡንም ምኑንም እዛ ደርድሪልን አንቺ ግን ጓደኞቼ መጥተው ምግብ በልተው ተጫውተው ከቤት እስኪወጡ ድረስ ከጓዳ እንዳትወጪ" አለ፡፡ መቼም እናት ሆዷ በጣም ሰፊ ነው ይባላል ሰፊ ነው በጣም በተለይ ለልጇ [. . .] ይቺም እናት ልጇ እንዲህ ቢላት አልከፋትም፡፡ ምግቡን አዘጋጁ (ጅታ) ጓደኞቹ መጡ በሉ ጠጡ ሄዱ፡፡ በሌላ ቀን ደግሞ ጓደኞቹን እራት ጋበዛቸው፡፡ "እማማ ጓደኞቼ ዛሬ ከእኔ ጋር ነው እራት የሚበሉት ስለዚህ እራት ይዘጋጅልን ይሄን ያህል ሰው ይመጣል ቁጥራቸው አንቺ ግን ምግብ ካዘጋጀሽ በኋላ ጓደኞቼ ከቤት እስከ ወጡ ከጓዳ . . . (እንዳትወጪ የሚለውን የምእመኑን መልስ በመጠበቅ) ስለዚህ ጓደኞቹ በመጡ ቁጥር እናቱ የሚሰጣቸው መመሪያ ጓዳ እንዲቀመጡ ነበር፡፡ ያበሰሉት ምግብ ይበላል እሳቸው ግን ይታፈርባቸዋል፡፡ እኚህ እናት አንድ ቀን ምን ይሆን ምክንያቱ ብለው አሰቡ ደግሞም ደረሱበት "ልጄ ና" አሉት "አንድ ታሪክ ልንገርህ አባትህ በልጅነትህ ነው የሞተው እኔና አንተ ብቻ ነበር የምንኖረው እና በጣም ጨቅላ እያለህ የምንኖርበት ቤት የሳር ቤት አንተን አስተኝቼ ውሀ ልቀዳ እወንዝ ወረድኩ ውሀ ቀድቼ ስመለስ ቤታችን ከየት እንደመጣ በማላውቀው እሳት ተያይዟል

ስለዚህ በጆርባዬ የያዝኩትን ማድጋ ወይንም ማሰሮ፣ ወይንም ገንቦ የት እንደጣልኩት አላውቅም ሮጬ ቤት ውስጥ ገባሁ ቤት ውስጥ ስገባ እሳቱ መሀል ታለቅሳለህ ብቻ የመጣልኝ ነገር በብርድልብስ ጠቀለልኩህ አንተን አቅፌ ስወጣ የቤቱ ጣራ በእሳት ተያይዞ መናድ ጀመረ ሁለት ምርጫ ነበረኝ ፊቴን ከእሳት መከላከል አንተን መልቀቅ ወይንም አንተን በብብቴ ውስጥ ሸጉጬ በብርድልብስ ሸፍኜ በእሳቱ መካከል ማለፍ የሚያምሩ አይኖቼን የሚያምር ፊቴን ለእሳቱ ወላፈን መማገድ ውሳኔዬ ግን ይሄ ነበር፡፡ ከእሳቱ መሀከል ይገፎህ ወጣሁ ግን ከእሳቱ መካከል ስትወጣ አንተ መልክህ እንደትናንቱ ቢሆንም የእኔ መልክ የተለየ ነበር፡፡ አይኖቼ ተጠብሰው፣ ከንፈሮቼ እጅግ ደርቀው አረሩ፤ ደምግባቴ በእሳቱ ጠፍቶ ነበር ግን እርካታዬ አንተን በልምላሜ በቁንጅና ይገፎህ ወጣሁ፡፡ አሳደኩህ፣ አስተማርኩህ እና ጓደኞችህ ሲመጡ የምታፍረው የእኔን አይን እንዳያዩ ነው?! ጓደኞችህ ሲመጡ የምታፍረው የእኔን አፍንጫ የእኔን ከንፈር እንዳያዩ ነው?! ታሪክህ ከፈለግህ ይሄ ነው ካፈርክበት እፈርበት ከኮራህበት ኩራበት፡፡(ልጁ) ጓደኞቹን ወዲያው ሰበሰበ "እያችኋት የኔን እናት የኔደምግባት እሷ ፊት ላይ ነው እሷ ተቃጥላ እኔን ውብ አደረገችኝ" አለ::

## ተረክ 49

መምህር ብርሃን አንለይ በ28/8/2002 በ8፡15 ከቃለምልልስ

በደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን

ባልና ሚስት፣ ሁለት ባለትዳሮች በአንድ ጣራ፣ ጎጆ ውስጥ ሲኖሩ በጣም በፍቅር ጎረቤት በሚያስቀና ፍቅር ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ግን ሰይጣን አነሳሳቸውና በሁለቱ መካከል ፀብ ተፈጠረ፡፡ ተጋጬ ተለያዩ፡፡ ሲለያዩ ግን ብቻቸውን አልነበረም በጣም ጎረቤት ሁሉ አዘነ "እነሱ እንደዚህ ይለያዩ ወይ?!" እያለ ሲያዝን ሲያዝን እነሱም ከልባቸው ስላልነበረ ባል ወደ ቤተክርስቲያን እየሄደ ዘወትር ፀሎት ይፀልይ ነበር፡፡ ፀሎቱ ምንድነው ሚስቴን ወደ ቤቴ አስገባልኝ የሚል ነበር፡፡ [ምክንያት ፈጥሮ ከመጣላት ምክንያት ፈጥሮ መታረቅ እንደሚገባ ነው ይሄን ምሳሌ የምነግርሽ ያለሁት] እና ስድስት ወር ዛሬ ትመጣለች ነገ ትመጣለች ሲል ስድስት ወር ሞላ፡፡ አንድ ቤት ነው ቤቱን ተካፍለው ባል በዚህ በኩል ይኖራል ሚስት በዚህ በኩል ትኖራለች በሌላ በር ከፍተው ሁለቱም ይገባሉ ይወጣሉ አብረው ግን አያድሩም፡፡ ይሄ ሁልጊዜ ባልን ይፀፅተዋል፡፡ እና "ሚስቴን. . . ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ምናለ ሚስቴን ወደ ቤቴ ብታስገባ እያለ ሁልጊዜ በልቡ ይጸልያል፡፡ ከስድስት ወር በኋላ ግን አንድ ቀን ወደቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሄዶ "ቅዱስ ገብርኤል ዛሬ የአመትህ ንግስ በአል ነው ሚስቴን እንደምንም ብለህ አንተ በአማላጅነትህ ወደጉያዬ አስገባልኝ" ብሎ ከምር ከልቡ ፀልዮ ወደቤቱ ይመጣል፡፡ ወደቤቱ መጥቶ ሚስትም እዛው ትሰማለች እመኝታ ክፍሉ ከመግባቱ በፊት ፀሎት እያደረገ "ቅዱስ ገብርኤል ሚስቴን አምጥተህ ከጉያዬ አስገባልኝ" እያለ ድምፁን አሰምቶ ሲናገር ሚስቱ ትሰማና በሯን ከፍታ ቀስ ብላ በሩ ላይ ትቆማለች፡፡ ትቆምና ፀሎት እየፀለየ ነው ሰውየው አሁን

ይሄንን ፀሎት እየፀለየ ባለበት ሰአት በር ላይ ቆማ ወደሱ ለመግባት ፍላጎት ስላላት "ቅዱስ ገብርኤል አትግፋኝ አትግፋኝ" እያለች ወደቤት ገባች ይባላል፡፡ እሱም ከዛ በኋላ ሚስቴን አመጣህልኝ ብሎ በፍቅር ኖሩ ይባላል፡፡

ተረክ 50

መምህር ሀብታሙ ከበደ በ29/8/2002 በ5፡00 ከቃለምልልስ

በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል

ሁለት እ. . . በጫካ ውስጥ ብዙ አውሬዎች ይኖራሉ መቼም ጫካ ያው የአውሬዎች መኖሪያ ነው፡፡ በዛ ጫካ ውስጥ የሚኖሩ አንበሳና ድኩላ ነበሩ፡፡ አንበሳው "እራበኝ እራበኝ፣ እራበኝ" ይላል "እራበኝ" ሲል አንድ ድኩላ ይመለከታል፡፡ ድኩላዋ ደግሞ አንበሳውን ስትመለከት አንበሳው ከያዘ እንደማይለቃት ስለምታውቅ "አውጣኝ፣ አውጣኝ፣ አውጣኝ" ማለት ጀመረች፡፡ አንበሳው አብላኝ ይላል፤ ድኩላ አውጣኝ ትላለች፡፡ በዚህን ሰዓት ያቺን ድኩላ ባየ ጊዜ አንበሳው፣ ድኩላዋን ለመያዝ ሲሮጥ ድኩላዋም ደግሞ ላለመያዝ ስትሮጥ ድንገት ከሜዳ ላይ አሳማ ተኝቷል፡፡ ያ አንበሳ ድኩላዋን መያዝ ስላልቻለ አሳማው ተኝቶ ባገኘ ጊዜ ያንን አሳማ ይዞ ጨፍልቆ በላው፡፡ እንግዲህ አውጣኝ ያለም ወጣ፣ አብላኝ ያለም በላ፣ ተኝቶ የተገኘ አሳማ ተበላ በማለት አባቶቻችን ይናገራሉ፡፡

ተረክ 51

በመምህር ላዕከወንጌል በዕደማርያም ይትባረክ በ29/8/2002 በ6፡30

ከቃለ ምልልስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብክት ቢሮ

አርብ ጠዋት ገበሬው በሬዎቹን ጠምዶ ያርሳል እያረሰ እያለ ጠላቱን ከሩቅ ያየዋል "አይ ዛሬ ጠላቴ አጋጥሞኝ ነበር እንደው ግን ምን ያደርጋል ጠመንጃዬ ያለው እቤት ነው ምን ላድርግ" ይልና ትንሽ ያስብና "ቆይ እስቲ እሱ ከ . . .ዛ እስኪመጣ እኔ እቤቴ ሄጄ ጠመንጃዬን ላምጣ" ይልና በሬዎቹ እንደተጠመዱ ትቶ ወደቤቱ ይሄዳል፡፡ ወደቤቱ ሄዶ፣ ወደቤቱ ገብቶ ጠመንጃውን ከተቀመጠበት ቦታ ብድግ አድርጎ ይዞ ሊወጣ ሲል ትይዘዋለች (ሚስት)፡፡ እንቅ አድርጋ ትይዘዋለች "ገና በጠዋቱ ጠመንጃህን ይዘህ የምትሄደው የት ነው ባይሆን አፍህን አግድፍ ባይሆን ቁርስህን ብላ" ትለዋለች፡፡ እሱ ደግሞ "ዛሬ እኮ ፆም ነው ዛሬ እኮ አርብ ነው እንዴት ቁርስ ብላ ትይኛለሽ" አላት፡፡

ተረክ 52

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ2/9/2002 በ12፡15

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

አንዴ ሰውየው እግዚአብሔር ተገለፀና ምን ልስጥህ አለው፡፡ "ጌታ ሆይ አንተ የምትፈልገውን ስጠኝ" (አለው)፡፡ "ግን ቃል ግባ" አለው (እግዚአብሔር) "አንተ ፀሎተኛ ነህ፣ መንፈሳዊ ነህ፣

ለአንተ አንድ ነገር ስሰጥ አንተ በለመንከው ልመና፣ አንተ በፀለይከው ፀሎት፣ በአንተ ቁመት ለጓደኛህ እጥፍ አድርጌ እሰጠዋለሁ" አለው። "እኔ በለመንኩት ለኔ አንድ ለጓኛዬ ሁለት" "አዎ" "እንዴት ይሆናል ይሄ እንዴ የእኔም የእሱም ይቅር እንጂ እኔ በለመንኩት ልመና ለሱ" [ክርስትና ይሄ ነው? ክርስትና ይሄ ነው?. . . ] "አሁን እኔ አንድ ለምኜ ለጓደኛዬ ሁለት" "አዎ" "አሁን ለምሳሌ. . ." ይሄንን ቃል ሲናገረው አሰበ አሰበና "ለምሳሌ ለእኔ አንድ ቤት ስጠኝ ብልህ ለጓደኛዬ ሁለት ቤት ነው የምትሰጠው" አለው "አሁን ለእኔ እንደው አንድ መኪና ስጠኝ ብልህ ለጓደኛዬ ሁለት" "አዎ" በኋላ "ጌታ ሆይ!" "አቤት" "የግራ አይኔን አጥፋልኝ" አለው የጓደኛው ስንቱ እንዲጠፋ?

## ተረክ 53

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ2/9/2002 በ12፡15

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

አንድ ልጅ አሁን እዚህ ጉባኤ ነበር የሚማረው። አሁን ከኢትዮጵያ ውጪ ነው። ታውቁት ይሆናል፣ ጓደኛውም እዚህ ሊኖር ይችላል። ዱርዬ ነበር ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነበር በአንድ ወቅት፣ እናቱን በሞት ተነጥቋል። ከብዙ ጊዜ በኋላ ወገኖቼ አንድ ጓኛው ነው "ና እስቲ የሰኞን ፕሮግራም እንከታተል" ብሎ ያመጣው። ጉባኤውን ሊካፈል ይመጣል፤ አጫሽ ጠጪ በአለም ያሉትን የሀጢያት አይነቶች . . . ወገኖቼ በሀጢያት ጎዳና ሲጓዝ የነበረ አንድ ቀን መጣ። ቃለ እግዚአብሔር ሠማና ቀረ እዚሁ ጉባኤ ይከታተል ጀመር። አሁን ቃለ እግዚአብሔር ይከታተል ጀመረ፣ መንፈሳዊ ሆነ። በኋላ ምን መጣ ከባድ ህመም ጀመረው የጀርባ ህመም። ሄዶ ሲመረመር ኢትዮጵያ ውስጥ መዳን አትችልም፣ ውጪ ካልሆነ አትችልም አሉት። ኢትዮጵያ ውስጥ መድሀኒቱ የለም አሉት። "መጥቼ ቁጭ ብዬ ጉባኤ ስከታተል አያመኝም" አለ "ስፀልይ አያመኝም፣ ሳስቀድስ አያመኝም" አለ። "አሁን ከኢትዮጵያ ውጪ ሄጄ ነው የምመረመረው?! በምንድነው?! አምላኬ በአለም አደባባይ ሳለሁ ጤነኛ ነበርኩ። አለም ላይ እያለሁ ህመም አያውቀኝም ነበር አሁን አንተን ብዬ ሙጥኝ ብዬ ስመጣ ልሸከመው የማልችለው በሽታ ውስጥ ትከተኛለህ?! በአለም እያለሁ እኮ እኔ ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይቅላ ብዬ የምኖር ሰው ነኝ ለምን?! አልኩኝ" አለ በቃ "ግን መንፈሳዊ ህይወቴ እየጨመረ መጣ"። ሌሎች ሰባክያንም ጋር እየሄደ ይማራል። በቃ በእግዚአብሔር ቃል ተመሰጠ። አሁን ጀርባው ላይ ያለው ህመም እያደረ እያደረ ከባድ ሆነ። ኢትዮጵያ ውስጥ መዳን የለም ውጪ ነው። (አሁን) የፃድቁ አባት የገብረመንፈስን ፀበል ተጠመቀ ፀበላቸውን ተጠመቀ፣ [እኔ እኮ በምን እንናገረው የእግዚአብሔርን ስጦታ?! ምን እንክፈለው?! ያደረገልንን ውለታ በምን ቋንቋ እናውጅለት?! እኛ እኮ አቅም የለንም ጉልበት የለንም ወገኖቼ] አሁን ተጠመቀ፣ በሚወርደው ፀበል በሽታው ወረደ! ድራሹ ጠፋ! ያ ልጅ

ተፈወሰ፡፡ ዛሬ አይደለም ውጪ የተላከው መድሀኒቱ ለካ እዚህ ነው፡፡ ዛሬ የፃድቁን የገብረመንፈስ ቅዱስን ምስል ክንዱ ላይ ተነቅሷል፡፡

## ተረክ 54

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ2/9/2002 በ12፡15

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

አንድ ቤት ሁለት ሌቦች ገቡ፡፡ ሁለት ሌቦች ሲገቡ ባልየው ብልጥ ነው፣ ብልጥ የመጨረሻው ዘመን ብልጥ (ነው)፡፡ ገብተው ሌቦቹ አንዱ በዚህ ጋ (ቀኙን እያሳየ) አንዱ በዚህ ጋ (ግራውን እያሳየ) እንደቆሙ አይቷቸዋል በጨለማ ጭላንጭሎች አሉ፡፡ ሚስትየው ተኝታለች ቀስ አለና በእግሩ ቢነካት ነቃች፡፡ ነቅታ ቀና ስትል አየቻቸው ምን የመሳሰለ ሰይፍ ይዘዋል፣ ቆመዋል "እንነቃለን ቢሉ ቆርጠን እንጥላለን" የሚሉ ናቸው፡፡ በኋላ "ወይኔ" ስትል "ምንድነው ዝምብለሽ ተኚ ምን አይነቷ ነች" (አለ) "ኧረ ይኸው አታይም" (ስትለው) "አይቻለሁ፤ ሚካኤልና ገብርኤል ሠይፍ ይዘው እየጠበቁን ነው ተኚ" አላት በኋላ እነዛ ሌቦች "ሚካኤል?! ገብርኤል?!" አሉና እንደሚካኤልና ገብርኤል አደረጋቸው ቀስ አሉና ሳይሰርቁ ወጡ፡፡

## ተረክ 55

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ2/9/2002 በ12፡15

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

ያኔ ዱሮ ዱሮ ግብረገብ ያስተማሩኝ መምህሬ መንኩሰዋል አሁን፡፡ ድሮ ነው ግብረገብ እንደ አንድ "ክሬዲት ሐወር" ይሰጥ ነበር፡፡ አስታውሳቸዋለሁ አንድ ቀን ትምህርት ቤቱ ውስጥ ከግብረገብ አስተማሪነት ሌላ ገንዘብ ያኙም ናቸው፡፡ ገንዘብ ያኙ መሆናቸውን ስለሚያውቅ ቤታቸውን ሠርስሮ ገባ ሌባ፡፡ የት እያሉ? ትምህርት ቤት እያሉ እሳቸው፡፡ አሁን በዛን ሰዓት (ጊዜ) ካዝና አለ ግን ብዙም የለም [. . .] አሁን የሚገርማችሁ ልክ ሲሄዱ የቤታቸው በር ተሰብሯል አልደነገጡም አማተቡ፣ አማተቡና ገቡ፡፡ ልክ ሲገቡ አመናችሁኝም አላመናችሁኝም ሰውየው መሰርሰሪያውን እንደያዘ የተሚላ መሳሪያውን እንደያዘ ደርቋል፡፡ ልክ እንደሚያስቀድስ ሰው ቆሟል፡፡ መጥተው አጠገቡ ቆሙ አያይም ፊት ለፊት ነው የሚያየው፣ ወዲያና ወዲህ የለም፡፡ በጣም አስታውሳለሁ፣ አሁን በጣም ገርሟቸው፣ አንደኛ በሩ ተሰብሯል፣ እንደገና ሰውየው ቆሟል [. . .] አሁን ስተት ብለው ገቡ አዩ፡፡ ወዲያው ሌባ እንደሆነ አወቁ፡፡ ወደ ቤተክርስቲያን ሰው ላኩ ካህናት ተጠርተው ፀሎት ተደርጎ ሰውየው፣ ሌባው ዲዳ ሆነ (ሰውነቱን ግን) ለቀቀው፡፡ ሰውየው ራሱ አገልጋይ ሆነ አየው የእግዚአብሔርን ስራ፡፡ እኚህ አባት ብዙም

አልቆዩ ከተወሰነ አመት በኋላ መንኩሰዋል፡፡ ለካስ ቤታቸው ውስጥ ስትገቡ ገብታችሁ እንዲህ ስትዞሩ (ፊቱን ወደቀኝ አዞሮ) ግድግዳው ላይ የስላሴ ስዕል አለ፡፡

## ተረክ 56

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ2/9/2002 በ12፡15

በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

አንድ ሰውዬ ለልጁ መጫወቻ የአለም ካርታ ገዛለትና ተጫወት ብሎታል፡፡ ይሄ ልጅ ለምዶታል በቃ (መጫወቻውን)፡፡ ከትምህርት ቤት ሲመጣ ሁልጊዜ ያቺን ካርታ የዓለም ናት፡፡ የአለም ካርታው ጀርባ ላይ የሰው መልክ አለ ሁሌ ግጥምጥ ያደርጋታል፡፡ አንድ ቀን አባት ከስራ በጊዜ መጣና ስራ ሲፈታ [ስራ የፈታ አእምሮ የሰይጣን ቢሮ ነው እንደበር እጄታ ያም ያም ይከፍተዋል]፡፡ አሁን እስቲ የልጄን መጫወቻ ልሞክር አለና አለምን ለማስተካከል አውስትራሊያን ሲያመጣ አፍሪካ ትወጣለች፤ አንዱን ወዲህ ሲያመጣ አንዱ ወዲያ ይወጣል፡፡ እንዲሁ እንደቀላል መጫወቻ ብሎ የገዛው ጭንቅላቱን ፈትኖት ላብ በላብ ሆኖ ልጁን መጠበቅ ጀመረ፡፡ "ባቢ እንደምን ዋልክ" ብሎ ሲገባ (ልጁ) ምንም እንደምን ዋልክ የለም "ና ይሄንን አለም አስተካክል፣ አለምን እንደነበረች አድርጋት" አለው፡፡ ልጁ መጣ ለልጁ ቀላል ነው፡፡ አሁን ሲመለከት "አባቢ" አለ "አለም እንድትስተካከል ሰው ይስተካከል" አለ ጀርባው ላይ የሰው ምስል አለ፡፡ ሰውየውን ማስተካከል ቀላል ነው፡፡ ግንባር፣ ጉንጭ፣ አፍንጫ፣ ምናምን አስተካከለና ሰውየው ሲመጣለት "አሁን ገልብጠው" አለው ሲገለብጠው አለም ትክክል ሆነች፡፡ ሰው ሲስተካከል ዓለም ምን ትሆናለች?! ትስተካከላለች፡፡

## ተረክ 57

በመምህር (ዲያቆን) ቸሬ አበበ በ4/9/2002 በ5፡30 ከቃለምልልስ

በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ

ክርስቶስ ሀዋርያትን አስከትሎ በሚያስተምራቸው፣ በሚዞርበት ሰአት በስጋዌ ወቅት አንድ ጥያቄ ጠይቋቸው ነበር ምንድነው ያላቸው . . . ሐዋርያት አስራ ሁለት ናቸው፡፡ ከአስራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ አለ እና አሳልፎ እንደሚሰጠው ያውቃል አንድ ፈተና ግን አቀረበላቸው፡፡ ይህ ጥያቄ፣ ሁላችሁም እያንዳንዳችሁ ድንጋይ አንሱ ይላቸዋል፡፡ እና እንዴት ድንጋይ የሚያሸክም ሰው መጣብን ብለው እሱ (ይሁዳ) በማጉረምረም ትንሽዬ ድንጋይ አንስቶ ትከሻው ላይ አስቀምጦ እንዲህ (የመንገዳገድ ምልክት እያሳየ) ይውተረተር ነበር፡፡ ሌሎቹ በአቅማቸው ልክ አንስተው ለመታዘዝ ፍቃዱን ለመፈጸም ፈቃዳቸውን ሁሉ በማሰብ ይጠብቁት ነበር ይላል፡፡ እና ይህን ድንጋይ "የያዛችሁት ድንጋይ ሁላችሁም" ምን ሁኖ ብሉት አለ "ዳቦ ሁኖ ብሉት" አለ፡፡

እና እሱ (ይሁዳ) ትንሽ ድንጋይ ስለሆነች ያቺን በልቶ ቁልጭ ቁልጭ ይል ነበር፡፡ ከዛ "ድጋሚ ካዘዘ እኔ ትልቅ ድንጋይ ነው የማነሳው መቼም ወርቅ ይሁን ነው የሚለው" ብሎ ቀጣይ ደግሞ በክፋት ልቡ ያስባል፡፡ (እየሱስ) አሁንም እነሱን ትንሽ ጠብቆ በልተው ከጠገቡ በኋላ ይጠይቃቸዋ፡፡ የተራበው ይሁዳ፤ በክፋቱ ማለት ነው፤ "አሁን ድንጋዩ ወርቅ ይሁን ስለሚል እኔ ትልቅ ድንጋይ ነው አሸክሙኝ ብዬ የምሸከመው" አለ፡፡ አሁንም ደግሞ ይህን ያልኳችሁን ትእዛዝ ትፈፅማላችሁ ሁላችሁም ድንጋይ አንሱ አላቸው፡፡ ድንጋይ አንሱ ሲላቸው አሁን እንደቀደመው ያቅማቸውን አነሱ እንደቀደመው፡፡ እሱ ግን "ሁላችሁም ተሰብሰቡና ይህንን ታላቅ ድንጋይ አሸክሙኝ" ብሎ ያንን አቅሙ የማይችለውን ትልቅ ድንጋይ (ተሸከመ)፡፡ ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ እስኪቸገር ድረስ ማለት ነው፡፡ እና "የያዛችሁትን ድንጋይ በአቅማችሁ ልክ ወርውሩት፤ በወረወራችሁት ልክ፣ መጠን እድሜያችሁ ይርዘም" አለ፡፡

## ተረክ 58

በመምህር (ዲያቆን) ቸሬ አበበ በ4/9/2002 በ5፡30 ከቃለምልልስ

በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ

አንዲት ሚዳቆ አለች ጠዋት ተነስታ የብርቱካኑ ዛፍ ጋ ሳትደርስ አትመለስም፡፡ እና እዛ ስር ትሄድና ወደላይ ስታይ ብርቱካኖች ታያለች አፍርተው፡፡ እላይ ስታይ አንድ ብርቱካን ለማግኘት እጅግ ደክማ ደክማ ቤቷ ትመለሳለች፡፡ አሁንም ጠዋት ትመጣና ረሀቧን የሚያስታግስላት አንድ ብርቱካን እንኳን አጥታ አሁንም ዘላ ዘላ ዛፉ ላይ ለመውጣት በእግሯ ሁሉ ጭራ ጭራ አልችል ስትል አቅሟን ስታውቀው ተመልሳ ትሄዳለች፡፡ እና ሁሌ እንዲህ ትደክማለች፣ ትደክማለች (አንድ ቀን ታድያ) "አይ ብርቱካኑ እኮ አላፈራም" ብላ ተመለሰች፡፡ በቃ አላፈራም እንደውም ለኔ የሚሆን አይደለም ሳያፈራ ምን አንቀዠቀዠኝ ብላ እራሷን አስታግሳ ወደቤቷ ተመለሰች እራቧንም በራሷ ወሰነች የሚል ነው፡፡

## ተረክ 59

በመምህር (ዲያቆን) ቸሬ አበበ በ4/9/2002 በ5፡30 ከቃለምልልስ

በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ

መሬትና ሚዳቋ እ. . .ተቀያየሙና ተጣሉ፡፡ ሚዷቋ ከመሬቷ ጋ ትቀያየማለች፡፡ ያው ሰው አብሮ ሲኖር መጋጨት አለ፡፡[. . .] መሬትና ሚዳቋም አንድ ላይ ስለሚኖሩ ሚዳቋ መሬት ላይ ስለምትኖር መጣላታቸው አይቀርምና ነው እና ተጣሉ፡፡ ሲጣሉ ግን ሚዳቆዋ ትልቅ በትር ይዛ መሬቷን አናት አናቷን ትቀጠቅጥ ነበር፡፡ "ምናባሽ" እያለች "ምንታመጪያለሽ" እያለች አናት አናቷን እያለች፡፡ ከዚያ ደብድባ! ደብድባ! ድብድባ! መጨረስ ሲያቅታት፣ ማድማት ሲያቅታት፣ ማባረር ሲያቅታት እሷም ከሷ ተለይታ እንደማትሄድ ስታውቅ "የታባሽ እንደውም

ከአንቺ ጋር መኖር አልችልም፤ አልፈልግም" ብላ ሚዳቆዋ እየዘለለች ስትሮጥ፣ ስትሮጥ፣ ስትሮጥ፣ ስትሮጥ፣ ስትሮጥ አሁንም ስታይ መሬት ነው፤ አሁንም ስታይ መሬት ነው መሬቱን ጨርሳ መሬቱ ዳር ባህር አለ ትልቅ ባህር እዛ ጋ ስትደርስ ባህሩ ጋ ልትገባ ስትል ባህሩን ስታይ "በቃ ህይወቴ ማለፉ ነው" ብላ አሰበችና "አይ ከምሞትማ ከዚህች ጋ ሳልጣላ ብኖር ይሻለኛል" አለችና ተመልሳ [. . .] ስትደበድባት ከነበረችው አካል ጋር ታረቀች፡፡

## ተረክ 60

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ10/9/2002 በ12:30

ማኅደረ ስብሃት ቅድስት ልደታ ለማርያምና ደብረ

መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን

ዛሬ ዛሬ ጠንቋዩ ዘመናይ ነው ስግደት ሁሉ ያዛል፡፡ ለልደታ አምስት ስገዱ ይላል፤ ለአቡነ አረጋዊ አስር ይላል፤ ለሚካኤል አምስት ይላል፤ ለገብርኤል ስገዱ ይላል ያዛል፡፡ አንዳንዴ እንደውም ፀበል ይፀፋል "ሪፈር ይጽፋል" ወደ ሚካኤል ጸበል፣ ለአንተ የሚሆነው የአቦ ነው ለአንቺ የሚሆነው . . . ከክርስትና ጋር ልዩነት የለውም እንድንል፡፡

## ተረክ 61

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ10/9/2002 በ12:30

ማኅደረ ስብሃት ቅድስት ልደታ ለማርያምና ደብረ

መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን

አንድ እናት ወንጌል እየተማሩ ነው ቤተክርስቲያን፡፡ ወንጌል ሲማሩ ቤታቸው ግን ጭንቀት ነው፡፡ እቤታቸው ብዙ የሚያስጨንቃቸውን ነገር ትተው ነው የመጡት፡፡ እንደአቅማቸው የሰናፍጭ እርሻ አላቸው በዚህ እርሻ ላይ እንዳይጠቀሙ እንደፈለጉ ወገኖቼ ወይ ደግሞ በመሬቱ ደህና አድርገው አምርተው እንዳይጠቀሙ ቦታው ላይ በጣም ግዙፍ የሆነ ድንጋይ ተንከባሎ ቁጭ ብሏል፡፡ እኚህ እናት ተጨንቀዋል፣ በጣም ተጨንቀዋል አንድ ቀን ቁጭ ብለው ሲማሩ ሰባኪው ልባቸውን ነካው "የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ካላችሁ ድንጋዩን ተነስተህ ወይም ቃሉ እንደሚለው ተራራውን ተነስተህ ገደል ግባ ብትሉት ይገባል የሚሳናችሁ የለም" የሚለውን ቃል ሲሰሙ ደስ ብሏቸው አገልጋዩ ሲጨርስ ሄዱ፡፡ "ዛሬ በጣም ልብ የሚፈትሽ ቃል ተናግረኸኛል" (አሉት)፡፡ "እናታችን እኔ አይደለሁም የተናገርኩት እኔም ስማር ነበር እርሶም ሲማሩ ነበር፡፡ እኔ ቆሜ እርሶ ቁጭ ብለው"[ሲያስተምር የነበረው ማን ነው?(ምእመኑን) እግዚአብሔር] "ግን ቃሉ ምንድነው?" አላቸው፡፡ የሰናፍጭ እርሻ አለኝ በዚህ እርሻዬ ውስጥ አርሼ እንዳልጠቀም ግዙፍ ድንጋይ ተንከባሎ ቁጭ ብሏል አሁን እምነት ያላችሁ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት ካላችሁ ድንጋዩን ተነስተህ ገደል ግባ ብትሉት፤ ተራራውን ተነስተህ ወደ ገደል ግባ ብትሉት ይነሳል ብለህል አምኛለሁ! አምኛለሁ! እኔ በእርሻዬ መካከል ግዙፍ ድንጋይ

አለ" አሉ፡፡ "እናታችን እግዚአብሔር እኮ በእኔ አድሮ የተናገረው ይሄን አይደለም የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት ካላችሁ ተራራውን ተነስተህ ገደል ግባ ብትሉት ይገባል ስል የእምነትን ታላቅነት ለማሳየት ነው" (አላቸው)፡፡ "ልጄ አሉት ተወደደም ተጠላም አምኛለሁ እግዚአብሔር እቤት ስራዬን እየሰራልኝ ነው ይሄን ጊዜ" አሉት፡፡ "እኔ እዚህ ነኝ እኔ በእውነት እዚህ ነኝ አላውቅም የድንግል ልጅ፣ አማኑኤል ቤቴ ምን እየሰራ እንደሆነ አላውቅም ግን ስራ እየሰራ ነው" አሉ፡፡ [ወገኖቼ እመኑ ባመናችሁ ጊዜ ለውጥ አለ] እኚህ እናት ልክ ሲሄዱ የሳቸው ቤት ተከቧል፡፡ "ምንድነው አሉ?" በእሳቸው ቤት አካባቢ የቀለበት መንገድ ሊሰራ ድንጋይ ተፈልጎ ተፈልጎ ጠፍቶ እሳቸው እርሻ ላይ ተገኘ ይሄ ድንጋይ ለእነዛ ለመንገድ ሰሪዎች እንቁ ነው፡፡ ለእነሱ ለምን ግዙፍ ነው ድንጋዩ ባያስጨርሳቸው ጥቂት መንገድ ያራምዳቸዋል፡፡ ባለቤትን በናፍቆት እየጠበቁ ነው እግራቸው ላይ ለመውደቅ ገንዘብ ሰጥተው ለዛውም ገንዘብ ሰጥተው[...] አሁን ሲመጡ (ሴትየዋ) እንደው እኔ አቅም የለኝም ትንሽ ገንዘብ አለችኝ ይህችን ገንዘብ ሰጥቻችሁ ይሄን ድንጋይ አንከባሉልኝ ብለው ለምነው ለምነው ለምነው አልቻሉም [. . .] አሁን እኚህ ሴትዮ ከርቀት ሲመለከቱ ሰው ተሰብስቧል "ደግሞ ምን መጣብኝ ባለኝ አመስግኜ እንዳልኖር" ሲሉ ምንም አልመጣም መጣላቸው እንጂ "እናታችን እባኮን እንዲህ እንዲህ አይነት. . ." አንዱ እግራቸው ላይ ይወድቃል አንዱ እጃቸውን ይስማል [. . .] እንደው አንዱ የፈለጉትን እንክፈል ይላል፡፡ "ምንድነው ነገሩ በህልሜ ነው በእውኔ" (አሉ፡፡) "በእርሻዎት መካከል" "እሺ" "ግዙፍ ድንጋይ አለ እኛ በእርሶ እርሻ ዳር ላይ መንገድ ለመስራት የመጣን ሰዎች ነን ለመንገድ ድንጋይ ያስፈልገናል" "ውይ! ውሰዱልኝ" "አይደለም እናታችን ገንዘብ ከፍለኖት የሚፈልጉትን ያህል ከፍለኖት እንውሰደው ነው የምንሎት" "እኔ አይደለም ከፍላችሁ ሳትከፍሉኝ ውሰዱልኝ" ተለምነው፣ ገንዘብ ተከፍሏቸው፣ ድንጋዩን አንከባለው ወስደው ያ የእርሻ ቦታ ታጥሮ ወገኖቼ እኛ አምላክ መጨረሻውን መጀመሪያ ያደረገላቸው እናት . . . እኔ ይገርመኛል ጠላት ለረጅም ጊዜ ሹክ ይላቸዋ "ዝም ብለሽ ነው ይሄን ድንጋይ ያለሽን ገንዘብ አንጡራሽን አውጪና ድንጋዩን ወደዚያ አስወርጂ ምን ላይ ታርሺያለሽ" የነገን የእግዚአብሔርን እቅድ ስለሚያውቅ፡፡

## ተረክ 62

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ16/9/2002 በ12፡30

መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

አንዴ አሉ አባቶች ቁቤና ማር ተከራከሩ አሉ ቅቤና ማር ተጨቃጨቁ፡፡ ማር ምን አለ "ስማ" አለው "እኔ ለሰው ጣፋጭ ሆኜ እያጣፈጥኩ አንተ መጥተህ ጭንቅላት ላይ ቁጭ" ቅቤን "እኔ ነበርኩ ጭንቅላት ላይ መቀመጥ የነበረብኝ" አለ፡፡ ማር "እኔ ነኝ የምጣፍጠው ሰው የሚበላው እኔን ነው የሰው ጭንቅላት ላይ ወጥተህ ቁጭ ያልከው አንተ ነህ" አለው፡፡ በኋላ ቂቤ ምን አለ

"አዬ አዬ ጓደኛዬ ማር አላወክም ለካ ዋጋ ከፍዬ ስንት መከራ አይቼ ተገፍቼ ስንት መከራ አይቼ ነው ዛሬ ዛሬ ጭንቅላት ላይ ቁጭ ያልኩት" አለ "እንዴት የተከፋሁት እኔ እየጣፈጥኩኝ ተገፍቼ እንኳን ጭንቅላት ላይ ልወጣ እንስራ ውስጥ አድርገው ገፍተው ገፍተው፣ ንጠው ንጠው፣ እኮ ነው መጨረሻ ነጥለው አውጥተው ቁጭ ያደረጉኝ" አለ "ዋጋ ከፍዬ ነው እዚህ የደረስኩ" አለ።

## ተረክ 63

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ16/9/2002 በ12:30

መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

አንድ ልጅ እናቱ ታመዋል። በህይወትና በሞት መካከል ታመዋል እናቱ፤ በህይወትና በሞት መካከል። ሲበር ሄደና ከፋርማሲ መድሀኒት እንዲገዛ ሀኪም ሰጥቶታል። እ. . . ማዘዣ እንትኑን እና ያን ይዞ ሄደ። አጋጣሚ ሲሄድ ፋርማሲስቱ ተኝቷል እንቅልፍ ላይ ነው። ቀሰቀሰው። ፋርማሲስቱ ለካ ሲነሳ በሙሉ ልቡ አልነበረም በደንብ አልነቃም ወረቀቱን አየና ያልሆነ መድሃኒት ሰጠው። ወረቀቱ የሚለውን ሳይሆን ይህንን መድሀኒት ወስዶ ለእናቱ ቢሰጣቸው ይገድላቸዋል። አሁን የሚገርማችሁ ልጅ በጣም በሩጫ ሄዷል እናቱን ለማትረፍ [. . .] አሁን የሚገርማችሁ ልክ ይሄ ልጅ ከሄደ በኋላ ፋርማሲስቱ ነቃ በደንብ ነቃ ሲያይ ማዘዣውን ሲመለከት የሰጠው መድሀኒትና የታዘዘው ሌላ ነው ይሄን መድሀኒት እዛ ቢሰጥ ሴትየዋ ይሞታሉ። በህይወቱ አንድ ቀን ፀሎት አድርጎ አያውቅም። ግን ፀሎት ማድረግ ጀመረ ያን ቀን ተንበረከከ "አምላኬ" አለ "አምላኬ" አለ [. . .] የሚገርማችሁ ይሄ ሰውዬ ብድግ አለና ተንበርክኮ "አምላኬ" አለ "አምላኬ እንደው ምንም ይሁን ምንም እኚህ እናት ሞተው የሳቸው ደም በእኔ ነውና እንደው ተአምርህን ግለፅ" አለው። በህይወቱ ፀሎት አድርጎ አያውቅም ሲበላ ጎበዝ ያዘው እያለ የሚበላ ነው ሲተኛ ልክ እንደውሃ ዋና ዘሎ አንሶላ ውስጥ ነው የሚገባው አንድ ቀን የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ አያውቅም [. . .]። አሁን ፀሎት እያደረገ በሩ በጣም ተንኳኳ ደንግጦ ሲከፍት ያ መድሀኒት ይዞ የሄደው ልጅ ነው። "ጌታዬ ይቅርታ አድርግልኝ እየሮጥኩ ስሄድ መድሀኒቱ ተሰበረ" አለ። "ተሰበረ" [ምን ያህል እንግዲህ ፀሎት ነገሮችን ይቀይራ] እውነተኛውን መድሀኒት ሰጠው አሁን ያ መድሀኒት እዛ ቢደርስ እኛ ሴት ሟች ናቸው።

## ተረክ 64

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ16/9/2002 በ12:30

መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

አሁን በኢትዮጵያ ታሪክ እሌኒ የምትባል ሚስት ያላቸው (ንጉስ ነበሩ)። በጣም ቆንጆ ናት በጣም ውብ ናት። ከንስሀ አባቷ ጋር ፍቅር ይዟታል። አሁን አንድ ቀን ፃድቁ ዮሐንስ

የሚባሉ፣ ፃድቁ ዮሐንስ አንድ ቀን ጠረጠሩ [. . .] አሁን አንድ ቀን ማታ ቁጭ ብለው ከጣና ውስጥ የተጠመደ አሳ እየተጠበሰ ይቀርባል ንስሀ አባት ቁጭ ብለዋል፣ ንግስት እሌኒ፣ አፄ ዮሐንስ፣ የቤተመንግስት ጃንደረቦች (ሁሉ አሉ)፡፡ በኋላ ፃድቁ ዮሐንስ ከምግቡ በፊት ፀሎት ከተደረገ በኋላ "አንድ የምናገረው ነገር አለኝ" አሉ ፃድቁ፡፡ "ለምንድነው እያስመሰልን የምንኖረው በቃ እውነት እንነጋገር እውነት ይለጠጣል እንጂ አይሰበርም፡፡ እውነት ብንናገር፣ እውነት ብንናገር ይሄ የጠበስነው አሳ እሳቱ ላይ ያለው ክንፍ የሌለው [ሲጠበስ ክንፉን አጥቷል] ይሄ አሳ ህይወት ዘርቶ ጣና ውስጥ ይገባ ነበር፡፡" አሉ ሁለቱም ደነገጡ፡፡ ንስሀ አባት ብድግ አሉ በቃ "እኔ ማለት ሲገባኝ ተቀደምኩ" አሉና "እኔ በጣም በጣም በጣም ከአቅሜ በላይ የሆነ ሀጢያት ውስጥ ነኝ ያለሁት እሌኒን ወድጃታለሁ" አሉ፡፡ እሌኒ ብድግ አሉ "እኔም አባቴን ወድጄያቸዋለሁ መልከመልካም ናቸው" አሉ፡፡ በዚህን ጊዜ አፄ ዮሐንስ ብድግ ብለው "እኔም ገዳም እገባለሁ" አሉ፡፡ [. . .] ዛሬ ጣና ውስጥ ከሚጠመዱ አሳዎች የፃድቁ ዮሐንስ አሳ የሚባሉ አሉ፡፡ ስታዩት ተጠምዶ ሲያዝ ክንፍ የለውም፡፡

## ተረክ 65

በመምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ በ16/9/2002 በ12:30

መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን

አንዴ አይጥ ለገበሬ ውለታ ዋለችለት አሉ፤ ለገበሬው ትልቅ ውለታ አይጥ እኮ ናት፡፡ አይጥና ገበሬ ውለታ ሲፈፃፀሙ አሁን ገበሬው ደስ አለው "አይጤ" አላት ሲያቆላምጣት [አይጥን ሲያቆላምጧት!] "አይጤ ምን ላድርግልሽ" አላት፡፡ ጎተራ ውስጥ ወስዶ የጥሬ መአት የተከመረበት ጎተራ ውስጥ አስቀምጧት አይጧን፡፡ ይገርማል እዚህ ጥሬ መሀል ላይ እንደፈለገች መብላት የምትችልበት ጎተራ ውስጥ አስቀምጧት "ምን" አላት "አይጤ ምን ልስጥሽ" አላት፡፡ የሚገርማችሁ ያለችው ምን ላይ ነው እህል ላይ እኮ ነው ምግቧ ላይ "ምን ልስጥሽ" ይላታል ተሽኮረመመች [አይጥ ስትሽኮረመም] "እንደው ያቺን ትሰጠኝ" አለችው የወደቀች ሽምብራ መሬት ላይ አይታ እህል ላይ ቁጭ ብላ ያቺን ስትል ገበሬው ተናደደ የምርጫ ችግር እኮ ነው፡፡

## ተረክ 66

በጫካ ውስጥ አውሬዎች ተሰብስበው ይኖሩ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ጦጣ በድንገት እየሮጠች ወደ ኤሊ ትመጣና "እመት ኤሊ እስከአሁንም እዚህ አለሽ እንዴ?!" ትላታለች፡፡ ኤሊም ደንግጣ "ምነው?" ስትላት የዱር አውሬ ሁሉ እኮ በአንቺ ላይ አምጿል፣ ሊገሉሽ፣ ሊበሉሽ እየፈለጉሽ ነው ሽሺ ትላታለች፡፡ እንደዛሬ ድንጋይ ያለበሰችው ኤሊ በሁኔታው ተደናግጣ "እነማን እነማን ናቸው የተነሱብኝ?" ብትላት ጦጣም "አንድም አልቀረ የአራዊት ንጉስ አንበሳም እንኳን"

ትላታለች፡፡ ኤሊ እንደተከዘች "አንድዬም ከእነሱ ጋር ነው?!" ብላ ትጠይቃታለች፡፡ ጦጣም "አይ እግዚአብሔር እንኳን ከእነሱ ጋር አልተነሳብሽም" ትላታለች፡፡ በዚህ ጊዜ ኤሊ ወዲያው ተጽናንታ "አይ አንድዬ እንኳን ከእነሱ ጋር ካልሆነ ተይው፣ ምንም አልሆን" ትላለች፡፡ ይህን እምነቷን ያየው እግዚአብሔር ወዲያው ኤሊን ድንጋይ ያለብሳትና ከጠላቶቿ ታመልጣለች፡፡ ይኸው እስካሁንም ኤሊ ድንጋይዋን እንደለበሰች ትኖራለች፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## አባሪ ሦስት

በዚህ አባሪ፣ በአባሪ ሁለት ስር የተካተቱ ስብስብ ተረኮች በአይነት (በዝርያ) ተፈርጀው በዝርዝር ቀርበዋል።

| እውነተኛ (factual) ቃላዊ ዝርው ተረኮች | | ፈጠራዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ትውስታዊ (reminiscences) ቃላዊ ዝርው ተረኮች | ሂሳዊ ቃላዊ ዝርው ተረኮች | ተረቶች (folktales) | | | ቀልዶች (jokes) |
| ተረክ 9 | ተረክ 8 | ተረክ 1 | ተረክ 19 | ተረክ 56 | ተረክ 38 |
| ተረክ 18 | ተረክ 25 | ተረክ 2 | ተረክ 20 | ተረክ 58 | ተረክ 41 |
| ተረክ 23 | ተረክ 26 | ተረክ 3 | ተረክ 21 | ተረክ 59 | ተረክ 42 |
| ተረክ 24 | ተረክ 27 | ተረክ 4 | ተረክ 22 | ተረክ 62 | ተረክ 43 |
| ተረክ 28 | ተረክ 34 | ተረክ 5 | ተረክ 29 | ተረክ 63 | ተረክ 44 |
| ተረክ 30 | ተረክ 35 | ተረክ 6 | ተረክ 31 | ተረክ 65 | ተረክ 45 |
| ተረክ 33 | ተረክ 60 | ተረክ 7 | ተረክ 32 | ተረክ 66 | ተረክ 46 |
| ተረክ 39 | | ተረክ 10 | ተረክ 36 | | |
| ተረክ 40 | | ተረክ 11 | ተረክ 37 | | |
| ተረክ 47 | | ተረክ 12 | ተረክ 48 | | |
| ተረክ 53 | | ተረክ 13 | ተረክ 49 | | |
| ተረክ 55 | | ተረክ 14 | ተረክ 50 | | |
| ተረክ 57 | | ተረክ 15 | ተረክ 51 | | |
| ተረክ 61 | | ተረክ 16 | ተረክ 52 | | |
| ተረክ 64 | | ተረክ 17 | ተረክ 54 | | |

## አባሪ አራት

ከዚህ ቀጥሎ ለዚህ ጥናት መሠረት ለሆኑ ተረኮች መረጃ አቀባዮች የሆኑ ግለሰቦች ስምና ዝርዝር መረጃዎች ቀርበዋል፡፡ ምንም እንኳን በጥናቱ በቅርበት የተጠኑ መምህራን ከ25 በላይ ቢሆኑም ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ የተጠቀሱት ባካሄዷቸው ስብከቶች ውስጥ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑ ተረኮችን ሲናገሩ የተደመጡ 14 ያህል ግለሰቦች ብቻ ናቸው፡፡ (መምህራኑ የተደረደሩበት ቅደም ተከተል የጥናቱ ትኩረት ያደረኳቸውን ተረኮች ሲናገሩ የሰማሁበትን የጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ያደረገ ብቻ ነው፡፡)

| ተራ ቁ. | ስም | ፆታ | የቤተክርስቲያን የትምህርት ሁኔታ | የሥራ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መምህር ዲያቆን አእምሮ አሰፋ | ወንድ | በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሶስተኛ አመት ተማሪ | — |
| 2 | መምህር ብርሃን አንለይ | ወንድ | የመንፈሳዊ ኮሌጅ ዲፕሎማ ምሩቅ | በደብረ ሀይል ቅዱስ ራጉኤል ትምህርት ቤት የግዕዝና የሥነ ምግባር መምህር |
| 3 | መምህር መጋቢ ሀዲስ ቀለመወርቅ ታደሰ | ወንድ | በዲማ ጊዮርጊስ የሰባት አመት የትርጓሜ ትምህርት | የአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ሐላፊ |
| 4 | መምህር ላዕከወንጌል በእደማርያም ይትባረክ | ወንድ | በቤተ ክርስቲያን (ከአለቃ ይትባረክ መርሻ )ቅኔ የተቀኙና የሀዲስ ትርጓሜ ትምህርት | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ሀገረብስከት የስብከተ ወንጌልና የትምህርት መምሪያ ሀላፊ |
| 5 | መምህር ሊቀማእምራን ፋንታሁን ሙጩ | ወንድ | የስነ መለኮት የዶክትሬት ተማሪ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ሀገረስብከት ዋና ስራ አስኪያጅ |
| 6 | መምህር ሀብታሙ ከበደ | ወንድ | በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የአምስተኛ አመት ተማሪ | በመካነ ህይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን ሰባኬ ወንጌል |
| 7 | መምህር ቀሲስ አስቻለው መሀሪ | ወንድ | የመንፈሳዊ ኮሌጅ ዲግሪ ምሩቅ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቤተክህነት የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ |
| 8 | መምህር ቀሲስ ይግዛው መኮንን | ወንድ | የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲፕሎማ ምሩቅ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ መሀበረ ቅዱሳን መደበኛ መምህር |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 9 | መምህር (ቀሲስ) መጋቤ ሐዲስ ኪዳኔ | ወንድ | በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የ5 ወራት ስልጠና | በፌዴራል ዋና ኦዲተር (ድሬዳዋ) ኦዲተር |
| 10 | አባ ሰላማ ብርሃን | ወንድ | በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሶስተኛ ዓመት ተማሪ | —— |
| 11 | መምህር (ዲያቆን) ደረጀ ጅማ | ወንድ | የቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲግሪ ምሩቅ | ሰባኬ ወንጌል |
| 12 | መምህር ዜናጥበብ ተስፋዬ ተሾመ | ወንድ | በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲፕሎማ | የአዲስ አበባ ሀገረስብከት የፉሪ ኤርቱ ደብረ ሀመልማል ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ኃላፊ |
| 13 | መምህር (ዲያቆን) ቸሬ አበበ | ወንድ | የመንፈሳዊ ኮሌጅ ዲግሪ ምሩቅ | በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የጥናትና ምርምር ሀላፊና የስብከት ሥነ-ዘዴ መምህር |
| 14 | * | * | * | * |

## አባሪ አምስት

ይህ አባሪ በዚህ ጥናት የስብከት ፕሮግራም ሲካሄድባቸው ከተቃኙ ሃያ ሁለት አብያተ ክርስቲያን መካከል የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት ተረኮች የተደመጡባቸውን የአስራ ሁለቱን አብያተ ክርስቲያን ዝርዝር ብቻ ይዟል።

1. ምስካየ ኅዙናን መድሀኔ ዓለም ገዳም
2. ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔ ዓለም መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ እና አቡነ አረጋዊ ካቴድራል
3. ቀበና ምስራቀ ፀሐይ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን
4. ታእካ ነገስት ባእታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን
5. ቅዱስ ባለእግዚአብሔር እና ባለወልድ ቤተ ክርስቲያን
6. መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን
7. ማኅደረ ስብሃት ቅድስት ልደታ ለማርያምና ደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን
8. መንበረ ጸባኦት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል
9. መንበረ መንግስት ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
10. ቦሌ ደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን
11. ደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ካቴድራል
12. ደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን

## ማረጋጫ

ይህ ጥናት የእኔ መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም ቤተልሔም፡ ሐይሉ

ፊርማ ______

የማስረከቢያ ቀን ______

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY